**የጎልማሶች ሰንበት ትምህርት፡የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መምሪያ**

**መደበኛ እትም**

# የዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ


አዘጋጅ፡ ራንኮ ስቴፋኖቪክ (ፒኤች.ዲ.)

**ዘላለም አስረስ እንደተረጎመው**


ይህ የጎልማሶች ሰንበት ትምህርት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መምሪያ የሚዘጋጀው በሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተ ክርስቲያን ዋና መስሪያ ቤት በሆነው በጀነራል ኮንፍረንስ ውስጥ ሆኖ፤ የጎልማሶች የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መምሪያን በሚያዘጋጀው ቢሮ ነው፡፡ መምሪያዎቹ የሚዘጋጁት የጀነራል ኮንፈረንስ አስተዳደር ኮሚቴ ንዑስ ኮሚቴ በሆነውና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መምሪያዎችን በሚያሳትመው የሰንበት ትምህርት ሕትመት ቦርድ ነው፡፡ የታተመው መምሪያ በውስጡ ዓለም አቀፋዊ የሆነ የምዘና ኮሚቴ ሀሳቦችንና የሰንበት ትምህርት ሕትመት ቦርድን ማረጋገጫ ስለሚያንጸባርቅ የአዘጋጁን (የአዘጋጆችን) ሀሳብ ብቻ የሚወክል አይደለም፡፡ በተለየ ካልተጠቀሰ በቀር በዚህ ሰንበት ትምህርት ጥቅም ላይ የዋሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በሙሉ የተወሰዱት ከአዲሱ መደበኛ ትርጉም ነው፡፡


በኢትዮጵያ አድቬንቲስት ማተሚያ ቤት ታተመ

**1ኛ ሩብ ዓመት**

**ታህሳስ፣ ጥር፣ የካቲት 2011**

# ማውጫ


| አርዕስት | ቀን | ገጽ |
|---|---|---|
| 1.የፍጥሞው ወንጌል | ከታህሳስ 20 –26 | 6 |
| 2. በመቅረዞቹ መካከል | ከታህሳስ 27 - ጥር 3 | 15 |
| 3. በከተሞች ውስጥ የሚኖሩ የእግዚአብሔር ሕዝቦች | ከጥር 4-10 | 24 |
| 4. የበጉ በዙፋኑ ላይ መቀመጥ | ከጥር 11-17 | 34 |
| 5.ሰባቱ ማኅተሞች | ከጥር 18-24 | 43 |
| 6. የታተሙት የእግዚአብሔር ሕዝቦች | ከጥር 25 - የካቲት 1 | 53 |
| 7. ሰባቱ መለከቶች | ከየካቲት 2-8 | 62 |
| 8. ሰይጣን፡ የተሸነፈ ጠላት | ከየካቲት 9-15 | 71 |
| 9. ሰይጣን እና ሁለቱ አበሮቹ | ከየካቲት 16-22 | 80 |
| 10. የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ወንጌል | ከየካቲት 23-29 | 89 |
| 11.ሰባቱ የመጨረሻ መቅሰፍቶች | ከየካቲት 30 - መጋቢት6 | 99 |
| 12. በባቢሎን ላይ የተሰጠ ፍርድ | ከመጋቢት 7-13 | 108 |
| 13.“እኔ ሁሉን ነገር አዲስ አደርጋለሁ” | ከመጋቢት 14-20 | 118 |

# ከፍጥሞ የተላከው የምስራች

ደቀ መዝሙሩ ዮሐንስ ለወንጌል በነበረው ቀናኢ ምስክርነት በሜዲቴራንያን ባሕረ ሰላጤ ኤግያን ባሕር (በግሪክና በዛሬዋ ቱርክ መሃል)በምትገኝ አንዲት አነስተኛና ድንጋያማ ደሴት በግዞት እንዲኖር ተገዶነበር--የዛሬ ሁለት ሺ ዓመታት ግድም፡፡ ዕድሜ ተጫጭኖት የነበረው ደቀ መዝሙር ሁሉንም ዓይነት አስከፊ የሮማውያን የእስር ዘመን አልፎአል፡፡ ታዲያ በአንድ ሰንበት ዕለት ይህን በሥቃይ የነበረ አገልጋዩን የሚያበረታና የሚያጽናና የተለየ ጉብኝት በየሱስ ክርስቶስ ተደረገለት፡፡ በተደጋጋሚ የሚለዋወጠውን የቤተ ክርስቲያን ታሪክና የእግዚአብሔር ሕዝቦች የጌታቸውን ዳግም ምጽአት እየተጠባበቁ እያለ የሚያልፉባቸውን ተሞክሮዎች የሱስ ተከታታይነት ባላቸው ራእዮች አሳየው፡፡

ዮሐንስ በራእይ የተመለከተውን ይህን "የኢየሱስ ክርስቶስ ራእይ" (ራእ. 1፥1) አንድም ሳያስቀር በጥንቱ የተሸበለለ ብራና በታማኝነት ጻፈው፡፡ ይህ ዮሐንስ የጻፈው መጽሐፍ የሱስ ወደ ሰማይ ካረገ ጀምሮ እየሰጠ ያለውን አገልግሎትና በዳግም ምጽአቱ የሚያከናውናቸውን ተግባራት ጥሩ አድርጎ ይገልጻል፡፡ መጽሐፉ በወደቀውና በታላቅ ውዝግብ ውስጥበሰጠመው ዓለም የሚኖሩ ክርስቲያኖች በዕለት ከዕለት የመከራ ተሞክሮአቸውለመደገፍና በዘመናት በክርስቶስ መገኘት ዙሪያ ላሉ ክርስቲያኖች ዋስትና ለመስጠትታልሞ የተዘጋጀ ነው፡፡

በዚህ ሩብ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታችን በራእይ መጽሐፍ ላይ ጥብቅ ምልከታ እናደርጋለን፡፡ ካለን ውሱን አቀራረብ አኳያ በእያንዳንዱ ጥቅስ ላይ ጥልቅ ትንተና ባናቀርብም ነገር ግን በዚያ ፋንታ በመጽሐፉ ዐቢይ ክፍሎችና ጭብጦች ላይ ትኩረት እናደርጋለን፡፡ አንባቢው ከጥቅሶቹ ጋር ግላዊ መስተጋብር እንዲፈጥር ይበረታታል፡፡ ዋናው ሃሳብ ከመጽሐፉ ቁልፍ ጭብጦች ጋር አግባብ መፍጠርና በእርግጥ የሱስ ክርስቶስን፣ ሕይወቱን፣ ሞቱንና ስለ ሕዝቡ እየሰጠ ያለውን አገልግሎት መግለጽ ነው፡፡

የራእይ መጽሐፍ ጥናታችን የሚከተሉትን ክፍሎች መሰረት አድርጎአል

1.የራእይ መጽሐፍ ጥናታችን መጽሐፍ ቅዱስ በመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት የመጻፉን ጽንሰ ሃሳብ መሰረት ያደረገ ነው፡፡ በመጽሐፉ የሰፈሩት መልእክቶች በሙሉ ከእግዚአብሔር የመጡ ሲሆን መልእክቱ ተደራሽ የሆነበት ቋንቋው ግን ሰብዓዊ ነው፡፡ ዮሐንስ ከብሉይ ኪዳኖቹ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ታሪክ የመጡትን ቋንቋዎችና ተምሳሌታዊ አቀራረቦች ጥቅም ላይ እያዋለከመልእክቶቹ ጋር ተግባቦት የፈጠረባቸውን አካሄዶችእንመለከታለን፡፡

2.የራእይ መጽሐፍ ትንቢቶች የተተነተኑትና ጥቅም ላይ የዋሉት ታሪክን በዋቢነት የሚቀበለውን የትንቢት አፈታት ዘዴ በመተግበር ሲሆን፤ ይኸውም ትንቢት ከጥንት ዘመን አንስቶ እስከ ምድር ፍጻሜ ያለውን የታሪክ ፍሰት እንደሚከተል የሚያስተምረውንስልት መሰረት ያደረገ ነው፡፡ አስቀድሞውኑ የተወሰነውን ፍቺ በጥቅሶቹ ላይ በመጫን ፋንታየጥቅሱን ቋንቋ፣ ተምሳሌታዊ አቀራረብና ዐውደ ሀሳብእየፈተሸን ከራሱ ከጥቅሱ ፍቺውን ለማግኘት ጥረት እናደርጋለን፡፡

3.ጥሩ ሆኖ የተደራጀው የራእይ መጽሐፍ አወቃቀር--ኃላፊነት ለተሞላው የትንቢት አተገባበር በብዙ መልኩ ወሳኝ ነው፡፡ በመጽሐፉ ላይ የምንሰጠው ትንታኔ የሚከተሉትን--ሦስቱን በአንድ የያዘውን አወቃቀር መሰረት ያደረገ ይሆናል፡፡

ሀ. ራእ. 1፡9-3፡22--በዮሐንስ ዘመን የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ትገኝበት የነበረው አሳሳቢ ሁኔታ

በቀዳሚነት የቀረበ ሲሆን፤ በተጨማሪ በተለያዩ ዘመናት ቤተ ክርስቲያን የምትገኝባቸው ትንቢታዊ

ሁናቴዎችም ተካትተዋል፡፡

ለ. ራእ. 4፡1-11--11፡18--ተምሳሌቶችንና ብዙም ያልተለመዱ ዝርዝሮችን በመጠቀም ቤተ ክርስቲያን

ከዮሐንስዘመን አንስቶ እስከ ዘመን መጨረሻ ያላትን ታሪክ በድጋሚ ያቀርባል፡፡

ሐ. ራእ. 11፡19-22፡5--በምድር ታሪክ መጨረሻ ሁናቴ ላይ ተቀዳሚ ትኩረት ያደርጋል፡፡

4.ትርጉም ያለው የራእይ መጽሐፍ አፈታት ክርስቶስን የመልእክቱ እምቡጥ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ ሙሉው የራእይ መጽሐፍ የተጻፈው ከክርስቶስ ምልከታ አኳያ እንደመሆኑ የመጽሐፉ ምሳሌያዊ አነጋገሮችና ትዕይንቶች የመጨረሻ ትርጓሜና ፍቺ የሚያገኙት በራሱ በክርስቶስ ብቻ ነው፡፡

የራእይን መጽሐፍ የሚያነቡ ወይም የሚያደምጡ፣ በጥንቃቄ የሚያስተውሉ፣ የሚቀበሉና ማስጠንቀቂውን የሚጠብቁ በረከትእንደሚያገኙ ይናገራል፡ "እንግዲህ ይህን የትንቢት ቃል የሚያነብብፁዕ ነው፤ የሚሰሙትና የተጻፈውንምየሚጠብቁ ብፁዓን ናቸው (ራእ. 1፡3)፡፡ የየሱስን ዳግም ምጽአትእየተጠባበቅን ባለንበት በዚህ ወቅትይህን መጽሐፍ ስንመረምር እርስዎ ለመስማትና ለመቀበልየሚሹዋቸውን አንዳንድ ነጥቦች ፈትሸውየራስዎ እንዲያደርጓቸው ግብዣ ቀርቦሎታል፡፡

የዚህ ሩብ ዓመት ሰንበት ትምህርት አዘጋጅ የሆኑት ራንኮ ስቴቫኖቪክ (ፒኤች. ዲ.) በአንድሪውስ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ነገረ መለኮት መንፈሳዊ ትምህርት ቤት የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ፕሮፌሰር ናቸው፡፡ በራእይ መጽሐፍ ላይ ልዩ ጥናትና ምርምር በማካሄድ የሚታወቁት እኚህ ግለሰብ፤ የየሱስ ክርስቶስ ራእይ እና ይፋ የሆነው ራእይ ሐተታ ደራሲ ናቸው፡፡ በራእይ መጽሐፍ ላይ የሰጧቸው ሌክቸሮች (አስተምህሮዎች) ለረጅም ጊዜ በ 3ABN የቴቪዥን ጣብያ በተከታታይ ቀርበዋል፡፡

# 1ኛ ትምህርት

ከታህሳስ 20 –26

# የፍጥሞው ወንጌል

ሰንበት ከሰዓት

*ለዚህ ሣምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ራእ. 1፡1–8፤ዮሐ. 14፡1–3፤ዘዳ. 29:29፤ዮሐ. 14:29፤ሮሜ 1:7፤ፊልጵ. 3:20፤ዳን. 13 7፤ 14፡፡*

**መታሰቢያ ጥቅስ:-** *"ዘመኑ ቀርቦአል፤ እንግዲህ ይህን የትንቢት ቃል የሚያነብ ብፁእ ነው፤ የሚሰሙትና የተጻፈውንም የሚጠብቁ ብፁዓን ናቸው፡፡" (ራእ. 1፡3)፡፡*

የራእይ ትንቢት ለሐዋርያው ዮሐንስ የተገለጠለት ከአስራ ዘጠኝ መቶ ዓመታቶች ቀደም ብሎ ሲሆን ይኸውም በኤግያን ባሕረ ሰላጤ ፍጥሞ በሚል ስያሜ ትታወቅ በነበር አንዲት አነስተኛ ደሴት በግዞት ይኖር በነበረበት ወቅት ነው (ራእ. 1፡9)፡፡ ይህ መጽሐፍ በቤተ ክርስቲያን እንዲነበብ ራእ. 1፡3 ያበረታታል፡፡ ይህን መጽሐፍ የሚያነብ፣ የሚያዳምጥም አምላካዊውን በረከት ይቀበላል የሚል የተስፋ ቃል ተሰጥቶአል፡፡ የሚሰሙት--በሚል ጥቅም ላይ የዋለው ቃል የቤተክርስቲያንን ጉባዔ ይወክላል፡፡ ሆኖም አማኙ በረከት የሚያገኘው እንደው እንደ ዋዛ መጽሐፉን በመሸምደዱ ወይም ሲነበብ በመስማቱ ሳይሆን ቃላቶቹን በመታዘዙ ነው

(ራእ. 22፡7)፡፡

የራእይ ትንቢቶች እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለውን ጥንቃቄ የሚያሳዩ ጥልቅ መገለጫዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ትንቢቶች ምድራዊው ህይወት ምን ያህል ተሰባሪና አጭር መሆኑን ከማሳየታቸው በተጨማሪ በየሱስ የሚገኘውን ደኅንነትና ወንጌልን እንድናሰራጭ የመጠራታችንን እውነታ ያመላክቱናል፡፡

መጽሐፍ ቅዱሳዊዎቹ ትንቢቶች ጨለማን ሰንጥቆ እንደሚያልፍ የብርሃን ጨረር ናቸው (2ጴጥ. 1፡19)፡፡ ለዛሬው ሕይወታችን ምሪት እንዲሰጡና የወደፊቱን ደግሞ በተስፋ እንዲሞሉ ታቅዶ የተበረከቱ ናቸው፡፡ ክርስቶስ ዳግም እስከሚገለጥና የእግዚአብሔር መንግሥት እስከሚመሰረት ይህን ትንቢታዊ ምሪት እንሻለን፡፡

## እሑድ

ታህሳስ 21

# የመጽሐፉ ርዕስ

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 1፡1-2፡፡ የመጽሐፉ ርዕስ ሙሉ ትርጓሜ ምንድን ነው? መጽሐፉ በትክክል ስለ ማን እንደሚናገር አስመልክቶ ርዕሱ ምን ያስተምረናል?

---

---

ራእ. 1፡1 የመጽሐፉን ርዕስ "የኢየሱስ ክርስቶስ ራእይ" በማለት ያስቀምጣል፡፡ ራእይ የተሰኘው ቃል የተወሰደው አፖካሉፕሲስ ከሚል የግሪክ አቻው ሲሆን፤ ቃሉ "መግለጥ" ወይም "ይፋ ማድረግ" የሚል ፍቺ አለው፡፡ በመሆኑም አፖካሉፕሲስ ከየሱስ እና ስለ የሱስ የተሰጠ የየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ነው፡፡ ይህ በየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ከእግዚአብሔር የመጣ ራእይ (ራእ. 22፡16)፤የራእዩ አስኳል የሱስ መሆኑንም ይመሰክራል፡፡ አፖካሉፕሲስ እርሱ ራሱን ለሕዝቡ የገለጠበት ራዕይ እና ለእነርሱ ያለው ጥበቃና ጥንቃቄ መግለጫ ነው፡፡

የሱስ የራእይ መጽሐፍ ማዕከላዊ አካል ወይም አስኳል ነው፡፡ መጽሐፉ በእርሱ ተጀምሮ (ራእ. 1፡5-8) በእርሱ ይደመደማል (ራእ. 22፡12-16)፡፡ "ትንቢተ ዳንኤል ይናገር፣ የራእይ መጽሐፍም ይናገር--እውነት የሆነውን አውሩ፡፡ ነገር ግን ማንኛውም የዚህ መልእክት ክፍል ሲቀርብ--የሁሉም ተስፋ የሆነውን 'የዳዊት ሥርና ዘር፣ የሚያበራ የንጋት ኮከብ' የሱስን ከፍ አድርጉ፡፡"—Ellen G. White, Testimonies to Ministers and Gospel Workers, p. 118.

ደግሞም የራእይ መጽሐፉ የሱስ የአራቱ ወንጌሎች የሱስ ነው፡፡ መጀመሪያ ላይ በወንጌላት እንደ ተወሳው የራእይ መጽሐፍ የሱስንና እርሱ ስለ ሕዝቡ የሠራውን የደኅንነት ሥራ መግለጹን ይቀጥላል፡፡ የራእይ መጽሐፍ በየሱስ አብሮነትና በአገልግሎቱ ልዩ ልዩ ገጽታዎች ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ በመሰረቱ መጽሐፉ የሚጀምረው ከወንጌል የመጨረሻ ጽሑፍ በመቀጠል ይኸውም ከየሱስ ትንሣኤና ዕርገት አንስቶ ነው፡፡ የራእይ መጽሐፍ ከዕብራውያን መልእክት ጋር በማበር ስለ የሱስ ሰማያዊ አገልግሎት አጽንኦት ይሰጣል፡፡ የሱስ ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ በሰማያዊው መቅደስ በንጉሣዊና ካኅናዊ አገልግሎቱ መከበሩን ያሳያል፡፡ ያለ ራእይ መጽሐፍ (እና ዕብራውያን) የሱስ ስለ እኛ በሰማያዊው መቅደስ እየሰጠ ስለሚገኘው አገልግሎት ይኖረን የነበረው ዕውቀት ውሱንና ስውር ሆኖ በተከደነ ነበር፡፡ ደግሞም የራእይ መጽሐፍ ከዕብራውያን ጋር ባለው ኅብር የሱስ ክርስቶስ ስለ እኛ እየሰጠ

ስላለው አገልግሎት በዓይነቱ ልዩ የሆነ ምልከታ ይሰጠናል፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ዮሐ. 14፡1-3፡፡ በጥቅሱ የቀረበው ሰፊ የተስፋ ቃል የሱስ በአሁኗ ሰዓት ስለ እኛ በሰማያዊው መቅደስ እያደረገ ስላለው ነገር በተሻለ ማስተዋል እንድንችል እንዴት ይረዳናል? ከዚህ አስገራሚ የተስፋ ቃል ብሩህ የሆነውን መጻኢ ጊዜ መሳል የምንችለው እንዴት ነው?**

**ሰኞ** ታህሳስ **22**

## መጽሐፉ የተጻፈበት ዓላማ

የራእይ መጽሐፍ የተጻፈበት ዓላማ መጽሐፉ ራሱ ከተጻፈበት ጊዜ አንስቶ በተከታታይ ገቢራዊ የሚሆኑ ክስተቶችን ለማሳየት እንደሆነ ራእ. 1፡1 ይነግረናል፡፡ ከራእይ መጽሐፍ ጋር ቅርበት ያለው ማንኛውም ሰው ይህ መጽሐፍ በአብዛኛው የተሞላው ከእኛ ኋላ በነበሩ ዘመኖች ፍጻሜ ባገኙ ክስተቶች እንዲሁም የወደፊቱን ጊዜያቶች የሚጠባበቁ ትንቢቶችን መያዙን ለማስተዋል አይቸገርም፡፡ የራእይ መጽሐፍ የመጀመሪያው አጋማሽ (ከምዕ. 1-11) ከመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን እስከ ዘመን መጨረሻ ባሉ ክስተቶች ላይ ትኩረት ሲያደርግ፤ ሁለተኛው አጋማሽ ግን (ከምዕ. 12-22) ወደ ዳግም ምጽአቱ የሚመሩ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡

የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች ተቀዳሚ ዓላማ ነገ የቱንም ዓይነት ያልተለመደ ነገር ይዞ ከተፍ ሊል ቢችል--ሁሉም ነገር በእግዚአብሔር ቁጥጥር ስር ለመሆኑ ማረጋገጫ መስጠት ነው፡፡ የራእይ መጽሐፍ ተግባር ይኸው ነው--የሱስ ክርስቶስ በዚህ ዓለም ታሪክ ውስጥ እና በወደፊቱ አሳሳቢ ሁኔታ ከሕዝቡ ጋር ለመሆኑ ማረጋገጫ መስጠት፡፡ በዚህ የተነሳ የራእይ ትንቢቶች ሁለት ተጨባጭ ዓላማ አላቸው፡--ዛሬን እንዴት መኖር እንዳለብን ማስተማር እና ለወደፊቱ ማዘጋጀት፡፡

ጥቅሱን ያንብቡ፡ ዘዳ. 29፡29፡፡ አንዳንድ ነገሮች ለምን እንዳልተገለጡልን ማስተዋል እንድንችል ጥቅሶቹ እንዴት ይረዱናል? በጥቅሱ መሰረት ለእኛ የተገለጡት ነገሮች ዓላማ ምንድን ነው? ስለ ምን ተነገሩን? (ራእ. 22፡7)

የራእይ የመጨረሻ ጊዜ ትንቢቶች የተገለጡልን እንደው ስለ ወደፊቱ እያሰብን በፍርሃትና መብሰልሰል እንዳንኖር ለመጠበቅ አይደለም፡፡ መጽሐፉ አሁን ለእኛ አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ብቻ ይገልጥልናል፡፡ የመጪውን ጊዜ ከባድነት

አስተውለን ከወዲሁ በእግዚአብሔር ላይ መተማመን--ይኸውም እርሱን መታዘዝ እንደሚኖርብን መገንዘብ እንችል ዘንድ እነሆ ትንቢቶቹ ተገልጠውልናል፡፡

የመጨረሻዎቹን ዘመናት ክስተቶች አስመልክቶ አያሌ መላ ምቶች እንደውም የተዋጣላቸው ስሜት ተኮር ግምቶች ለምዕተ ዓመታት ሲስተናገዱ ኖረዋል፡፡ ምዕመናን የመጨረሻው መቃረቡን እንናገራለን በሚሉ ትንቢት ተናጋሪ ነን ባይ ቀበኛ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መጨረሻው ደርሶአል በሚል ማስፈራሪያ ታልበዋል፡፡ ሆኖም ማስፈራሪያው እንደ ማንኛውም ቀን ያለ አንዳች ልዩ ክስተት መጥቶ ሲሄድ--በቁም ቅዠት ውስጥ የነበሩ ሰዎች በብርቱ ተስፋ መቁረጥ ሲወድቁ በተደጋጋሚ ተስተውለዋል፡፡ ከእግዚአብሔር የተቀበልናቸው አያሌ በጎ ነገሮች አሉታዊ ተግዳሮት እንደሚገጥማቸው ሁሉ በተመሳሳይ ትንቢትም በተሳሳተና ተገቢ ባልሆነ መንገድ ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል፡፡

## ማክሰኞ ታህሳስ 23

# የራእይ መጽሐፍ ተምሳሌታዊ ቋንቋ

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 13፡1፣ ዳን. 7፡1-3፣ ሕዝ. 1፡1-14፡፡ ሁሉም ራእዮች በጋራ የያዙት አንድ ነገር ምንድን ነው?

---

---

የራእይ መጽሐፍ ስለ መልእክቱ ተጨማሪ ማብራሪያ ሲሰጥ “መልአኩን ልኮ ለአገልጋዩ ለዮሐንስ ገለጠለት” ይላል (ራእ. 1፡1 )፡፡ ይህ ሃረግ የመልእክቱ በጣም አስፈላጊ ክፍል ነው፡፡ በጥቅሱ ገለጠለት በሚል ጥቅም ላይ የዋለው ቃል የተወሰደው ሴማይኖ ከሚል የግሪክ አቻው ሲሆን “በምሳሌያዊ ምልክቶች አሳየው” የሚል ፍቺ አለው፡፡ እንዲሁም ይህ ቃል በግሪክ ቋንቋ በተጻፈው የብሉይ ኪዳን ትርጉም “ወደ ፊት የሚሆነውን” (ዳን. 2፡45) በሚል ዳንኤል ለንጉሡ ናቡከደነጾር ከወርቅ፣ ከብር፣ ከነሐስ እና ከብረት ስለ ተሠራው ምስል ሲያብራራለት ቀርቦ እንመለከታለን፡፡ ዮሐንስ በተምሳሌታዊ አቀራረብ የተሞሉት ክስተቶችና ትዕይንቶች በራእይ እንደ ተገለጡለትተመሳሳይ ቃል ተጠቅሞ ይነግረናል፡፡ በመንፈስ ቅዱስ ይመራ የነበረው ዮሐንስ በተምሳሌታዊ አቀራረብ የተመለከታቸውን እነዚህን ራዕዮች በታማኝነት አስፍሮአል (ራእ. 1፡20፡፡

የራእይ ትንቢቶች የተገለጡበት ቋንቋ ውስጠ ወይራ እንደመሆኑ ቃል በቃል መተርጎም የለበትም፡፡ በአጠቃላይ መጽሐፍ ቅዱስን ስናነብ (ጥቅሱ ራሱ ወደ

ተፈለገው ተምሳሌታዊው አቀራረብ ካላመለከተ በቀር) ፊት ለፊት የተቀመጠውን ቀጥተኛ ትርጉም መውሰዳችን እርግጥ ነው፡፡ ሆኖም የራእይ መጽሐፍን ስናነብ ጥቅሱ ቀጥተኛውን ትርጉም ካላመላከተ በቀር በተምሳሌታዊ መንገድ ፍቺ መስጠታችን ተገቢ ነው፡፡ እነዚህ በትንቢት የቀረቡ ትዕይንቶች እና ድርጊቶች ተጨባጭ ቢሆኑም ነገር ግን አቀራረባቸው በተምሳሌታዊ ቋንቋ ነው፡፡

የራእይ መጽሐፍ በአብዛኛው ተምሳሌታዊ ጸባይ የተላበሰ መሆኑን ከግምት ማስገባታችን ትንቢታዊውን መልእክት አዛብተን ከማቅረብ እንድንጠበቅ ይረዳናል፡፡ በመጽሐፉ ጥቅም ላይ የዋሉ ምሳሌያዊ አቀራረቦችን ፍቺ ለመወሰን በምናደርገው ሙከራ ሰዋዊውን እሳቤ እንዳንጭን ጥንቃቄ ልናደርግ ይገባል፡፡ ይልቁንም ወደ ራሱ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ በማምራት በሌሎች ገጾች የሚገኙ ምሳሌያዊ አቀራረቦችን እየቃኘን በራእይ መጽሐፍ የምናገኛቸውን ተምሳሌታዊ አቀራረቦች በአግባቡ ማስተዋል ተገቢ ይሆናል፡፡

በራእይ መጽሐፍ የምናገኛቸውን ምሳሌያዊ አቀራረቦች ለመፍታት በምናደርገው ሙከራ አብዛኞቹ የተወሰዱት ከብሉይ ኪዳን መሆኑን ማስታወስ የግድ ይሆናል፡፡ የወደፊቱ የማዳን ሥራው ካለፈው ጋር አንድ ዓይነት የሆነው እግዚአብሔር አምላክ እነዚያን የቀደሙ ቋንቋዎች ተጠቅሞ የወደፊቱን በማሳየት አእምሮአችንን ለማነቃቃት ፍላጎቱ ነው፡፡ እርሱ ቀደም ባለው ዘመን ለሕዘቡ ያደረገውን እነሆ ወደፊትም ያደርጋል፡፡ የራእይ መጽሐፍን ተምሳሌቶች እና ምስሎች ለመፍታት በምናደርገው ሙከራ ከወዲሁ ለብሉይ ኪዳን ትኩረት መስጠት መጀመር ይኖርብናል፡፡

## ረቡዕ ታህሳስ 24

# መለኮት (ሥላሴ)

የራእይ መጽሐፍ ከጳውሎስ መልእክቶች በተመሳሳይ በሰላምታ ይጀምራል፡፡ ሲጀመር፤መጽሐፉ በዮሐንስ ዘመንለነበሩ ሰባቱየእስያ አብያተ ክርስቲያናት የተላከ ደብዳቤ ቢሆንም (ራእ. 1፡11)፤ የራእይ መጽሐፍ የተጻፈው ለእነርሱ ብቻ ሳይሆን በዘመናት ለነበሩ፣ ላሉና ለሚኖሩ ክርስቲያኖች ጭምር ነው፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ.1፡4-5፣ ሮሜ 1፡7፡፡ ሁለቱ መልእክቶች የሚጋሩት ሰላምታ ምንድን ነው? ሰላምታው የተሰጠው ከማን ነው?

የራእይም ሆነ የጳውሎስ መልእክቶች “ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን” የሚል ደብዳቤያዊ ሰላምታ ያቀርባሉ፡፡ ይህ ኃረግ የግሪኮችን ሰላምታ ቻሪስ (ጸጋ) እና የዕብራውያኑን ሻሎም (ሰላም፣ ደኅና መሆን) በአንድ ይዞአል፡፡ ጸጋና ሰላም ሰጪ እግዚአብሔር አብ፣ እግዚአብሔር ወልድ እና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ መሆኑን ከእነዚህ ጥቅሶች ተነስተን መመልከት እንችላለን፡፡ እንደ ቀሪው የመጽሐፉ ክፍል ሁሉ እነዚህ ሦስት ባህሪያትም በተምሳሌታዊ ቋንቋ ተለይተው ቀርበዋል፡፡ እግዚአብሔር አብ “ያለውና የነበረው፣ የሚመጣውም” (ራእ. 1፡8፣ 4፡8) በሚል የቀረበ ሲሆን፤ ይህ አነጋገር “እኔ፣ ያለሁና የምኖር ነኝ” (ዘፀ. 3፡14) የሚለውን የዘላማዊውን እግዚአብሔር ህልዎት ይወክላል፡፡

መንፈስ ቅዱስ “ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስት” በሚል ተጠቅሶአል (ራእ. 4፡ 5፣ 5፡6)፡፡ ሰባት ቁጥር ሙላትን ያሳያል፡፡ “ሰባቱ መናፍስት” መንፈስ ቅዱስ ከሚሠራባቸው ሰባቱ ቤተ ክርስቲያኖች ጋር የተሳሰረ ነው፡፡ ይህ ገጽታ በዘመናት የእግዚአብሔር ሕዝቦች የተጠሩበትን ከፍጻሜ ለማድረስ የሚያስችላቸውን ዓለማቀፋዊ ገጽታ ያለውን የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ያሳያል፡፡

የሱስ ክርስቶስ “ታማኝ ምስክር፣ ከሙታን በኩርና የምድር ነገሥታት ገዥ”(ራእ.1፡5) በሚሉ ሦስት ስያሜዎች ቀርቦአል፡፡ ስያሜዎቹ የመስቀል ላይ ሞቱን፣ ትንሣኤውንና ሰማያዊ ንግሥናውን ያሳያሉ፡፡ ከዚያም “ለወደደንና ከኃጢአታችንም በደሙ ነጻ ላወጣን፣ አምላኩንና አባቱን እንድናገለግልም መንግሥትና ካኅናት ላደረገን” (ራእ. 1፡5-6) በማለት የሱስ ያደረገውን ዮሐንስ ይጠቅሳል፡፡

“ለወደደን” የሚለው ቃል በመጀመሪያው የግሪክ ቋንቋ--ያለፈውን፣ የአሁኑንና የወደፊቱን በአንድ ያቀፈው የክርስቶስ ፍቅር የማያባራ መሆኑን ይገልጻል፡፡ እኛን የወደደው፣ እርሱ በደሙ ከኃጢአታችን ነፃ አድርጎናል፡፡ በግሪኩ ትርጉም፣ አባባሉ ያለፈው ድርጊት ፍጻሜ ማግኘቱን ይጠቅሳል፡፡ የሱስ በመስቀል ላይ በሞተ ጊዜ--እኛን ተከታዮቹን ከኃጢአታችን ለዘላለም ነፃ አወጣን፡፡

**የተዋጁ ወገኖች በትንሣኤ ተነስተው በሰማያዊው ስፍራ ከየሱስ ጋር እንደሚቀመጡ--ኤፌ.2፡6 እና ፊልጵ.3፡20 ይገልጻሉ፡፡ ለመሆኑ ይህ ምን ማለት ነው? ዛሬ በዚህ በኃጢአት የተረገመ ምድር እየተመላለስን ይህን በክርስቶስ “መንግሥትና (ነገሥታትና) ካኅናት” ስለ መሆናችን በክብር የተሞላ ማንነት ሐሴት የምናደርገው እንዴት ነው? እውነታው በዚህ ህይወት ምን ዓይነት ተጽእኖ ሊኖረው ይገባል?**

## ሐሙስ ታህሳስ 25

# የመጽሐፉ ዋና መንፈስ

የራእይ መጽሐፍ መግቢያ አጠቃላይ ገጽታ መጽሐፉ ሙሉ ለሙሉ ትኩረት የሚያደርግበትን-- ይኸውም በኃይልና በግርማ እውን ወደሚሆነው የየሱስ ዳግም ምጽአት ያመላክታል፡፡ የክርስቶስ ዳግም ምጽአት የተስፋ ቃል በመጽሐፉ መደምደሚያ ላይ ሦስት ጊዜ ተደጋግሞ ቀርቦአል (ራእ. 22፡7፣ 12፣ 20)፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ--ራእ. 1፡7-8፡፡ የዚህ ጥቅስ አጻጻፍ ወይም የቃላት አጠቃቀም ግኝት ብዛት ያላቸው ትንቢቶች ናቸው፡ ዳን. 7፡13-14፣ ዘካ. 12፡10፣ ማቴ. 24፡30፡፡ ጥቅሶቹ ዳግም ምጽአቱ የተረጋገጠ ስለመሆኑ ምን ይነግሩናል?

---

---

በራእይ መጽሐፍ እንደ ተመለከተው የክርስቶስ ዳግም ምጽአት የታሪክ ሁሉ መደምደሚያ ነው፡፡ የዚህን ዓለም ታሪክ ፍጻሜና የአምላካዊውን መንግሥት ጅማሮ የሚያመለክተው ዳግም ምጽአት--የክፉ፣ የጣር፣ የህመምና የሞትን ፍጻሜ ያበስራል፡፡

ራእ. 1፡7--እንደ ሌሎቹ የአዲስ ኪዳን መልእክቶች ሁሉ ግላዊ ብሎም ልክ እንደ ተባለው ገቢራዊ ወደ ሚሆነው፣ ንጉሣዊና ባለ ታላቅ ግርማ የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ያመላክቱናል፡፡ እያንዳንዱ ሰብዓዊ ፍጡር እንደውም "የወጉት እንኳ ሳይቀሩ" የዳግም መገለጡ ምስክር ይሆናል፡፡ ይህ አባባል የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ገቢራዊ ከመሆኑ ጥቂት ቀደም ብሎ እርሱን የወጉ ሰዎችን ጨምሮ በተለየትንሳኤ የሚነሱ መኖራቸውን ይጠቁማል፡፡ በዳግም ምጽአቱ እርሱን ለሚጠባበቁ ደኅንነት--ለፍቅሩና ምኅረቱ ዘለፋዊ ምላሽ ለሰጡ ደግሞ ፍርድ ይዞ ይመጣል፡፡

የተረጋገጠው የክርስቶስ ዳግም ምጽአት "አዎ፤ አሜን!" በተሰኙ ቃላት የጸና ነው (ራእ. 1፡7)፡፡ እነዚህ አዎ እና አሜን የተሰኙ ቃላት--ሁለቱም አዎንታዊ ወይም አዎንታን ይዘዋል (ራእ. 22፡20)፡፡

"በቅርቡ በሰማያት ደመና በሚገለጠው የሰው ልጅ መምጣት ላይ ጽኑ እምነት እስካለ ድረስ--ተራና መናኛ የሆነው ምድራዊ ነገር እውነተኞቹን ክርስቲያኖች ቸልተኛና ግዴለሽ አያደርግም. . . ትክክለኝነታቸው፣ ታማኝነታቸውና ሐቀኝነታቸው በአላፊ ምድራዊ ነገሮች ይፀናል፣ ይረጋገጥማል፡፡"—Ellen G. White, Testimo-

nies for the Church, vol. 4, p. 309.

***አንድ የተስፋ ቃል ሲሰጥ--የተስፋ ሰጪው ቃል ጥንካሬ የሚለካው ቃሉን ጠብቆ መዝለቅ በመቻሉ ሐቀኝነትላይ ብቻ ነው፡፡ ከዚህ ቀደም ሰጥቶ የነበረውን የተስፋ ቃል በሙሉ በጠበቀው በእግዚአብሔር የተቸረን የዳግም ምጽአቱ የተስፋ ቃል ሐቅ--ክርስቶስ በተናገረው መሰረት ዳግም ስለ መመለሱ ምን ዓይነት ማረጋገጫ ይሆንዎታል?***

## አርብ ታህሳስ 26

*ተጨማሪ ሃሳብ፡* Read Ellen G. White, "The Study of the Books of Daniel and the Revelation," pp. 112–119, in Testimonies to Ministers and Gospel Workers.

"ቤተ ክርስቲያን በዘመናት ምሪትና መጽናናት ታገኝ ዘንድ እነሆየራእይ መጽሐፍ ተሰጠ…ራእይ--የተገለጠ የሚል ፍቺ አለው፡፡ በዚህ መጽሐፍ የቀረቡትን ምስጢሮች ጌታ ራሱ ለአገልጋዩ የገለጠ ሲሆን፤ መጽሐፉን ለሚያጠኑ ሁሉ መልእክቱን የተከፈተ አድርጎአል፡፡ መጽሐፉ የያዛቸው እውነቶች የዮሐንስን ዘመን ብሎም በምድር ታሪክ መደምደሚያ የሚኖሩ ሕዝቦችን ዒላማ ያደረገ ነው፡፡ በዚህ ትንቢት የቀረቡት አንዳንድ ትዕይንቶች ቀደም ባሉት ዘመናት ፍጻሜ ያገኙ፣ በምድር ታሪክ መጨረሻ ገቢራዊ የሚሆነውን የጨለማውን ኃይልና የሰማይን ልዑል ውዝግብ የሚያስቃኙ እንዲሁም በጸጋው የዳኑ አሸናፊዎች በአዲሲቱ ምድር የሚኖራቸውን ደስታና ፍስሐ የሚገልጡ ናቸው፡፡

"መጽሐፉ የያዛቸውን እውነቶች ፍቺ ለማወቅ በምናደርገው ጥረት፤ ለእያንዳንዱ ተምሳሌታዊ አቀራረብ ትርጓሜና ማብራሪያ ባለመስጠቱ፤ መጽሐፉን መመርመር ዋጋ እንደሌለው አድርገን ልንቆጥር አይገባም፡፡ እነዚህን ምስጢሮች ለዮሐንስ የገለጠለት ጌታ፤ እውነትን ለማወቅ ለሚሹ ትጉሃን የሰማዊውን ነገር ምሳሌ ይገልጥላቸዋል፡፡ እውነትን ለመቀበል ልቦቻቸው ክፍት የሆኑ ወገኖች አስተምህሮውን የሚያስተውሉበት ኃይል ይሰጣቸዋል፡፡'ይህን የትንቢት ቃል የሚያነብ ብፁዕ ነው፤ የሚሰሙትና የተጻፈውንም የሚጠብቁ ብፁዓን ናቸው' በሚል የቀረበው በረከትና የተስፋ ቃል ባለቤት ይሆናሉ፡፡"—Ellen G. White, The Acts of the Apostles, pp. 583–585.

## የመወያያ ጥያቄዎች፡

1.ራእይ የተሰኘው ቃል በየሱስ ክርስቶስ የተገለጠ የሚል ፍቺ ቢኖረውም ነገር ግን ብዙዎች አሉታዊ ከሆነ  የዓለም ፍጻሜ፣ ከአሰቃቂ ክስተትና አስፈሪ የፍርድ ቀን አኳያ ይመለከቱታል፡፡ መጽሐፉ በአብዛኛው የክርስትና እምነት ተከታዮች እንዴት እንደሚታይ አስመልክቶ ይህ ምን ይነገረናል?አስፈሪ የተሰኘው ቃል ተደጋግሞ የቀረበው ለምንድን ነው?

2.ባለፉት 20 ዓመታት ብቻ ስለ ዓለም ፍጻሜ እንዲሁም ስለ የሱስ ዳግም ምጽአት በአንዳንዶች ተነግረው ፍጻሜ ሳያገኙ ስለቀሩ ትንቢቶች አሰብ ያድርጉ፡፡ ትንቢቶቹ ከየትኛውም እሳቤ አኳያ ሊሰጡ ቢችሉም፤ሳይሰምሩ የመቅረታቸው አሉታዊ ውጤት ምን ሊያስከትል ይችላል? ትንቢቶቹን አምነው በተቀበሉ ላይ ምን ዓይነት ስሜት ይፈጥራል? ሳይሰምሩ የቀሩት ትንቢቶች ለአጠቃላዩ ሕዝበ ክርስቲያን ምን ዓይነት ገጽታ ያሰጣሉ? እኛ ትንቢትን አምነን የምንቀበልና ወደ መጨረሻው የሚያደርሱ ምልክቶችን በጥንቃቄ የምንመለከት ሕዝቦች እንደ መሆናችን፤ ትንቢትን በማስተዋሉና ለሌሎች በማስተማሩ ረገድ ትክክለኛውን ሚዛን ጠብቀን መጓዝ የምንችለው እንዴት ነው?

# 2ኛ ትምህርት

ከታህሳስ 27 - ጥር 3

# በመቅረዞቹ መካከል

ሰንበት ከሰዓት

ለዚህ ሣምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ራእ. 1:9–18፣ ሐዋ. 7:54–60፣ ማቴ. 12:8፣ ዘፀ. 20:11፣ ዳን. 10:5-6፣ ራእ. 1:20፣ ራእ. 2:1–7፡፡

**መታሰቢያ ጥቅስ :-** " 'እኔ ድል ነስቼ ከአባቴ ጋር በእርሱ ዙፋን ላይ እንደ ተቀመጥኩ፣ ድል የሚነሳውንም ከእኔ ጋር በዙፋኔ ላይ እንዲቀመጥ አደርገዋለሁ' " (ራእ. 3፡21)፡፡

መዝ. 73-- በዐመፀኞች ስኬት ግራ ስለ ተጋባው ባለ መዝሙር ገለጻ ያደርጋል፡፡የእነዚህ ሰዎች ኑሮ ከጻድቃን በተቃራኒ በብልጽግና የተሞላ ከመሆኑ በተጨማሪ፤ በብዙዎች የሚደርሰው ጣጣ አያውቃቸውም፡፡ ይህ ኢፍትሐዊነት በጉዳዩ እየተብሰለሰለ ወደ ቤተ መቅደስ ያመራውን (መዝ. 73፡16-17) ባለ መዝሙር አብልጦ ቢረብሸውም፤ ሆኖም በእግዚአብሔር ፊት በቆመ ጊዜ--ስለ ጉዳዩ ጥልቅ ማስተዋል አገኘ፡፡

ይህ ከሆነ ከብዙ መቶ ዓመታት በኋላ አንድ ዕድሜ የተጫጫነው ሐዋርያ ስለ ታማኝ ምስክርነቱ ራሱን በዐለታማ የግዞት ደሴት መሃል እንዲያገኝ ተገድዶ ነበር፡፡ በዚያ አስጨናቂ ሁናቴ ውስጥ የነበረው ይህ ሐዋርያ በእርሱ ጥንቃቄ ስር የነበሩ ቤተ ክርስቲያኖች በአስቸጋሪ ሁናቴ የመውደቃቸውን ወሬ ሰማ፡፡ ሆኖም በዚያ ወሳኝ ወቅት--በትንሣኤ የተነሳውን ክርስቶስ በሰማያዊው ቤተ መቅደስ የመመልከት ተሞክሮ ማግኘት ችሎ ነበር፡፡ ቀደም ሲል ከባለ መዝሙሩ ጋር የነበረው ጌታ አንዳንድ የዚህን ህይወት ዕንቆቅልሾችና ተግዳሮቶች በተመሳሳይ ለዮሐንስ ሲገልጥለት ይታያል፡፡ የዚህ ምድር ታሪክ እስኪደመደም ረጅሞቹን ምዕተ ዓመታት አቋርጦ በሚያልፈው የክርስትና ትውልድ መሃል የክርስቶስን ሕልዎት፣ ጥንቃቄና ጥበቃ በቤተ ክርስቲያን ላይ የመኖሩን አዎንታዊ የምስራች ለመግለጥ--እነሆ የቤተ መቅደሱ ትዕይንት ለዮሐንስ ተሰጠ፡፡

**እሑድ** ታህሳስ **28**

## በፍጥሞ ደሴት

ጥቅሱን ያንብቡ፡ ራእ. 1፡9፡፡ ዮሐንስ ራእዩን ስለ ተቀበለበት ሁናቴ ምን ይለናል?

---

---

በሜዲቴራንያን ባሕረ ሰላጤ ኤግያን ባሕር (በግሪክና በዛሬዋ ቱርክ መሃል) የምትገኘው ዐለታማዋ ፍጥሞ ደሴት 16 ኪሎ ሜትር ርዝመትና 9.6 ኪሎ ሜትር የጎን ስፋት ነበራት፡፡ ፍጥሞን ጨምሮ ዙሪያ ገባውን ደሴቶች በቅኝ ግዛት ያስተዳድሩ የነበሩት የያኔዎቹ ልዕለ ኃያል ሮማውያን የፖለቲካ ወንጀለኞች ያሏቸውን ወደ እነዚህ ደሴቶች በግዞት ይልኩ እንደ ነበር የታሪክ ድርሳናት ያረጋግጣሉ፡፡ የዮሐንስ ለወንጌል ታማኝ መሆን በሮም ባለ ሥልጣናት ትእዛዝ ወደ ግዞት እንዲላክ መንስኤ እንደነበር መጽሐፉ በተጻፈበት ዘመን አካባቢ የነበሩ ቀደምት ክርስቲያን ጸሐፊዎች በአንድ ይስማማሉ፡፡ አዛውንቱ ሐዋርያ በፍጥሞ ህይወቱ ሁሉንም ዓይነት የሮማውያን የእስር ጉስቁልና ማለፉ እሙን ነው፡፡ ምናልባትም እንደ ወንጀለኛ ተቆጥሮ በእግር ብረት እንዲታሠር፣ በቂ ምግብ እንዳያገኝና በእነዚያ ርኅራኄ ያልፈጠረባቸው ጨካኝ የሮም ዘቦች ጅራፍ ከባድ የጉልበት ሥራ እንዲሠራ ሳይገደድ እንዳልቀረ ይታመናል፡፡

"ዐለታማና ጠፍ ደሴት የሆነው ፍጥሞ፤ ወንጀለኞች እንዲጋዙበት በሮም መንግሥት ቢመረጥም--ተስፋ አስቆራጩና የጨገገው ስፍራ ለእግዚአብሔር አገልጋይ የሰማይ ደጃፍ መመልከቻ ሆነ፡፡ ከተለመደው በውጥረት የተሞላ ባተሌ የዕለት ከዕለት ህይወቱ ብሎም ከንቁ አገልጋይነቱ ፍጹም የተቆራረጠው ሐዋርያ--ከእግዚአብሔር፣ ከክርስቶስና ከሰማያዊ መላእክት ጋር አብሮነት በመፍጠር እስከ ምድር ታሪክ መዝጊያ ላለችው ቤተ ክርስቲያን የሚበጅ መመሪያ ተቀበለ፡፡"—Ellen G. White, The Acts of the Apostles, pp. 570, 571.

ለእግዚአብሔር ባላቸው ታማኝነት በአስቸጋሪ ሁናቴ እንዲያልፉ የተገደዱ ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ መሪ ተዋናይ እነማን ናቸው? ዳን. 3:16–23፣ ሐዋ. 7:54–60፡፡

---

---

የክርስቶስ ተከታዮች ራሳቸውን በየትኛውም እንደ ዮሐንስ ባለ አስቸጋሪ ሁናቴ ውስጥ ሊያገኙ ቢችሉ ብቻቸውን አለመተዋቸውን ፈጽሞ መርሳት የለባቸውም፡፡

ዮሐንስ በፍጥሞ በነበረበት ፈታኝ ሰዓት የተስፋና የማጽናኛ ቃል ይዞ ወደ እርሱ የመጣው የሱስ፤ ሕዝቡ አስቸጋሪ ሁናቴ ሲገጥመው ለመደገፍ ብሎም ለመርዳት በመካከላቸው ይሆናል፡፡

**ስለ ክርስቶስ *ሥቃይ* በመቀበል እና የራሳችንን የተሳሳተ ምርጫ ጨምሮ በሌላ ምክንያት *ሥቃይ* በመቀበል *መካከል ያለውን* ልዩነት *ማስተዋል* የምንችለው እንዴት ነው? ወይስ *ለማንኛውም* ነገር *ሥቃይ መቀበል መልካም* ጎን የለው ይሆን? በእያንዳንዱ ሁናቴ ጌታን *መታመን መማር* የምንችለው እንዴት ነው?**

## ሰኞ ታህሳስ 29

## በጌታ ቀን

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 1፡10፣ ዘፀ. 31፡13፣ ኢሳ. 58፡13፣ ማቴ. 12፡8፡፡ በጥቅሶቹ መሰረት የጌታ ቀን በሚል በግልጽ የተቀመጠው የትኛው ቀን ነው? ዮሐንስ ባሳለፋቸው በእነዚያ የመከራ የግዞት ዘመናት ዕለቱ ምን ያህል ለእርሱ ትርጉም ነበረው?

---

---

"የክብር ጌታ በግዞት ለነበረው ሐዋርያ የተገለጠው በሰንበት ዕለት ነበር፡፡ ዮሐንስ በይሁዳ ከተሞችና መንደሮች ይሰብክ እንደ ነበረው በፍጥሞ ሰንበትን በቅድስና ይጠብቅ ነበር፡፡ ዮሐንስ ስለዚያ ቀን የተሰጠውን የከበረ ተስፋ ሙሉ ለሙሉ አምኖ የተቀበለ ሰው ነበር፡፡"—Ellen G. White, The Acts of the Apostles, p. 581.

ሐዋርያው ዮሐንስ ራእዩን በሰባተኛው ቀን ሰንበት ስለ መቀበሉ ጥቅሱ ራሱ በግልጽ ይናገራል፡፡ ምንም እንኳ ራእዩ እስከ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ያሉ የወደፊት ክስተቶችን አሻግሮ ቢቃኝም (ራእ. 1፡7) ነገር ግን ዮሐንስ የሚጠቅሰው እርሱ ራሱ የወደፊቱን ክስተት የሚገልጸውን ራእይ የተቀበለበትንና በተጨማሪ "የጌታ ቀን" (ኢሳ. 13፡6-13፣ 2ጴጥ. 3፡10) በሚል የሚታወቀውን የሰንበት ዕለት ነው፡፡

ዮሐንስ በዚያ አስከፊ ሁናቴ ውስጥ ሆኖ ከዳግም ምጽአቱ በኋላ እርሱና በዘመናት ታማኝ ሆነው የኖሩ ወገኖች የሚኖሩትን ራእይ በሰንበት መመልከቱ፤ በመጠኑም ቢሆን ከሥቃይ ነጻ የሆነውን ህይወት እንዲያጣጥም መርዳቱ እሙን ነው፡፡ እርግጥ ነው ሰንበት በአይሁዳውያን እሳቤ የመጪው ዓለም አላምባ ወይም ቅድመ ልምድ ነው፡፡

"እግዚአብሔር በኤድን ገነት ያቋቋመው የሰንበት ቀን... በሰው ዐልባዋ ደሴት ለነበረው ዮሐንስ የከበረ ዕለት ነበር።

"በክርስቶስ ዐይን ሁሌም የከበረውና አሁን ደግሞ በዚህ ትዕይንት ተጨማሪ ሞገስ ያገኘው ሰንበት--ብቸኝነት ያንከላውሰው ለነበረው ዮሐንስ እንዴት ያለ ዕለት ሆኖለት ይሆን! ከዚያ በፊት እንዲህ ዓይነት ዕውቀት ስለ የሱስ ኖሮትም ሆነ ይህን እውነት ሰምቶ አያውቅም፡፡"—Ellen G. White Comments, The SDA Bible Commentary, vol. 7, p. 955.

በአራተኛው ትእዛዝ ዙሪያ በዘፀ. 20፡11 እና ዘዳ. 5፡15 የቀረቡትን ሁለቱን ሐተታዎች ያመሳክሩ፡፡ ጥቅሶቹ እግዚአብሔር ፈጣሪያችንና ቤዛችን መሆኑን እያወሱ የፍጥረት ብሎም የመዋጀታችን መታሰቢያ የሆነውን ሰባተኛውን ቀን ያስታውሱናል፡፡

***እግዚአብሔር ፈጣሪያችንና አዳኛችን መሆኑን በተጨባጭ ተገንዝበን እያንዳንዱን ሰንበት በተሻለ መጠበቅ የምንችለው እንዴት ነው? እግዚአብሔር ፈጣሪያችን ከመሆን ውጪ አዳኛችን ባይሆን ኖሮ መልካምነቱ እንዴት መገለጥ ይችል ነበር?***

## ማክሰኞ ታህሳስ 30

# ክርስቶስን በፍጥሞ ደሴት መገናኘት

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 1፡12-18፡፡ ዮሐንስ ክርስቶስን ያሳየበትን መንገድ በዳን. 10፡ 5-6 ከቀረበው መለኮታዊ ባህሪ ጋር ያመሳክሩ፡፡ የሱስ በራእዩ የቀረበበት መንገድ ምን ይመስላል? ምን እያደረገ ነው?

---

---

ዮሐንስ በልብሰ ተክኅኖ የተሸለመውን የሱስ በመቅረዞቹ መካከል ተመለከተ፡፡ ራእዩ መቅረዞች ብርሃን የሚፈነጥቁበትን የጥንቱን የእስራኤል መቅደስ ያሳያል (1ነገሥ. 7፡49)፡፡ የሱስ በመቅረዞቹ መካከል መራመዱ እግዚአብሔር አምላካቸው ሆኖ በመካከላቸው እንደሚመላለስ ለጥንት እስራኤላውያን የገባውን ኪዳን ያመለክታል (ዘሌዋ. 26፡12)፡፡ በራእይ መጽሐፍ የቀረቡት መቅረዞች መልእክቱ በቀዳሚነት የተጻፈላቸውን በእስያ ይገኙ የነበሩ ሰባቱን አብያተ ክርስቲያናት ይወክላሉ (ራእ. 1፡20)፡፡ የየሱስ በመቅረዞቹ መካከል መራመድ፡ ሕዝቡን ወደ ዘላለማዊው ቤት እስኪያመጣ ድረስ ሁሌም ከእነርሱ ጋር እንደሚሆን ለእስራኤል የሰጠውን የተስፋ ቃል ፍጻሜ ያመለክታል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የየሱስ በመቅረዞቹ መካከል መራመድ ከየሩሳሌም ቤተ መቅደስ አምልኮአዊ ሥርዓት ጋር ትስስር አለው፡፡ መቅረዙ በቅዱሱ ስፍራ ፍንትው ብሎ እንዲበራ ጥንቃቄ ማድረግ የካኅኑ ዕለታዊ ተግባር እንደ መሆኑ እያንዳንዱን መቅረዝ በሚገባ አያስተካከለና ዘይት እየሞላ ብርሃን መስጠታቸው እንዳይቋረጥ ይተጋል፡፡ ይህም ካህኑ የእያንዳንዱን መቅረዝ ሁናቴ በሚገባ እንዲያስተውል ያስችለዋል፡፡ በተመሳሳይ የሱስ በእነዚያ አብያተ ክርስቲያናት ብቻ ሳይገደብ--ሁሉም የሚያስፈልጋቸውን ነገርም ሆነ የሚገኙበትን ሁናቴ በግል ያውቃል፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 2፡2፣9፣13፣19፣ 3፡1፣8፣15፡፡ "ዐውቃለሁ" የተሰኘው ቃል የሱስ በእነዚህ አብያተ ክርስቲያናት የሚገኙ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ስላሉበት ሁናቴም ሆነ ስለሚያስፈልጋቸው ነገር ዕውቀት እንዳለው ምን ይነግረናል?

---

---

የሱስ በእግዚአብሔር መገለጫ ማዕረግ የሚታወቀውን ሃረግ ራሱን ሲገልጥበት ይስተዋላል "የፊተኛውም እኔ ነኝ፤ የኋለኛውም እኔ ነኝ" (ኢሳ. 44፡6፣ 48፡12)፡፡ "የኋለኛው" የሚለው ቃል በግሪክኛው ኢሻቶስ "የዘመን መጨረሻ" የሚል ፍቺ አለው፡፡ አባባሉ የመጨረሻው ዘመን ትኩረት--በመጨረሻዎቹ ክስተቶች ላይ የመጨረሻ ቃል ባለቤት የሆነው የሱስ ክርስቶስ መሆኑን ያሳየናል፡፡ እርሱ "ሕያው" ነው "የሞትና የሲኦል መክፈቻም" በእጁ ነው (ራእ. 1፡18)፡፡ ቁልፍ--የኃይልና የሥልጣን ተምሳሌት ነው፡፡ የጠፉት እንኳ በእርሱ ጥበቃና ጥንቃቄ ስር እንደመሆናቸው የጌታ ታማኝ ተከታዮች አንዳችም ፍርሃት ሊያድርባቸው አይገባም፡፡ እርሱ ለሙታን እንዲያ ከሆነ ታዲያ ለሕያዋን ምን ያህል የላቀ ይሆን! (ማቴ. 22፡32)፡፡

**ረቡዕ** **ጥር 1**

## የክርስቶስ መልእክት ለያኔ እና ለዛሬ

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ.1፡11፣ 19-20፡፡ እንዲሁም የሱስ በዮሐንስ አማካይነት በእስያ ለነበሩት ሰባት ቤተ ክርስቲያኖች የተለየ መልዕክቶች ሰጥቶ ነበር፡፡ በአውራጃው ከሰባት በላይ አብያተ ክርስቲያናት የመኖራቸው ሐቅ መልእክቱ በአጠቃላይ ለክርስቲያኖች ያለውን ተምሳሌታዊ አንደምታ ምን ያደርገዋል?

---

---

ዮሐንስ ለሰባቱ ቤተ ክርስቲያኖች እንዲልክ በየሱስ የተሰጡት መልእክቶች በምዕ. 2እና 3 የሚገኙ ሲሆን ትርጉማቸውም በሦስት ቅደም ተከተሎች መተግበር ይችላል፡፡

ታሪካዊ አንደምታ፡ መልእክቶቹ በቅድሚያ የተላኩት በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን በእስያ ለነበሩ በምጣኔ ሐብት የበለጸጉ ከተሞች ነበር፡፡ በዚያ ይኖሩ የነበሩ ክርስቲያኖች ብርቱ ተግዳሮቶች ገጥመዋቸዋል፡፡ ሕዝቡ ለሮም ልዕለ ኃያል መንግሥት ታማኝነቱን ያሳይ ከነበረባቸው አስገዳጅ ሥርዓቶች አንዱና ዋንኛው በአረማውያን ቤተ አምልኮ ለንጉሡ ይደረግ የነበረ ስግደት ነበር፡፡ በተጨማሪ ዜጎች በሕዝባዊ ሥነ ስርዓቶችና በአረማውያን የባዕድ አምልኮ መርኅ ግብሮች ተሳትፎ ማድረግ ይጠበቅባቸው ነበር፡፡ ሆኖም አያሌ ክርስቲያኖች በዚህ አምልኮ ሥርዓት ተካፋይ ለመሆን በመቃወማቸው ሥቃይ ይደርስባቸዋል፣ አልፎ አልፎም የሰማዕትነት ሞት ለመቀበል ይገደዱ ነበር፡፡ እነዚህ ወገኖች ይገጥሟቸው ለነበሩ ፈታኝ ሁኔታዎች እገዛ ይሆን ዘንድ በክርስቶስ የታዘዘው ዮሐንስ ሰባቱን መልዕክቶች ጻፈ፡፡

ትንቢታዊ አንደምታ፡ የራእይ መጽሐፍ ትንቢታዊነት እሙን ቢሆንም ነገር ግን እነዚህን መልእክቶች እንዲቀበሉ የተመረጡት ሰባት ቤተ ክርስቲያኖች ብቻ ነበሩ፡፡ ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ይገኙበት የነበረው መንፈሳዊ ሁናቴ በተለያዩ ዘመናት ከኖሩ የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያኖች ጋር ስምሙ ነው፡፡ ሰባቱ መልእክቶች--በሰማያዊው ዕይታ ከመጀመሪያው ክፍለ ዘመን አንስቶ እስከ ምድር ታሪክ መዝጊያ ያለውን የክርስትና ሁናቴ አጠቃላይ ቅኝት ለማሳየት ቀርበዋል፡፡

ዓለማቀፋዊ አንደምታ፡ ምንም እንኳ መልእክቱ በቀዳሚነት የተላከው በእስያ ለነበሩ አብያተ ክርስቲያናት ቢሆንም፤ እነዚህ ሰባት መልእክቶች በተለያዩ ዘመናት ለሚገኙ ክርስቲያኖች መተግበር የሚችሉ ትምህርቶችን ይዘዋል፡፡ በየቤተ ክርስቲያኖቹ እንደ አንድ ደብዳቤ እንዲነበቡ ሆነውም ተልከዋል (ራእ. 1፡11)፡፡ በዚህ መልኩ በተለያዩ ቦታዎችና ጊዜዎች የሚኖሩ የተለያዩ ክርስቲያኖችን ይወክላሉ፡፡ ለምሳሌ የዚህ ዘመኑ ክርስትና አጠቃላይ ባህሪ በላውዶቅያ የሚጠቃለል ቢሆንም የአንዳንድ ክርስቲያኖች መለያ ግን ከዚህ ውጪ ነው፡፡ የትኛውም ዓይነት መንፈሳዊ ሁናቴ ላይ ልንገኝ ብንችል እንኳ ሰብዓዊው ፍጡር በሚኝገበት ሁኔታ እግዚአብሔር የሚገናኘው መሆኑ መልካም የምስራች ነው፡፡”—Ellen G. White, Selected Messages, book 1, p. 22.

*ጌታ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንዎ እየገጠሟት ስለሚገኙ ተግዳሮቶችና መንፈሳዊ ሁናቴዋ ደብዳቤ ቢጽፍ የመልእክቱ ይዘት ምን ሊሆን ይችላል?*

## ሐሙስ ጥር 2

## በኤፌሶን ለምትገኘው ቤተ ክርስቲያን የተሰጠ መልእክት

በዋንኛ የንግድ መናኸሪያ መስመር ላይ ትገኝ የነበረችው ኤፌሶን በሮም ስር ትተዳደር የነበረችው የእስያ አውራጃ መዲና ነበረች፡፡ በእስያ ቀዳሚ የባህር ወደብ መሆኗ ቁልፍ የንግድና የኃይማኖት ማዕከል አድርጓት ነበር፡፡ ከተማዋ በነዋሪዎቿ ቤቶች፣ ቴያትር ቤቶች፣ ጂምናዚየሞች፣ መታጠቢያ እና ግልሙትና ቤቶች የተሞላች ነበረች፡፡ ኤፌሶን በአስማት እና በሥነ ጥበብ የታወቀች ነበረች፡፡ በተጨማሪ ከተማዋ የብልሹ ሥነ ምግባር አጉል ስምና ዝና ቢኖራትም፤ የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን በአውራጃው ብርቱ ተጽእኖ ነበራት፡፡

*ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 2፡1-4፣ ኤር. 2፡2፡፡ የሱስ ራሱን ለዚህች ቤተ ክርስቲያን ያቀረበበት መንገድ ምን ይመስላል? ምስጋናውን እንዲቸር ያደረገው ላቅ ያለ ተግባር ምንድን ነው? ሥጋቱስ?*

---

---

---

ቀደም ባሉት ቀናት ኤፌሶናውያን በታማኝነታቸውና በፍቅራቸው ይታወቁ ነበር (ኤፌ. 1፡15)፡፡ ምንም እንኳ ከቤተ ክርስቲያን ውጪም ሆነ ከውስጥ ጫና እና ግፊት ቢበረታባቸውም እነርሱ ግን በጽናትና በታማኝነት መዝለቅ ችለው ነበር፡፡ የኤፌሶን ክርስቲያኖች ጠንካራ ሠራተኞችና ያልተበረዘውን ኃይማኖታዊ አስተምህሮ የሚከተሉ እንደመሆናቸው በሐሰተኛ ምሁራንን ላይ የነበራቸው አቋም ጽኑ ነበር፡፡ ሆኖም አግባብ ላለው አስተምህሮ አጽንኦት የሚሰጡና ለቀጥተኛው እምነት ብሎም አስተሳሰብ ገጣሚ ባህሪ ቢኖራቸውም፤ ለክርስቶስ እና ለእምነት ተጓዳኞቻቸው የነበራቸው ፍቅር ግን እየተዳከመ መሄድ ጀመረ፡፡ ምንም እንኳ ሕዝቡ በእምነቱ ጥብቅና ታማኝ ቢሆንም፤ ያ ፍቅር የሌለበት ሥራቸው ቀዝቃዛና ሕግ ጠባቂ ብቻ አድርጎአቸው ቀረ፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 2፡5-7፡፡ የዚህች ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን የቀደመው የእርስ በርስ ፍቅራቸውና ለክርስቶስ የነበራቸው ታማኝነት ዳግም ሕይወት ይዘራ ዘንድ የሱስ አጥብቆ ያስገነዘባቸው ሦስት ነገሮች ምንድን ናቸው? እነዚህ ሦስት ነጥቦች እንደየ ቅደም ተከተላቸው ያላቸው ዝምድና ምንድን ነው?

---

---

ከትንቢቱ አኳያ በኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን የተስተዋለው ሁናቴ በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ከነበረችው ቤተ ክርስቲያን አጠቃላይ መንፈሳዊ ገጽታ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ የቀደመችው ቤተ ክርስቲያን በፍቅሯና ለወንጌል በነበራት ታማኝነት ትታወቅ ነበር፡፡ ሆኖም በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን መገባደጃ ላይ ቤተ ክርስቲያኗ ከወንጌል ንጽህናና ግልፅነት እየራቀች በመሄዷ የቀደመውን የሞቀ ፍቅሯን ማጣት ጀመረች፡፡

**ፍቅሩ እየደበዘዘና እየተዳከመ ይሄድ እንደ ነበረው የዚያ ጉባዔ አባል አድርገው ራስዎን ያስቡ፡፡ በእርግጥ አባላት ምንም ዓይነት የሚታወቅ ወይም ግልጽ ኃጢአት ላይሠሩ ይችላሉ፡፡ በአንድ በኩል ትክክል የነበረውን ነገር እያደረጉ ቢሆንም በሌላ በኩል ግን ቀዝቃዛና ፌደላውያን ብቻ የመሆንን ቁልቁለት ተያይዘውት ነበር፡፡ የሱስ በዚህ ቦታ የሰጠው ምክረ ሃሳብ ቤተ ክርስቲያንን ከዚህ ሁናቴ ነፃ ማድረግ የሚችለው እንዴ ነው?**

## አርብ ጥር 3

ተጨማሪ ሀሳብ፡ Read Ellen G. White, “Patmos,” pp. 568–577, in The Acts of the Apostles.

“በዮሐንስ ላይ የደረሰው ስደት የአምላካዊው ጸጋ ዓይነተኛ መንገድ ለመሆን በቃ፡፡ የትንሳዔ ባለቤት የሆነው የአዳኙ ክብር ፍጥሞን አንጸባራቂ አደረጋት፡፡ ዮሐንስ--የእጆቹና የእግሮቹ ጠባሳ ክብሩ የሆነውንና ለዘላለም አብሮት የሚኖረውን ክርስቶስ ቀደም ብሎ ተመልክቶት እንደ ነበር ሁሉ፤ አሁን ደግሞ ሰብዓዊው ዐይኖች እርሱን ተመልክተው በሕይወት መቀጠል የሚችሉትን ያህል ክብር የተጎናጸፈውን የትንሳዔ ባለቤት ጌታውን እንዲመለከት ተፈቀደለት፡፡

“ለዮሐንስ የተገለጠውና በተጨባጭ የቀረበው ከሞት የተነሳው ክርስቶስ ማስረጃ ለሐዋርያው ብቻ ሳይሆን ለመላው አማኝም ሆነ ኢአማኒ ሊሆን ይገባል፡፡

ለቤተ ክርስቲያን ሕያው ኃይል ሊያጎናጽፉት ይገባል፡፡ አንዳንዴ ጭቆናና ስደት የእግዚአብሔርን ሕዝቦች ከምድረ ገጽ የሚያጠፉቸው እስኪመስል ድረስ በድቅድቅ ጨለማ ደመናዎች እስከ መዋጥ የደረሱባቸው ጊዜያቶች ነበሩ፡፡ ሆኖም በእነዚህ ጊዜያቶች ውስጥ በዓይነታቸው ልዩ የሆኑና አማኞችን የሚያንጹ ትምህርቶች ተሰጥተዋል፡፡ ክርስቶስ በተደጋጋሚ ወህኒ እየገባ ራሱን ለተመረጡ ወገኖች ገልጦአል፡፡ ወደ እሳት የመጣል አደጋ ሲገጥማቸው አብሮአቸው አለ፡፡ የከዋክብት ብርሃን ድቅድቁን ሌሊት ወገግ እንደሚያደርግ ሁሉ፤ ጨፍጋጋ በሆነው ሁናቴ እጅግ ደማቅ አምላካዊ ጨረሮች ተገልጠዋል፡፡ ሰማዩ በጨለመ ቁጥር የትንሣኤው አዳኝ የጽድቅ ፀሐይ ጨረሮች አብልጠው ግልጽና መሳጭ ይሆናሉ፡፡”—Ellen G. White, The Youth'sInstructor, April 5, 1900.

# የመወያያ ጥያቄዎች

**1.ባለ ራእዩ ዮሐንስ በፍጥሞ የተመለከተውንና የሰማውን ለአንባቢዎቹ ያጋራል፡፡ እርስዎ በራእ. 1፡12-20 የሚመለከቱትና የሚሰሙት ነገር ምንድን ነው? በዚህ ከተገለጠ መልእክት ምን ዓይነት የመጽናኛ ቃላት ማግኘት ይችላሉ?**

**2.በመጨረሻው ዘመን የሚገኙ የምድር ሕዝቦች “ሰማይንና ምድርን፣ ባሕርንና የውሃ ምንጮችን ለፈጠረው” ይሰግዱ ዘንድ የመጀመሪያው መልአክ በራእ. 14፡7 አጥብቆ ያስገነዝባል፡፡ ይህ አነጋገር ከዘፀ. 20፡11 የተወሰደ ነው፡፡ በራእይ መጽሐፍ በተገለጠው መሰረት ይህ በመጨረሻው ዘመን ስለ ሰንበት በተሰጠው አጽንኦት ዙሪያ ምን ይነግረናል?**

**3.አያሌ ክርስቲያኖች እየተጋፈጡት ያለ ዕንግዳ ምጸታዊ ነገር ያለ ሲሆን ይኸውም ሰዎች በቤተ ክርስቲያን በቆዩ ቁጥር እምነታቸው እየመነመነ ይሄዳል ወይም ከነአካቴው ይጠፋል፡፡ ይህ በእርግጥ መሆን የነበረበት በተቃራኒው ነበር፡፡ ከየሱስ ጋር አብልጠን በተጓዝን ቁጥር ስለ እርሱ አብልጠን ልንማርና ለእኛ ያለውን ፍቅር ልናውቅ የግድ ነው፡፡ ታዲያ የእምነት እሳት መንደድ ብቻ ሳይሆን ይበልጥ እየተንቀለቀለ እንዲሄድ ማድረግ የምንችለው እንዴት ነው?**

## 3ኛ ትምህርት

**ከጥር 4-10**

# በከተሞች ውስጥ የሚኖሩ የእግዚአብሔር ሕዝቦች

ሰንበት ከሰዓት

ለዚህ ሣምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ራእ. 2፡8-11፤ 3:7–11፤ 2:12–17፤ 14:12፤ 2:18–29፤ 3:1–6፤ 3:14–22፤ ኢሳ. 61:10፡፡

**መታሰቢያ ጥቅስ :-** “ ‘መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚናገረውን ጆሮ ያለው ይስማ’ ” (ራእ. 3፡22)፡፡

የሱስ ፍጥሞ በነበረው ዮሐንስ በኩል ሰባት መልእክቶች የያዘውን መልእክት ለሕዝቡ ላከ፡፡ ምንም እንኳ የመልእክቶቹ ቀዳሚ ጭንቀት በዮሐንስ ዘመን በእስያ የነበሩት አብያተ ክርስቲያናት ቢሆኑም፤ መልእክታቸው እስከ ምድር ታሪክ መደምደሚያ የሚኖሩ ክርስቲያኖችን ያካትታል፡፡

መልእክቶቹ እርስ በርስ ሲመሳከሩ ሁሉም አንድ ዓይነት አወቃቀር መከተላቸውን እንመለከታለን፡፡ በሁሉም መልእክቶች መግቢያ የሱስ እያንዳንዱን ቤተ ክርስቲያን በስም ይጠራል፡፡ በቀጣይ ደግሞ “ ‘ “እንዲህ ይላል…” ’ ” የሚል ሃረግ ይከተላል፡፡ የሱስ ገላጭ ባህሪዎችን ተጠቅሞ ራሱን ለእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን የሚያስተዋውቅበት መንገድ በምዕራፍ አንድ ይገኛል፡፡ እነዚህ የሱስ የተጠቀማቸው መግለጫዎች የእያንዳንዱን ቤተ ክርስቲያን ጉድለት ማሳየታቸውና በትክክል ገጣሚ መሆናቸው፤ የተለያዩ የዕለት ከዕለት ትግልና አስቸጋሪ ሁናቴዎችን ለመፍታት ያለውን ክህሎት ያመላክታል፡፡ በመቀጠል የሱስ ቤተ ክርስቲያኗ የምትገኝበትን ሁናቴ ካመዛዘነ በኋላ እንዴት ከገጠማት አስቸጋሪ ሁናቴ መውጣት እንደምትችል ምክረ ሃሳብ ይለግሳል፡፡ በመጨረሻ፤ ቤተ ክርስቲያን መንፈስ የሚያቀርብላትን ተማጽኖ እንድትሰማ ጥሪ በማድረግ እና ለአሸናፊዎች በተሰጠው የተስፋ ቃል--እያንዳንዱ መልእክት ይደመደማል፡፡

መልእክቶቹን ለማጤንና ለመመርመር ስንሞክር ቤተ ክርስቲያን በየትኛውም ሁናቴ ውስጥ ብትገኝ፤ የሱስ እያንዳንዱን ችግሯን የመረዳትና መፍትሔ የማምጣት ክህሎት እንዳለው እንመለከታለን፡፡ እርሱ በእርግጥ ዛሬ እየገጠሙን ላሉ ችግሮችም ሆነ ተግዳሮቶች መፍትሔ አለው!

## እሑድ ጥር 5

# ክርስቶስ ለሰምርኔስ እና ጴርጋሞን አብያተ ክርስቲያናት የላከው መልእክት

የሱስ በሁለተኛና በስድስተኛ ቅደም ተከተል የላካቸው መልእክቶች በቀዳሚነት የተላኩት ለስምርኔስ እና ፊላደልፊያ አብያተ ክርስቲያናት ነበር፡፡ እነዚህ ሁለት ቤተ ክርስቲያኖች ከየሱስ የተቀበሉት ግሳጼ አልነበረም፡፡

ሰምርኔስ ውብና ባለጠጋ ከተማ ከመሆኗ በተጨማሪ ለንጉሠ ነገሥቱ አምልኮ የሚቀርብባት ማዕከላዊ ስፍራ ነበረች፡፡ ይህን በገዢው መደብ የተደነገገ የአምልኮ ሕግ መቃወም ለስደት ብሎም ሰማዕትነት ሞት ይዳርግ ነበር፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡--ራእ. 2፡8-11፡፡ የሱስ ራሱን ለዚህች ቤተ ክርስቲያን ያቀረበበት መንገድ ከተቋሟ ሁናቴ ጋር እንዴት ይዛመዳል? ቤተ ክርስቲያኒቱ ትገኝበት የነበረው ሁናቴ ምን ይመስላል? እየመጣ ስለነበረው ነገር ለዚህች ቤተ ክርስቲያን የሰጠው ማስጠንቀቂያ ምን ነበር?

---

---

በሰምርኔስ ለነበረችው ቤተ ክርስቲያን የተሰጠው መልእክት ክርስቲያኖች አሰቃቂውን የስደት ገፈት የቀመሱበትን ድኅረ ሐዋርያት ዘመን ያመለክታል፡፡ በራእ. 2፡10 "ዐሥር ቀን" በሚል የተጠቀሰው ሃረግ በዲዮክሊታን ትእዛዝ 303 ዓ.ም. ላይ ተጀምሮ እስከ 313 ዓ.ም. የዘለቀውን የዐሥር ዓመት የስደት ጊዜ የሚያመለክት ሲሆን፤ ትእዛዙ የተሻረው ታላቁ ቆስጠንጢኖስ የሚላን ዐዋጅ በሚል መጠሪያ የሚታወቀውንና ለክርስቲያኖች የኃይማኖት ነፃነት የሰጠበትን ድንጋጌ ባጸደቀበት ወቅት ነበር፡፡

ከየሱስ መልእክት የተላከባት ስድስተኛዋ ቤተ ክርስቲያን የምትገኘው በፊላድልፍያ ("ወንድማማቻዊ ፍቅር") ነበር፡፡ ከተማዋ የታነጸችው በንጉሠ ነገሥታዊው የንግድ ጎዳና ሲሆን መላውን ምስራቃዊ ክፍል ከምዕራባዊው አውራጃ ጋር የምታስተሳስር

ነበረች፡፡ የተቆረቆረችውም በሊዲያ እና ፍሪግያ አካባቢዎች የግሪክን ቋንቋና ባህል ለማበልጸግ በሚል እሳቤ ነበር፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 3፡7-13፡፡ የሱስ ራሱን በዚህ መልእክት ውስጥ የሚያቀርብበት መንገድ ከዚህች ቤተ ክርስቲያን ሁናቴ ጋር ያለው ዝምድና ምን ይመስላል? የሱስ "ኀይልህ ትንሽ እንደ ሆነ ዐውቃሁ" (ራእ. 3፡8) ብሎ መናገሩ ቤተ ክርስቲያኒቱ ስለምትገኝበት ሁናቴ ምን ይነግረናል? የሱስ ለዚህች ቤተ ክርስቲያን የሚሰጠው የተስፋ ቃል ምንድን ነው?

---

---

ለዚህች ቤተ ክርስቲያን የተሰጠው መልእክት በዐሥራ ስምንተኛውና ዐሥራ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከተስተዋለው ታላቅ የተሐድሶ እንቅስቃሴ ጋር ገጣሚ ነው፡፡ እነዚህ ወገኖች በእርግጥም የነበራቸውን ብርሃን ሰጥተዋል፤ ቃሉንም ጠብቀዋል (ራእ. 3፡8)፡፡ በዚህ ዘመን የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ወንጌልን ለዓለም ለማዳረስ ከልብ በመነጨ ቅንአት መገፋፋቷን ተከትሎ--ከጴንጤቆስጤ አንስቶ ያልታየ ግዙፍ የወንጌል ስርጭት ገቢራዊ መሆን ቻለ፡፡

**ሰኞ** **ጥር 6**

## ክርስቶስ በጴርጋሞን ለነበረችው ቤተ ክርስቲያን የላከው መልእክት

ጴርጋሞን "አዳኝ" በሚል ስያሜ የሚጠራውንና በእባብ የሚወከለውን አስሊፒየስ--የግሪክ የፈውስ አምላክ ጨምሮ የአያሌ የቤተ ጣዖት አምልኮ ማዕከል ነበረች፡፡ ብዙዎች ፈውስ ፍለጋ የተቀደሰ ብለው ወደሚጠሩት አስሊፒየስ ይጎርፉ ነበር፡፡ እንደ ስምርኔስ ሁሉ ጴርጋሞን ለንጉሡ ነገሥቱ ይቀርብ ለነበረው የግዳጅ ሥርዓተ አምልኮ የመሪነቱን ሚና ትጫወት ነበር፡፡ በጴርጋሞን ከተማ ይኖሩ የነበሩ ክርስቲያኖች "የሰይጣን ዙፋን ባለበት" እንደሚኖሩ በጥቅሱ መቅረቡ ከዚህ አኳያ እምብዛም የሚገርም አይሆንም፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 2፡14-15፡፡ የሱስ ራሱን ለዚህች ቤት ክርስቲያን ያቀረበበት መንገድ ምን ይመስላል? ቤተ ክርስቲያኒቱ ስለምትገኝበት መንፈሳዊ ሁኔታ ያቀረበውስ ቅኝት?

---

---

በባዕድ አምልኮና በታላላቅ ቤተ ጣዖቶቿ ተከብባ በነበረችው በጴርጋሞን ይኖሩ የነበሩ ክርስቲያኖች ከቤተ ክርስቲያን ውጪም ሆነ በራሷ በቤተ ክርሰቲያኗ ውስጥ የሚነሱ ብርቱ ፈተናዎችን መጋፈጥ ግድ ሆኖባቸው ነበር፡፡ ምንም እንኳ አብዛኞቹ ክርስቲያኖች በታማኝነታቸው ቢጸኑም ነገር ግን ኒኮላይቲያንስ በመባል ይጠሩ የነበሩ ጥቂቶች ሊደርስባቸው ከሚችል ስደት ለመጠበቅ ከአረማዊ አምልኮ አራማጆች ጋር ሊያስታርቁ የሚችሉ ሀሳቦችን ያቀነቅኑ ነበር፡፡ በተጨማሪ ከበለዓም በኋላ በመባል ይታወቅ ከነበረ ሌላ ውጉዝ ቡድን ጋር ትስስር ፈጥረው ነበር፡፡ በለዓም እስራኤላውያን ወደ ተስፋው ምድር ያደርጉ በነበረው ጉዞ ለከፉ ሥራው ያባበለ ግለሰብ ነበር (ዘኁ. 31፡16)፡፡ እነዚህ ሁለት ቡድኖች ምቾት ነሺውን ስደት ለማስወገድ በማሰብ ከባዕድ አምልኮ አራማጆች ጋር ስምምነት በመፍጠሩ ዙሪያ ያቀነቅኑ ነበር፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 2፡16-17፡፡ አማኞች የሚገኙበትን መንፈሳዊ ሁናቴ ለማሻሻል ማድረግ በሚኖርባቸው ነገሮች ዙሪያ የሱስ ቤተ ክርስቲያንን አጥብቆ ያሳሰበው ነገር ምንድን ነው? ምን ዓይነት ተስፋዎች ሰጣቸው?

________________________________________

________________________________________

________________________________________

ለጴርጋሞን ቤተ ክርስቲያን የተሰጠው መልእክት ተቋሟ ከ313 ዓ.ም. በኋላ ትገኝበት የነበረውን ሁናቴ በተገቢው መንገድ ይገልጣል፡፡ ምንም እንኳ ክርስትና ከባዕድ አምልኮ ጋር የነበረውን ትግል በአሸናፊነት ቢወጣም፤ ብዙዎች የቤተ ክርስቲያን ሰዎች ግን ከአረማውያን ጋር ስምምነት መፍጠር ጀመሩ፡፡ በእርግጥ አንዳንዶች በወንጌል ላይ የነበራቸው አቋም የማያወላዳና ለቃሉ ታማኝ ቢሆኑም በእነዚያ በአራተኛው እና በአምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመኖች መንፈሳዊ ቁልቁለትና ክህደት ተስተውሎአል፡፡

**"በእኔ ያለህን እምነት አልካድክም" (ራእ. 2፡13፣ 14፡12) ሲል ምን ማለቱ ነው? አባባሉ ወደ ስምምነት እንድናመራ ተጽእኖ ሊያደርጉ የሚችሉ እንደ ሞት ያሉ አስፈሪ ፈተናዎች ቢገጥሙን እንኳ--ስለ እምነት ጅማሮ ብሎም እምነትን አጥብቆ ስለመያዝ ቅዱስ የውዴታ ግዴታ ምን ይነግረናል?**

## ማክሰኞ ጥር 7

# ክርስቶስ በትያጥሮን ለነበረችው ቤተ ክርስቲያን የላከው መልእክት

ትያጥሮን ከሌሎቹ ከተሞች ጋር ስተወዳደር በዘመኗ እዚህ ግባ የሚባል ፖለቲካዊም ሆነ ባህላዊ ግዝፈት ባይኖራትም በንግድ ቀጠናነት ግን ትታወቅ ነበር፡፡ ሰዎች ገቢ የሚያስገኝ ሥራ ለመሥራት ከንግድ ጋር ቁርኝት ያላቸው ማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች ማድረግ ነበረባቸው፡፡ አባላት በልዩ ልዩ ማኅበራዊ ፌስቲቫሎችና ባብዛኛው ግብረገብነት በጎደላቸው የቤተ ጣዖት ሥርዓቶች መሳተፍ ይጠበቅባቸው ነበር፡ ፡ በእነዚህ ተግባራት ለመሳተፍ ፈቃደኞች የማይሆኑ ከማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች የመገለልና የኢኮኖሚ ዕቀባ ይጠብቃቸዋል፡፡ በከተማዋ ይኖሩ የነበሩ ክርስቲያኖች ከሰጥቶ መቀበል እና ለወንጌል ታማኝ ሆኖ ከመዝለቅ አንዱን መምረጥ ነበረባቸው፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 2፡18-29፡፡ የሱስ ራሱን ለእነዚህ ሕዝቦች ያቀረበበት መንገድ ምን ይመስላል? (ዳን. 10፡6) የሱስ ንጽህናቸው እንዲጠበቅ ለቤተ ክርስቲያን አደራ ያላቸው ነገሮች ምን ነበሩ? ይህን ጉዳይ ያናወጠውስ ጉዳይ ምን ነበር?

---

---

እንደ ጴርጋሞን ቤተ ክርስቲያን ሁሉ በትያጥሮን የደረሰው አስጊ ሁናቴ መንስዔ ከባዕድ አምልኮ ጋር የተደረሰ የልከክልህ እከክልኝ መታረቂያ ሃሳብ ነበር፡፡ "ኤልዛቤል" በመባል የሚታወቀው ስያሜ እስራኤልን ወደ ክህደት የመራችውን የንጉሥ አክዓብን ሚስት ይወክላል (1ነገሥ. 16፡31-33)፡፡ የሱስ በመንፈሳዊ ግልሙትና የሚስላትን ኤልዛቤል ትምህርት እንደ ዋዛ የሚያልፉ ከእርሷ ጋር መንፈሳዊ ምንዝር ይፈጽማሉ፡፡

በትያጥሮን ቤተ ክርስቲያን የተገለጸው አጠቃላይ ሁናቴ በመካከለኛው ዘመን የነበረውን የቤተ ክርስቲያን ገጽታ ይወክላል፡፡ በቤተ ክርስቲያን ላይ ይረሰው አደጋ የመጣው ከውጪ ሳይሆን ሥልጣናቸውን ከእግዚአብሔር እንደ ተቀበሉ ይናገሩ በነበሩ የኃይማኖት መሪዎች ነው፡፡ በዚያን ወቅት መጽሐፍ ቅዱሳዊው እውነት በወግ እና ልማድ ተተካ፡፡ ሰብዓዊ ክኅነት እና ቅዱሶቹ ኃይማኖታዊ ጉዳዮች የክርስቶስን ክኅነት ተክተው ወሰዱ፡፡ ሥራ እንደ ደኅንነት ማግኛ መንገድ ታየ፡፡ የተቋማዊውን ቤተ ክርስቲያን ብልሹ ተጽእኖ ለመቀበል ፈቃደኞች ያልሆኑ ስደት፣ ከዚያም አልፎ ሞት ደረሰባቸው፡፡ በዚህ የተነሳ ወንጌል ለአያሌ ምዕተ ዓመታት (ዳን. 7፡25) ተዳፍኖ ኖረ፡፡

***ስለነዚህ ቃላት አሰብ ያድርጉ፡ “ ‘ብቻ እኔ እስክመጣ ድረስ ያላችሁን አጥብቃችሁ ያዙ’ ” (ራእ. 2፡25)፡፡ ቃላቶቹ በጋራም ሆነ በግል ምን ትርጉም አላቸው? ይህ አጥብቀን ልንይዘው የሚገባ ከየሱስ ያገኘነው ነገር ምንድን ነው?***

## ረቡዕ ጥር 8

# ክርስቶስ ለሰርዴስ ቤተ ክርስቲያን የላከው መልእክት

ሰርዴስ የድንቅ ታሪክ ባለቤት የነበረች ቢሆንም--በሮማውያን የግዛት ዘመን የቀደመውን ክብርና ሞገስ አጣች፡፡ ከተማዋ የነበራት ሐብት ባይመክንም ነገር ግን ክብርናዝናዋከዚያንወቅትይልቅበቀደመውታሪኳውስጥእንደተቀበረቀረ፡፡ከተማዋ የተገነባቸው በከፍታ ስፍራ ስለነበር በቀላሉ የምትቀመስ አልነበረችም፡፡ በዚህ የተነሳ የከተማዋ ቅጥር እንደ ነገሩ ቢጠበቅ እንኳ ነዋሪዎች የደኅንነት ስሜት ይሰማቸው ነበር፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 3፡1-6፣ ማቴ. 24፡42-44፣ 1ተሰ. 5፡1-8፡፡ የሰርዴስ ክርስቲያኖች ይገኙበት ለነበረው መንፈሳዊ ሁናቴ ፈውስ ያገኙ ዘንድ አጥብቆ ያሳሰባቸው ሦስት ነገሮች ምን ነበሩ? የሱስ “ንቃ” ሲል የሰጠው ማስጠንቀቂያ ከከተማዋ ታሪካዊ ዳራ አኳያ እንዴት ይስማማል?

________________________________________

________________________________________

________________________________________

ምንም እንኳ የሱስ በሰርዴስ ለነበሩ ጥቂት ክርስቲያን ታማኞች ዕውቅና ቢሰጥም፤ አብዛኞቹ የመንፈሳዊ ሞት ሰለባ ነበሩ፡፡ በእርግጥ ቤተ ክርስቲያኒቱ ከገጠማት መንፈሳዊ ልፍስፍስነት በቀር የትኛውም ዓይነት ግልጽ ኃጢአት ክስ አልቀረባትም (እንደ ጴርጋሞን እና ትያጥሮን)፡፡

ተቋሟ ትገኝበት በነበረው መንፈሳዊ ሁኔታ የነበራት እርካታ እንዲሁም ቀስ በቀስ ወደ ሕይወት ዐልባ ቅርጻዊነት አዘቅት እያሽቆለቆለች መሄዷ፤ በሰርዴስ ለነበረችው ቤተ ክርስቲያን የተሰጠውን መልእክት ከፕሮቴስታንት ድኅረ ተሐድሶ ሁኔታ ጋር በትክክል ገጣሚ ያደርገዋል፡፡ አስተሳሰብ በምክኒያት እንጂ በእምነት ላይ መመስረት የለበትም የሚለውና--መንፈሳዊ አስተሳሰብ በሕዝብ ላይ ተጽእኖ ሊኖረው አይገባም የተሰኘው ሙግት ያስነሳው ተጽእኖ፤ የወንጌልን አዳኝ ጸጋ እንዲሁም ለክርስቶስ ሊኖር የሚገባ ቁርጠኝነት እንዲዳከምና እንዲጠፋ አደረገው፡፡ ምንም እንኳ በዚህ

ዘመን የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ሕይወት ያላት ብትመስልም፤ ተጨባጭ እውነታ ያመላከት የነበረው በተቃራኒ መገኘቷን ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ደብዳቤው ከእያንዳንዱ ክርስቲያን ትውልድ ጋር ገጣሚና አግባብ አለው፡፡ ቀደም ባሉት ጊዜያቶች ስለ ክርስቶስ የነበራቸውን ቅንአትና መንፈሳዊ ህይወት ቢያወሩ የማይጠግቡ ክርስቲያኖች አሉ፡፡ ሆኖም የዛሬውን ተሞክሮ እንደ ቀድሞው መናገር አለመቻላቸው ግን በእጅጉ ያሳዝናል፡፡ ምንም እንኳ የቀደመውን እውነት ባይለቁም ለወንጌል የነበራቸው ከልብ የመነጨ ቁርጠኝነት ግን ደብዝዟል፡፡

***መዳን በክርስቶስ ላይ ባለን እምነት ብቻ እንደሆነ የሚገልጽውን ታላቅ እውነት ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ጠብቀን መጓዛችን አማራጭ ባይኖረውም፤ ሥራችን በእግዚአብሔር ፊት "ፍጹም" ሆኖ አልተገኘም ልንል የምንችለው እንዴት ነው? ይህ ምን ማለት ነው? ሥራችንን በፊቱ "ፍጹም" ማድረግ የምንችለውስ እንዴት ነው? ማቴ. 5፡44-48፡፡***

## ሐሙስ ጥር 9

# ክርስቲያኖች በሎዶቅያ

የሱስ መልእክት የላከባት የመጨረሻዋ ቤተ ክርስቲያን ሎዶቅያ ስትሆን፤ ይህች ባለጸጋ ከተማ በዋንኛ የንግድ መስመር ላይ ትገኝ ነበር፡፡ የሱፍ ጨርቅ ምርቷ፣ ከባሕር ዳርቻዎቿ ይታፈስ የነበረው መጠነ ሰፊ የወርቅ ማዕድን እንዲሁም በህክምና ትምህርት ቤት ይመረት የነበረ የዐይን መድኃኒት ስሟን ገናና አድርገውት ነበር፡፡ ይህ ሐብት ዜጎች በኢኮኖሚ ራሳቸውን የሚችሉበትን አቅም ፈጠረላቸው፡፡ በ60 ዓ.ም. ገደማ በከተማዋ ላይ የደረሰው ርዕደ መሬት ዜጎች በሮም ድጋፍና እርዳታ ሥር እንዲወድቁ መንስዔ ሆኖ ነበር፡፡ ከተማዋ የመጠጥ ውሃ ችግር ስለነበረባት ሔራፖሊስ በመባል ከሚታወቅ አካባቢ በቦይ እንዲደርሳት ተደርጎ ነበር፡፡ ታዲያ ውሃው ይገኝ የነበረበት ስፍራ ሩቅ ስለነበር ሎዶቅያ ሲደርስ የቀድሞ ይዞታውን አጥቶ ለብ ይል ነበር፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 3፡14-17፤ ሆሴ. 12፡8፡፡ ከተማዋ በነበራት ታሪካዊ ባህሪ እና ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያኑን በገመገመበት አካሄድ መሃል ያሉ ተዛማጅ ሁናቴዎችን ለይተው ለማውጣት ይሞክሩ፡፡ ከተማዋ ትገኝበት ከነበረው የኤኮኖሚ ሁኔታ አኳያ በነዋሪዎች ላይ ይነበብ የነበረው መንፈስ፤ በሎዶቅያ ክርስቲያኖች ላይ የታየበት

መንገድ ምን ይመስላል?

---

---

የሱስ በሎዶቅያ የነበሩ ክርስቲያኖችን እንደ የሐሰት አስተምህሮ ወይም ክህደት ዓይነት ከባድ ኃጢአት ውስጥ ወድቃችኋል ሲል አልገሰጻቸውም፡፡ ይልቁንም የእነርሱ ችግር ወደ መንፈሳዊ ልፍስፍስነት ሊያመራ የሚችል የእርካታ ስሜት ነበር፡ ፡ በራድ ወይም ትኩስ ሳይሆኑ ልክ ወደ ከተማዋ ይደርስ እንደ ነበረው የመጠጥ ውሃ ለብ ያሉ ነበሩ፡፡ ራሳቸውን ሐብታም አድርገው ስለሚቆጥሩ ምንም ነገር እንደማያስፈልጋቸው አድርገው ያስቡ ነበር፡፡ ነገር ግን--ድኻ፣ የተራቆተና የታወረ መንፈሳዊ ህይወት ነበራቸው፡፡

በሎዶቅያ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን በምድር ታሪክ መደምደሚያ የምትኖረውን ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ሁኔታ በትክክል ትወክላለች፡፡ የሎዶቅያዋና የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ትስስር በራእ. 16፡15 ጠንከር ባሉ ቃላት የተገለጸ ሲሆን፤ በዚህም ቤተ ክርስቲያኒቱ በዚያ አስከፊ ወቅት ሊደረግ ከሚገባ ዝግጅት አኳያ ለመጨረሻው ዘመን እንደ ምሳሌ ቀርባለች፡፡ በምድር ታሪክ መዝጊያ የምትገኘው ቤተ ክርስቲያን የቀደመው ትውልድ አይቶም ሆነ ሰምቶ የማያውቀው ዓይነት ፖለቲካዊ፣ ኃይማኖታዊም ሆነ ዓለማዊ ነውጥ መሃል የምትገኝ ትሆናለች፡፡ ይህም ሆኖ ይህች ቤተ ክርስቲያን በራሷ የምትመካና ከሐቀኝነቷ ጋር የምትታገል ትሆናለች፡፡ ይህ ክርስቶስ የሰጣት ማስጠንቀቂያ የእርሱ የመጨረሻው ዘመን ቤተ ክርስቲያን አካል ለሆኑ ሁሉ እጅግ የላቀ አንደምታ አለው፡፡

ሎዶቅያን እንደሚወዳትና በእርሷ ተስፋ እንደማይቆርጥ ማረጋገጫ የሰጠው የሱስ (ራእ. 3፡19) በማሕልየ ማሓልይ 5፡2-6 ከደጃፍ ቆሞ በሩን በሚያንኳኳና ለመግባት በሚለምን አፍቃሪ ተማጽኖ መልእክቱን ይደመድማል፡፡ የሱስ በሩን ከፍቶ ከሚያስገባው ከማንኛውም ሰው ጋር አብሮ እራት እንደሚበላ የተስፋ ቃል ሰጥቶአል፡፡ ይህ ጥሪ ምላሽ ሳይሰጠው ፈጽሞ መቅረት የለበትም፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 3፡18-22፡፡ የሱስ ለሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን ምዕመን የሰጠው ምክረ ሀሳብ ምን ነበር? ወርቅ፣ ነጭ ልብስ እና ኩል ምን ይወክላሉ--(1ጴጥ. 1:7፣ ኢሳ. 61:10፣ ኤፌ. 1:17-18)? ራሳችንን እንደ ሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን ለምንመለከት ለእኛ ለሰባተኛ ቀን አድቬንተስቶች ያላቸው መልእክት ምንድን ነው?**

# አርብ ጥር 10

ተጨማሪ ሀሳብ፡ Read Ellen G. White, “The Revelation,” pp. 578–592, in The Acts of the Apostles.

ለቤተ ክርስቲያኖቹ የተላኩት ሰባት መልእክቶች በሁሉም አብያተ ክርስቲያናት የተከሰተውን የመንፈሳዊነት መውረድ ያሳያሉ፡፡ ምንም እንኳ በኤፌሶን የነበረችው ቤተ ክርስቲያን የቀደመ ፍቅሯን ብታጣም፤ በታማኝነቷ ጸንታ ቀጥላለች፡፡ ሰምርኔስ፣ ጴርጋሞን እና ፊላድልፊያ አብያተ ክርስቲያናትን በተመለከተ--ጥቂት አኻዝ የነበራቸው አመጸኞች ብቻ ታማኝነታቸውን አጉድለው ነበር፡፡ ትያጥሮን ለክርስቶስ የነበራት ታማኝነት በሁለት የተከፈለ ነበር፡፡ በሰርዴስ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን በከፋ ሁናቴ ውስጥ ትገኝ ነበር፡፡ ከዚህች ቤተ ክርስቲያን ምዕመን መሃል ጥቂቶች ብቻ ታማኝ ሲሆኑ አብላጫው ሕዝበ ክርስቲያን ከወንጌል ጋር ውህደት አልነበረውም፡፡ በሎዶቅያ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን የምትገኘው መልካም ሊባልላት በማይችል ሁናቴ ውስጥ እንደሆነ ልብ ይሏል፡፡

የሱስ ለአብያተ ክርስቲያናቱ በሰጠው በእያንዳንዱ መልእክት ድምዳሜ፤ ምክረ ሀሳቡን ለሚቀበሉ ሁሉ የተስፋ ቃል ይሰጣል፡፡ በየአብያተ ክርስቲያናቱ የተከሰተውን የመንፈሳዊነት አዘቅት ቀልብሶ ዳግም እንዲያንሰራራ የሚያደርግ ተስፋ መሰጠቱን ማንም አንባቢ በተጨባጭ ሊያስተውል ይችላል፡፡ ለየአብያተ ክርስቲያናቱ የተሰጠውን የተስፋ ቃል ስንመለከት--የመጀመሪያዋ ማለትም ኤፌሶን የተቀበለችው ተስፋ አንድ ብቻ ሲሆን፤ በዚህም የኋለኞቹ ከመጀመሪያዋ የላቀ ተስፋ መቀበላቸውን እንመለከታለን፡፡ በመጨረሻው ቅደም ተከተል የምትገኘው ሎዶቅያም እንዲሁ አንድ ብቻ የተስፋ ቃል ቢሰጣትም፤ የምትቀበለው ግን የላቀውን ነው--የዙፋኑ ተጋሪ ያደርጋታል (ራእ. 3፡21)፡፡

## የመወያያ ጥያቄዎች፡

**1.እነዚህ እየጨመሩ የሚሄዱ የተስፋ ቃሎች ከየአብያተ ክርስቲያናቱ በተጓዳኝ ከተስተዋለው የመንፈሳዊነት መውረድ አኳያ ኃጢአት በጨመረ ቁጥር ጸጋው አብልጦ የመትረፍረፉን አባባል እንዴት ያንጸባርቃሉ (ሮሜ 5፡20)? “ቤተ ክርስቲያን የቱንም ያህል ድካምና ጉድለት ሊደርስባት ቢችል እንኳ በዚህ ምድር የክርስቶስ ከፍ ያለ**

ጥበቃ ያላት ብቸኛ ተቋም ናት፡፡ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ያለማቋረጥ በብቸኝነት በዐይኖቹ ይጠብቃታል፣ ይጨነቅላታል፣ በመንፈስ ቅዱስም ያበረታታል፡፡"—Ellen G. White, Selected Messages, book 2, p. 396.

2.በኢንዱስትሪና በንግድ በበለጸጉ ታላላቅ ከተሞች ክርስትናንን ጠብቆ መጓዝ አስቸጋሪ እንደሆነ አንዳንዶች ሲናገሩ ይደመጣሉ፡፡ በእስያ በሐብት የበለጸጉ ከተሞች--ዙሪያ ገባውን በቤተ ጣዖቶች ተከብበው ይኖሩ ከነበሩና ለወንጌል ታማኝ ሆነው አረማዊውን ተጽእኖ ተቋቁመው ከዘለቁ ክርስቲያኖች ምን እንማራለን? እነዚያን በእስያ የነበሩ ክርስቲያኖች የሱስ በዮሐ. 17፡15-19 በጸለየው ጸሎት ብርሃን አሰብ ለማድረግ ይሞክሩ፡፡ በዓለም ውስጥ እየኖሩ ነገር ግን ከዓለም ሳይሆኑ የመኖር ጽንሰ ሃሳብ በዛሬዎቹ ክርስቲያኖች ላይ መሥራት የሚችለው እንዴት ነው? በተለይ--በታላላቅ ከተሞች የሚኖሩ አማኞች?

3.እኛ እንደ አድቬንቲስት ለሎዶቅያ የተሰጡትን መልእክቶች አክብረንና በጥንቃቄ አስተውለን መራመድ የምንችለው እንዴ ነው?

# 4ኛ ትምህርት

ከጥር 11-17

# የበጉ በዙፋኑ ላይ መቀመጥ

ሰንበት ከሰዓት

ለዚህ ሣምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ራእ. 4፣ ሕዝ. 1:5–14፣ ራእ. 5፣ ኤፌ. 1:20–23፣ ዕብ. 10:12፣ ሐዋ. 2:32–36፡፡

**<u>መታሰቢያ ጥቅስ :-</u> " 'እኔ ድል ነስቼ ከአባቴ ጋር በእርሱ ዙፋን ላይ እንደተቀመጥሁ፣ ድል የሚነሣውም ከእኔ ጋር በዙፋኔ ላይ እንዲቀመጥ አደርገዋለሁ፡፡' " (ራእ. 3፡21)፡፡**

እስካሁን የተመለከትናቸው ቀደም ያሉ ራእዮች ክርስቶስ ለምድር ሕዝቦቹ የላከውን መልእክት ፍንትው አድርገው ያሳያሉ፡፡ አሁን ግን ራእዩ ከምድር ወደ ሰማይ በማቅናት ትኩረቱን “ከዚህ በኋላ ሊሆን የሚገባው ነገር” ላይ ያደርጋል”(ራእ. 4፡1)፡፡

በራእ. ምዕ. 4-5 የቀረበው ራእይ የታላቁን ተቃርኖ አጠቃላይ ገጽታ ያስቃኘናል፡፡ በራእ. 12 እንደ ቀረበው ትዕይንት ሁሉ--በራእ. 4-5 የምናገኘው ተምሳሌታዊ አነጋገር ከየሱስ ምድራዊ አገልግሎት አንስቶ ያለውን የደኅንነትን እቅድ ታሪክ ያስቃኘናል፡፡ ሆኖም የወደፊቱ ወለል ብሎ ከመገለጡ አስቀድሞ፤ ክርስቶስ በድኅረ ቀራንዮ በሰማይ የከበረበትን ሁኔታ በጨረፍታ የምንመለከትበት ዕድል ተሰጥቶናል፡፡ በዚህም ምዕ. 4 እና 5 በወደፊቱ ክስተት ዙሪያ--በቀሪው የመጽሐፉ ክፍሎች በሰፈሩት የመልእክቶች ፍቺ ላይ ሰማያዊውን ምልከታ ይሰጠናል፡፡

ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት የተጻፈው መልእክት ቀጥተኛ በሚባል ዓይነት ቋንቋ የቀረበ ቢሆንም ነገር ግን ከአሁን በኋላ በመጽሐፉ የምናገኛቸው መልእክቶች እንደ ወትሮው ለመፍታት ቀላል ሊሆኑ የማይችሉ ተምሳሌታዊና ውስጠ ወይራ ዘይቤዎችን የተላበሱ ይሆናሉ፡፡ ይህ ጥቅም ላይ የዋለ ቋንቋ ከብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ሕዝቦች ታሪክ የተወሰደ ነው፡፡ የራእይ መጽሐፍን ትክክለኛ ፍቺ ለማግኘት፤ ተምሳሌታዊውን ቋንቋ ከብሉይ ኪዳን ብርሃን አኳያ ማስተዋል ይጠይቃል፡፡

# እሑድ

ጥር 12

## በሰማያዊው ዙፋን ቅጥር

ዮሐንስ ከእርሱ ዘመን እስከ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ያለውን ጊዜ ያካተተውን የታሪክ ቅኝት አጠቃላይ ገጽታ ለመመልከት ወደ ሰማይ እንዲወጣ በየሱስ ግብዣ እንደቀረበለት እንመለከታለን፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 4፡1-8፣ ሕዝ. 1፡26-28፡፡ ራእ. 5፡11-14 ከሚሰጠን ብርሃን አኳያ ስለ ሰማያዊው ዙፋን ዕጹብነት ምን መማር እንችላለን?

---

---

ሐዋርያው በተከፈተው በር ወደ ሰማያዊው መቅደስና የእግዚአብሔር ዙፋን ተመለከተ፡፡ ዙፋኑ የእግዚአብሔርን ሥልጣንና በፍጡራኑ ላይ ያለውን ገዢነት ሲወክል፤ በዙፋኑ ዙሪያ ያለው ቀስተ ደመና ደግሞ ለሕዝቦቹ ያለውን ታማኝነት ያሳያል፡፡ሆኖም ባላንጣው ሰይጣን ይህን አምላካዊ ሥልጣን ተቀናቀነ። በእግዚአብሔርና በሰይጣን መካከል ላለው ቅራኔ ዋንኛ መንስዔ የገዢነት ባለመብቱ--ማን ነው? የሚለው ነው፡፡ በሰማያዊው ዙፋን ዙሪያ የተደረገው ሰማያዊ ጉባዔ ዓላማ በእግዚአብሔር የዩኒቨርስ ገዢነት ባለመብትነት ዙሪያ ለሚነሳው ጥያቄ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መፍትሔ ለመስጠት ነበር፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 4፡8-11፣ 5፡9-14፡፡ ከጥቅሶቹ ስለ እውነተኛ አምልኮ ምን መማር ይችላሉ? በምዕ. 4 ጌታ እግዚአብሔር መመለክ ያለበት እንዲሁም በራእ. 5፡ 9-14 በጉ የከበረ የሆነው ለምንድን ነው?

---

---

ስለ ሰማያዊው ዙፋን እና በዚያ ስፍራ ያለማቋረጥ ስለሚደረገው አምልኮ ራእ. ምዕ. 4 አጠቃላይ መግለጫ ይሰጣል፡፡ በምዕ. 4 የቀረበው አምልኮ የእግዚአብሔርን የመፍጠር ኃይል ሲያወድስ ምዕ. 5 ደግሞ በታረደው በግ ለተገኘው ቤዛነት ውዳሴ ያቀርባል፡፡ ይህ ደግሞ እውነተኛ አምልኮ አምላካዊውን የመፍጠር ሥራና ቤዛነት የሚቆጥር፣ ብሎም በዚያ ሐሴት የሚያደርግ መሆኑን ያሳያል፡፡ በመጀመሪያ ዓለምን የፈጠረው እግዚአብሔር አምላክ፤ በሰጠው የተስፋ ቃል መሰረት ይህቺኑ ምድር ዘላለማዊ የሕዝቦቹ መኖሪያ አድርጎ ወደ ቀደመ ንጽሕናዋ የመመለስ ኃይልና ችሎታ አለው፡፡

**በወንጌል አስተምህሮ ዙሪያ አሰብ ያድርጉ፡ ስለ እኛ "የታረደው በግ" (ራእ. 5፡12) እኛን ብቻ ሳይሆን ነገር ግን መላውን ዩኒቨርስ የፈጠረው አምላክ ነው፡፡ በዚህ ህመም፣ ብጥብጥና ዐመጽ በበዛበት ዓለም እንዴት ያለ ተስፋ ተሰጥቶናል?**

**ሰኞ** **ጥር 13**

# በአምላካዊው ዙፋን የተሰየመው ሰማያዊ ጉባዔ

በራእ. 4፡4 የምናገኛቸው ሽማግሌዎች የተገለጹበት መንገድ መላእክት አለመሆናቸውን ያሳያል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ "ሽማግሌዎች" የተሰኘው መጠሪያ ማዕረግ ሁሌም ጥቅም ላይ የሚውለው ለሰብዓዊ ፍጡራን ነው፡፡ እነዚህ ሽማግሌዎች ዘወትር በእግዚአብሔር ሕልዎት ዙሪያ ከሚቆሙት መላእክት በተቃራኒ በዙፋኖች ላይ ተቀምጠዋል፡፡ ነጫጭ ልብሶቻቸው የታማኞቹ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ልብሶች ናቸው (ራእ. 3፡4-5)፡፡ በራሳቸው ላይ የደፉት የድል አክሊል (በግሪክኛው ስቴፋኖል) በተለይ ድል ለነሱ ቅዱሳን የተዘጋጀ ነው (ያዕ. 1፡12)፡፡ በዚህም እነዚህ 24 ሽማግሌዎች አምላካዊው ክብር የተቸራቸው ቅዱሳን መሆናቸውን መመልከት ይቻላል፡፡

24 ቁጥር ተምሳሌታዊ ነው፡፡ በውስጡ ሁለት የ12 ስብስቦችን የያዘው ይህ ቁጥር በእግዚአብሔር ሕዝቦች ተምሳሌትነት መቅረቡን በመጽሐፍ ቅዱስ እንመለከታለን፡፡ እነዚህ 24 ሽማግሌዎች በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን ዘመን ያሉትን የእግዚአብሔር ሕዝቦች በድምሩ መወከል ይችላሉ፡፡ በተጨማሪ 24 ቁጥር በቀደመው ምድራዊ የቤተ መቅደስ አገልግሎት አካል የነበሩት የ24ቱ አለቆች ካህናት አመዳደብ ነጸብራቅ መሆን ይችላል (1ዜና 24፡1-19)፡፡

24ቱ ሽማግሌዎች ከዮሐንስ ራእይ አስቀድሞ በመጽሐፍ ቅዱስ ተጠቅሰው አለመታወቃቸው በሰማያዊው ዙፋን የተሰየሙ አዲስ ቡድኖች መሆናቸውን ያመለክታል፡፡ ምናልባትም ትዕይንቱ ገቢራዊ ከመሆኑ ጥቂት ቀደም ብሎ የተሰየሙ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ሰዎች በየሱስ የመስቀል ላይ መሥዋዕትነት ወቅት ከሞት የተነሱ ሊሆኑ እንደሚችሉ ይታመናል (ማቴ. 27፡51-53)፡፡ የሱስ ወደ ሰማይ ባረገ ጊዜ ምርኮን ይዞ እንደወጣ ኤፌ. 4፡8 ይነግረናል፡፡

በዘላለማዊው የደኅንነት ዕቅድ የእግዚአብሔርን ፍትሐዊነት ይመሰክሩ ዘንድ እነዚህ 24 ሽማግሌዎች ሰብዓዊውን ዘር ወክለው ከየሱስ ጋር ወደ ሰማይ ዐረጉ፡፡ በራእ. 4 እንደ ተመለከተው ሽማግሌዎቹ ከተቀረው ጉባዔ ጋር ወደ ሰማያዊው

ዙፋን የተወሰዱት የሱስ በመስቀል ላይ የአሸናፊነት ሞት ከሞተ በኋላ ለዕርገቱና በሰማያዊው ሥልጣን ለመከበሩ እማኝ ለመሆን ብሎም እርሱን ለመቀበል ነው፡፡

በተጨማሪ በራእ. 4፡6-8 ስለ አራቱ ሕያዋን ፍጡራን ተጠቅሶአል፡፡ ይህን አገላለጽ በሚከተሉት ጥቅሶች ከቀረቡት ጋር ያስተያዩ፡ ሕዝ. 1፡5-14፣ 10፡20-22፣ ኢሳ. 6፡ 2-3፡፡

---

---

አራቱ ሕያዋን ፍጡራን የእግዚአብሔር የዙፋኑ ጠባቂዎችና ወኪል መላእክቶች ናቸው (መዝ. 99፡1)፡፡ ክንፎቻቸው አምላካዊውን ትእዛዝ ለማስፈጸም ያላቸውን ፍጥነት ሲያመላክት ዐይኖቻቸው ደግሞ የጥልቅ አስተሳሰብ ባለቤት መሆናቸውን ይገልጣል፡፡ የአንበሳ፣ የጥጃ፣ የሰው እና የንስር ገጽታ መላበሳቸው መላውን የፍጥረት ሥርዓት መወከላቸውን ያሳያል፡፡ የእነርሱ መገኘት መላውን የእግዚአብሔር ፍጥረታት በዙፋኑ ፊት ይወክላል፡፡

## ማክሰኞ ጥር 14

## በማኅተም የታሸገው ጥቅል መጽሐፍ

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 5፡1፣ ኢሳ. 29፡11-12፡፡ በማኅተም የታሸገው የጥቅል ፍቺ ምንድን ነው?

---

---

ይህ የታሸገ ጥቅል በዙፋኑ ላይ በተቀመጠው አብ ቀኝ እጅ እንደ ነበር ይኸው በግሪክ የተጻፈ አምላካዊ ቃል ያመለክታል፡፡ ጥቅሉን የሚወስደውና በዙፋኑ ላይ ለመቀመጥ የተገባው መጠበቅ ነበረበት፡፡ እንደ ኤለን ጂ. ኋይት ገለጻ ጥቅሉ “የአምላካዊውን ጥበቃና ቸርነት እንዲሁም ትንቢታዊውን የሕዝቦችና የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ልቅም አድርጎ ይዞአል፡፡ መለኮት የተናገራቸውን ቃላት፣ ሥልጣኑን፣ ትእዛዛቱን፣ ሕጋጋቱን፣ በተምሳሌታዊ መንገድ የተናገራቸውን ሁሉንም ዘላለማዊ ምክሮች፣ እንዲሁም የመላውን ኃያላን የምድር ነገሥታት ታሪክ ይዞ ነበር፡፡ በዚያ ጥቅል ከምድር ታሪክ መጀመሪያ እስከ መጨረሻ ያለው እያንዳንዱ መንግሥት፣ ሕዝብና ቋንቋ በተምሳሌታዊ መንገድ ተገልጾ ነበር፡፡”—Ellen G. White, Manuscript Releases,vol. 9, p. 7.

ባጭሩ የታሸገው ጥቅል ለኃጢአት ችግር መፍትሔ የማምጣትና የወደቀውን ሰብዓዊ ዘር የመታደግ አምላካዊ ምስጢር ይዞ ነበር። ያ ምስጢር በሙላት መስተዋል የሚቻለው በክርስቶስ ዳግም ምጽአት ወቅት ይሆናል (ራእ. 10፡7)።

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 5፡2-7። ክርስቶስ የታሸገውን ጥቅል ለመውሰድና ማኅተሙን ለመፍታት ከመላው ዩኒቨርስ ብቸኛው የሆነው ለምንድን ነው?

---

---

ዙፋኑ ባለበት ስፍራ ተከስቶ የነበረው ቀውስ ከሰይጣን ዐመጻ ጋር ቁርኝት አለው። ምንም እንኳ ይህች ምድር በእግዚአብሔር ብትፈጠርም ነገር ግን የሥልጣን ነጠቃ ባደረገው ሰይጣን ቁጥጥር ሥር ዋለች። የዮሐንስ ልቅሶ ከአዳም አንስቶ ከኃጢአት ባርነት አርነት ለመውጣት የተደረገውን የእግዚአብሔር ሕዝቦች እምባ ያሳያል። ጥቅልሉ መጽሐፍ ለኃጢአት ችግር የሚበጀውን አምላካዊ መፍትሔ ይዞ ነበር። ያን ዕቅድ መገንዘብ የሚችለው በየትኛውም መስፈርት የማይለካው ራሱ አምላካዊው ኃይል ብቻ መሆኑ እሙን ነው። ሆኖም የወደቀውን ሰብዓዊ ዘር ለመቤዠት ከተለመደው ፍጹም የተለየ ክስተት አስፈልጎ የነበረ ሲሆን ይኸውም ድል የነሳውና መጽሐፉን ለመክፈት የተገባው በምድር ጌታና የሰማያዊው መቅደስ አማላጃችን የሆነው የሱስ ነበር።

**በክርስትና ተሞክሮአችን የሱስን ከሁሉም ማስቀደም የምንማረው እንዴት ነው?**

## ረቡዕ ጥር 15

## የበጉ በዙፋኑ መንገሥ

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 5፡8-14፣ ኤፌ. 1፡20-23፣ ዕብ. 10፡12። ጥቅሶቹ በአንድነት ምን ዓይነት የላቀ ተስፋና መጽናኛ ይሰጡናል?**

---

---

---

ክርስቶስ የእግዚአብሔር በግ ወደ ዙፋኑ ቀርቦ ጥቅልሉን ወሰደ፡፡ እንዴት ያለ ትዕይንት ነበር! ሥልጣናትና ኃይላት ሁሉ ራሳቸውን በፊቱ አስገዙ (ኤፌ. 1፡20-22)፡፡ በዚያን ወቅት መላው ዩኒቨርስ ለክርስቶስ ሕጋዊ የምድር ገዢነት እውቅና ሰጠ፡፡ በአዳም ጠፍቶ የነበረውም እነሆ ዳግም በክርስቶስ ተገኘ፡፡

ክርስቶስ በማኅተም የታሸገውን ጥቅል መጽሐፍ በመውሰዱ የመላው ሰብዓዊው ዘር ዕጣ ፈንታ በእጆቹ ላይ ዋለ፡፡ አራቱ ሕያዋን ፍጡራንና 24ቱ ሽማግሌዎች በራእ. 5፡9 እንዳደረጉት " 'መጽሐፉን ልትወስድ፣ ማኅተሞቹንም ልትፈታ ይገባሃል፤ ምክንያቱም ታርደሃል' "በማለት በግምባራቸው ተደፍተው ሰገዱለት፡፡ በዚህም ከፍ ያሉት መላእክትና የተዋጀው ሰብዓዊ ዘር ተወካዮች ክርስቶስ ስለ ሰው ልጆች የከፈለውን መሥዋዕት ተቀበሉ፡፡ በኃጢአት የወደቀው ሰብዓዊው ፍጡር በመተላለፉ ይጠየቅ ለነበረው የሞት ዕዳ ክርስቶስ በደሙ ቤዛ ሆኖ ፍጹም ልናስብ የማንችለውን የመዳን ተስፋ አሟልቶ ሰጠን፡፡

አሁን አራቱ ሕያዋን ፍጡራን እና ሽማግሌዎቹ እጅግ ከፍተኛ ቁጥር ከነበራቸው የመላእክት ሰራዊት ጋር በአንድነት ዙፋኑን ከብበው በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው አዲሱ ንጉሥ በታላቅ ድምፅ ምስጋናና ውዳሴ አቀረቡ፡ "'የታረደው በግ ኀይልና ባለ ጠግነት፣ ጥበብና ብርታት፣ ክብርና ሞገስ፣ ምስጋናም፣ ሊቀበል ይገባዋል'" (ራእ. 5፡12)፡፡

በዚህ ወቅት የሰማይና የምድር ፍጥረታት ባንድነት ሆነው "' በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠውና ለበጉ፣ ምስጋናና ሞገስ፣ ክብርና ኃይል፣ ለዘላለም እስከ ዘላለም ይሁን" (ራእ. 5፡13) ሲሉ ለእግዚአብሔር አብ እና ለእግዚአብሔር ወልድ ንጉሣዊውን አክብሮት አቀረቡ፡፡ አራቱ ሕያዋን ፍጡራን " 'አሜን' " ሲሉ፤ 24ቱ ሽማግሌዎች ደግሞ በግምባራቸው ተደፍተው ውዳሴያቸውን በማቅረብ ይህ በብርቱ ድምፆች ታጅቦ በሰማያዊው ዙፋን የተደረገ ታላቅ ሥነ ስርዓት ፍጻሜ ሆነ፡፡

***ዩኒቨርስ አንድ ቀን በብርቱ ንዳድ ወይም በራሱ ምክንያት ብትንትኑ ይወጣል ሲሉ የፊዚክስ ምሑራን መላምታቸውን ይደረድራሉ፡፡ አስተሳሰቡ የእግዚአብሔር ቃል ከሚናገረው ፍጹም ተጻራሪ ነው፡፡ ከፊት ለፊታችን የሚጠብቀንን አሻግረን እያየን ሐሴት ማድረግን ዛሬ መጀመር የምንችለው እንዴት ነው?***

## ሐሙስ ጥር 16

# የጴንጤቆስጤው አንደምታ

በሰው ልጆች የመዳን ታሪክ እጅግ ወሳኝ ከሆኑ ክስተቶች መሃል አንዱ በራእ. ምዕ. 5 የቀረበው፡ ክርስቶስ በድኅረ ቀራኒዮ እንደ ንጉሥና ሊቀ ካህናት ለሚሰጠው ሰማያዊ አገልግሎት መከበሩ ነው፡፡ የደኅንነትን እቅድ በአስገራሚ አኳኋን እውን ማድረግ የቻለው ክርስቶስ በሰማያዊው የእግዚአብሔር ቀኝ ዙፋኑን ወሰደ (ዕብ. 12፡2፣ ራእ. 3፡21)፡፡ ክርስቶስ በሰማያዊው መቅደስ አማላጃችን መሆኑን ተከትሎ የወደቀው ሰብዓዊ ዘር በእርሱ አማካይነት ወደ እግዚአብሔር መድረስና የኃጢአት ይቅርታ ማግኘት ቻለ፡፡

ጥቅሶቹን ያነጻጽሩ፡ ሐዋ. 2፡32-36፣ ዮሐ. 7፡39፡፡ የክርስቶስ በሰማይ መከበር ለመንፈስ ቅዱስ መውረድ ያለው አስፈላጊነት ምንድን ነው? ክርስቶስ በሰማይ ከመከበሩ አስቀድሞ መንፈስ ቅዱስ ለደቀ መዛሙርቱ መውረድ ያልቻለበት ምክንያቱ ምን ነበር?

---

---

---

ክርስቶስ በሰማያዊው መቅደስ መከበሩን ተከትሎ መንፈስ ቅዱስ በደቀ መዛሙርቱ ላይ ወረደ፡፡ ራእ. 5፡6 ወደ ምድር ሁሉ ስለ "ተላኩት ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስት" ይጠቅሳል፡፡ ሰባቱ መናፍስት--መንፈስ ቅዱስ በዓለም የሚፈጽመውን ተግባር ፍጹምነት ያመለክታል፡፡ መንፈስ ቅዱስ ዘወትር በዙፋኑ ፊት እንደ ነበር የተገለጸ ቢሆንም (ራእ. 1፡4፣ 4፡5) ክርስቶስ በሰማያዊው ዙፋን በተቀመጠ ጊዜ ወደ ምድር ተላከ፡፡ የመንፈስ ቅዱስ ወደ ምድር መላክ ከክርስቶስ ድኅረ ቀራኒዮ አገልግሎት መከበር ጋር ይተሳሰራል፡፡ ይህ ደግሞ የሱስ በአባቱ ፊት መቅረቡንና ስለ ሰብዓዊው ፍጡር የከፈለው መስዋዕትነት ተቀባይነት ማግኘቱን ያሳያል፡፡

"የክርስቶስ ወደ ሰማይ ማረግ ተከታዮቹ ቃል የተገባላቸውን በረከት የማግኘታቸው ምልክት ነበር. . . በሰማያዊው ደጃፎች ያለፈው ክርስቶስ በመላእክት ክብርና ውዳሴ በዙፋኑ ተቀመጠ፡፡ ይህ ሥነ ስርዓት እንዳበቃ መንፈስ ቅዱስ በደቀ መዛሙርቱ ላይ በሙላት ወረደ፤ በዚህም በአባቱ ዘንድ ዘላለማዊ ክብር የነበረው ክርስቶስ እነሆ አሁን ከበረ፡፡ ለሰብዓዊው ዘር ቤዛ የሆነው ጌታ መከበርና የጴንጤቆስጤው የመንፈስ

ቅዱስ መፍሰስ የእጅና ጓንት ግንኙነት ነው፡፡ ክርስቶስ አስቀድሞ በተናገረው መሰረት መንፈስ ቅዱስን ለተከታዮቹ ላከ፤ በሕዝቡ ላይ የተቀባው እርሱ--እንደ ካህንና እንደ ንጉሥ ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ወሰደ፡፡"—Ellen G. White, The Acts of the Apostles, pp. 38, 39.

***ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ዕብ. 4፡16፣ 8፡1፡፡ የሱስ እንደ ንጉሣችንና እንደ ካኅናችን በሰማያዊው ዙፋን የመቀመጡ እውነታ ምን ዓይነት ተስፋና መጽናናት ይሰጥዎታል? ከወደፊቱ የማያስተማምን ሁናቴና ከየቀኑ የህይወት መስተጋብር አኳያ በእርስዎ ላይ የሚኖረው ተጽእኖ ምንድን ነው?***

## አርብ ጥር 17

*ተጨማሪ ሀሳብ*: Read Ellen G. White, " 'To My Father, and Your Father,' " pp. 829–835, in The Desire of Ages; "The Gift of the Spirit," pp. 47–56, in The Acts of the Apostles.

በራእ. ምዕ. 4-5 የቀረበው መልእክት በተለይ በምድር ታሪክ መደምደሚያ ለሚኖሩ የእግዚአብሔር ሕዝቦች አስፈላጊ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ በጴንጤቆስጤ ወቅት በመውረድ የወንጌልን መሰበክ ጅማሮ አበሰረ፡፡ የወንጌል መልእክት አስኳል--እንደ ካኅንና ንጉሥ በሰማያዊው ዙፋን የተቀመጠው የሱስ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የቀደመው የክርስትና እምነት እምብርትና (ዕብ. 8፡1) የስብከታቸው የማዕዘን ድንጋይ ነበር (ሐዋ. 2፡32-36፣ 5፡30-31)፡፡ አማኞች ስደት ሲደርስባቸውና አስቸጋሪ ሁናቴ ሲገጥማቸው ይህ እውነት የመነቃቂያ ሰበባቸውና የእምነታቸው መበረታቻ ምንጭ ነበር፡፡ (ሐዋ. 7፡55-56፣ ሮሜ 8፡34)፡፡ በውጤቱም አያሌዎች ለዚህ ስብከት ምላሽ ሰጡ፡፡ በመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት የየሱስ መገኘት ገቢራዊ ከሆነበት ጊዜ አንስቶ የእግዚአብሔር መንግሥት ራሱን ገለጠ፤ ይህን ማድረጉንም ቀጠለ፡፡ ሰብዓዊውን ልብ በመለወጥ ሰዎች እግዚአብሔርን እንዲፈሩ፣ ለእርሱ ክብር እንዲሰጡና እርሱን ብቻ በማምለክ ለዘላለማዊው ወንጌል (ራእ. 14፡7) ምላሽ እንዲሰጡ መምራት የሚችለው የክርስቶስ መልካም የምስራች ብቻ መሆኑ ለአፍታ እንኳ መዘንጋት የለበትም፡፡ ብቸኛው ተስፋችን በንጉሥነትና በካኅንነት በሰማያዊው መቅደስ አገልግሎት እየሰጠ የሚገኘው አዳኛችን ነው፡፡ እርሱ ዛሬ ከሕዝቡ ጋር እንደሆነ፤

እስከ ምድር መጨረሻ አብሮአቸው ይሆናል (ማቴ. 28፡20)፡፡ እነሆ አንድም ሳይቀር የወደፊቱ ሁሉ በእጁ ውስጥ ነው፡፡

ስለዚህ የመጨረሻውን መልእክት ለጠፉና በሥቃይ ላሉ ሰብዓዊ ወገኖች ስናደርስ፤ የወንጌልን መሰረታዊ ባህሪ ሁሌም በአእምሮችን ጠብቀን ማኖራችን ሙሉ ስኬት ሊያስገኝልን እንደሚችል መርሳት የለብንም፡፡ ማንኛውም ስብከታችን ከመስቀሉና መስቀሉ ስለ እግዚአብሔር ከሚያስተምረው እውነት ውጪ አጽንኦት ሊሰጥ አይገባም፡፡

# የመወያያ ጥያቄዎች

***1.ስለ ጌታ መልካምነት፣ ስለ ኃያልነቱ በተለይ ደግሞ ስለ ጸጋው እያወደስነውና እያመለክነው በሰማይ የምንሆንበት ቀን ይመጣል፡፡ ለዚያ ታላቅ ቀን ዛሬ የምንለማመዳቸው ነገሮች ምንድን ናቸው? ጌታ ላደረገልንና ለሚያደርግልን ሁሉ ከወዲሁ ባመስጋኝ ልብ ልናመልከውና ልናወድሰው የምንችለው እንዴት ነው?***

***2.ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 4፡11፤ 5፡9፡፡ የሱስ እያደረጋቸው ያሉ ምን ዓይነት ሁለት ሚናዎች እንመለከታለን? ሁለቱ ሚናዎች ከደኅንነት እቅድ አኳያ ሳይሆን ነገር ግን ጌታ አምልኮአችንን ለመቀበል እጅግ የተገባው የትኩረት ነጥብ ያደረጋቸው ነገር ምንድን ነው? ሰንበት እና ከሰንበት የምንማራቸው ነገሮች--እግዚአብሔርን አስመልክቶ የእነዚህ ሁለት አስደናቂ እውነቶች መግለጫ የሆኑት እንዴት ነው?***

# 5ኛ ትምህርት

ከጥር 18-24

# ሰባቱ ማኅተሞች

ሰንበት ከሰዓት

ለዚህ ሣምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ራእ. 6:1–14፣ ዘሌዋ. 26:21–26፣ ሕዝ. 4:16፣ ዘዳ. 32:43፣ 2ተሰ. 1:7–10.

**<u>መታሰቢያ ጥቅስ :-</u> “ ‘ማኅተሞቹን ልትፈታ ይገባሃል፤ ምክንያቱም ታርደሃል፤ በደምህም ከነገድ ሁሉ፣ ከቋንቋ ሁሉ፣ ከወገን ሁሉ፣ ከሕዝብ ሁሉ ሰዎችን ለእግዚአብሔር ዋጅተሃል፡፡ ለአምላካችንም መንግሥትና ካህናት አድርገሃቸዋል፤ እነርሱም በምድር ላይ ይግዛሉ’ ” ራእ. 5፡9-10፡፡**

ክርስቶስ በማኅተም የታሸገውን ጥቅልል ስለ መውሰዱና በአዳም ታጥቶ የነበረው ዳግመኛ በእርሱ መገኘቱን የሚገልጸውና በራእ. 4-5 ቀርቦ የነበረው ይኸው ትዕይንት በምዕ. 6 ይቀጥላል፡፡ አሁን በጥቅሉ ያሉትን ማኅተሞች ለመክፈትና የደኅንነትን ዕቅድ ወደ መጨረሻው ግብ ለማድረስ ዝግጁ ነው፡፡

ጴንጤቆስጤ ክርስቶስ ወንጌልን ለዓለም በማዳረስ መንግሥቱን የሚያስፋፋበት ጅማሮ ሆኖ በገሃድ ታየ፡፡ የማኅተሞቹ መከፈት በጴንጤቆስጤ የተጀመረው የወንጌል መሰበክ መጀመርንና ይህን መልእክት መቃወም ሊያስከትል የሚችለውን ውጤት ያመላክታል፡፡ የሰባተኛውና የመጨረሻው ማኅተም መከፈት ወደዚህ ዓለም ታሪክ መደምደሚያ ያመጣናል፡፡

ራእ. 3፡21 የሰባቱን ማኅተሞች ፍቺ ቁልፍ ይሰጠናል፡ “ ‘እኔ ድል ነሥቼ ከአባቴ ጋር በእርሱ ዙፋን ላይ እንደ ተቀመጥሁ፣ ድል የሚነሣውንም ከእኔ ጋር በዙፋኔ ላይ እንዲቀመጥ አደርገዋለሁ’ ”፡፡ ምዕ. 4 እና 5 ስለ ክርስቶስ አሸናፊነትና በአባቱ ዙፋን ሀሴት ማድረግ ሲነግረን፤ ምዕ. 7 ደግሞ አሸናፊዎች በክርስቶስ ዙፋን መቀመጣቸውን ይፋ ያደርግልናል፡፡ እንዲሁም ምዕ. 6 የየሱስን ዙፋን መጋራት ይችሉ ዘንድ በማሸነፍ ሂደት ስላሉ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ይናገራል፡፡

## እሑድ ጥር 19

# የመጀመሪያው ማኅተም መከፈት

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 6፡1-8፤ ዘሌዋ. 26፡21-26፤ ማቴ. 24፡1-14፡፡ በእነዚህ ጥቅሶች በጋራ የቀረቡትን ቁልፍ ቃላት ልብ ይበሉ፡፡ ትይዩ ሆነው በቀረቡት ጥቅሶች መሰረት ስለ መጀመሪያዎቹ አራት ማኅተሞች ፍቺ ምን ይማራሉ?

______________________________________________________________

______________________________________________________________

ሰባቱን ማኅተሞች ተከትለው የሚመጡት እንደ ሠይፍ፣ ረሐብ፣ ቸነፈርና የምድር አራዊት (ዘሌዋ. 26፡21-26) ዓይነት መርገሞች ከብሉይ ኪዳን ዐውድ ሊስተዋሉ የግድ ይሆናል፡፡ እነዚህን ሕዝቅኤል--የእግዚአብሔር "አራቱ አስፈሪ ፍርዶች" (ሕዝ. 14፡21) ብሎ ይጠራቸዋል፡፡ የእግዚአብሔር ሕዝብ መንፈሳዊነት ሲደበዝዝና ከእርሱ ጋር የገቡትን የታማኝነት ኪዳን ሲያፈርሱ፤ ከተኙበት ለመቀስቀስ ቁጣውን የሚገልጽባቸው የቅጣት ፍርዶች ነበሩ፡፡ በተመሳሳይ አራቱ ፈረሰኞች የእርሱን ዳግም ምጽአት የሚጠባበቁ ወገኖች ነቅተው እንዲገኙ እግዚአብሔር የተጠቀመባቸው ናቸው፡፡

በተጨማሪ በመጀሪያዎቹ አራት ማኅተሞች እና የሱስ በማቴ. 24፡4-14 በዓለም ላይ ምን እንደሚደርስ የሱስ ከሰጠው ገለጻ ጋር ግልጽ መስተጋብር አለ፡፡ አራቱ ፈረሰኞች ይህ ዓለም ለእግዚአብሔር ሕዝቦች ፍጹም ቤታቸው አለመሆኑን ተገንዝበው በትክክለኛው አቅጣጫ ይራመዱ ዘንድ እነርሱን የሚጠብቅበት ዘዴ ነው፡፡

ምንም እንኳ ራእ. 6፡1-2 ተምሳሌታዊ ቢሆንም ነገር ግን እንደ ከዚህ ቀደሙ ሁሉ ስለ ድል አድራጊነት ይናገራል፡፡ ጥቅሶቹ ክርስቶስ በሰማይ ሰራዊት መሪነት በነጭ ፈረስ እየጋለበ ወደ ምድር ታሪክ መደምደሚያ ዐውደ ውጊያ የሚገሰግስበትን የራእ. 19፡11-16 ትዕይንት አእምሮ ላይ ያጭራሉ፡፡ የንጽሕና ተምሳሌት የሆነው ነጭ ቀለም ሁሌም የሚወክለው ክርስቶስንና ተከታዮቹን ነው፡፡ በፈረሱ ላይ የተቀመጠው ጋላቢ ቀስት የያዘ ሲሆን፤ አክሊል ሲሰጠው ይስተዋላል፡፡ ይህ ደግሞ ቀስት ይዞ እየጋለበ የሕዝቡን ጠላቶች ድል የነሳውን የብሉይ ኪዳኑን አምላካዊ አምሳል ገልጦ ያሳያል (ዕንባቆ. 3፡8-13፤ መዝ. 45፡4-5)፡፡ የፈረሱ ጋላቢ በዐናቱ የደፋው አክሊል በግሪክኛው እስጢፋኖስ የሚል ስያሜ ያለው ሲሆን፤ ይኸውም የድል አክሊል እንደ

ማለት ነው (ራእ. 2፡10፣ 3፡11)፡፡ ይህ ጋላቢ ድል እያደረገ ወደ ፊት የሚገሰግስ አሸናፊ ነው፡፡

በመጀመሪያው ማኅተም የተስተዋለው ትዕይንት ክርስቶስ መንግሥቱን ማስፋፋት የጀመረበትንና በጴንጤቆስጤ በብርቱ ኃይል ገቢራዊ የሆነውን የወንጌል ስርጭት ይገልጻል፡፡ ክርስቶስ በክብር ዳግም ሲገለጥ ገቢራዊ እስከሚሆነው የመጨረሻው ድል--እንደ ያኔ ሁሉ ዛሬም ለእርሱ አሸንፊን የየሱስ ተከታይ የምናደርጋቸው ሕዝቦች አሉ፡፡

በኤፌሶን ከነበረችው ቤተ ክርስቲያን ጋር ትስስር ያለው የመጀመሪያው ማኅተም ትንቢታዊ ትዕይንት፤ ወንጌል በዓለም ዙሪያ በፍጥነት የተሰራጨበትን የሐዋርያት ዘመን ይገልጻል (ቆለ. 1፡23)፡፡

**በኃጢአት ብንወድቅም ነገር ግን በክርስቶስ ሁሌም በአሸናፊው በኩል መሆናችንን ዘወትር ማስታወስ የሚኖርብን ለምንድን ነው?**

## ሰኞ ጥር 20

# ሁለተኛውና ሦስተኛው ማኅተም

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 6፡3-4፡፡ ስለ ቀዩ ፈረስና ጋላቢው በተሰጠው መግለጫ ወንጌልን ከመጥቀስ አኳያ እየተነገረ ያለው ነገር ምንድን ነው?

ቀይ ቀለም ደምን ይወክላል፡፡ ትልቅ ሰይፍ የነበረው የፈረሱ ጋላቢ በምድር የነበረውን ሰላም እንዲወስድ ተፈቅዶለት የነበረ ሲሆን፤ ይህም ሰዎች እርስ በርስ የሚጋደሉበትን መንገድ የከፈተ ነበር፡፡

ሁለተኛው ማኅተም ወንጌልን መቃወም ሊያስከትል የሚችለውን ውጤት ይገልጻል። ክርስቶስ በወንጌል ስርጭት መንፈሳዊ ጦርነት ሲያካሄድ፤ የክፉው ኃይል በምላሹ ጠንካራ መቋቋም ያሳያል፡፡ ይህን ተከትሎ ስደት የማያጠራጥርና አይቀሬ ይሆናል። የፈረሱ ጋላቢ ግድያ አይፈጽምም፡፡ በዚህ ፋንታ ሰላምን ከምድር ይወስዳል፡፡ በውጤቱም ስደት ይከተላል (ማቴ. 10፡34)፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 6፡5-6፣ ዘሌዋ. 26፡26፣ ሕዝ. 4፡16፡፡ ስለ ጥቁሩ ፈረስና ጋላቢው የተሰጠው መግለጫ ወንጌልን ስለ መስበክ ከተጠቀሰው ጋር በተጨባጭ የሚያዛምደው ምንድን ነው?

በጥቁሩ ፈረስ ላይ የተቀመጠው ጋላቢ ምግብ የሚመዝንበት ሚዛን ይዞአል፡፡ ከዚያም እንዲህ ተባለ "'አንድ እርቦ ስንዴ ለአንድ ቀን ደመወዝ፤ ሦስት እርቦ ገብስም ለአንድ ቀን ደመወዝ' " (ራእ. 6፡6)፡፡ በዚያ ዘመን እህል፣ ዘይት እና የወይን ጠጅ መሰረታዊ ፍጆታዎች ነበሩ (ዘዳ. 11፡14)፡፡ በጥንቃቄ ከተመዘነው እህል የሚጋገረውን ዳቦ መብላት ታላቅ እጦት ወይም ረሃብ መኖሩን ያመላክታል (ዘሌዋ. 26፡26፣ ሕዝ. 4፡16)፡፡ ዮሐንስ በኖረበት ዘመን እርቦ የአንድ ቀን ደመወዝ ነበር (ማቴ. 20፡2)፡፡ ረሃብ በሌለበት መደበኛው ጊዜ፤ የአንድ ቀን ደመወዝ ለአንድ ቤተሰብ የሚያስፈልገውን የዕለት ወጪ የመሸፈን አቅም ነበረው፡፡ ሆኖም ረሃብ መደበኛው የመገበያያ ዋጋ በብርቱ እንዲዋዥቅ የማድረግ ተጽእኖ አለው፡፡ በሦስተኛው ማኅተም ትዕይንት እንደ ተመለከተው ለአንድ ሰው ብቻ የሚበቃ ምግብ ለመግዛት ሙሉ ቀን መሥራት የግድ ነበር፡፡ የቀን ደመወዝ--አነስተኛ መጠን ያለውን የቤተሰብ አባላት ለመመገብ የሚያስችለውን፣ ርካሹንና የድኾች ምግብ የሆነውን ሦስት እርቦ ገብስ ለመግዛት ይውል ነበር፡፡

የሦስተኛው ማኅተም ሁኔታ ወንጌልን አበክሮ መቃወም ሊያስከትል የሚችለውን ውጤት ያመላክታል፡፡ ነጩ ፈረስ የወንጌልን መሰበክ የሚወክል ከሆነ፤ ጥቁሩ ፈረስ ደግሞ የወንጌልን አለመኖር ያሳያል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ እህል የእግዚአብሔር ቃል ተምሳሌት ነው (ሉቃ. 8፡11)፡፡ ወንጌልን መቃወም በአሞጽ ትንቢት ከተነገረው በተመሳሳይ የእግዚአብሔር ቃል ረሃብ እንዲከሰት መንስዔ መሆኑ አያጠራጥርም (አሞጽ 8፡11-13)፡፡

## ማክሰኞ ጥር 21

# የአራተኛው ማኅተም ሁኔታ

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 6፡7-8፡፡ እዚህ ላይ የምናገኘው ትዕይንት ምን ይመስላል? ይህ ሁኔታ ከዚህ አስቀድሞ ከነበረው ጋር እንዴት ይነጻጸራል?

---

---

በአራተኛው ማኅተም ላይ የምናገኘው ፈረስ ቀለም በግሪክኛው እንደ ቀረበው አመድማ ወይም ግራጫ ነው፡፡ የጋላቢው ስም ሞት ሲሆን፤ ይህ በእንዲህ እንዳለ የሙታን ስፍራ የሆነው ሲኦል ደግሞ አጅቦ ይከተለው ነበር፡፡ እነዚህ ሁለቱ የምድርን አንድ አራተኛ ሕዝቦች በሰይፍ፣ በረሃብ፣ በመቅሰፍትና በምድር አራዊት እንዲያጠፉ ተፈቅዶላቸው ነበር፡፡

አራተኛው ማኅተም ለቸነፈርና መቅሰፍት ጥሪ ያደርግ ነበር፡፡ ትዕይንቱ ከያዘው እውነት መረዳት እንደሚቻለው ሰዎች ወንጌልን በመቃወማቸው ምክንያት የሚደርስባቸው መንፈሳዊ ረሃብ በማያጠራጥር መልኩ ወደ መንፈሳዊ ሞት ይመራቸዋል፡፡

የሞትና የሲኦል ኃይል ውሱን መሆኑ በእርግጥም መልካም የምስራች ነው፡፡ ደግሞም ሥልጣን የተሰጣቸው ከምድር በአንድ አራተኛው ክፍል ላይ ብቻ ነው፡፡ የሱስ የሲኦልና የሞት ቁልፍ እንዳለው ማረጋገጫ ይሰጠናል (ራእ. 1፡18)፡፡

በራእ. 2 ለቀረቡት አብያተ ክርስቲያናት ማለትም ለኤፌሶን፣ ሰምርኔስ፣ ጴርጋሞን፣ ትያጥሮን፣ የተሰጡትን መልእክቶች ይዘት አንዴ መለስ ብለው ለመቃኘት ይሞክሩ፡፡ በእነዚህ አብያተ ክርስቲያናት የነበረውን ሁናቴ ከመጀመሪያዎቹ አራት ማኅተሞች መከፈት ትዕይንት ጋር ያስተያዩ፡፡ በመሃላቸው ምን ዓይነት መመሳሰል አለ?

---

---

የሰባቱ ማኅተሞች ትዕይንት የወደፊቷን ቤተ ክርስቲያን ሁናቴ ያሳያል፡፡ በሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት እንደተስተዋለው ሁሉ፤ ማኅተሞቹ ከተለያዩ የክርስትና ታሪክ ዘመኖች ጋር ይዛመዳሉ፡፡ በሐዋርያት ዘመን ወንጌል በዓለም ዙሪያ በፍጥነት ተስፋፍቶ ነበር፡፡ ይህን ተከትሎ በሁለተኛው ማኅተም እንደታየው፤ በሮም ዘመነ

መንግሥት ከመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ እስከ አራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ክርስቲያኖች ላይ ብርቱ ስደት ደረሰ፡፡ ሦስተኛው ማኅተም በአራተኛውና አምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተስተዋለውን አስታራቂ ሃሳብ የመከተል አካሄድ የሚያመለክት ሲሆን፤ ይህ ዘመን በታሪክ "የጨለማው ዘመን" ተብሎ ወደሚታወቀው፣ የመጽሐፍ ቅዱስ እጦትና መንፈሳዊ ረሃብ የሰፈነበት ጊዜ ያመራ ነበር፡፡ አራተኛው ማኅተም በጨለማው ዘመን በክርስቲያኖች ላይ የደረሰውን መንፈሳዊ ሞት በተገቢ መንገድ ይገልጽልናል፡፡

**"ዘይቱና የወይን ጠጁ" በሦስተኛው ማኅተም መቅሰፍት እንደማይጎዳ ራእ. 6፡6 ይነግረናል፡፡ ዘይት መንፈስ ቅዱስን፣ ወይን ደግሞ የየሱስ ክርስቶስን ማዳን ይወክላል፡፡ የእግዚአብሔር ቃል እጦት በሚከሰትበት ጊዜ እንኳ እውነትን ለሚሹ ሁሉ መንፈስ ቅዱስ ያለማቋረጥ በሥራ ላይ ስለ መሆኑ ይህ በተጨባጭ ምን ይነግረናል?**

## ረቡዕ ጥር 22

# የአምስተኛው ማኅተም መከፈት

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 6:9-10፡፡ ምንድን ነው--እየተከሰተ ያለው ነገር?

---

---

በመጽሐፍ ቅዱስ ነፍስ የተሰኘው ቃል መላውን ሰብዓዊ ማንነት ይወክላል (ዘፍ. 2፡7)፡፡ የእግዚአብሔር ታማኝ ሕዝቦች ላይ የደረሰው ሞትና ስደት በዚህ ስፍራ የቀረበበት መንገድ--በምድራዊው የመስዋዕት ሥርዓት ይቀርብ ከነበረው በተመሳሳይ ደማቸው ከመሠዊያው በታች ፈስሶ ነው (ዘፀ. 29፡12፣ ዘሌዋ. 4፡7)፡፡ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ለወንጌል ታማኝ መሆናቸው ኢፍትሐዊ ፍርድና ሞት አስከትሎባቸዋል፡፡ በዚህም አምላካቸው ጣልቃ ገብቶ አሳዳጆቻቸውን እንዲበቀል ወደ እግዚአብሔር አልቅሰዋል፡፡ እነዚህ ጥቅሶች በምድር ስለተፈጸመው ግፍ ከመናገር ውጪ ስለ ሙታን ሁኔታ የሚሉት አንዳችም ነገር የለም፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 6፡11፣ ዘዳ. 32፡43፣ መዝ. 79፡10፡፡ እግዚአብሔርን አጥብው ይዘው ለነበሩ ሰማዕታት የሰማይ ምላሽ ምን ነበር?

---

---

ሰማዕት ቅዱሳን የክርስቶስን ጽድቅ የሚያመለክተው ነጭ ልብስ የተሰጣቸው ሲሆን፤ ንጽህናቸውን የሚያመላክተው ይህ ገጸበረከት የጸጋ ስጦታውን ለሚቀበሉ የተዘጋጀ ነው (ራእ. 3፡5፣ 19፡8)፡፡ ከዚያም እነርሱ ባለፉበት ተመሳሳይ ጎዳና ወንድሞቻቸው አልፈው ፍጹም እስኪሆኑ እንዲታገሱ ተነገራቸው፡፡ እዚህ ላይ በግሪክ ቋንቋ የተጻፈው ራእ. 6፡11 ቁጥር የሚል ቃል እንደሌለው ልብ ይሏል፡፡ ከክርስቶስ ዳግም ምጽአት አስቀድሞ የሰማዕት ቁጥር የተፈለገ አኻዝ ላይ መድረስ ይኖርበታል የሚል መልእክት የራእይ መጽሐፍ የለውም፡፡ ይልቁንም በባህሪያቸው ፍጽምና ዙሪያ ይናገራል፡፡ የእግዚአብሔር ሕዝቦች በመልካም ሥራቸው ሳይሆን፤ ነገር ግን የክርስቶስ ጽድቅ የሆነውን ነጭ መጎናጸፊያ በመልበስ ፍጹማን ሆኑ (ራእ. 7፡9-10)፡፡ ሰማዕት የሆኑት ቅዱሳን እስከ ክርስቶስ ዳግም ምጽአትና የሺ ዓመቱ መጀመሪያ በመቃብር ይቆያሉ (ራእ. 20፡10)፡፡

ምንም እንኳ የሰባተኛው ማኅተም ሁኔታ በታማኝነታቸው የተነሳ ሚሊዮኖች ሰማዕት የሆኑበትንና በታሪክ መካከለኛው ዘመን ተብሎ የሚጠራውን ጊዜ ቢሸፍንም፤ ከዚህ በተጨማሪ ከአቤል ደም አንስቶ (ዘፍ. 4፡10) እግዚአብሔር በመጨረሻ " 'ስለ አገልጋዮቹ ደም' " (ራእ. 19፡2) እስከሚበቀል ያለውን የእርሱን ሕዝቦች ሥቃይና መከራ ወደ አእምሮ ያመጣል፡፡

"ጌታ ሆይ እስከ መቼ?" የተሰኙት ቃላት በዘመናት በሥቃይ ያለፉ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ልቅሶ ነው፡፡ **ለመሆኑ በዚህ ሕይወት ስለ ፍትሕ መጓደል ያልጮኸ ማን አለ? አንድ ቀን ኢፍትሐዊነት በእርግጠኝነት ፍጻሜ ያገኛል ከሚል እምነት--ከአምስተኛው ማኅተም ትዕይንት ምን ዓይነት መጽናናት ያገኛሉ?**

## ሐሙስ ጥር 23

# የስድስተኛው ማኅተም መከፈት

በዚህ ጥላቻ በነገሠበት ዓለም የእግዚአብሔር ሕዝቦች ላይ የሚደርሰውን ኢፍትሐዊነትና አምላካቸው ጣልቃ እንዲገባላቸው የሚያሰሙትን ልቅሶ በአምስተኛው ማኅተም እንመለከታለን፡፡ እነሆ እግዚአብሔር የሕዝቡን ጸሎት ሰምቶ ጣልቃ የሚገባበት ጊዜ ደርሶአል!

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 6፡12-14፣ ማቴ. 24፡29-30፣ 2ተሰ.1፡7-10፡፡ በመልእክቶቹ የምናገኘው የተገለጠ ነገር ምንድን ነው?

እነዚያ አስቀድሞ በየሱስ የተነገሩ (ማቴ. 24፡29-30) እና በመካከለኛው ዘመን “ታላቁ መከራ” (ራእ. 7፡14) ማብቂያ ወቅት ገቢራዊ የሆኑ የዳግም ምጽአቱ ጠቋሚዎች--የስድስተኛው ማኅተም ፈለካዊ ምልክቶች ናቸው፡፡ በዚህ ስፍራ ፀሐይ፣ ጨረቃ እና ከዋክብት በተምሳሌታዊ አባባል ሳይሆን በግልጽ ቀርበዋል፡፡ እንደ እና የመሰለ ዓይነት ቃላት ጥቅም ላይ ሲውሉ፤ ከተምሳሌታዊ አባባል ጋር የማመሳሰል ሁናቴ ይስተዋላል፡፡ ፀሐይዋ እንደ ማቅ ጠቆረች፣ ጨረቃዋም በሙሉ እንደ ደም ቀላች፣ የበለስ ዛፍ በብርቱ ነፋስ ስትወዛወዝ ያልበሰለው ፍሬ ከእርሷ እንደሚረግፍ ከዋክብት ረገፉ፣ ሰማይም እንደ ጥቅልል መጽሐፍ ተጠቅልሎ ዐለፈ፡፡ የምዕራቡ ዓለም ክርስቲያኖች በ1755 ለደረሰው ርዕደ መሬት ዕውቅና ይሰጣሉ፡፡ በምስራቃዊው ኒው ዮርክ እና ደቡብባዊው ኒው ኢንግላንድ ግንቦት 19/ 1780--እንደ ወትሮው ሳይሆን በጽልመት የተዋጠ ዕለት ማለፉ ተዘግቦአል፡፡ በተጨማሪ አስገራሚ የተባለ የተወርዋሪ ከዋክብት ዝናብ--ሕዳር 13/ 1833 በአትላንቲክ ውቂያኖስ ዘንቦአል፡፡ እነዚህ እንግዲህ ከየሱስ ዳግም ምጽአት ጋር ተያይዞ የተነገሩ ትንቢቶች ፍጻሜ ማመሳከሪያ ናቸው፡፡ ሁናቴዎቹ--ታላቁ ዳግም መነቃቃት በመባል ለሚታወቀው በብዙ ምዕራፎች የተከፋፈለ የመነቃቂያ መርኀ ግብር መጀመር መንስኤ ሆኖአል፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 6፡15-17፣ 19፡11-21፣ ኢሳ. 2፡19፣ ሆሴ 10፡8፣ ሉቃ. 23፡30፡፡ ክርስቶስ ዳግም ሲገለጥ በተለያየ የኑሮ ዘይቤ ያለፉ ሕዝቦች ከሚከሰተው ነውጥ ራሳቸውን ለመደበቅ የሚያደርጉትን ጭንቀትና ጥበት በጥቅሶቹ የቀረቡት ትዕይንቶች ያስቃኙናል፡፡ “ ‘ተራሮቹንና ዐለቶቹንም፣ በላያችን ውደቁ፤ በዙፋኑ ከተቀመጠው ፊት ከበጉም ቁጣ ሰውሩን’ ” (ራእ. 6፡16)፡፡ ፍትሕ ሊሰፍንና ክርስቶስ “በቅዱሳኑ ዘንድ ሊከብር” (2ተሰ. 1፡10) እነሆ ጊዜው ደርሶአል፡፡ የዐመጸኞች መጨረሻ በራእ. 19፡17-21 ቀርቦአል፡፡

በሽብር ሥቃይ የወደቁት ዐመጸኞች “‘ታላቁ የቁጣው ቀን መጥቶአልና፤ ማንስ ሊቆም ይችላል?’ ” ሲሉ በሚያቀርቡት የሸንገላ ጥያቄ ትዕይንቱ ይደመደማል፡፡

“‘ እርሱ የሚመጣበትን ቀን ማን ሊቋቋመው ይችላል?’ ” (ሚልክ. 3፡2)፡፡ ለዚህ ጥያቄ ምላሽ የሚሰጡበት መንገድ ምን ይመስላል? ለመልስዎ የሚያቀርቡት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምክንያትስ ምንድን ነው? መልስዎን በሰንበት ትምህርት ጥናት ላይ ይዘው ለመቅረብ ይሞክሩ፡፡

# አርብ

ጥር 24

ተጨማሪ ሃሳብ ፡ Read Ellen G. White, “The World’s Need,” pp. 457–460, in Testimonies to Ministers and Gospel Workers.

የሰባቱን ማኅተሞች መከፈት የሚያሳየው ራእይ እግዚአብሔር በምድር ላሉ ሕዝቦቹ የሚጠነቀቅ አምላክ መሆኑን የሚያመላክት ተምሳሌት ነው፡፡ ኬኔት ኤ. ስትራንድ በመባል የሚታወቁት ጸሐፊ የሚከተለውን ሃሳብ አስፍረዋል፡

“እግዚአብሔር ሁሌም ለሕዝቡ የሚጠነቀቅ አምላክ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ያረጋግጥልናል፡፡ እግዚአብሔር ሕዝቦቹ የሚያስፈልጋቸውን ለማሟላት ዘወትር ከጎናቸው እንደ ነበር ታሪክ ራሱ እማኝ ይሆነናል፡፡ እንዲሁም ስለ ምድር መጨረሻ የተሟላ መረጃ በመስጠት በልግስና የተሞላና የተትረፈረፈ ዘላለማዊ ህይወት ባለቤት ያደርጋል፡፡ የራእይ መጽሐፍ ይህን ርዕሰ ጉዳይ አንስቶ ሰፋ ባለ ውብ አቀራረብ ይተነትነዋል፡፡ ስለዚህ የራእይ መጽሐፍ በምንም ዓይነት ከተለመደው የመጽሐፍ ቅዱስ ሥነ ጽሑፋዊ ቅኝት ያፈነገጠ፣ በውድቀትና ጥፋት የተሞላ ሥራ አይደለም፡፡ ይልቁንም የመጽሐፍ ቅዱስን መሰረተ ሃሳብ የያዘና የመልእክቱ የልብ ትርታ ነው፡፡ የራእይ መጽሐፍ አጥብቆ እንደሚያመለክተው ሞትና ሲኦልን ድል ያደረገው ‘ሕያው’ የሆነው እርሱ (ራእ. 1፡15) በእርግጥ ታማኝ ተከታዮቹን ፈጽሞ አይተዋቸውም፡፡ ደግሞም በሥቃይ የተሞላ የሰማዕት ሞት ቢሞቱም እንኳ ‘የሕይወት አክሊል’ የሚጠብቃቸው ባለ ድል ናቸው (ራእ. 2፡10፣ 21፡1-4፣ 22፡4)፡፡ ”—Kenneth A. Strand, “The Seven Heads: Do They Represent Roman Emperors?” in Symposium on Revelation—Book 2, Daniel and Revelation Committee Series (Silver Spring, Md.: Biblical Research Institute, 1992), vol. 7, p. 206.

*የመወያያ ጥያቄዎች፡*

1.ሰባቱ *ማኅተሞች ከተከፈቱበት ትዕይንት ምን ዓይነት ጠቃሚ ትምህርቶች አገኙ? ነገሮች የቱንም ያህል በምድር የከፉ ሊሆኑ ቢችሉ--እግዚአብሔር ግን ዛሬም ኃያል ገዢ በመሆኑ ውሎ አድሮ በክርስቶስ ያለን የተስፋ ቃል ሙሉ ለሙሉ ፍጻሜ ያገኛል ብለው የሚያምኑት ለምንድን ነው?*

2.“*ቤተ ክርስቲያን ሰዎች ይድኑ ዘንድ በእግዚአብሔር የተሰየመች ተቋም ናት፡፡ ይህች ተቋም አገልግሎት እንድትሰጥ ሆና የተደራጀች ሲሆን ተልዕኮዋ ወንጌልን ለዓለም ማዳረስ ነው፡፡”*—Ellen G. White, The Acts of the Apostles, p. 9. *ስለ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንዎ አሰብ ያድርጉ፡፡ የወንጌልን መልእክት ይዞ ወደ ሕዝብ ለመድረስ ይበልጥ ታማኝ መሆን የሚቻለው እንዴት ነው?*

3.*በሐሙስ ትምህርት መጨረሻ ለቀረበው ጥያቄ ያዘጋጁትን መልስ በሰንበት ትምህርት ላይ ይዘው ይቅረቡ፡፡ በዚያ ቀን (በዳግም ምጽአቱ) ታማኝ ሆኖ መገኘት የሚችል ማን ነው? ለዳግም ምጽአቱ ዝግጁ ሆነን ለመገኘት ዛሬን እንዴት እንኑር--ከሚል ሃሳብ አኳያ በመልስዎ አንደምታዎች ላይ ተወያዩ፡፡*

# ፪ኛ ትምህርት

ከጥር 25 - የካቲት 1

# የታተሙት የእግዚአብሔር ሕዝቦች

ሰንበት ከሰዓት

*ለዚህ ሣምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ራእ. 7፤ 2ጴጥ. 3:9–14፤ ዘዳ. 8:11–17፤ ራእ. 14:4-5፤ 12፤ 17:5፤ ሮሜ 3:19–23፡፡*

**መታሰቢያ ጥቅስ :-** "'እነዚህ ከታላቁ መከራ የመጡ ናቸው፤ ልብሳቸውንም በበጉ ደም አጥበው አንጽተዋል'" (ራእ. 7፡14)፡፡

በክርስቶስ አምናለሁ የሚል እያንዳንዱ ግለሰብ ስለታማኝነቱ አምላካዊውን በረከት ሲቀበል፤ በተቃራኒው በዐመጻ የቀጠሉ--ከኩነኔ ጋር እንደሚጋፈጡ የሰባቱ ማኅተሞች መከፈት መልእክት ያሳየናል፡፡ የመጀመሪያዎቹ አራት ማኅተሞች እግዚአብሔር ሕዝቡን ከመንፈሳዊ ልፍስፍስነት አንቅቶ ባለ ድል የሚያደርግበትን ቅጣት ነክ አካሄዶች ይገልጻሉ፡፡ በተጨማሪም የእግዚአብሔር ሕዝቦች ለወንጌል ጸለምተኛ ብሎም ጸር በሆነው በዚህ ዓለም ኢፍትሐዊ ፍርድና የመከራ ገፈት ይቀበላሉ፡፡ እግዚአብሔር ሕዝቦቹን የጎዱትን ለማስተናገድ ያለው ዝግጁነት በስድስተኛው ማኅተም መከፈቻ ላይ ይታያል፡፡ እዚህ ላይ ምዕራፍ 7 በተለይ በስድስተኛውና በሰባተኛው ማኅተሞች መካከል መግባቱን ልብ ይሏል፡፡ ስድስተኛው ማኅተም ወደ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ይዞን ይመጣል፡፡ በክርስቶስ ዳግም ምጽአት ዐመጸኞች ፍርድ ሲጠብቃቸው፤ በታማኝነት ጸንተው የቆሙት ግን ይታተማሉ ሲል ራእ. 7 ይነግረናል፡፡

ከዳግም ምጽአቱ አስቀድሞ ያሉትን የእግዚአብሔር የመጨረሻ ዘመን ሕዝቦች ራእ. 7 ለይቶ ያስቀምጣቸዋል፡፡ የእነዚህ ሕዝቦች ሌሎች መለያ ባህሪዎች በራእ. 14፡1-5 ቀርበዋል፡፡ ስድስተኛውና ሰባተኛው መለከት በሚነፋበት ወቅት በመሃል የገባ አንድ ሌላ የዕረፍት ጊዜ አለ (ራእ. 10፡1፤ 11፡14)፡፡ ይህ የዕረፍት ጊዜ ከምዕ. 7ቱ ትዕይንት የጊዜ ሁናቴ ጋር ስምሙ በመሆን የእግዚአብሔርን የመጨረሻ ጊዜ ሕዝቦች ተሞክሮና ተግባር ይገልጻል፡፡

# እሑድ ጥር 26

## ነፋሳቱን መያዝ

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 7፡1–3፣ 2ጴጥ. 3:9–14፡፡ መላእክቱ ነፋሶቹን የሚይዙት እስከ መቼ ነው? በግንባር ላይ የማተሙ ሥራ ከተጠናቀቀ በኋላ ምን ይከሰታል?

---

---

ነፋሳት በብሉይ ኪዳን አውዳሚውን ኃይል ይወክላሉ፡፡ ነፋስ እግዚአብሔር በዐመጸኞች ላይ የሚሰጠውን ፍርድ የሚያስፈጽምበት መንገድ በመሆን ይታወቃል፡ ፡ዳግም ምጽአቱ እውን ከመሆኑ ጥቂት ቀደም ብሎ ንስሐ ባልገቡ ዐመጸኞች ላይ የሚወርዱት መቅሰፍቶች፤ የመጨረሻዎቹ ሰባት መቅሰፍቶች የሚገለጡበት ሌላው መንገድ ነው (ራእ. 16)፡፡ ሆኖም የእግዚአብሔር ሕዝቦች መታተም እስኪጠናቀቅ እነዚህ አውዳሚ ኃይላት ከሚያደርሱት ጥፋት እንዲገቱ ይደረጋሉ፡፡

ጥንታዊው የማኅተም ተቀዳሚ ፍቺ ባለቤትነትን ያመላክታል፡፡ በአዲስ ኪዳን መታተም ማለት " 'ጌታ የእርሱ የሆኑትን ያውቃል' " (2 ጢሞቴ. 2:19) የሚል ተምሳሌታዊ ፍቺ አለው፡፡ የገዛ ሕዝቦቹን ጠንቅቆ የሚያውቀው እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ ማኅተም ያትማቸዋል (ኤፌ. 1፡13-14፣ 4፡30)፡፡ በመጨረሻዎቹ ቀናት በግንባር ላይ የሚታተመው የእግዚአብሔር ማኅተም በእርሱ በኩል ለመቆም የመረጡትን ወገኖች የሚያመላክት ይሆናል (ራእ. 14፡1)፡፡ የእግዚአብሔር ማኅተም በዐይን የሚታይ ምልክት ሳይሆን "እንዳይናወጡ ሆኖ በአእምሮም ሆነ በመንፈስ በእግዚአብሔር እውነት ላይ ተረጋግቶ ማረፍ ነው"—Ellen G. White, Last Day Events, p. 220. ፈቅደውና ዐውቀው በአውሬው ወገን የቆሙ የአውሬውን ምልክት ይቀበላሉ (ራእ. 13፡16-17)፡፡

በአምላካዊው ማኅተም የታተሙ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ታማኝነት በያንዳንዱ ትውልድ ሲፈተን ኖሮአል፡፡ ሆኖም ታማኞች በመጨረሻው አስከፊ ወቅት የሚደርስባቸው ፈተና የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ያለ ጥሰት መጠበቅ ይሆናል (ራእ. 12፡17፣ 14፡12)፡፡ በተለይ አራተኛው ትእዛዝ እግዚአብሔርን የመታዘዛችን መፈተኛ ይሆናል (ራእ. 14፡7)፡፡ በረጅሙ የመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን ሰንበት የእግዚአብሔር ሕዝቦች ምልክት እንደ ነበር (ዘፀ. 31፡12–17፣ ሕዝ. 20፡12፣ 20) ሁሉ በመጨረሻውም ቀውስ ወቅት ለእግዚአብሔር የሚኖረን ታማኝነት ምልክት ይሆናል፡፡

በተጨማሪ ማኅተም በኋለኛው ዘመን ገቢራዊ ከሚሆኑት የመጨረሻዎቹ አውዳሚ ሰባት መቅሰፍቶች መጠበቂያ ምልክት ሆኖ ያገለግላል (ሕዝ. 9፡1-11፣ ራእ. 7፡1-3)፡፡ ይህን ተከትሎ በራእ. 6፡17 ለሚነሳው ጥያቄ የመጨረሻ ምላሽ ይሰጣል፡ በእግዚአብሔር ቁጣ ቀን ከለላ አግኝተው መቆም የሚችሉት የታተሙት የእግዚአብሔር ሕዝቦች ይሆናሉ፡፡

ጳውሎስ ለቤዛ ቀን የታተምንበትን መንፈስ ቅዱስ ማሳዘን እንደ ሌለብን ያስጠነቅቀናል (ኤፌ. 4፡30)፡፡ **ሐዋርያው ምን ማለቱ ነው? ለመሆኑ አንድ ሰው መንፈስ ቅዱስን የሚያሳዝነው እንዴት ነው? መልሱን ካገኙ፤ እርሱን እንዳያሳዝኑ ሊረዳዎ የሚችሉ ምን ዓይነት ምርጫዎች ማድረግ ይችላሉ?**

**ሰኞ** ጥር **27**

# የታተሙት የእግዚአብሔር ሕዝቦች

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 7፡4-8፡፡ ለመሆኑ የታተሙት የእግዚአብሔር ሕዝቦች ቁጥር ምን ያህል ነው? የዚህ ዉሱን ሆኖ የቀረበ አኻዝ ትርጉም ምንድን ነው?

---

---

የታተሙት ወገኖች ቁጥር የተቀመጠበት አካሄድ የኅትመት ሥራው ፍጻሜ ማግኘቱን ያመለክታል፡፡ ከ12ቱ የእስራኤል ነገዶች የተውጣጡት 144 ሺ መሆናቸውን ዮሐንስ የሰማው ቁጥር ይገልጻል፡፡ እዚህ ላይ የቀረበውን የቁጥር ማጣቀሻ ቃል በቃል በመውሰድ ፋንታ በተምሳሌትነት ሊያመላክት ለፈለገው ነጥብ አጽንኦት መስጠት ተገቢ ነው፡፡ ይህ አኻዝ 12 x 12 x 1,000 = 144,000 ውጤት ነው፡፡ አሥራ ሁለት ቁጥር የእግዚአብሔር ሕዝቦች ተምሳሌታዊ አኻዝ ነው፡፡ 12ቱ የእስራኤልን ነገዶች እንዲሁም በ12ቱ ሐዋርያት መሠረት ላይ የታነጹት ቤተ ክርስቲያናት (ኤፌ. 2፡20) ለአብነት መወሳት ይችላሉ፡፡ ስለዚህ ይህ የጥንቷ እስራኤል ዘመናዊ ማሳያ የሆነ ተምሳሌታዊ 144,000 የመጨረሻውን ዘመን የእግዚአብሔር ሕዝቦች ይወክላል፡፡

በእርግጥ በራእ. 7 የቀረቡት 12ቱ የእስራኤል ነገዶች ተምሳሌታዊ አይደሉም፡፡ ምክንያቱም 12ቱን የእስራኤል ነገዶች ዛሬ አናገኛቸውም፡፡ እስራኤላውያን በአሦራውያን ሽንፈት በገጠማቸው ወቅት ዐሥሩ ነገዶች በምርኮ ተወስደው የነበረ ሲሆን (2ነገሥ. 17፡6-23) በዚህም ከሌሎች ሕዝቦች ጋር ተዋህደው ነበር፡፡ ስለዚህ የዛሬው ይሁዲነት 12ቱን ነገዶች የሚያሟላ አይደለም፡፡

እንዲሁም በራእ. 7 የቀረቡት 12 ነገዶች መደበኛውን ዝርዝር አያመላክቱም፡፡ በሮቤል ነገድ ፋንታ ይሁዳ በመጀመሪያ የተጠቀሰ ሲሆን፤ ዳን እና ኤፍሬም ግን ከነጭራሹ አልተጠቀሱም፡፡ በእነርሱ ምትክ ዮሴፍ እና ሌዊ ተካትተዋል፡፡ ዳን እና ኤፍሬም ያልተካተቱበት ዋንኛ ምክንያት በብሉይ ኪዳን ዘመን ክህደት የፈጸሙና በጣኦት አምልኮ የወደቁ ስለነበሩ ነው (ይሁዳ 18:27–32፣ ሆሴ 4:17)፡፡

በራእ. 7 የተጠቀሱት ነገዶች ዝርዝር ታሪካዊ ሳይሆን መንፈሳዊ ነው፡፡ የዳን እና ኤፍሬም ነገዶች ታማኝ አለመሆን--ከታተሙት የእግዚአብሔር ሕዝቦች መሃል ስፍራ እንደሌላቸው ያሳየናል፡፡ እንዲሁም የአዲስ ኪዳኗ ቤተ ክርስቲያን እንደ 12ቱ የእስራኤል ነገዶች መጠቀሷን እንመለከታለን፡፡ በራእ. 7 የተጠቀሱት 12ቱ ነገዶች አይሁዳውያንንና አረማውያንን ጨምሮ መላውን የእግዚአብሔር ሕዝቦች ይወክላሉ፡፡

እነዚህ 144000 የቀረቡበት መንገድ የጥንት እስራኤላውያን ለውጊያ ሲሄዱ ይከተኩት በነበረ ዓይነት የጦር አሰላለፍ ነው፡፡ በጥንታዊቷ እስራኤል ተዋጊው የጦር ክፍል 1ሺ ወታደሮች ነበሩት (ዘኁ. 31፡3-6)፡፡ ተምሳሌታዊ አኻዝ የሆነው 144,000 ለመጨረሻው ውጊያ ዝግጁ የሆኑ በ1ሺ የጦር ክፍል ውስጥ ያሉ 144 ምድብተኞችን የያዘ የቤተ ክርስቲያን ተዋጊ ሰራዊት ነበር(ራእ. 17፡14)፡፡ ከዚህ በተቃራኒ የሚገኘው የጠላት ሰራዊት ደግሞ 200 ሚሊዮን ነበር (ራእ. 9:16)፡፡

***ምንም እንኳ በመጽሐፍ ቅዱስ የተለመደ ቢሆንም በወታደራዊ አኻዞችና አገላለጾች ሁሌም ምቾት ላይኖረን ይችላል፡፡ የታላቁን ተቃርኖ ተጨባጭ ሁኔታ ጠብቀን መጓዛችን ወታደራዊውን አኻዝና አገላለጽ መገንዘብ እንድንችል እንዴት ይረዳናል?***

## ማክሰኞ ጥር 28

# እጅግ ብዙ ሕዝብ

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 7፡9-14፡፡ ዮሐንስ የሚመለከተው እንዴት ያለውን የቅዱሳን ወገን ነው? እነዚህ ወገኖች የተገለጹበት መንገድ ምን ይመስላል? ከወዴትስ ነው የመጡት? በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት በታላቅ ድምፅ ምን ብለው ጮኹ?

ዮሐንስ የተመለከታቸው እነዚህ እጅግ ብዙ ሕዝቦች “ ‘ከታላቁ መከራ የመጡ፤ ልብሳቸውንም በበጉ ደም አጥበው ያነጹ’ ” (ራእ. 7፡14) ነበሩ፡፡ ታማኝነታቸውን በሚያመለክት ፍጹም በሆነ የእርሱ የጽድቅ ሸማ የተሸፈኑ ሲሆን፤ ይህም በየትኛውም ዓይነት አሰቃቂ መከራ ውስጥ ቢያልፉም ለየሱስ በነበራቸው ታማኝነት ጸንተው የኖሩ ልዩ ሕዝቦች መሆናቸውን ያመለክታል፡፡ በመላው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የምናገኘው ታላቁ የጽድቅ በእምነት ርዕሰ ጉዳይ እነሆ በዚህ ስፍራም ቀርቦ እንመለከታለን፡፡ እነዚህ ሕዝቦች ከየትኛውም ዓይነት የሕብረተሰብ ክፍል ቢመጡ፣ ከረጅሙ የምድር ታሪክ ወይም የምድር የመጨረሻዎቹ ቀናት 144000 አካል ቢሆኑ--የደኅንነት፣ የዘላለማዊ ህይወት፣ የአዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ባለቤት መሆን የቻሉት በጸጋው በተሰጣቸው የክርስቶስ ጽድቅ ብቻ ነው!

“ከዙፋኑ አጠገብ ያሉት ወገኖች ለክርስቶስ በነበራቸው ቅንአት ከሰይጣን ጋር ብርቱ ተጋድሎ ያደረጉ ከእሳት የተነጠቁ ትንታጎች ሲሆኑ፤ አዳኛቸውን ጥልቅ በሆነና በማያባራ አምልኮ ተከትለዋል፡፡ በቀጣይ ያሉት ደግሞ ሐሰተኝነትና ኪዳን ማፍረስ በተንሰራፋበት ዓለም የክርስትናን ባህሪ ጠብቀው በንጽሕና የተመላለሱ፣ የክርስትናው ዓለም አፉን ሞልቶ ተሽረዋል ላላቸው አምላካዊ ሕጎች ተገቢውን ዋጋ የሰጡ፣ በረጅሙ እልህ አስጨራሽ ግብግብ ስለ እምነታቸው ሰማዕት የሆኑ ናቸው፡፡ ‘እነሆ፤ በዙፋኑና በበጉ ፊት ማንም ሊቆጥራቸው የማይችል ከሕዝብ፣ ከነገድ፣ ከወገን፣ ከቋንቋም ሁሉ እጅግ ብዙ ሕዝብ ቆመው ነበር፤ እነርሱም ነጭ ልብስ ለብሰው፣ የዘንባባ ዝንጣፊ በእጃቸው ይዘው ነበር’ ራእ. 7፡9፡፡ ከእንግዲህ የውጊያቸው ዘመን አከትሞ የድል ባለቤቶች ሆነዋል፡፡ ሩጫቸውን በአሸናፊነት ጨርሰው ሽልማታቸው ላይ ደርሰዋል፡፡ በእጃቸው የያዙት የዘንባባ ዝንጣፊ የድል አድራጊነታቸው ተምሳሌት ሲሆን ነጩ ልብስ ደግሞ አሁን የራሳቸው ያደረጉት የክርስቶስ እንከንየለሽ ጽድቅ ነው፡፡”—Ellen G. White, The Great Controversy, p. 665.

***አዎ፡ የእምነት ስጦታ በሆነው በክርስቶስ ጽድቅ ተሸፍነናል፡፡ ሆኖም ፈተናና ታላቅ መከራ ሊገጥመን ቢችል እንኳ ታማኝነታችንን ሳናጓድል የእምነታችንን ንጽህና እንደ ጠበቅን መጓዝ የምንችለው እንዴት ነው? ወይም ምቾት በበዛበትና ብልጽግና በተንሰራፋበት ህይወት ያንን እምነትና ታማኝነት ጠብቀን መዝለቅ የምንችለው እንዴት ነው? (ዘዳ. 8:11–17)፡፡***

ረቡዕ ጥር 29

## በጉን የሚከተሉ

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 14፡1-5፡፡ የ144000ዎቹ ሦስት ዓይነተኛ መለያ ባህሪያት ምንድን ናቸው? ባህሪያቱ በራእ. 14፡12 ከቀረቡት የመጨረሻው ጊዜ ቅዱሳን ጋር እንዴት ይዛመዳሉ?

---

---

አንድ መቶ አርባ አራት ሺዎቹ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁና የየሱስ እምነት ያላቸው (ራእ. 14፡12) ሕዝቦች አድርጎ ራእ. 14፡4-5 ያቀርባቸዋል፡፡ ምንም እንኳ በምድር የመጨረሻ ምስቅልቅል ወቅት የሰይጣንን ቁጣ በሙላት ቢጋፈጡም፤ ከየሱስ ጋር በነበራቸው የቀረበ ግንኙነት በጽናት መቆም ችለዋል፡፡

ራእ. 17፡5 ከሚሰጠን ብርሃን አኳያ--አንድ መቶ አርባ አራት ሺዎቹ ከሴቲቱ ጋር እንዴት ሳይረክሱ ቀሩ? ይህ “ለእግዚአብሔርና ለበጉ በኵራት” (ራእ. 14፡4) ሆነው ከሕዝቦች መካከል ከመዋጀታቸው እውነታ ጋር እንዴት ይዛመዳል?

---

---

ፆታዊ እርክስና ለእግዚአብሔር ታማኝነትን የማጉደል ተምሳሌት ነው፡፡ ራእ. 17፡5 በምድር ታሪክ መዝጊያ ከመላው የዓለም ሕዝቦች ጋር ምንዝር ስለምትፈጽመው ባቢሎንና ልጆቿ ይናገራል (ራእ. 18፡3)፡፡ ሆኖም አንድ መቶ አርባ አራት ሺዎቹ ግን ለክርስቶስ ታማኝ ሆነው በመጽናት፤ ከባቢሎንና በክህደት ካሉ ኃይማኖታዊ ተቋማት ጋር ሊያረክሱ የሚችሉ ግንኙነቶችን ተቋቁመው ይዘልቃሉ፡ “በጉ ወደሚሄድበት ሁሉ ይከተሉታል” (ራእ. 14፡4)፡፡

“ለእግዚአብሔርና ለበጉ በኵራት እንዲሆኑ ከሰዎች መካከል የተዋጁ” (ራእ. 14፡4) በሚል ስለ 144000ዎቹ ተጨማሪ መግለጫ ተሰጥቶአል፡፡ በጥንታዊቷ እስራኤል ምርጦቹ የመኸር በኵር ፍሬዎች ለእግዚአብሔር ይቀርቡ ነበር፡፡ በኵራት የተሰኘው ቃል ከዓለም ሕዝቦች በተለየ የዳኑትን የእግዚአብሔር ሕዝቦች ይወክላል (ኤር. 2፡3፤ ያዕ. 1፡18)፡፡ 144000ዎቹን የተለዩ የሚያደርጋቸው የዳኑበት መንገድ ሳይሆን ሞትን ሳይቀምሱ መለወጣቸው ነው፡፡ ስለዚህ ረጅም ዘመን ላስቆጠረው መከር በኵራት ናቸው (ራእ. 14፡14-16)፡፡

***ሳይታወቀን በመንፈሳዊ ምንዝር አደጋ ላይ ልንወድቅ የምንችልባቸው መንገዶች የትኞቹ ናቸው? በእንዲህ ዓይነቱ አደጋ ላይ እንዳልሆን እያሰብን ራሳችንን ለምን እናሞኛለን?***

## ሐሙስ ጥር 30

# ማዳን የአምላካችንና የበጉ ነው

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 14፡5፣ 2ጴጥ. 3፡14፡፡ የራእይ መጽሐፍ የእግዚአብሔርን የመጨረሻ ጊዜ ሕዝቦች "ነቀፋም የለባቸውም" ሲል ይገልጻቸዋል፡፡ ለመሆኑ በእንዲህ ዓይነት የንጽህና ሁናቴ መድረስ የሚቻለው እንዴ ነው?

---

---

"ከአፋቸው ምንም ዓይነት ውሸት አልተገኘም፤ ነቀፋም የለባቸውም" (ራእ. 14፡5) ይህ 144000ዎቹ የመጨረሻ የባህሪያቸው ሁኔታ ነው፡፡ "ውሸት" በሚል የተነገረው ቃል በመጨረሻው ጊዜ የሚገለጡትን የሰይጣን ማታለያዎች ያመለክታል (ራእ. 13፡14)፡፡ አብዛኛው የዓለም ሕዝብ እነዚህን ውሸቶች አምኖ ለመቀበል ሲመርጥ፤ የእግዚአብሔር የመጨረሻው ጊዜ ሕዝቦች ግን መዳን የሚያገኙበትን እውነት የሚወዱበት ፍቅር ይቀበላሉ (2ተሰ. 2፡10-11)፡፡ "ነቀፋም የለባቸውም" የተሰኘው አባባል 144000ዎቹ ለክርስቶስ ያላቸውን ታማኝነት ያመላክታል፡፡ የብሉይ ኪዳን ዘመኖቹ አብርሃም (ዘፍ. 17፡1) እና ኢዮብ (ኢዮ. 1፡1) ምንም እንኳ እንደ ማንኛውም ሰው ኃጢአት ቢሠሩም ነገር ግን ያለ ነቀፋ ነበሩ፡፡ ከሁለት ሺ ዓመታት በፊት ክርስቲያኖች ቅዱስና ጉድፍ የሌለው ህይወት እንዲኖሩ ጥሪ ቀርቦላቸዋል (ኤፌ. 5፡27፣ ፊልጵ. 2፡15)፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ሮሜ 3፡19-23፡፡ ሁሌም ቢሆን ይህን ወሳኝ እውነት ከፊታችን እንደ ጠበቅን መራመድ የሚኖርብን ለምንድን ነው?

---

---

የዚህ ዓለም ታሪክ ወደሚዘጉባቸው ቀናት እየተቃረብን ስንመጣ 144000ዎቹ የክርስቶስን ፀባይ በብርቱ ኃይል ያንጸባርቃሉ፡፡ ከቅድስናቸውና መልካም ሥራቸው ይልቅ መዳናቸው ክርስቶስ ለእነርሱ ያደረገውን ያንጸባርቃል (ኤፌ. 2፡8-9)፡፡ 144000ዎቹ ልብሶቻቸውን በበጉ ደም አጥበው በማንጻታቸው (ራእ. 7፡14) በእግዚአብሔር ፊት "ያለ ነውርና ያለ ነቀፋ" (2ጴጥ. 3፡14) መገኘት ችለዋል፡፡

"'የመለኮታዊው ተፈጥሮ ወራሾች' መሆን እስክንችልና የአዳኛችንን አምሳል በሙላት እስከምናንጸባርቅ ልንነጥርና ከማንኛውም ምድራዊነት ልንጠራ ይገባል...

"በውዝግብ የተሞላው ይህ ህይወት ሲያበቃ፣ ጥሩርና ሠልፍ በየሱስ እግሮች ስር ሲውል፣ የእግዚአብሔር ቅዱሳን ሲከብሩ፣ ያኔና ያኔ ብቻ--እነሆ ዳንን ያለ ኃጢአትም ሆንን ብለን ባስተማማኝ መናገር እንችላለን፡፡"—Ellen G. White, Selected Messages, book 3, pp. 355, 356.

***ወደፊት ለሚጠብቀን ዘላለማዊ ህይወት ንቁ ዝግጅት እያደረግን--ከአክራሪ ፍጹማዊነትና ወግ አጥባቂ ቅድስና ወጥመድ ተጠብቀን በቅድስና የተሞላ ህይወት መኖር የምንችለው እንዴት ነው? በሮሜ 3፡19-23 የምናገኛቸውን ታላላቅ እውነቶች ሁሌም መመሪያችን አድርገን መኳዝ የሚኖርብን ለምንድን ነው?***

# አርብ የካቲት 1

ተጨማሪ ሃሳብ፡ Read Ellen G. White, "Sinlessness and Salvation," pp. 353–357, in Selected Message, book 3.

የ144000ዎቹ ማንነት ሁሌም ትኩስ መከራከሪያ ርዕሰ ጉዳይ ሲሆን ይስተዋላል። ቅዱሳኑ በምድር ታሪክ መዝጊያ የሚገኙ የመጨረሻ ትውልዶች መሆናቸው በጣም ግልጽና ሁሉም የሚስማማበት ነጥብ ነው፡፡ እነዚህ ወገኖች ሰባቱ መቅሰፍቶች የሚወርዱባቸውን ብርቱ የመከራ ወቅቶች እንደሚያልፉና (ራእ. 7፡ 15-17) ታማኝነታቸው ከእነርሱ አስቀድሞ በየትኛውም ትውልድ ባልታየ መልኩ እንደሚፈተን እናውቃለን፡፡

ሆኖም እነማን የዚያ አኻዝ አካል እንደሚሆኑ ግልጽ ሆኖ አልቀረበልንም፡፡ እግዚአብሔር ለራሱ በምስጢር ከያዛቸው ነገሮች መሃል እንደ አንዱ ልንወስደው እንችላለን (ዘዳ. 29፡29)፡፡ የዳኑት ቅዱሳን ስብስብ እነማን እንደሚሆኑ የወደፊቱ ጊዜ ብቻ የሚገልጠው ይሆናል፡፡ ሆኖም በዚህ ዙሪያ የሚከተለው ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶናል፡

"ተረትና የይሆናል ልቦለዶችን በቤተ ክርስቲያን የሚያቀርቡ እንደሚኖሩ ክርስቶስ ተናግሮአል፡፡ እግዚአብሔር በአንጡራ ሐብትነት በልብ ጓዳ ተጠብቆ እንዲቆይ በማሰብ እነሆ የከበረውን፣ የሚያንጸውንና ባለ ግርማውን እውነት ሰጠ፡፡ ሰዎች ሊያውቁት ብዙም የማያስፈልጋቸውን ይህን ንድፈ ሃሳብ የሙጥኝ ብለው ልዩ

የማወቅ ጉጉት ሲያድርባቸው በእግዚአብሔር ምሪት ስር መሆናቸው ይቀራል። ሰዎች--ሊሆን ይችላል ወይም--እንበልና በሚል መነሾ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ ድምዳሜ ላይ ይደርሱ ዘንድ የእርሱ ፈቃድ አይደለም፡፡ የመቶ አርባ አራት ሺዎቹ አካል የሚሆኑት እነማን ናቸው? በሚሉ ለመንፈሳዊ ህይወታቸው አንዳችም ፋይዳ በሌላቸው ጥያቄዎችና ተቃርኖዎች ውስጥ ሕዝቦቹ እንዲወድቁ አምላካዊው ፍላጎት አይደለም፡፡ እነዚህ በእግዚአብሔር የተመረጡ--ያለ አንዳች ጥያቄ በአጭር ጊዜ ውስጥ ይህን ይረዳሉ፡፡"—Ellen G. White, Selected Messages, book 1, p. 174.

## የመወያያ ጥያቄዎች፣

**1.“ከመቶ አርባ አራት ሺዎቹ መካከል መገኘት እንድንችል እግዚአብሔር በሰጠን በሙሉ ኃይላችን እንትጋ፡፡”—Ellen G. White Comments, The SDA Bible Commentary, vol. 7, p. 970. እነዚህን አባባሎች ወደ ተግባር መለወጥ የሚችሉት እንዴ ነው? ይህ ትግል የየቀኑ ውሳኔዎ ላይ ተጽእኖ ማሳደር የሚችለው እንዴ ነው?**

**2.በምድር መጨረሻ የሚኖሩት የመቶ አርባ አራት ሺዎቹ አዲስ ዝማሬ ሌላው አጽንኦት የሚሰጠው ቁልፍ ባህሪያቸው ነው፡፡ ስለ ራስዎ ሕይወት ሲያስቡ--የዛሬው መንፈሳዊ ሁናቴዎ ከእግዚአብሔር ጋር ያሎትን ትኩስ ተሞክሮ ያንጸባርቃል? ወይስ የዛሬው ሕይወትዎ የሚያንጸባርቀው የአሁኑን ሳይሆን እግዚአብሔር ቀደም ባሉት ጊዜያት በእርስዎ ውስጥ ያደረገውን ታሪክ ብቻ ነው? የዛሬው ህይወትዎ የመንፈሳዊ ህይወትዎን አዲስ ዝማሬና ከክርስቶስ ጋር ያሎትን ተሞክሮ የሚያንጸባርቀው እንዴት ነው?**

**3.ክርስቶስን በማወቅና እርሱን በእውነት በማወቅ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? አንድ ሰው “ክርስቶስ ምን ይመስላል?” ብሎ ቢጠይቅዎ መልስዎ ምን ይሆናል? ለምን?**

**7ኛ ትምህርት**

**ከየካቲት 2 - 8**

# ሰባቱ መለከቶች

ሰንበት ከሰዓት

ለዚህ ሣምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ራእ. 8:1–13፣ ዘኍ. 10:8–10፣ ሕዝ. 10:2፣ ራእ. 10:1–11፣ ዳን. 12:6-7፣ ራእ. 11:1–13፣ ዘሌዋ. 16.

**መታሰቢያ ጥቅስ ፡-** **"ነገር ግን ሰባተኛው መልአክ መለከቱን በነፋባቸው ቀኖች፣ ለአገልጋዮቹ ለነቢያት በተገለጠላቸው መሠረት የእግዚአብሔር ምስጢር ይፈጸማል" (ራእ. 10፡7)፡፡**

በዘመናት በእግዚአብሔር ታማኞች ላይ የደረሰውን ሰቆቃ የሚያመለክተውን በመከራ ውስጥ ያለፉ የእግዚአብሔርን ሕዝቦች ልቅሶ በአምስተኛው ማኅተም ትዕይንት ተመልክተናል፡፡ እነርሱም " 'ጌታ ሆይ እስከ መቼ አትፈርድም?' " ሲሉ ከመሰዊያው ስር የእግዚአብሔርን ፍትሕ ሲማጸኑ በኖሩ ነፍሳት ሁኔታ ተገልጸዋል፡፡ በእነርሱ ላይ ጉዳት ያደረሱ አምላካዊውን ፍትሕ የሚቀበሉበት ጊዜ መቃረቡን የገለጸላቸው ከሰማይ የመጣ ድምፅ በጽናት እንዲጠብቁ አሳሰባቸው፡፡

የየሱስን ዳግመኛ ወደዚህ ምድር መጥቶ በታማኝ ተከታዮቹ ላይ ክፉ ያደረጉትን ለፍርድ እንደሚያቀርብ ራእ. 6፡15-17፡፡

የአምስተኛው ማኅተም ትዕይንት በዘመናት በእግዚአብሔር ሕዝቦች ላይ የደረሰውን አስከፊ ስቃይ--ይኸውም እግዚአብሔር ከአቤል አንስቶ እስከ ምድር ታሪክ መዝጊያ "ስለ አገልጋዮቹ ደም" (ራእ. 19፡2) ጻድቅ ፍርዱን እስከሚሰጥ ያለውን ጊዜ ይወክላል፡፡ በመከራ ያሉ ወገኖች እግዚአብሔር የሕዝቦቹን ጸሎት የሚሰማ አምላክ መሆኑን ሊያምኑና በጽናት ሊቆሙ የግድ ይሆናል፡፡

እግዚአብሔር ስለ ተገፉ ሕዝቦቹ በዘመናት ጣልቃ ሲገባና በጎዷቸው ላይ ፍርድ ሲሰጥ መኖሩን የሰባቱ መለከቶች ራእይ ያሳያል፡፡ የሰባቱ መለከቶች ዓላማ ሰማይ የእግዚአብሔርን ሕዝቦች ሥቃይና እንግልት በግዴለሽነት የሚያልፍ ላለመሆኑ ማረጋገጫ መስጠት ነው፡፡

እሁድ የካቲት 3

# የቅዱሳን ጸሎት

የራእ. 8 ትዕይንት--ሰባቱን መለከቶች ለመንፋት በተዘጋጁ በእግዚአብሔር ፊት የሚቆሙ ሰባት መላእክት ትዕይንት ይጀምራል፡፡ ሆኖም መለከቶቹ ከመነፋታቸው አስቀድሞ--ዓላማው የመለከቶቹን ሥነ መለኮታዊ ፍቺ መግለጽ የሆነ አንድ ሌላ ትዕይንት ይጨመራል፡፡

በራእ. 8፡3-4 የቀረቡትን ጥቅሶች በመቀጠል በየሩሳሌም መቅደስ ይከናወን ከነበረ የሠርክ መሥዋዕት የአይሁድ ሐተታ ጋር ያገናዝቡ፡፡ የእኩለ ቀን መሥዋዕት ሲቀርብ የመሥዋዕቱ ጠቦት በሚቃጠለው መሥዋዕት ማቅረቢያ ላይ ይደረግና ደሙ ከመሠዊያው ሥር ይፈሳል፡፡ ለአገልግሎት የተመደበው ካኅን የወርቁን ጥና ይዞ ወደ ቅዱሱ ስፍራ ይገባና በወርቅ መሠዊያው ላይ የዕጣን መሥዋዕት ያቀርባል፡፡ ካኅኑ ከወጣ በኋላ ጥናውን ከእጁ ሲለቀው ከፍ ያለ ድምፅ ያወጣል፡፡ በዚህ ጊዜ የዕለቱን የቤተ መቅደስ አገልግሎት ፍጻሜ የሚያበስሩ ሰባቱ ካኅናት መለከቶቻቸውን ይነፋሉ፡፡

የእኩለ ቀኑ አገልግሎት በራእ. 8፡3-5 ጥቅም ላይ የዋለበትን መንገድ ለማየት እምብዛም አያዳግትም፡፡ መልአኩ "በዙፋኑ ፊት ባለው የወርቅ መሠዊያ" (ራእ. 8፡3) የሚሠዋው ዕጣን መሰጠቱ ታላቅ ትርጉም አለው፡፡ ዕጣኑ የእግዚአብሔርን ሕዝቦች ጸሎት ይወክላል (ራእ. 5፡8)፡፡ ስለዚህ መልአኩ በእግዚአብሔር ፊት የሚያቀርበው የስደት ሥቃይ የደረሰባቸውን የእግዚአብሔር ሕዝቦች ጸሎት ነው። አሁን ጸሎታቸው በእግዚአብሔር ፊት ተሰምቶአል፡፡

ራእ. 8፡3-5 በመጽሐፉ ስለቀረቡት መለከቶች ጠቃሚ መረጃ ይሰጠናል፡

ሀ. ሰባቱ መለከቶች ሕዝቦቹ በዐመጻኞች ለደረሰባቸው ጭቆና ለእግዚአብሔር ላቀረቡት ጸሎት የአምላካዊው ፍርድ ምላሽ ናቸው፡፡

ለ. መለከቶቹ ከየሱስ እንደ በግ መሞት አንስተው እስከ ረጅሙ የዳግም ምጽአቱ ትዕይንት ይዘልቃሉ፡፡ (ራእ. 11፡15-18)፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 8፡5፣ ሕዝ. 10፡2፡፡ በእግዚአብሔር ሕዝብ ጠላቶች ላይ የተወረወረው እሳት ምንጩ ምንድን ነው? በሕዝቅኤል ራእይ ክህደት የፈጸመችው የሩሳሌም ላይ የተወረወረው እሳት በራእ. 19 ስለቀረበው መለከት ተፈጥሮ ምን ያብራራል?

መልአኩ ጥናውን ይዞ የመሠዊያውን እሳት ሞላበትና ወደ ምድር ወረወረው፡፡ እዚህ ላይ እሳቱ የመጣው የቅዱሳን ጸሎት ከሚቀርብበት መሰዊያ መሆኑን ልብ ይሏል። የሰባቱ መለከት ፍርዶች የእግዚአብሔርን ሕዝቦች ጸሎት በመመለስ በምድር ነዋሪዎች ላይ ማረፉን ያሳያል፡፡ የእግዚአብሔር ሕዝቦች አልተዘነጉም፡፡ እነሆ እርሱ በራሱ ጊዜ ስለ እነርሱ ጣልቃ ሊገባ ነው፡፡

**ሰኞ** የካቲት 4

## የመለከቶቹ ፍቺ

የራእይ መጽሐፍ እግዚአብሔር ስለ ሕዝቡ ጣልቃ የሚገባበትን መንገድ ለመግለጽ የብሉይ ኪዳኖቹን ምሳሌያዊ መለከቶች ጥቅም ላይ ሲያውል ይታያል፡፡ መለከት ለየቀኑ የጥንቷ እስራኤል ህይወት በእጅጉ አስፈላጊ ነበር (ዘኍ. 10፡8-10፣ 2ዜና 13፡14-15)፡፡ የመለከቶች ድምፅ በቤተ አምልኮ ስግደት መኖሩን ያስታውሳል፡፡ እንዲሁም በጦርነት፣ በመኸርና በልዩ ልዩ ክብረ በዓሎች የመለከት ድምፅ ይሰማ ነበር፡፡

መለከት የመንፋቱ ተግባር ጸሎት ከማድረስ ጋር ጎን ለጎን ይከናወን ነበር፡፡ በቤተ መቅደስ ይካሄድ በነበረ የአምልኮ ጊዜ ወይም በክብረ በዐላት ወቅት የሚሰማ የመለከት ድምፅ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የገባውን ኪዳን “ያስታውስ” ነበር፡፡ እንዲሁም ሕዝቡ “ለጌታ ቀን” (ኢዮ. 2፡1) እንዲዘጋጅ ያስታውስ ነበር፡፡ በጦርነት ወቅት እግዚአብሔር ሕዝቡን እንዲታደግ በሚደረግ ጸሎት ይታጅብና መለከት ይነፋል፡፡ ይህ ጽንሰ ሃሳብ በራእይ ለቀረቡት መለከቶች መነሻ ታሪክ ነው፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 8፡13፣ 9፡4፣ 20፡፡ የሰባቱ መለከቶች ፍርድ ግባቸው ምንድን ነው?

---

---

በራእይ መጽሐፍ የቀረቡት መለከቶች መነፋት መነሾ--እግዚአብሔር ለሕዝቡ ጸሎት ምላሽ ለመስጠት በዘመናት ጣልቃ የገባባቸውን ሁናቴዎች ያመለክታሉ። የማኅተሞቹ ቀደምት ተግባር ከእግዚአብሔር ሕዝቦች ጋር የተቆራኘ ሲሆን መለከቶቹ ደግሞ በምድር ነዋሪዎች ላይ ፍርድ ያውጃሉ (ራእ. 8፡13)፡፡ በተመሳሳይ ሕዝቡ ሳይረፍድ በጊዜ ወደ ንስሐ እንዲመጣ ማስጠንቀቂያ ድምፆች ናቸው፡፡

ሰባቱ መለከቶች ከዮሐንስ ዘመን አንስቶ እስከ ምድር ታሪክ መደምደሚያ ያሉትን

ጊዜአቶች ይሸፍናሉ (ራእ. 11፡15-18)፡፡ መለከቶቹ የሚነፉት በሰማይ የማማለድ ሥራ እየተሠራና (ራእ. 8፡3-6) በምድር ወንጌል እየተሰበከ ባለበት ጊዜ ነው (ራእ. 8፡ 3-6)፡፡ የመለከቶቹ ፍርድ የሚነካው ከፍጥረት አንድ ሦስተኛውን ብቻ እንደመሆኑ ሁሉንም አይጠቀልልም፡፡ ሰባተኛው መለከት የፍጥረት ሁሉ ባለ መብት የሆነው አምላክ የሚገዛበት ጊዜ መድረሱን ያመለክታል፡፡ ሰባቱ መለከቶች--ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ከሚሸፍኑት የጊዜ ሠሌዳ ጋር ገጣሚነት ሊኖራቸው ይችላል፡

(ሀ) የመጀመሪያዎቹ ሁለት መለከቶች ክርስቶስን በሰቀሉትና የቀደመችውን ቤተ ክርስቲያን ባሳደደዱ--በዐመጸኞቹ ኢየሩሳሌምና የሮም ግዛት ላይ ፍርድ ያውጃሉ፡፡

(ለ) ሦስተኛውና አራተኛው መለከት መካከለኛው በመባል በሚታወቀው ዘመን እና በድኅረ ተሐድሶ ተከስተው ለነበሩ ክህደቶች ሰማያዊውን ምላሽ ያስቃኛሉ፡፡

(ሐ) አምስተኛውና ስድስተኛው መለከት አምላካዊ ጥበብ የጎደለው ፍልስፍና በስፋት ከተንሰራፋበት (18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን) ትርምስ በኋላ ዓለምን ወደ አርማጌዶን ጦርነት የሚዘፍቃት መጠነ ሰፊ ዲያብሎሳዊ አካሄድ ጋር ቁርኝት ያለው--ከመንፈሳዊነት ያፈነገጠ ዓለም የሚገኝበትን ሁኔታ ይገልጻል፡፡

**የምድር ታሪክ በደም የጨቀየና በብርቱ ሰቆቃ የተሞላ መሆኑ አያጠያይቅም፡፡ ይህ አሳዛኝ ተጨባጭ ሁኔታ በየሱስ እንዴት ያለ ግሩም ተስፋ እንደ ተሰጠን ማስተዋል እንድንችል እንዴት ይረዳናል?**

## ማክሰኞ የካቲት 5

# የተከፈተውን መጽሐፍ የያዘው መልአክ

ስድስተኛው መለከት ወደ ምድር የመጨረሻ ጊዜ ያመጣናል፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ምን እንዲያደርጉ ተጠርተዋል? የሰባተኛው መለከት ድምፅ ከመሰማቱ አስቀድሞ በመጨረሻው ጊዜ የእግዚአብሔር ሕዝቦች የሚኖራቸውን ኃላፊነትና ተሞክሮ የሚገልጽ የእረፍት ጊዜ መግባቱ ተመልክቶአል፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 10፡1-4፡፡ እየሆነ ያለው ነገር ምን ይመስላል?

የክርስቶስ ዓይነት ገጽታ የሚስተዋልበት ይህ መልአክ የተከፈተ መጽሐፍ ይዞአል። አንደኛው እግሩ በየብስ ሌላኛው ደግሞ በባህር ላይ ማረፉ በዩኒቨርስ ላይ ያለውን ገዢነትና የሚያውጀው መልእክት ዓለም አቀፍ አንደምታ እንዳለው ያሳያል፡፡ የአንበሳ ግሳት የእግዚአብሔር ድምፅ ተምሳሌት እንደመሆኑ፤ እርሱም እንደሚያገሣ አንበሳ ድምፁን ከፍ አድርጎ ይጮኻል (ሆሴ 11፡10)፡፡

ነጎድጓዶቹ ባስተጋቡት ድምፅ ያሉትን ዮሐንስ እንዲጽፍ አልተፈቀደለትም። የወደፊቱን አስመልክቶ እግዚአብሔር በዮሐንስ በኩል ያልገለጻቸው ነገሮች መኖራቸው እሙን ነው፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 10፡5-7፡፡ ይህን ጥቅስ ከዳን. 12፡6-7 ጋር ያስተያዩ፡፡ መልእክቶቹ በጋራ የያዙዋቸው ሀሳቦች ምንድን ናቸው?

---

---

---

መልአኩ “ከእንግዲህ መዘግየት አይኖርም” (ራእ. 10፡6) ብሎ ሲናገር chromos የተሰኘው የግሪክ ቃል አንድ የተወሰነ የጊዜ ሠሌዳ መጥቀሱን ያሳያል፡፡ ይህም መልአኩ በዳን. 12፡6-7 የቅዱሳን ስደት--ለዘመን፣ ለዘመናት፣ ለዘመንም እኩሌታ ወይም ለ1,260 ዓመታት (538-1798 ዓ.ም.) ድረስ ይቆያል በማለት ወደ ተናገረው ይመልሰናል፡፡ ከዚህ ትንቢታዊ ጊዜ በኋላ በአንዱ ቀን መጨረሻው እውን ይሆናል፡፡

በተለይ ከዳን. 8፡14 የ2,300 ትንቢታዊ ቀናት (ከክርስቶስ ልደት በፊት 457 እስከ 1844 ዓ.ም.) በኋላ ምንም ዓይነት ትንቢታዊ የጊዜ ሠሌዳ እንደማይኖር ኤለን ኋይት ትገልጻለች፡፡ “በዚህ ወቅት መልአኩ የሚያውጀው የተከበረና የረጋ ብርቱ ቃል ከጌታችን ምጽአት አስቀድሞ ገቢራዊ መሆን ይኖርበታል፡፡ ይኸውም ሕዝቡ በዚህ ጊዜ ይመጣል የሚል ቁርጥ ያለ መልእክት የለውም ማለት ነው፡፡ ከ1842 እስከ 1844 በኋላ በዚህ ወቅት የሚል ቁርጥ ያለ ትንቢታዊ ጊዜ የሚያርፍበት ዕለት ሊኖር አይችልም፡፡ ረጅሙ ስሌት ያረፈው በ1844 መከር ላይ ነበር፡፡”—Ellen G. White Comments, The SDA Bible Commentary, vol. 7, p. 971.

ክርስቶስ በዚህ ጊዜ ይመጣል ብሎ ጊዜ መወሰን ፍጹም ሊወገድ እንደሚገባ ከላይ የቀረበው ሃሳብ ምን ይነግረናል?

ረቡዕ የካቲት 6

# ጥቅልሉን መጽሐፍ መብላት

ጥቅሱን ያንብቡ፡ ራእ.10፡8-11፡፡ መብላት--ከእግዚአብሔር የመጣውን መልእክት መቀበል፤ ከዚያ ለሕዝቡ ማወጅ በሚል አንደምታ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅም ላይ ውሎአል (ሕዝ. 2:8–3:11፣ ኤር.15:16)፡፡ መጽሐፍ ቅዱሳዊውን መልእክት ስንቀበል መልካም የምስራች ቢሆንልንም፤ ነገር ግን ለሌሎች ስንመሰክረው አልፎ አልፎ መልእክቱን ለመቀበል ዳተኞች በሆኑ ብሎም በሚቃወሙ ዘንድ ምሬት ይፈጥራል፡፡

ዮሐንስ ጥቅልሉን መጽሐፍ ሲበላ የገጠመው መራርና ጣፋጭ ተሞክሮ ከዳንኤል የመጨረሻው ዘመን ያልተከፈቱ ትንቢቶች ጋር ዝምድና አለው፡፡ እዚህ ላይ ዮሐንስ የሚወክለው በዳንኤል ትንቢት 1,260 ቀናት መጨረሻ ወንጌልን እንድታውጅ ተልዕኮ የተቀበለችውን ቤተ ክርስቲያን ነው፡፡

ዮሐንስ የተመለከተው ራእይ በ2,300 ዓመቱ ትንቢታዊ ጊዜ መደምደሚያ ወደ ሌላ ጣፋጭና መራር ተሞክሮ እንደሚያመራ ዐውደ ሃሳቡ ያመላክተናል፡፡ የዳንኤልን ትንቢቶች መሰረት አድርገው ስሌት የሠሩት ሚለርና ተከታዮቹ፤ ክርስቶስ በ1844 ይመጣል ብለው ድምዳሜ ላይ በመድረስ ያካፈሉት መልእክት በእርግጥ ጣፋጭ ሆኖላቸው ነበር፡፡ ሆኖም ስሌታቸው እንደ ታሰበው ሳይሆን ሲቀር፤ ዐውጀውት በነበረው መልእክት ብርቱ የምሬት ስሜት ተፈጠረባቸው፡፡

ዮሐንስ "እንደገና ትንቢት ልትናገር ይገባሃል" በሚል ለዓለም የተሰጠው ተልዕኮ፤ ዳግም ምጽአቱን ከዳንኤል ትንቢቶች ጋር ካለው ትስስር አኳያ እንዲያውጁ የተወከሉ ሰንበት ጠባቂ የምጽአቱን ተጠባባቂዎች ያመለክታል፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 11፡1-2፡፡ ዮሐንስ ምን አድርግ ተብሎ ነበር የታዘዘው?

---

---

እነዚህ ጥቅሶች በራእ. ምዕ. 10 ቀርቦ የነበረው ትዕይንት ቀጣይ ክፍል ናቸው፡፡ ዮሐንስ ቤተ መቅደሱን፣ መሠዊያውንና የሚያመልኩትን ምዕመን እንዲለካ መታዘዙን እንመለከታለን፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ዘይቤያዊ አቀራረብ--የመለካት ጽንሰ ሃሳብ ፍርድን ያመለክታል (ማቴ. 7፡2)፡፡ በራእዩ የተለካው--የሱስ ስለ እኛ አገልግሎት የሚሰጥበት ሰማያዊው ቤተ መቅደስ ነበር፡፡ ለቤተ መቅደሱ፣ ለመሠዊያውና ለሚያመልኩት ምዕመን የቀረበው ማጣቀሻ የሥርየትን ቀን ያመላክታል (ዘሌ.

16፡16-19)፡፡ የሥርየት ቀን እግዚአብሔር የሕዝቡን ኃጢአት ለክቶ የሚዳኝበት ዕለት ነው፡፡ በመሆኑም ራእ. 11፡1 ከዳግም ምጽአቱ አስቀድሞ ስለሚኖረው ፍርድ ይጠቅሳል፡፡ ይህ ፍርድ በተለይ በቤተ መቅደስ ለአምልኮ የሚሰበሰቡትን ወገኖች ብቻ ይመለከታል፡፡

የሰማያዊው መቅደስ መልእክት፤ በመጨረሻው የወንጌል ዕወጃ የልብ ትርታ ላይ እንደሚያርፍ ራእ. 11፡1 ያሳየናል፡፡ አምላካዊው ባህሪ ነፃ እንደሚያወጣ በጽኑ ያሳስባል፡፡ በዚህም ወንጌል--ሰብዓዊው ፍጡር ሊድን የሚችልበት ብቸኛ መንገድ የሆነውን የክርስቶስ የሥርየት ተግባርና ጽድቅ፣ በስፋትና በሙላት ያስቃኘናል፡፡

***ደም--ምን ያህል የሚዳዊው የሥርየት ቀን ማዕከላዊ ክፍል እንደሆነ በአእምሮአችን እንደያዝን (ዘሌዋ. 16)፤ የፍርድን መልካም የምስራችነት እውነታ ሁሌም ጠብቀን መጓዝ የምንችለው እንዴት ነው?***

## ሐሙስ የካቲት 7

## ሁለቱ ምስክሮች

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 11:3–6፡፡ ሁለቱ ምስክሮች በንጉሣዊና ካኅናዊ ሚናቸው ዘሩባቤልን እና ኢያሱን እንዴት ያንጸባርቃሉ? ዘካ. 4፡2-3፣ 11-14

---

---

የሁለቱ ምስክሮች ጽንሰ ሃሳብ ምንጩ የአንድን ጉዳይ እውነትነት ለማጣራት ቢያንስ ሁለት ምስክሮች ያስፈለገበት የአይሁድ ሕግ አወቃቀር ነው (ዮሐ. 8፡17)፡፡ ሁለቱ ምስክሮች መጽሐፍ ቅዱስን የሚወክሉ ቢሆንም፤ ነገር ግን በተጨማሪ ለመጽሐፍ ቅዱስ ምስክር የሆኑትን የእግዚአብሔር ሕዝቦችንም ይወክላሉ፡፡ የእግዚአብሔር ሕዝቦች መጽሐፍ ቅዱስን ለዓለም እንዲያውጁ የተጠሩ በመሆናቸው፤ ሁለቱ ሊነጣጠሉ አይችሉም፡፡

ምስክሮቹ ለ1,260 (538 ዓ.ም.-1798) ትንቢታዊ ቀናት ማቅ ለብሰው ትንቢት እንደሚናገሩ ሆነው ቀርበዋል፡፡

ሁኔታው ዮሐንስ ትንቢት ልትናገር ይገባሃል ወደ ተባለበት ራእ. 10፡11 ይመልሰናል። ጥሪው የእግዚአብሔርን እውነት ወደምታውጀው ቤተ ክርስቲያን ያመራ መሆኑን ይህ ቁልጭ አድርጎ ያሳየናል፡፡ ማቅ የሚለበሰው በሐዘን ወቅት ነው (ዘፍ. 37፡34)። የእግዚአብሔር ሕዝቦች “እንደ ገና ትንቢት ሊናገሩ” ከመሆኑ አኳያ፤ በአስቸጋሪ ሁኔታ ማለፋቸው የግድ መሆኑ ይህ በማቅ የቀረበው ምሳሌ ያመላክታል፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 11፡7-13፡፡ በ1,260 ትንቢታዊ ቀናት መጨረሻ በሁለቱ ምስክሮች ላይ ምን እንደተከሰተ በራስዎ ቃላት በጽሁፍ ይግለጹ፡፡

ሁለቱን ምስክሮች የሚገድለው አውሬ መነሾው ጥልቁ ሲሆን ይኸውም የሰይጣን መኖሪያ ነው፡፡ ይህ ምስክሮችን ማጥፋትና መደምሰስ--በእግዚአብሔር ላይ ክህደት ፈጽሞ በመጽሐፍ ቅዱስን ላይ ጥቃት መሰንዘርና ኃይማኖትን ከምድረ ገጽ ማጥፋት--ከፈረንሳይ አብዮት ጋር ቁርኘት አለው፡፡ ይህ ጸረ ኃይማኖት የአገዛዝ ዘይቤ ወይም ሥርዓት የዘቀጠውን የሶዶም ሥነ ምግባር፣ በእብሪት የተሞላውን የግብፅ ክህደት እና የኢየሩሳሌምን ዐመጸኝነት በአንድ አጣምሮ የያዘ ነበር፡፡

ከፈረንሳይ አብዮት ትርምስ በኋላ የምስክሮቹ ዳግም ማንሰራራት መጽሐፍ ቅዱስን ያማከለ ታላቅ መንፈሳዊ መነቃቃት ፈጠረ፡፡ ይህም መጽሐፍ ቅዱስን ማሰራጨት ዓላማው አድርጎ የተነሳውን፤ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማኅበረሰብንና አያሌ የሚሽነሪ እንቅስቃሴዎች እንዲፈጠሩ መንስዔ ሆነ፡፡

መጨረሻው ከመምጣቱ አስቀድሞ ዓለም በታሪክ ታይቶ በማይታወቅ መልኩ ለመጽሐፍ ቅዱሳዊው መልእክት ምስክር ትሆናለች፡፡ ይህ ኃይል ከዲያብሎሳዊው እንቅስቃሴ በሚያገኘው ሥልጣን በሚያደርጋቸው ታምራቶች ዓለምን በመሳብና በማማለል ተቃዋሚዎችን በማነሳሳት ከእግዚአብሔር ታማኝ ምስክሮች ጋር ወደ መጨረሻው ውጊያ ያመራል፡፡ ስለዚህ ይህ የመጨረሻ እወጃ ጣፋጭና መራር ውጤት ይኖረዋል፡፡

## አርብ የካቲት 8

**ተጨማሪ ሃሳብ፡** ሰባተኛው መለከት (ራእ. 11፡15-18) ይህ ዓለም ወደ ፍጻሜ ለመድረሱ ምልክት ይሰጠናል፡፡ እግዚአብሔር ኃይሉንና ንጉሣዊ ገዢነቱን የሚገልጥበት እነሆ ጊዜው ደርሶአል፡፡ ይህች በሺዎች ለሚቆጠሩ ዓመታት በሰይጣን ቁጥጥር ሥር የኖረች ዐመጸኛ ምድር፤ በእግዚአብሔር ግዛትና አመራር ስር የምትሆንበት ቀን ተቃርቦአል፡፡ የሥልጣን ነጠቃ ለማድረግ ያሴረው ሰይጣን ክርስቶስ በመስቀል ላይ ከሞተና ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ ለዘላለም ከሰማይ ታገደ፡፡ እነሆ የክርስቶስ የምድር ሕጋዊ ገዢነትም ታወጀ (ራእ. 12፡10)፡፡ ሰይጣን ግን ጥቂት ዘመን ብቻ እንደቀረው በመገንዘብ (ራእ. 12፡12) ቁጭቱን ለመወጣት የሚችለውን ሁሉ ጥፋት ማድረሱን ገፍቶበታል፡፡ ሰባተኛው መለከት በአምላካዊ ዙፋን ላይ የተነሱ ኃይላት ጉዳይ እልባት

ማግኘቱንና በመጨረሻ ይህች ዓለም በትክክለኛው ባለቤት ስር መዋሏን ያውጃል፡፡

ሰባተኛው መለከት ከመጨረሻው ዘመን ክስተቶች ጋር ተጓዳኝነት ያላቸውን የመጽሐፉ ሁለተኛ አጋማሽ ዋና ዋና ሀሳቦች ላይ አጽንኦት ይሰጣል፡ (1) አሕዛብ ተቆጥተው ነበር፡ ራእ. 12-14 የሰይጣንን በቁጣ መሞላት ይገልጻል (ራእ. 12፡17)፡ ፡ ከሁለቱ አበሮቹ ማለትም ከባሕር የወጣው እና ከምድር የወጣው አውሬ ጋር በመሆን የምድር ነዋሪዎችን በእግዚአብሔር ሕዝቦች ላይ ለውጊያ ያዘጋጃል፡፡ (2) የእግዚአብሔር ቁጣ ፍጻሜ ያገኛል፡ እግዚአብሔር በዐመጻኞች ላይ ቁጣውን የሚገልጸው አምላካዊው ቁጣ በሚል በተገለጹት በመጨረሻዎቹ ሰባት መቅሰፍቶች ነው (ራእ. 15፡1)፡፡ (3) ሙታን የሚዳኙበት ጊዜ፡ በራእ. 20፡11-15 ተብራርቶአል፡ ፡ (4) የእግዚአብሔር አገልጋዮች የሚቀበሉት ሽልማት፡ በራእ. 21-22 ቀርቦአል፡፡ (5) ምድርን ያጠፉ ይጠፋሉ፡ በመጨረሻ ላይ ባቢሎን ይፈረድባታል ምክንያቱም ምድርን አጥፍታለችና--ራእ. 19፡2፡፡ በሰይጣንና መላእክቱ እንዲሁም በሁለቱ አበሮቹ ላይ የሚደርሰው ውድመት የታላቁ ተቃርኖ ታሪክ መደምደሚያ ይሆናል ራእ. 19፡11-20፡15፡፡

## የመወያያ ጥያቄዎች፡

1.አልፎ አልፎ ወንጌልን መስበክ መራራ የሚሆንበት ወቅት አለ (ራእ. 10፡10)። ከአንደበታችን የሚወጡት ቃላቶችም ሆኑ እኛ ራሳችን ሊፌዝብንና ተቃውሞ ሊገጥመን ይችላል፡፡ አንዳንዴ አምላካዊውን ቃል መስበክ ብርቱ ተቃውሞ ሊቀሰቅስ ይችላል፡፡ እንዲህ ያሉ ፈተናዎች ከገጠሟቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ገጸ ባህሪያት እነማንን ያስታውሳሉ? ከእነርሱ ተሞክሮዎች ምን እንማራለን?

2.“ክርስቶስ በዚህ ዕለት ይመጣል በሚል እሳቤ ጊዜ መወሰን እንደሌለብን ተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶኛል፡፡ ከዚህ በኋላ የምጽአቱን ጊዜና ወቅት መሰረት ያደረገ ምንም ዓይነት መልእክት ለእግዚአብሔር ሕዝቦች አይሰጥም፡፡ መንፈስ ቅዱስ በሙላት የሚፈስበትን ጊዜም ሆነ ክርስቶስ ዳግም የሚገለጥበትን ትክክለኛ ጊዜ እንድናውቅ አልተደረግንም፡፡”—Ellen G. White, Selected Messages, book 1, p. 188. ከ1844 በኋላ--ስለ መጨረሻዎቹ ቀናት የሚያሳዩ የትንቢት ስሌቶችን ነቅሶ ማውጣት ምን ዓይነት ችግር ሊያስከትል ይችላል ብለው ያምናሉ? አንድ ሰው የትንቢት ስሌቶቹ ሊያመጡ ከሚችሉት ያልተጠበቀ መሰናክል መጠበቅ የሚችለው እንዴት ነው?

8ኛ ትምህርት

ከየካቲት 9–15

# ሰይጣን - - የተሸነፈ ጠላት

ሰንበት ከሰዓት

ለዚህ ሣምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ራእ. 12፣ ዘፍ. 3:15፣ ኢሳ. 14:12–15፣ ዳን. 7:23–25፣ 2ተሰ. 2:8–12፣ ራእ. 13:13-14፣ 19:20፡፡

**መታሰቢያ ጥቅስ :-"'እነርሱም በበጉ ደም፣ በምስክርነታቸውም ቃል፣ ድል ነሱት፤ እስከ ሞት ድረስ እንኳ ለነፍሳቸው አልሳሱም' " (ራእ. 12፡11)፡፡**

የመጽሐፉ የመጨረሻው ዘመን መልእክት ክፍል ራእ. ምዕ. 12 ላይ ይጀምራል። የመጀመሪያው አጋማሽ፤ በጥላቻ በተሞላው ዓለም ቤተ ክርስቲያን በዘመናት የገጠማትን መንፈሳዊ ትግል ሲገልጽ፤ ሁለተኛው አጋማሽ ደግሞ ወደ ክርስቶስ ዳግም ምጽአትና ዘላለማዊ መንግሥት የሚያመሩ ክስተቶች ዙሪያ ትኩረት ያደርጋል፡፡

የምዕ 12 ዓላማ ከዓለም ታሪክ የመጨረሻ ቀውስ በስተጀርባ ያለውን ብርቱ ገጽታ ቁልጭ አድርጎ ማሳየት ነው፡፡ የመጨረሻው ዘመን ክስተቶች በክርስቶስና በሰይጣን መካከል እየተካሄደ ያለ ሥነ ፈለካዊ ተቃርኖ አካል መሆኑን ይነግረናል፡፡

ሰይጣን የእግዚአብሔር እና የሕዝቦቹ ዋንኛ ጠላት ተደርጎ በራእይ መጽሐፍ መቅረቡን እናያለን፡፡ ይህ መልአክ ምናባዊ ሳይሆን በእርግጥ ያለ እና በዩኒቨርስ ለሚፈጠር ማንኛውም ክፉ ተግባርም ሆነ ዐመጻ ስውር አንቀሳቃሽ ሞተር ነው፡፡ ሰይጣን ከዚህ በኋላ በእግዚአብሔር ላይ ስኬት ለማግኘት የሚያስችለው የመጨረሻ ዕድል ውጊያውን ማሸነፍ ብቻ እንደሆነ ያውቃል፡፡ ስለዚህ ሙሉ ትኩረቱ ለዚያ ክስተት መዘጋጀቱ ላይ ነው፡፡

በምዕ. 12 የቀረበው ራእይ ፋይዳ ሰይጣን በእርግጥ የተሸነፈ ጠላት መሆኑን በበቂ ማረጋገጫ ለእግዚአብሔር ሕዝቦች ማበርከት ነው፡፡ ክርስቶስ በምድራዊ አገልግሎቱ፣ በመስቀል ላይ እንዲሁም በትንሳዔው ሰይጣንን እንዳሸነፈ፤ በመጨረሻም እንዲሁ ድል ይነሳዋል፡፡ ስለዚህ በመጨረሻው ዘመን ለሚኖሩ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ብቸኛው ተስፋ የሚገኘው በክርስቶስ ነው፡፡

እሑድ
የካቲት 10

# ሴቲቱ እና ዘንዶው

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 12፡1-4፡፡ ዮሐንስ ሁለት ታላላቅና አስደናቂ ተምሳሌታዊ ምልክቶችን በራእይ የተመለከተ ሲሆን አንደኛው ምጥ የያዛት ነፍሰጡር ሴት ነበረች። ለመሆኑ ይህች ሴት ማን ናት? ጥቅሶቹ ምን ያስተምሩናል?

---

---

በመጽሐፍ ቅዱስ ሴት የእግዚአብሔር ሕዝቦች ተምሳሌት ናት (2ቆሮ. 11፡2)፡፡ ንጽህት ሴት ታማኝ የሆኑትን አማኞች ስትወክል በተቃራኒው ያለችው አመንዝራዋ ደግሞ ክህደት የፈጸሙትን ትወክላለች፡፡ በራእ. 12 የቀረበችው ሴት መሲህ ወደ ዓለም የወጣባትና (ራእ. 12፡1-5) ከመስቀሉ አስቀድሞ የነበረችው የብሉይ ኪዳኗ እስራኤል ተምሳሌት ናት፡፡ ከቁ. 13-17 ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን ትወክላለች፡፡

ይህች ሴት ፀሐይን ለብሳና በጨረቃ ላይ በጽናት ቆማ ተስላለች፡፡ ፀሐይ የክርስቶስን ክብር (ማቴ. 17፡2፣ ራእ. 1፡16) እና ሕዝቦቹን ትወክላለች (ማቴ. 13፡43)፡፡ ጨረቃ እንደ ፀሐይ ነጸብራቅነቷ ወደ ብሉይ ኪዳን የተስፋ ቃል ትንቢቶች ታመላክታለች፡፡

ዮሐንስ በራእይ ያየው ቀጣዩ ተምሳሌታዊ ምልክት ቀይ ዘንዶ ነበር፡፡ ዘንዶው የቀደመው እባብ (ራእ. 12፡9) ይኸውም ዲያብሎስና እና ሰይጣን ነው፡፡ ጅራቱ የከዋክብትን አንድ ሦስተኛ ከሰማይ ስቦ ወደ ምድር እንደ ጣላቸው ጥቅሱ ይናገራል፡፡ ጅራት የማታለልና የማጭበርበር ዓይነተኛ ተምሳሌት ነው (ኢሳ. 9፡14-15፣ ራእ. 9፡10)፡፡ በሰማይ ከነበረው የከበረ ማዕረግ ቁልቁል የተምዘገዘገው ሰይጣን (ኢሳ. 14፡12-15) ከፍተኛ ቁጥር የነበራቸውን የሰማይ መላእክት ለክፉ ዓላማው እያባበለ አታልሎ እርኩስ መናፍስት አደረጋቸው (2ጴጥ. 2፡4፣ ይሁዳ 6)፡፡ እነዚህ እርኩሳን መናፍስት በመልካምና በክፉ መካከል ብርቱ ተቃርኖ በነገሠበት የዩኒቨርስ ዘመን እግዚአብሔርን እና የማዳን ሥራውን የሚቃወሙ ተባባሪ ኃይሎች ሆነው በመሥራት ላይ ይገኛሉ፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 12፡1-5፡፡ ዘንዶው "የጥንቱ እባብ" (ራእ. 12፡9) በሚል ተጠቅሶአል፡፡ በዘፍ. 3፡15 እና የሴቲቱን ዘር ለማጥፋት አጥብቆ በሚተጋው በጥንቱ እባብ ገጽታ መካከል ምን ዓይነት ግንኙነት አለ?

---

---

ሰይጣን ገና ከመጀመሪያው የሚወለደውን ልጅ ይኸውም መሲሁን ለማጥፋት እየተጠባበቀ ነበር፡፡ ረጅሙ የትዕይንቱ አካል በውልብታ ቀርቦአል፡ በመጨረሻ መሲህ ተወለደ፣ ዘንዶው ሊያጠፋው ሳይችል ቀረ፤ ልጁም "ወደ እግዚአብሔርና ወደ ዙፋኑ ተነጠቀ" (ራእ. 12፡5)፡፡

***በራእ. 12፡11 መሰረት-የእግዚአብሔር ሕዝቦች በሕይወታቸው ሰይጣንን ድል መንሳት የቻሉት እንዴት ነበር? የሱስ በሰይጣን ላይ ያገኘው ድል እርስዎ ከኃጢአት ጋር ለሚያደርጉት መንፈሳዊ ግብግብ መጽናናት ሊሆንዎ የሚገባው እንዴት ነው?***

**ሰኞ** **የካቲት 11**

# የሰይጣን ለዘላለም ከሰማይ መባረር

በሰማይ ተካሂዶ ስለነበረው ጦርነት የሚናገሩትን እነዚህን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ራእ. 12፡7-9፡፡ ለመሆኑ ሰይጣንን ከሰማይ ያስባረረው የዚያ ጦርነት ተፈጥሮ ምን ነበር?

ሰይጣን በእግዚአብሔር መንግሥት ላይ ዐመጻ ባደረገ በታላቁ ተቃርኖ መጀመሪያ ከሰማይ ተባረረ፡፡ ሰይጣን የእግዚአብሔርን ዙፋን ገልብጦ "ራሴንም እንደ ልዑል አደርጋለሁ" (ኢሳ. 14፡12-15) የሚል ከፉ ምኞት ተጸናውቶት ነበር፡፡ በእግዚአብሔር ላይ ግልጽ ዐመፃ ለማድረግ ቢሞክርም ሽንፈት ገጥሞት የኋላ ኋላ ወደ ምድር ተጣለ፡ ፡ ሰይጣን የመጀመሪያዎቹን ሰብዓዊ ጥንዶች አስቶ የዚህን ዓለም ገዢነት ሥልጣን ያለ አግባብ ከእጁ አስገባ (ሉቃ. 4፡6)፡፡ በመሆኑም በዚህ ዓለም ገዢነቱ (ዮሐ. 12፡31) የምድር ተወካይ ሆኖ በሰማይ ጉባዔ ላይ መገኘት ቻለ (ኢዮ. 1፡6-12)፡፡ ሆኖም ሰይጣን ከሰማይ ከተባረረ አንስቶ እርሱና የወደቁት መላእክቶቹ የመጨረሻ ቅጣታቸውን እስኪቀበሉ የዚህ ምድር ግዞተኞች ተደረጉ (2ጴጥ. 2፡4፣ ይሁዳ 6)፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ--እነሆ የሱስ ጠፍቶ የነበረውን ሰብዓዊ ዘር በሞቱ ዋጀ። የሰይጣንም እውነተኛ ጸባይ በመላው ዩኒቨርስ ፊት ይፋ ሆነ፡፡ "ሰይጣን ማሳቻ ጭምብሉ ተገልጦ እውነተኛ ማንነቱ መውጣቱን ተመለከተ፡፡ የአገዛዝ ባህሪው ባልወደቁት መላእክትና በዩኒቨርስ ፊት ፍንትው ብሎ ታየ፡፡ ሰይጣን ያለ አንዳች መሸፋፈን ገዳይነቱን ገልጦ አሳይቶ ነበር፡፡ የእግዚአብሔርን ልጅ ደም በማፍሰስ ራሱን ከሰማያዊ አካላት አዘኔታና ርኅራኄ ውጪ አደረገ፡፡ ከዚህ በኋላ ለሥራው ገደብ እንዲበጅ ተደረገ፡፡"—Ellen G. White, The Desire of Ages, p. 761.

አሁን መላው ሰማያዊ አካላት በተካተቱበት በዩኒቨርስ ፊት የምድር ገዢነት ሥልጣን ወደ የሱስ ተዛወረና የእርሱ ሕጋዊ የምድር ገዢነት ታወጀ (ኤፌ. 1፡20-22፣ 1ጴጥ. 3፡22)፡፡

ሰይጣንና አጋሮቹ ተጠራርገው ከሰማይ የተባረሩት በዚህ ወቅት ነበር፡፡ የሱስ ይህን ሁኔታ እንዲህ ሲል አስቀድሞ ተናግሮ ነበር፡ "'ይህ ዓለም የሚፈረድበት ጊዜ አሁን ነው፤ የዚህም ዓለም ገዥ አሁን ወደ ውጭ ይጣላል' " (ዮሐ. 12:31)፡፡

ይህ ፍርድ በሰይጣን ላይ ከተሰጠ በኋላ " 'የአምላካችን ማዳን፣ ኀይልና መንግሥት፣ የእርሱ ያክርስቶስ ሥልጣንም መጥቶአል' " (ራእ. 12:10)፡፡ "ጥቂት ዘመን ብቻ እንደቀረው" (ራእ. 12፡12) የሚያውቀው ሰይጣን፤ ያ ቀን እስኪመጣ በዚህ ምድር የእግዚአብሔርን ሕዝቦች የሚጎዳበት ኃይል ውሱን ተደርጎበታል፡፡ ምንም እንኳ የቀረው ጊዜ "ጥቂት" ቢሆንም፤ በእያንዳንዱ ሽርፍራፊ ሰከንድ በሰዎች ላይ ሕመምና ሥቃይ በምድር ደግሞ ጥፋትና ውድመት እያደረሰ ይገኛል፡፡

***ራሳችንን ከሰይጣን ስለምንከላከልበት ብቸኛ መንገድ ራእ. 12፡11 ምን ያስተምረናል?***

## ማክሰኞ የካቲት 12

# የምድር ውጊያ

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 12፡13-14፡፡ ሰይጣን ከሰማይ ከታገደ በኋላ በ1,260 ትንቢታዊ ቀናት ቤተ ክርስቲያንን መዋጋቱን ገፍቶበት ነበር፡፡ በእነዚያ ጊዜያቶች ውስጥ እግዚአብሔር ከቤተ ክርስቲያን ጋር የነበረው አግባብ ምን ይመስላል?

"ክርስቶስ ሕይወቱን ሰጥቶ የሠራው ታላቅ ሥራ፤ በሰማይ የወንድሞች ከሳሽ የነበረው ሰይጣን ወደ ምድር እንዲጣል አስቻለ፡፡ ምንም እንኳ ሰይጣን በማያባራ ተቃውሞው ቢገፋበትም፤ ሰብዓዊውን ዘር የመታደጉ የደኅንነት እቅድ እነሆ እንደቀጠለ ይገኛል... ይህን ያላግባብ የወሰደውን ግዛት በስተ መጨረሻ በኃይል እንደሚነጠቅ የሚያውቀው ሰይጣን፤ እግዚአብሔር በአምሳሉ በፈጠረው ሰብዓዊ ዘር ላይ የተቻለውን ውድመት ለማድረስ ቆርጦ ተነስቶአል፡፡

ክርስቶስ ለሰብዓዊው ዘር ያሳየው ይቅር ባይነት፣ ፍቅርና አዘኔታ ስላበገነው፤ ሰብዓዊው ፍጡር ለዘላለም ጠፍቶ የሚቀርበትን እያንዳንዱን የረቀቀ ማታለያ ዘዴ ጥቅም ላይ እያዋለ ይገኛል፡፡ ሰይጣን በተስፋ አስቆራጭ አዙሪት መውደቁ፤ አውዳሚ አካሄዱን ከቀድሞ በበለጠ ጉልበት እንዲቀጥልበት አድርጎታል፡፡”—Ellen G. White, The Spirit of Prophecy, vol. 3, pp. 194, 195.

ክርስቶስ በምድር አጥብቆ የሚወዳትና የዐይኑ ማረፊያ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ላይ ሰይጣን በቁጣና በንዴት ጦዞ በተቃራኒ መሥራቱን መቀጠሉ አያከራክርም። ይህም ቢሆን ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስን ዳግም ምጽአት በምትጠባበቅበት በትንቢታዊው 1,260 ቀናት የበረሓ ቆይታዋ መለኮታዊውን ከለላ ታገኛለች፡፡

ሰይጣን ስደት የሚያደርስበት ዘመን--1,260 ቀናት እና “ለአንድ ዘመን፣ ለዘመናትና ለዘመን እኩሌታ” በሚል በራእ. 12--ለሁለት ጊዜ ተጠቅሶአል፡፡ ሁለቱም በመረጃ አስደግፈው የሚናገሩት በዳን. 7፡23-25 የተጠቀሰው ትንሹ ቀንድ ተግባራቱን የሚያከናውንባቸውን ዘመናት ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱሳዊው ተምሳሌታዊ ቀመር አንድ ትንቢታዊ ቀን ከአንድ ዓመት ጋር እኩል ነው፡፡ በታሪክ ከዚህ ትንቢታዊ አቀራረብ ጋር በእጅጉ ስምሙ ሆኖ የምናገኘው ከ538 ዓ.ም. እስከ 1798 ዓ.ም. ያለው ጊዜ ነው፡፡ የሮም ጳጳሳዊ ሥርዓት በምዕራቡ ዓለም ላይ ተንሰራፍቶ በጭቆና ይገዛ በነበረበት ወቅት የፈረንሳይ አብዮት ፍንዳታ መከሰት ብርቱ ጉዳት አደረሰበት። ጉዳቱ እስኪጠግለት፤ ለጊዜውም ቢሆን፤ የነበረውን ኃይል ሙሉ ለሙሉ አጣ፡፡

በበረሓ የነበረችው ሴት ትንቢት ድምዳሜ ላይ ሰይጣን በድጋሚ ኃይሉን አስተባብሮ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ለማጥፋት ጥቃት ይሰነዝራል፡፡ ዘንዶው ሴቲቱን ለማጥፋት እንደ ወንዝ ያለ ውሃ ወይም ጎርፍ ከአፉ ይተፋል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ተደጋግሞ እንደ ቀረበው ጎርፍ ስደትን ያመላክታል (ኢሳ. 59፡19)። በዚህ ወቅት ለሴቲቱ ሰላማዊ የሆነችው ምድር ውሃውን መጥጣ ትታደጋትና ምቹ ሁናቴ ትፈጥርላታለች፡፡

**እዚህ ላይ ስደቱ እንዴት ለ1,260 ቀናት እንደ ቆየ አሰብ ያድርጉ። በእኛ ግንዛቤ ረጅም ዘመን የሚያስቆጥር የሚመስል እንደ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ያለውን ክስተት ለማስተዋል ምን ያህል ውሱን እንደሆን ይህ ምን ሊነግረን ይችላል?**

ረቡዕ የካቲት 13

## በትሩፋኖች ላይ የተከፈተ ውጊያ

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 12፡17፡፡ ሰይጣን በመጨረሻ የሚዋጋው ከማን ጋር ነው?

---

---

አብላጫው የምድር ሕዝብ ክህደት በፈጸመበት ሁናቴ ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆነው የቆሙ ወገኖች--የተቀሩት ወይም ትሩፋን በሚል ተጠቅሰዋል (1ነገሥ. 19፡ 18፤ ራእ. 2፡24)፡፡ በምድር ፍጻሜ ላይ አብዛኛው ሕዝብ በሰይጣን በኩል የሚቆም ቢሆንም፤ ነገር ግን ለክርስቶስ ታማኝ ሆነው በመጽናት የሰይጣንን ቁጣ የሚጋፈጡ ሕዝቦችም ይኖራሉ፡፡

በራእ. 12፡17 የተገለጹት ትሩፋን ሁለቱ መለያ ባህሪያት ምንድን ናቸው? አንድ ሰው የእግዚአብሔር የመጨረሻው ዘመን ትሩፋን ነኝ ብሎ ለመቀበል የሚያስችለው አሳማኝ ሁናቴ ምንድን ነው?

---

---

የመጨረሻው ዘመን ትሩፋን የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ይጠብቃሉ፡፡ ለመጨረሻው ዘመን ውዝግብ ዋንኛ መንስዔ የዐሥርቱ ትእዛዛት የመጀመሪያዎቹ ሦስት ተራ ቁጥሮች እንደሚሆኑ ራእ. 13 ያሳየናል፡፡ የመጀመሪያዎቹ አራት ትእዛዞች ቁልፍ አካል አምልኮ ነው፡፡ የመጨረሻው አስጨናቂ ጊዜ ዐበይት ርዕሰ ጉዳይ ሊመለክ የሚገባው ማን ነው? የሚል ይሆናል፡፡ የዓለም ሕዝቦች የአውሬውን ምስል ለማምለክ ሲመርጡ የእግዚአብሔር ትሩፋት ግን ፈጣሪን ያመልካሉ (ራእ. 14፡7)፡፡ አራተኛው ትእዛዝ ከሌሎቹ በተለየ እግዚአብሔር ፈጣሪያችን መሆኑን ያመለክታል፡፡ ይህ ደግሞ በመጨረሻው ቀውስ ወቅት ዋንኛና አስፈላጊ ሚና ይጫወታል ብለን የማመናችን አንዱ መንስዔ ነው፡፡

የመጨረሻው ጊዜ ትሩፋን ሁለተኛ ባህሪ "የኢየሱስን ምስክር የያዙ" መሆናቸው (ራእ. 19፡10) ሲሆን፤ ይህም በዚያው ቁጥር ላይ "የትንቢት መንፈስ" በሚል ሀረግ ተገልጾአል፡፡ "የትንቢት መንፈስ" የተሰኘው አገላለጽ ዮሐንስ በኖረበት ዘመን--የትንቢት ስጦታ የሚል አንደምታ አለው፡፡ ይህ ሀረግ የሱስ በዮሐንስ በኩል እንዳደረገው (ራእ. 2) በተመሳሳይ በትንቢት ስጦታ አማካይነትም የራሱን ምስክርነት

እንደሚሰጥ ይጠቅሳል፡፡ ሰይጣን ሊያስታቸውና ሊያጠፋቸው ማንኛውንም ጥረት በሚያደርግበት በእነዚያ አስቸጋሪ የመጨረሻ ጊዜያቶች የእግዚአብሔር ሕዝቦች የሚመሩበት የትንቢት ስጦታ በመካከላቸው እንደሚገለጥ የራእይ መጽሐፍ ያሳየናል፡፡ እኛ እንደ የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ተጠባባቂነታችን በኤለን ጂ. ኋይት አገልግሎትና ጽሑፎች አማካይነት ስጦታው እንደ ተሰጠን እናምናለን፡፡

**በ"ትንቢት መንፈስ" በኩል ስለ ተሰጡን ጥልቅ ማስተዋልና መገለጦች ምን ይላሉ? ስጦታው በየግላችን እንዲሁም እንደ ቤተ ክርስቲያን ምን ዓይነት የውዴታ ግዴታ አስቀምጦብናል?**

## ሐሙስ የካቲት 14

# የሰይጣን የመጨረሻ ስልት

ሰይጣን የውግያ የስልቱን ለውጥ የዓለምን ሕዝቦች ከመዳፉ ለማስገባት በሚያደርገው እንቅስቃሴ ታማኞቹን የክርስቶስ ተከታዮች ሳይቀር የማሳት ሙከራ እንደሚያደርግ ራእ. 12፡17 ያመለክታል፡፡ ሰይጣን ማስገደድንና ማሳደድን ተቀዳሚ ስልቱ አድርጎ አምላካዊውን የደኅንነት ሥራ ለመግታት መሞከሩን የዘመናት የክርስትና ታሪኮች በዋቢነት ይነግሩናል፡፡ ይህ ስልት የፈለገውን ስኬት እንዳላስገኘለት ታሪክ ያሳየናል፡ ፡ ሆኖም በመጨረሻው ዘመን ትሩፋን ላይ የመጨረሻውን ጥቃት ለመሰንዘር በሚያደርገው ዝግጅት በማስገደድ ስልቱ ላይ መጠነ ሰፊ ማታለያ ዘዴ ያክልበታል፡፡

የሚያስት በሚል ጥቅም ላይ የዋለው ቃል የታሪክን ዐውድ በሚያስቃኘን ክፍል (ራእ. 4-11) አለመጠቀሱ አጽንኦት ሊሰጠው ይገባል፡፡ ሆኖም ሰይጣን ለመጨረሻው ውጊያ በሚያደርገው ዝግጅት በንቃት የተሞሉ እንቅስቃሴዎቹን ለመግለጽ ቃሉ በቋሚነት ጥቅም ላይ መዋሉን እንመለከታለን (ራእ. 12-20)፡፡ የሰይጣንን የመጨረሻውን ዘመን እንቅስቃሴ ገላጭ የሆነው የሚያስት በሚል የቀረበው ቃል በራእ. 12፡9 ይጀምርና ራእ. 20፡7-10 ይደመደማል፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ 2ተሰ. 2፡8-12፣ ራእ. 13፡13-14፣ 19፡20፡፡ የመጨረሻው ዘመን ማሳቻ ተፈጥሮ ምን ይመስላል?

ሰይጣን በዓለም ያሉ የእግዚአብሔርን ታማኞችን ለማሸነፍ በሚያደርገው ሙከራ መጠነ ሰፊ እውነት መሳይ ሽንገላዎችን እንደሚለቅ ራእ. 13-20 ያሳየናል፡፡ በራእ. 13 ዘንዶውና ሁለቱ ተባባሪ ኃይላት ማለትም ከባሕር የወጣው አውሬ (ራእ. 13፡1-10) እና ከምድር የወጣው አውሬ (ራእ. 13፡11-18) የሦስትዮሽ ግንኙነት ይመሰርታሉ፡፡ የሰይጣን የሦስትዮሽ ቅንጅታዊ አመራር ከአምላካዊው ሥላሴ በተቃራኒ የተዋቀረ ነው (ራእ. 1፡4-6)፡፡ እግዚአብሔር በዚህ ምድር የሚያደርገውን እንቅስቃሴ በመቃወምና ሕዝቦችን አስቶ በመጨረሻው ቀውስ ወቅት ፊታቸውን ከእግዚአብሔር እንዲመልሱና ከሰይጣን ጋር እንዲቆሙ የማድረግ ሥራ የሚሠሩት እነዚህ በሦስት አካል የተዋቀሩ ሰይጣናዊ ኃይላት፤ በተቀረው የመጽሐፉ ክፍል እንዳይነጣጠሉ ሆነው ቀርበዋል (ራእ. 16፡13-14፣ 19፡20፣ 20፡10)፡፡ በመጨረሻው ዘመን ገቢራዊ የሚሆነው የማሳቻ ዘዴ እጅግ ታላቅ ከመሆኑ የተነሳ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሕዝብ እንደሚማልል የራእይ መጽሐፍ ይነግረናል፡፡

በመጨረሻው ዘመን አብልጦ የሚሠራውን አሳች ተፈጥሮ የያዘውን የሰይጣን እንቅስቃሴ ለይቶ ለመገንዘብ ብሎም ለመቋቋም ጥበብ ያለው አእምሮ እንዲሁም መንፈሳዊ ዐይኖች ሊኖሩ የግድ እንደሆን የራእይ መጽሐፍ ከአንዴም ሁለቴ ጥሪ አቅርቦአል (ራእ. 13፡18፣ 17፡9)፡፡ **በዚህ ስፍራ የቀረበው ጥበብ ምን ዓይነት ነው? ይህን ጥበብ እንዴት ማግኘት እንደምንችል ያዕ. 1፡5 ምን ይለናል?**

## አርብ የካቲት 15

ተጨማሪ ሃሳብ፡ Read Ellen G. White, “Snares of Satan,” pp. 518–530, in The Great Controversy.

የመጨረሻው ዘመን ክስተቶች በክርስቶስና በሰይጣን ኃይላት መካከል የሚደረገው ታላቁ ተቃርኖ አካል መሆናቸውን ለእግዚአብሔር ሕዝቦች መንገር--ከሁሉ የቀደመው የራእ. 12 ዓላማ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ዛሬ እየተጋፈጡ ስለሚገኙት አስቸጋሪ ሁናቴ የሚናገረው አምላካዊ ቃል--በቅርቡ ደግሞ በላቀ ተሞክሮ ያለፈና በቁጣ የነደደ ጠላት አሰፍስፎ እንደሚጠብቃቸው ያስጠነቀቅቃል፡፡ ጳውሎስ በመጨረሻው ዘመን ስለሚደረጉ የሰይጣን እንቅስቃሴዎች እንዲህ ይላል፡ “ይህም በሐሰተኛ ታምራት በምልክቶችና በድንቅ ነገሮች ሁሉ ይሆናል፤ እንዲሁም ይድኑ ዘንድ እውነትን ባለ መውደድ የሚጠፉትን ሰዎች በሚያታልል በተለያየ የክፋት ሥራ ይመጣል” (2ተሰ. 2፡9-10)፡፡

የራእይ መጽሐፍ የወደፊቱን ጉዳይ በዋዛ እንዳንመለከትና በእግዚአብሔር ላይ ለመታመን ቅድሚያ እንድንሰጥ አጥብቆ ያስጠነቅቀናል፡፡ በሌላ በኩል ምንም እንኳ ሰይጣን ብርቱና በከፍተኛ ተሞክሮ ያለፈ ጠላት ቢሆንም ክርስቶስን ለመቋቋም የሚያስችል አቅም እንደሌለው የራእይ መጽሐፍ ያረጋግጥልናል (ራእ. 12፡8)፡፡ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ተስፋ የተመሰረተው ሰይጣንንና ዲያብሎሳዊ ኃይላትን ድል በነሳው በክርስቶስ ላይ ነው፡፡ ጌታ ሁል ጊዜ ከታማኝ ተከታዮቹ ጋር እንደሚሆን ጽኑ የተስፋ ቃል ሰጥቶናል "'እኔም እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ' " (ማቴ. 28፡20)፡፡

## የመወያያ ጥያቄዎች፥

***1.እንደ ዳግም ምጽአቱ ተጠባባቂ ሕዝብ የመጨረሻዎቹን ትሩፋን ባህሪ እንደምናሟላ አድርገን ራሳችንን እንመለከታለን፡፡ እንዴት ያለ ልዩ መብትና ጥቅም--ብሎም ኃላፊነት ነው! (ሉቃ. 12፡48)፡፡ ይህን ልዩ መብትና ጥቅም ለግል መዳናችን እንደ ዋስትና ላለመውሰድ ጥንቃቄ ማድረግ ያለብን ለምንድን ነው?***

***2."ብዙውን ጊዜ ሰብሰብ ብለን ስለ ሰይጣን ኃይል ስናወራ እንስተዋላለን። ሰይጣን ኃይል ያለው ፍጡር መሆኑ እርግጥ ቢሆንም ነገር ግን ክፉውን ከሰማይ ስለ ወረወረው አዳኜን ኃያሉን አምላክ አመሰግናለሁ። ስለዚህ ጠላታችን ማውራታችን፣ መጸለያችንና ማሰባችን አስተሳሰባችን ላይ እየገዘፈ የሚሄድ ማንነት እያገኘ እንዲሄድ ያስችለዋል። ለመሆኑ ስለ የሱስ የማንጨዋወተው ለምንድን ነው? ስለ ኃያልነቱም ሆነ ስለ ፍቅሩ የማናሰላስለው ለምንድን ነው? የባላንጣችንን ኃይል አግዝፈን በመመልከታችን ሰይጣን በእጅጉ ደስተኛ ነው፡፡ በየሱስ እየተመሰጥን እርሱን አጥብቀን ስንይዝ ወደ አምላካዊው አምሳል እየተለወጥን እንመጣለን፡፡"***—Ellen G. White, Advent Review and Sabbath Herald, March 19, 1889. ***ለመሆኑ ክርስቲያኖች የሰይጣንን ኃይል የሚያገዝፉት እንዴት ነው? በሌላ በኩል ስለ ሰይጣን ኃይል ሳይሆን ነገር ግን ከነአካቴው መኖሩን መካድ ምን ዓይነት አደጋ አለው?***

# 9ኛ ትምህርት

ከየካቲት 16–22

# ሰይጣን እና ሁለቱ አበሮቹ

ሰንበት ከሰዓት

ለዚህ ሣምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ራእ. 13፣ ራእ. 17:8፣ ዳን. 7:24፣ 2ተሰ. 2:2–12፣ ራእ. 12:14–16፣ 1ነገሥ. 18:38፡፡

**መታሰቢያ ጥቅስ ፡-** "ዘንዶውም በሴቲቱ ላይ ተቆጣ፤ ከቀሩት ልጆቿም ጋር ሊዋጋ ሄደ፤ እነርሱ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁና የኢየሱስን ምስክር አጥብቀው የያዙ ናቸው" (ራእ. 12፡17)፡፡

ራእ. ምዕ. 12 በንዴት የጦዘው ሰይጣን የክርስቶስን ታማኝ ሕዝቦች ለመውጋት ዝግጅት እያደረገ እንደሆነ በመንገር ይደመደማል፡፡ ምዕ. 13 ደግሞ ሰይጣን ለመጨረሻው ውጊያ በሚያደርገው ዝግጅት በክፉ አውሬነት የተሳሉትን ሁለት አበሮቹን አጋዡ አድርጎ ያሰልፋል፡፡ ይህ በሦስት አካላት የተዋቀረ ቅድስና የጎደለው ሐሳዊ ሥላሴ (ራእ. 1፡4-6) እንዲህ ያለውን ኅብረት የፈጠረው ለሰብዓዊው ዘር ደኅንነት የማምጣት ኃይል ያለውን አምላካዊውን ኃይል ለመቃወምና ሰዎችን ለዓለም ታማኝ አድርጎ ለማሸነፍ ነው፡፡

በእስካሁኑ ጥናታችን ቀደም ባሉት ዘመናት ፍጻሜ ያገኙ ትንቢቶችን ተመልክተናል፡፡ በመቀጠል ሙሉ ለሙሉም ባይሆን ነገር ግን አብዛኛው ምልከታችን ትኩረት የሚያደርገው ወደፊት ፍጻሜ በሚያገኙ ትንቢቶች ላይ ይሆናል፡፡ በምድር ታሪክ መዝጊያ ወቅቶች ገቢራዊ የሚሆኑ ክስተቶችን እግዚአብሔር አስቀድሞ የሚያሳየን ጊዜው ሲደርስ ያልታሰቡ እንዳይሆኑብን በማሰብ ነው፡፡

ትንቢቶቹ በመጨረሻው ጊዜ እውን የሚሆኑትን ነገሮች ቢነግሩንም ነገር ግን መቼ እና በትክክል እንዴት ፍጻሜ እንደሚያገኙ የሚሉት ነገር የለም፡፡ ይህን ደግሞ ሁሌም ማስታወስ ከእኛ ይጠበቃል፡፡ ስለዚህ ከትንቢት ባሻገር የሚሰነዘሩ መላ ምቶችን ከመቀበል ብሎም ከማስተላለፍ መቆጠብ የግድ ይሆናል፡፡ የራእይ ትንቢቶች ተጨባጭ አንደምታ እንዳላቸው እናስታውስ፡--ዛሬን እንዴት መኖር እንዳለብን ማስተማር እና ለወደፊቱ እንድንዘጋጅ ማድረግ፡፡

**እሁድ** **የካቲት 17**

# ከባሕር የወጣው አውሬ

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 13፡1-4፣ 8፣ 17፡8፡፡ የዚህ አውሬ ልዩ ባህሪያት ምንድን ናቸው? የሕልውናው የዕድገት ደረጃስ?

---

---

ዮሐንስ አንድ አስፈሪ አውሬ ከባሕር ሲወጣ ተመልክቶአል፡፡ አውሬ ፖለቲካዊ ሥልጣንን የሚወክል እንደመሆኑ፤ ከባሕር የወጣው አውሬ የተገለጸበት መንገድ ኃይማኖታዊ እና ፖለቲካዊ ሥልጣን ያለውን ኃይል ያመለክታል፡፡ ባሕር የሮም ልዕለ ኃያል አገዛዝ ውድቀትን ተከትሎ የተከሰተው ጽንፈኛ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ሁናቴ ተምሳሌት ነው (ዳን. 7፡2-3፣ 23-24)፡፡

ዮሐንስ አስፈሪ ሲል የገለጸው አውሬ ከባሕር ሲወጣ መመልከቱን ተናግሮአል፡፡ አውሬው ሰባት ራሶችና ዐሥር ቀንዶች የነበሩት ሲሆን--በራእ. 12፡3 ከቀረበው ዘንዶ ጋር ያለው ተመሳሳይነት በሁለቱ መካከል ያለውን ግንኙነት ያሳያል፡፡ በራሶቹ ላይ የስድብ ስሞች፣ በቀንዶቹ ላይ ደግሞ ዘውዶች ደፍቶአል፡፡ የአውሬው ራሶች ሰይጣን በዘመናት የእግዚአብሔርን ሕዝቦች ለማሳደድ የሚጠቀምባቸው ኃይሎች ናቸው (ራእ. 17፡9-11)፡፡ የስድቡ ስም አውሬው አለኝ የሚለውን መለኮታዊ ማዕረግ ይወክላል፡፡ ወደ ዳን. 7፡24 የሚያመላክቱት ዐሥሩ ቀንዶች የልዕለ ኃያሉን ሮም አስተዳደር መክሰም ተከትሎ የወጡት መንግሥታት ተምሳሌቶች ናቸው፡፡

አውሬው ከውሃ ሲወጣ--የነብር፣ የድብ እና የአንበሳ የሚመስል ገጽታ ይዞ ነበር፡፡ ይህ ደግሞ አውሬው በዳን. 7፡2-7 የተጠቀሰውንና (የዓለም መንግሥታት ተምሳሌት የሆነውን) የአራት አውሬዎችን መለያ ባህሪያት በአንድ አጣምሮ መያዙን ያሳያል፡፡ መንግሥታቱ--ባቢሎን፣ ሜዶንና ፋርስ፣ ግሪክ እና ሮም (ዳን. 7፡17) ናቸው፡፡ ሆኖም ዮሐንስ የሚያስቀምጣቸው ቅደም ተከተላቸውን ጠብቆ ሳይሆን በተገላቢጦሽ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ከባሕር የወጣው አውሬ የሮም ንጉሠ ነገሥታዊ ግዛት ከሆነው ከዳን. 7 አራተኛው አውሬ ጋር ያለውን ዝምድና ያሳያል፡፡ ዘንዶው ኃይሉን፣ ዙፋኑንና ታላቅ ሥልጣን ለአውሬው ሰጥቶታል፡፡ አብ ዙፋኑን እንዲሁም ሥልጣን ሁሉ ለክርስቶስ እንደ ሰጠ (ራእ. 2፡27) በተመሳሳይ ዘንዶውም የምድር አጋር፣ ገዢና ወኪሉ አድርጎ ይሰጠዋል፡፡ ከባሕር የወጣው አውሬ የሦስትዮሹ ሰይጣናዊው ኅብረት ሁለተኛው

አካል ሲሆን ይህ ደግሞ የሱስ ክርስቶስን ከሰብዓዊው ልብ ለማውጣት የሚደረግ ሙከራ ነው።

አውሬው በሥልጣን የሚሠራባቸው ጊዜያቶች 42 ትንቢታዊ ወራት ወይም 1,260 ቀናት (ዓመታት) መሆናቸው ተገልጾአል። ከአውሬው ራሶች በአንደኛው ላይ ለሞት የሚያደርስ ጊዜያዊ ቁስል በደረሰበት ጊዜ ይህ ምዕራፍ ይደመደማል። ሆኖም ቁስሉ በተፈወሰለት ጊዜ አውሬው ዳግም በሕይወት ያንሰራራል። ይህ ሁናቴ በዓለም ከፍተኛ አድናቆት እንዲገኝ የሚያስችል በመሆኑ ብዙዎች ለዘንዶውና ለአውሬው ይሰግዳሉ።

## ሰኞ የካቲት 18

# ከባሕር የወጣው አውሬ ተግባራት

ራእ. 15፡5 በአንድ የተወሰነ ወቅት ስለሚደርስ ስደት መናገሩን በትናንቱ ጥናታችን ተመልከተናል። የአውሬው ለ42 ወራት በሥልጣን መቆየት ከራእ. 12፡14--የ1,260 ቀናት የሴቲቱ (የቤተ ክርስቲያን) የስደት ዘመን ጋር እኩል ነው። ተምሳሌታዊዎቹ ትንቢታዊ ቀናት ገሃዱን ዓመታት ይወክላሉ። 538 ዓ.ም.--የትንቢታዊው ምዕራፍ ጅማሮ ሲሆን፤ ይኸውም ጳጳሳዊውን ሥርዓት የበላይ አድርጋና ራሷን በክርስትና ተቋም ኃይልነት ሰይማ፣ በመካከለኛው ዘመን ምዕራቡን ዓለም በበላይነት የተቆጣጠረችው የሮም ቤተ ክርስቲያን መነሳት ነው። የፈረንሳይ አብዮት ሲፈነዳ ይዞት የመጣው ነውጥ በ1798 ዓ.ም. አውሬው ከፉኛ እንዲቆስል መንስዔ ሆነ። በዚህም ቤተ ክርስቲያን የነበራት ጨቋኝ ሚና እና የመንግሥት ቀኝ የነበረው ኃይማኖታዊ ተቋም ለጊዜውም ቢሆን ያከተመለት መሰለ።

ጥቅሶቹን ያስተያዩ፡ ራእ. 13፡5-8፣ ዳን. 7፡24-25፣ 2ተሰ. 2፡2-12። ከባሕር የወጣው አውሬ ተግባራት ስለ ትንሹ ቀንድ እና ስለ ዐመፅ ሰው የቀረበውን መግለጫ በተሻለ የሚያንጸባርቁት እንዴት ነው?

---

---

በ1,260 ትንቢታዊ ቀናት ውስጥ የተስተዋለው የአውሬው እንቅስቃሴ የስድብ ቃል በሚል አነጋገር ተወስቶአል። የስድብ ቃል--ከእግዚአብሔር ጋር እስተካከላለሁ እንደ ማለት ነው ሲል አዲስ ኪዳን ይነግረናል (ዮሐ. 10፡33፣ ማቴ. 26፡63-65፣ ማር. 2፡7)። ከባሕር የወጣው አውሬ የስድብ ቃላት የሚያነጣጥሩት ወደ እግዚአብሔር ነው፡ “እርሱም እግዚአብሔርን ለመሳደብ እንዲሁም ስሙንና ማደሪያውን፣

በሰማይም የሚኖሩትን ለመሳደብ አፉን ከፈተ” (ራእ. 13፡6)፡፡ የእግዚአብሔር ማደሪያ ክርስቶስ ስለ እኛ ደኅንነት አገልግሎት የሚሰጥበት ሰማያዊው መቅደስ ነው፡፡ የደኅንነት ሥራን የመቆጣጠርና የመምራት እንዲሁም ኃጢአትን ይቅር የማለት መብት እንዳለው የሚናገረው ከባሕር የወጣው አውሬ ድርጊት፤ ከክርስቶስ የማማለድ ሥራ ጋር የሚጻረረው የዚህ የስድብ ቃል ትክክለኛ ፍቺ ነው፡፡

ራእ. 13 በጳጳሳዊው ሥርዓት የበላይነት የምዕራቡ ዓለም ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት በሮም ጥበቃና ምሪት ስር የዋለባቸውንና፤ ጳጳሱ ከእግዚአብሔር ልዩ መብትና ጥቅም እንደ ተቀበለ ተደርጎ የታመነበት ይህ የበላይነት--በቤተ ክርስቲያን ላይ መሰረታዊ ክህደት የተፈጸመባቸውን ዘመኖች ያመላክታል፡፡ ሰብዓዊውን ዘር የሚዋጀው ሰማያዊው የክርስቶስ አገልግሎት በቤተ ክርስቲያን ከጎነት ተተካ፡፡ ለሮም ቤተ ክርስቲያን ታማኝ ያልሆኑ ስደት ደረሰባቸው፣ የሰማዕትነት ሞትም ተቀበሉ፡፡ ምንም እንኳ ዛሬ እንደነዚህ ዓይነቶቹ አነጋገሮች እንደ ጨካኝና ፍጹም አክራሪ ድርጊት ቢታዩም፤ ነገር ግን የዛሬው ሁኔታ የትናንቱን ታሪክ ፈጽሞ ሊፍቅ አይችልም፡፡

***የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ አስመልክቶ ለትንቢት ታማኝ መሆን ያለብን እንዴት ነው? በተጨማሪ እነዚህን እውነቶች ለሌሎች ስናቀርብ ደግነትና ጥንቃቄ እንዳይለየን መዘንጋት የለብንም፡፡***

## ማክሰኞ　　　　　የካቲት 19

## ከምድር የወጣው አውሬ

የራእይ ምዕ. 13 የመጀመሪያው ግማሽ በ1,260 ትንቢታዊ ቀናት/ ዓመታት በጉልህ የታየውን የመካከለኛውን ዘመን የቤተ ክርስቲያን ዐምባ ገነንነት ይገልጻል፡፡ በፈረንሳይ ተቀጣጥሎ የፈነዳው አብዮት በዚህ ኃይማኖትንና ፖለቲካን በአንድ አጣምሮ በያዘ ተቋም ላይ ለሞት የሚያደርስ ቁስል አደረሰ፡፡ ሆኖም ውሎ አድሮ ለሞት የሚያደርሰው ቁስል ሻረና ሥርዓቱ ወደ ቀድሞ ህልውናው ተመለሰ፡፡ ይህ ለሞት ያደረሰው ቁስል ፈውስ--እንዴት ገቢራዊ እንደሚሆን የምዕራፉ ሁለተኛ አጋማሽ ይገልጽልናል፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 13፡11፡፡ የሁለተኛው አውሬ ባህሪያት ምንድን ናቸው? በራእ. 12፡14-16 መሰረት የዚህ አውሬ ከምድር መውጣት አንደምታ ምንድን ነው?

________________________________________

________________________________________

ዮሐንስ ሌላ አውሬ ከምድር ሲወጣ እንደተመለከተ ይናገራል፡፡ ይህ ከምድር የወጣ አውሬ አስፈሪ ገጽታ ከነበረው ከመጀመሪያው አውሬ በተቃራኒ “እንደ በግ ሁለት ቀንዶች” የነበሩትና ጉዳት የሌለው ዓይነት ነበር (ራእ. 13፡11)፡፡ በራእይ መጽሐፍ በግ ክርስቶስን በብቸኝነት ይወክላል፡፡ ስለዚህ ይህ በዘመን መጨረሻ ላይ የሚነሳ ኃይል የክርስቶስ ዓይነት ገጽታ ይኖረዋል፡፡

ይህ ከቤተ ክርስቲያን ጋር ወዳጃዊ ሆኖ በበግ የተመሰለው አውሬ ኃይል የተነሳው ሴቲቱን ወይም ቤተ ክርስቲያንን በ1,260 ቀናት መደምደሚያ (ራእ. 12፡14-16) ላይ ከዘንዶው የጎርፍ ውሃ ከተከላከላት ግዛት ነው፡፡ ከባሕር የወጣው አውሬ በፈረንሳይ አብዮት ለሞት የሚያደርስ ቁስል ከደረሰበት በኋላ የዓለም ልዕለ ኃያል ሆኖ ብቅ ያለ የመጨረሻው ዘመን ትዕይንት አዲስ ተዋናይ መሆኑ እርግጥ ነው፡፡

ሆኖም ይህ በበግ የተመለሰለ ኃይል ውሎ አድሮ እንደ ራሱ እንደ ዲያብሎስ ማለትም እንደ ዘንዶ መናገር እንደሚጀምር ከጥቅሱ እንመለከታለን፡፡ ይህ የመጨረሻው ዘመን ኃይል መላው ዓለም ለሞት የሚያበቃ ቁስል ደርሶበት ለነበረው የመጀመሪያው አውሬ እንዲሰግድ ለሚደረገው እንቅስቃሴ ቁልፍ መሣሪያ ይሆናል፡፡ በድኅረ መካከለኛው ዘመን፤ በአንድ ወቅት ለቤተ ክርስቲያን መጠጊያ በመሆን ደኅንነቷን ያስጠበቀው ይህ ግዛት፤ በመጨረሻው ዘመን ገቢራዊ በሚሆኑ ክስተቶች የማሳደድ ሚና እንደሚጫወት ከዚህ እንመለከታለን፡፡

“ብርቱ እና ታላቅ እንደሚሆን የተስፋ ቃል የተሰጠውና የዓለምን ትኩረት እየሳበ በ1798 በአዲሱ የዓለም ሥርዓት ወደ ሥልጣን የመጣው የትኛው መንግሥት ነው? የተምሳሌቱ አተገባበር አንዳችም ጥያቄ የሚያስነሳ አይደለም፡፡ የዚህን ትንቢት ዝርዝር መመሪያ በብቸኝነት የሚያሟላ አንድ እና አንድ ብቻ አገር ሲሆን ይኸውም ዩናይትድ ስቴስ ኦቭ አሜሪካ ነው፡፡”—Ellen G. White, The Great Controversy, p. 440.

**አሜሪካ የትንቢቱ ፍጻሜ በመሆን ተለይታ በተቀመጠችበት ወቅት ዛሬ በዓለም ዙሪያ ካላት ልዕለ ኃያልነት ጫፉ የሚደርስ ኃይልም ሆነ ተጽእኖ አልነበራትም፡፡ ዩናይትድ ስቴትስ በዚህ ትንቢት የቀረበችበት ይህ የልዕለ ኃያልነቷ ሐቅ፤ አገሪቱ የትንቢቱን መስፈርት ማሟላቷን አጽንተን እንድንይዝ እንዴት ሊረዳን ይችላል?**

ረቡዕ

የካቲት 20

# የአውሬው ምስል

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 13፡12-13፡፡ እሳት ከሰማይ እስከ ማውረድ ታላቅ ታምራት የሚያደርገውን የዚህን አውሬ ተፈጥሮ ማስተዋል እንድንችል 1ነገሥ. 18፡38 እና ሐዋ. 2፡3 እንዴት ይረዱናል?

---

---

በመጨረሻው ዘመን በግ የሚመስለው አውሬ የመጀመሪያውን አውሬ ሥልጣን መለማመድ የሚጀምር ሲሆን፤ የእርሱ ድርጊትም ሆነ እንቅስቃሴ ከመንፈስ ቅዱስ ተግባርና ኃላፊነት ጋር ይመሳሰላል፡፡ መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን ወደ ክርስቶስ በማመላከት (ዮሐ. 15፡26) ስለ ክርስቶስ ሥልጣን ምስክርነት እንደሚሰጥ ሁሉ፤ ይህ ምድራዊ ኃይልም ከባሕር የወጣው አውሬ ላለው ሥልጣን ምስክርነቱን ለሕዝብ ይሰጣል፡፡

በግ መሳዩ አውሬ ለመጀመሪያው አውሬ እጅግ ከፍ ያለ ክብር በመስጠት የምድር ሕዝቦች የመጀመሪያውን አውሬ እንዲያመልኩ መንስዔ ይሆናል፡፡ ይህ ሁናቴ ለሞት ከሚያደርስ ቁስል ከተፈወሰው አውሬ ጋር ዝምድና እንዳለው ጥቅሱ ያሳየናል። ለመሆኑ በግ የሚመስለው አውሬ ዓለም ከባሕር ለወጣው አውሬ እንዲሰግድ የሚያደርገው እንዴት ነው? በመጀመሪያ--ታምራቶችንና ምልክቶችን በማድረግ (ራእ. 13፡13-14) በቀጣይ--በማስገደድ (ራእ. 13፡15-17)፡፡

ከባሕር የወጣው አውሬ ለሞት ያደርስ የነበረ ቁስል መፈወስ የመካከለኛው ዘመን ኃይማኖታዊ ሥርዓት ወደ ቀድሞው ሁናቴ መመለሱን ያሳያል፡፡ በግ የሚመስለው አውሬ ለሞት የሚያደርስ ቁስል ለደረሰበት አውሬ ምስል በማቆም ታምራቶችን ተጠቅሞ የምድርን ሕዝቦች ማሳት የሚቻለው ይሆናል፡፡

ምስል የአንድ ተጨባጭ ነገር ግልባጭ ነው፡፡ ዓለም የቀደመውን አምሳያ፤ ይኸውም የመካከለኛውን ዘመን ኃይማኖታዊ ሥርዓት ለመፍጠር የሚገፋፋ ይሆናል። ሕዝቦች አሳቾቹን ታምራቶች የመለኮታዊ ኃይል መገለጫ አድርገው የሚቀበሉ ይሆናሉ፡፡ ሕዝባዊና ፖለቲካዊ ኃይላት ኃይማኖትን በሕዝቡ ላይ ለመጫን ዓለምን እየመሩ ከሚገኙ ኃይማኖታዊ ተቋማት ጋር በሚሰለፉበት ወቅት የአውሬው ምስል ይፈጠራል፡፡

ራእ. 13፡14-15 ያንብቡና ከዘፍ. 2፡7 የወጣው ቋንቋ--የአውሬው ምስል ለመሥራት የሚያስችለው እስትንፋስ እንዴት እንደተሰጠው የሚገልጽበትን አካሄድ ለማስተዋል ይሞክሩ፡፡

በግ የሚመስለው አውሬ--የአውሬው ምስል እግዚአብሔር ሰውን ከፈጠረበትና ሕይወት ከሰጠበት ሂደት በተመሳሳይ እንዲሠራ ያደርጋል ሲል ይኸው ትንቢት በዘፍ. 2፡7 የቀረበውን ቋንቋ ተጠቅሞ ይነግረናል፡፡ ይህን ማስገደድን ጫና አድርጎ የተከተለ የማሳመን ሥራ ተከትሎ፤ የዓለም ሕዝቦች ለአውሬው ሥልጣን እውቅና ለመስጠት እና እርሱን ለመቀበል ይገፋፋሉ፡፡

## ሐሙስ የካቲት 21

# የአውሬው ምልክት

በመጨረሻው ቀውስ ወቅት በግ የሚመስለው አውሬ የመሪነቱን ሚና እንደሚጫወት ራእ. 13 ይጠቁመናል፡፡ ይህ የዓለም ልዕለ ኃያል--የሕዝቦችን የማምለክ ነፃነት ለመቆጣጠር እንዲቻለው የመካከለኛው ዘመን ክርስትናን ነጸብራቅ በዓለማቀፋዊ ሕግና አሠራር ያቋቁማል፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 13፡16-17፤ ዘዳ. 6፡4-8፡፡ በግምባር ላይ እና በቀኝ እጅ ላይ ምልክት ማስቀመጥ ከእግዚአብሔር ሕግ ጋር ምን ዓይነት ግንኙነት አለው?

---

---

ሐብታም ደኻ ሳይል ሁሉም የዓለም ሕዝቦች የአውሬውን ምልክት በግምባራቸውና እና በቀኝ እጃቸው እንዲቀበሉ ይገደዳሉ፡፡ ይህን ምልክት መቀበል ከአውሬው ጋር ማበር ይሆናል፡፡ አምላካዊው ማኅተም የእግዚአብሔር የሆኑት መለያ እንደመሆኑ (ራእ. 14፡1)፤ የአውሬው ምልክት ደግሞ ለእርሱ የሚሰግዱ የሚለዩበት ይሆናል፡፡

የአውሬው ምልክት በዐይን ተለይቶ የሚታይ ነገር አይደለም፡፡ ምልክቱ በቀኝ እጅ ወይም በግምባር ላይ ማረፉ እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ሕግ በእጆቻቸው ላይ ምልክት አድርገው እንዲያስሯቸውና በግምባራቸውም ላይ እንዲሆኑ (ዘዳ. 6፡ 8) ሙሴ የሰጣቸውን መመሪያ መሰረት ያደረገ ነው፡፡ በዚህም የምልክቱ በግምባር ላይ መሆን የእግዚአብሔር ሕግ በአእምሮ ላይ ያለውን ተጽእኖ ሲገልጽ፤ በቀኝ እጅ መሆኑ ደግሞ የሰዎችን የሥራ ባህሪ ያሳያል፡፡

አምልኮ እና የእግዚአብሔርን ትእዛዛት እየጠበቁ እርሱን መታዘዝ፤ ዋንኛው የመጨረሻው ቀውስ ወቅት ጉዳይ ይሆናል (ራእ. 14፡12)፡፡ በተለይ ሰንበትን እንድንጠብቅ የተሰጠው ትእዛዝ--ሕዝቦቹ ለእግዚአብሔር ያላቸው ታማኝነትና መታዘዝ የሚፈተንበት ይሆናል፡፡ ሰንበት የእግዚአብሔር ታማኝ ሕዝቦች እርሱን የመታዘዛቸው ግልጽ ምልክት ሲሆን (ሕዝ. 20፡12)፤ የአውሬው ምልክት ደግሞ አውሬውን የመታዘዝ መለያ ይሆናል፡፡ የአውሬው ምልክት የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በሰብዓዊው ትእዛዝ በመተካት በአራተኛው ትእዛዝ ላይ ቀጥተኛ ጥቃት ይፈጽማል፡፡ የዚህ ተጨባጭ እውነታ ግዙፍ ማስረጃ በመጽሐፍ ቅዱስ በተሰየመው በሰባተኛው ቀን ቅዳሜ ሰንበት ምትክ እሁድ የአምልኮ ቀን ሆኖ በሰው መቋቋሙ ነው (ዳን. 7፡25)፡፡ ጌታን በፈጣሪነቱ የምናመልከው ሲሆን፤ ሰባተኛው ቀን ሰንበት ደግሞ ከምድር መፈጠር አንስቶ የእውነተኛ አምላክነቱ ምልክት ሆኖ እንደ ጸና ይገኛል፡፡ የእግዚአብሔርን የመፍጠር ምልክት በሌላ ቀን ለመቀየር መሞከር የራሱን የእግዚአብሔርን ሚና እና ኃይል መቀማት ይሆናል፡፡

**በጥቅሶቹ የቀረቡትን ትዕይንቶች ያስተያዩ፡ ራእ. 13፡14-18፣ ዳን. 3፡1-7፡፡ በታሪኩ ምን ዓይነት ተመሳሳይነት ያላቸውን ሁናቴዎች ማግኘት እንችላለን? በዘመን መጨረሻ ምን ይከሰታል?**

## አርብ የካቲት 22

ተጨማሪ ሀሳብ፡ ሰንበት በምድር ታሪክ መደምደሚያ ላይ የመታዘዝ ምልክት እንደሚሆን የራእይ መጽሐፍ ያስገነዝበናል፡፡ ሆኖም ዛሬ እሁድን መጠበቅ የአውሬውን ምልክት መቀበል አለመሆኑን ማስታወስ ተገቢ ነው፡፡ ልዩ ልዩ ማደናገሪያዎችና ማታለያዎች መኖራቸው እሙን ቢሆንም፤ እሑድን መጠበቅ "የአውሬው ምልክት" የሚሆነው ሰዎች አምልኮ የሚያደርጉበትን ቀን መመምረጣቸውን ተከትሎ የሚመጣውን አንገብጋቢ ጉዳይ በግልጽ አስተውለው እግዚአብሔርን ወይም ከእርሱ በተቃራኒ የተሰለፈውን ኃይል ሲመርጡ ብቻ ነው፡፡ ሆኖም ያ ዕለት ገና አልደረሰም፡፡

"እስካሁን የአውሬውን ምልክት የተቀበለ ሰው የለም፡፡ የመፈተኛውም ጊዜ ቢሆን ገና አልደረሰም፡፡ ከሮም ጳጳሳዊው ሥርዓት ጋር ኅብረት የሌላቸው አያሌ ክርስቲያኖች በብዙ ቤተ ክርስቲያኖች አሉ፡፡ በሰባተኛው ቀን ዙሪያ ብርሃን እስኪቀበሉና የአራተኛውን ትእዛዝ አስገዳጅነት እስኪያስተውሉ አንዳቸውም ውግዘት የለባቸውም፡፡ ነገር ግን የሐሰተኛው ሰንበት አስገዳጅ ዐዋጅ ሲወጣ እና

ሰዎች ለአውሬውና ለምስሉ እንዳይሰግዱ የሚያስጠነቅቀው የሦስተኛው መልአክ ተማጽኖ ዳር እስከ ዳር ሲያስተጋባ፤ ያኔ በሐሰተኛውና በእውነተኛው አምልኮ መሃል ያለው ልዩነት ግልጽ ሆኖ ይሰመራል፡፡ በዚህ ወቅት አምላካዊውን ትእዛዝ በመተላለፍ የሚጸኑ የአውሬውን ምልክት ይቀበላሉ፡፡"—Ellen G. White, Evangelism, p. 234.

የእሑድ አምልኮ ዛሬ ማንንም ለጥፋት እንደማይዳርግ ሁሉ፤ በተቃራኒው ቅዳሜ ማንንም ሊያድን እንደማይችል እናስታውስ፡፡ ሆኖም "የአውሬው ምልክት" የነገሮች ሁሉ ማዕከላዊ ጉዳይ የሚሆንበትና የአምልኮ ቀን መምረጥ የታማኝነት መፈተኛ ሆኖ ብቅ የሚልበት ጊዜ እየመጣ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ሕዝቦች እውነትን ለማወቅ በሚሻ መንፈስ ልባቸውን ከፍተው የአምላካዊውን ቃል ትንቢቶች ለግላቸው እንዲያጠኑና፣ ይህን የክርስቶስ ወንጌል ወዳላገኙ ለመድረስ ማንኛውንም ጥረት ያደርጉ ዘንድ የራእይ መጽሐፍ ተማጽኖውን ያቀርባል፡፡

## የመወያያ ጥያቄዎች፡

**1.ከዛሬው የዓለም ሁኔታ አኳያ በኃይማኖታዊውና በፖለቲካው አድማስ ወደ ራእ. 13 ትንቢት ፍጻሜ ሊያመሩ የሚችሉ ምን ዓይነት አካሄዶችን ይመለከታሉ?**

**2.መጨረሻውን እየተጠባበቅን እያለን፣ በሌሎች የኃይማኖት ድርጅቶች በሚገኙ ክርስቲያኖች ላይ የሚኖረን አመለካከት ምን ሊሆን ይገባል? ስለሚከተለው ምክረ ሃሳብ አሰብ ያድርጉ፡ "አገልጋዮቻችን ሌሎች አገልጋዮችን ለመቅረብ ጥረት ማድረግ አለባቸው፡፡ ክርስቶስ እየማለደላቸው ለሚገኝ ለእነዚህ ሰዎች ይጸልዩ እንዲሁም ከእነርሱ ጋር አብረው ልመና ያቅርቡ፡፡ እነሆ የተከበረ ኃላፊነት አለባቸው፡፡ እኛ እንደ ክርስቲያን መልእክተኝነታችን ለእነዚህ የመንጋ እረኞች ጥልቅና ቅን ፍላጎት ማሳየት ይኖርብናል፡፡"—**Ellen G. White, Testimonies for the Church, vol. 6, p. 78.

**አልፎ አልፎ በሌሎች የክርስትና ድርጅቶች በሚገኙ ክርስቲያኖች ላይ የምንገልጠውን ክርስቲያናዊ ያልሆነ መንፈስ ማስወገድ የምንችለው እንዴት ነው? ያመንናቸውን እውነቶች ለድርድር ሳናቀርብ ለእነርሱም ሆነ ለግል እምነታቸው አክብሮት ማሳየት የምንችለው እንዴት ነው?**

# 10ኛ ትምህርት

ከየካቲት 23- 29

# የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ወንጌል

ሰንበት ከሰዓት

ለዚህ ሣምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ራእ. 14:6–12፣ ማቴ. 24:14፣ መክ. 12:13-14፣ ዘፀ. 20:2–11፣ ኢሳ. 21:9፣ 34:8–10፡፡

**መታሰቢያ ጥቅስ፡ - "የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁና ለኢየሱስም ታማኝ ሆነው በትዕግሥት የሚጸኑ ቅዱሳን የሚታወቁት በዚህ ነው" (ራእ. 14፡12)።**

በመጨረሻው ጊዜ ሰይጣን በማሳት ሥራው ውጤታማ እንደሚሆንና ዓለም ለአውሬው ለመሥገድና ምልክቱን ለመቀበል እንደሚመርጥ የራእይ መጽሐፍ ያሳየናል፡፡ ሆኖም እግዚአብሔር ከአብዛኛው የዓለም ሕዝብ በተቃራኒ ለጌታ የሚቆሙ ትሩፋን እንደሚኖሩት ራእ. 14፡1-5 ይናገራል፡፡ ሰዎች ሁሌም አምልኮ ቢያደርጉም ነገር ግን በመጨረሻ ላይ ማንን ማምለክ እንዳለባቸው ሊመርጡ የግድ ይሆናል፡፡ ለአውሬው የሚሠግዱ በአእምሮአቸውና በድርጊታቸው ይህን ክህደት የፈጸመ ሥርዓት ለማገልገል የመምረጣቸው ምሳሌ የሆነውን ምልክት በግምባራቸው ወይም በቀኝ እጃቸው ይቀበላሉ፡፡

በተመሳሳይ ወቅት ከጴንጤቆስጤ ዕለት ወዲህ ታይቶም ሆነ ተሰምቶ ለማይታወቅ የወንጌል ዕወጃ ዓለም ምስክር ይሆናል፡፡ አምላካዊው ፍርድ በዐመጻኛው ሰብዓዊ ፍጡር ላይ ከመውረዱ አስቀድሞ እግዚአብሔር የማስጠንቀቂያ መልእክቱን ይልካል፡፡ ሰይጣን ሥራውን በዓለማቀፍ ደረጃ እንደሚያፋፍም ሁሉ የመጨረሻው ዘመን የወንጌል ዕወጃም እንደዚያው ይሆናል፡፡ የእግዚአብሔር ፍላጎት አንድም ሰው እንኳ እንዲጠፋ ሳይሆን ነገር ግን ሁሉም እንዲድን በመሆኑ እነሆ ክርስቶስ ስለ ሰብዓዊው ዘር መሥዋዕት ሆነ፡፡ ይህን ስጦታ ማን ይቀበላል ማንስ ይቃወማል-- የሚለው ነው አንገብጋቢው ጉዳይ፡፡

# እሑድ  የካቲት 24

## የሦስቱ መላእክት መልእክት

የምድር መጨረሻ ሊደርስ ጥቂት ጊዜ ሲቀር እግዚአብሔር በሰማይ መካከል በሚበሩት በሦስቱ መላእክት ተምሳሌት የቀረበውን የማስጠንቀቂያ መልእክቱን ይልካል፡፡ በግሪክኛ መልአክ (angelos) የተሰኘው ቃል እንደ አማርኛው ሁሉ “መልእክተኛ” የሚል ትርጉም አለው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ መልአክ መልእክተኛን ወክሎ ሲቀርብ ይታያል (ሚልክ. 2፡7፣ ማቴ. 11፡10)፡፡ ሦስቱ መላእክት ለዓለም የሚያካፍሉት የመጨረሻው ጊዜ መልእክት የተሰጣቸውን የእግዚአብሔር ሕዝቦች እንደሚወክሉ ከራእይ መጽሐፍ የሚገኙ ማስረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 14፡6፣ ማቴ. 24፡14፡፡ የመጀመሪያው መልአክ መልእክት “የዘላለም ወንጌል” (ራእ. 14፡6) በሚል ማጣቀሻ ቀርቦአል፡፡ ይህ ሁኔታ ስለ መጀመሪያው መልአክ መልእክት ይዘትና ዓላማ ምን ይነግረናል? ይህ መልእክት የሁሉም የእምነታችን ክፍል አስኳል የሆነው ለምንድን ነው?

________________________________________________

________________________________________________

የመጨረሻው ጊዜ--የመጀመሪያ መልእክት ወንጌል ነው፡፡ ወንጌል ሰብዓዊውን ፍጡር በመስቀል ስላዳነው አምላክ--የሱስ ክርስቶስ የሚተርክ የምሥራች ነው። የመጀመሪያው መልአክ መልእክት “ዘላለማዊ” ወንጌል የሆነበት ምክንያት፤ የወደቀውን ሰብዓዊ ዘር ወደ ቀድሞው ንጽህና ለመመለስ እየተደረገ ያለ የእግዚአብሔር የማያቋርጥ ጥረት አካል በመሆኑ ነው፡፡ እንደውም ከመፈጠራችን አስቀድሞ የተጠነሰሰ እቅድ ነው (2ጢሞቴ. 1፡9፣ ቲቶ 1፡2)፡፡ ወንጌል ደኅንነትን እና ፍርድን በአንድ አካትቶ ይዞአል፡፡ ለሚቀበሉት የሚድኑበት መልካም የምሥራች፤ የሚሰጠውን ተስፋ ለሚቃወሙ ደግሞ የፍርድ ማስጠንቀቂያ ይዞአል፡፡

ሦስቱ መላእክት መልእክቱን “በታላቅ ድምፅ” ማወጃቸው ተገልጾአል (ራእ. 14፡7፣9)፡፡ የሰብዓዊውን ፍጡር ዘላማዊ መዳረሻ የሚወስነው ይህ መልእክት አስቸኳይና እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ ለሁሉም ጆሮ መድረሱ የግድ ይሆናል። በዚህም ለሕዝብ፣ ለነገድ፣ ለቋንቋ እንዲሁም ለወገን መሰበክ ይኖርበታል፡፡ በመጨረሻው ዘመን አውሬው በሰይጣን ውክልና የተሰጠውን ሥልጣን በነገድ፣ በወገን፣ በቋንቋና በሕዝቡ ሁሉ ላይ (ራእ. 13፡7) እንደሚለማመድ ከተበረከተልን ብርሃን አኳያ መመልከታችን በእጅጉ ወሳኝ ነው፡፡ የሰይጣን አሳች እንቅስቃሴዎች

በዓለም ዙሪያ ሲንሰራፉ የመጨረሻው ዘመን የወንጌል ዕወጃ ገቢራዊ ይሆናል፡፡ ከሰይጣናዊው ሦስትዮሽ ኅብረት (ሐሰተኛ ሥላሴ) አፍ የሚወጡትን እንቁራሪት መሳይ እርኩሳን መናፍስት በመቃወም የሦስቱ መላእክት መልእክት በእግዚአብሔር ሕዝቦች ይሰበካል (ራእ. 16፡13-14)፡፡ መልእክቶቻቸው ለሦስቱ መላእክት መልእክት የተመቻቹ ሐሰተኛ የመልስ ምቶች ይሆናሉ፡፡ በዚህ የተነሳ በመጨረሻው ዘመን ሕዝቦችን ለየራሳቸው ታማኝ ለማድረግ ባለሙ ኃይላት አማካይነት ዓለም የሁለት ባላንጣዎች መልእክት ይቀርብላታል፡፡

**እኛ እንደ ሰባተኛ ቀን የዳግም ምጽአቱ ተጠባባቂነታችን ዓለምን በወንጌል እንድንደርስ ጥሪ ቀርቦልናል፡፡ ይህን ጥሪ ከዳር ለማድረስ እርስዎ ምን እያደረጉ ነው? አሁን እያደረጉ ካለው በተጨማሪ ምን ማበርከት ይችላሉ?**

## ሰኞ የካቲት 25

## የመጀመሪያው መልአክ መልእክት - - ክፍል 1

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 14፡7፣ መክ. 12፡13-14፡፡ "እግዚአብሔርን ፍሩ" ማለት ትርጉሙ ምንድን ነው? እግዚአብሔርን የመፍራት ጽንሰ ሃሳብ ከወንጌል ጋር እንዴት ይዛመዳል? ወንጌል የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ከመጠበቅ ጋር ያለው ተዛምዶ ምንድን ነው? (ሮሜ. 7፡7-13)፡፡ እግዚአብሔርን በመፍራትና ለእርሱ ክብር በመስጠት መካከል ያለው ግንኙነትስ እንዴት ይገለጻል?

---

---

"'እግዚአብሔርን ፍሩ፤ ክብርም ስጡት'" (ራእ. 14፡7) የተሰኘው ጥሪ የቀረበው ከ "ዘላለማዊው ወንጌል" እወጃ ዐውድ ነው፡፡ ክርስቶስ ለእኛ መዳን ያደረገውን መገንዘብ መቻላችን ለእርሱ አዎንታዊ ምላሽ ያስገኝለታል፡፡

በራእይ መጽሐፍ--እግዚአብሔርን መፍራትና ለእርሱ ክብር መስጠት ውሁድ ጽንሰ ሀሳቦች ናቸው (ራእ. 11፡13፣ 15፡4)፡፡ የመጀመሪያው--ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖርን ትክክለኛ ግንኙነት ሲያሳይ (ኢዮ. 1፡8) ቀጣዩ ደግሞ እርሱን መታዘዝ እንደሚገባ ያመለክታል፡፡ እግዚአብሔርን ፍሩ ማለት--በሥጋትና በጥበት ኑሩ ከሚለው ሃሳብ በተቃራኒ አምላካዊውን ጉዳይ እንደው በዋዛና በፈዛዛ ሳይሆን በጽኑ ወይም የምር አርጋችሁ ያዙት፣ በሕይወታችሁም ሕጋዊ የባለቤትነት ስፍራ ስጡት--የሚል አንደምታ አለው፡፡ የእግዚአብሔር የመጨረሻው ዘመን ሕዝቦች እርሱን የሚፈሩ

ይሆናሉ (ራእ. 11፡18፣ 19፡5)፡፡ እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው እርሱን በመታዘዝ (ዘዳ. 5፡29፣ መክ. 12፡13) እና ባህሪውን በማንጸባረቅ ያከብረዋል (ዘፍ. 22፡12)፡፡

እግዚአብሔርን እንድንፈራና ለእርሱ ክብር እንድንሰጥ የሚያነሳሳን የፍርዱ ሰዓት መድረሱ ነው (ራእ. 14፡7)፡፡ እዚህ ላይ የቀረበው ፍርድ ከዳግም ምጽአቱ ቀደም ብሎ ያለው ፍርድ ነው፡፡ የቅድመ ምጽአቱ ፍርድ ዓላማ እግዚአብሔርን በእውነት እያገለገልን መሆን አለመሆኑን በመጨረሻው ምርጫችን ማሳየት ነው (በሥራችን የምንገልጸው ምርጫ)፡፡ በፍርዱ መደምደሚያ የእያንዳንዱ ሰው የመጨረሻ መዳረሻ ይወሰናል (ራእ. 22፡11)፡፡ ከዚያም የሱስ ለእያንዳንዱ ሰው እንደ ሥራው ሊከፍለው ዳግም ይገለጣል (ራእ. 22፡12)፡፡

በራእ. 14 የቀረበው ፍርድ የወንጌል አካል ነው፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር በትክክለኛ ግንኙነት ላሉ ፍርድ ማለት--ነፃ መውጣት፣ መዳን እና ነፃነትን መቀዳጀት እንደ መሆኑ ለእነርሱ መልካም የምስራች ነው፡፡ ሆኖም ታማኝ ላልሆኑት ግን መጥፎ ዜና ነው፡፡ ከፊታችን ያለው የፍርድ መልእክት እነዚህ ወገኖች በንስሐ ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ የቀረበ ጥሪ ነው፡፡ ሁሉም በንስሐ እንዲመጡ እንጂ ማንም እንዳይጠፉ የእግዚአብሔር ፍላጎት ነው (2ጴጥ. 3፡9)፡፡

***በፍርድ ወንበር ፊት ብቻዎን መቆም የሚችሉት እንዴት ነው? ሥራዎችዎ ለየትኛው ፍርድ ዋስትና ሊሆንዎ ይችላሉ? መልስዎ ስለ ወንጌል አስፈላጊነት ምን ይነግሮታል? ከመጀመሪያው መልአክ መልእክት ጋር እንዲህ በቅርበት የተቆራኘው ለምንድን ነው?***

## ማክሰኞ የካቲት 26

## *የመጀመሪያው መልአክ መልእክት፣ ክፍል 2*

የእግዚአብሔርን ትእዛዛት መጠበቅ በሚል እንደ ተገለጠው (ራእ. 14፡12) በምድር ታሪክ መዝጊያ ለሚከሰተው ቀውስ ዋንኞቹ ጉዳዮች አምልኮ እና እግዚአብሔርን መታዘዝ ይሆናሉ (ራእ. 14፡12)፡፡ የዓለም ሕዝቦች በሁለት ቡድን ይከፈላሉ፡ እግዚአብሔርን የሚፈሩና እርሱን የሚያመልኩ እንዲሁም እግዚአብሔርን የሚፈሩና ለአውሬው የሚሰግዱ፡፡

የዐሥርቱን ትእዛዛት የመጀመሪያ ክፍሎች ደግመው ይቃኙና (ዘፀ. 20፡2-11) በመቀጠል ወደ ራእ. 13 ያምሩ፡፡ አውሬው እንዲመለክ የሚጠይቅበት መንገድ (ራእ. 13፡15)፤ አውሬው የሚመለክበትን ምስል ማቆሙ (ራእ.13፡14-15)፣ እግዚአብሔርንና

የእርሱን ስም መስደቡ (ራእ. 13፡5-6)፣ እንዲሁም ሰዎች የአውሬውን ምልክት መቀበላቸው (ራእ. 13፡16-17)--እነዚህ ሁሉ ሰይጣን በመጀመሪያዎቹ አራት ትእዛዛት ላይ የፈጸመውን ጥቃት እንዴት ያመላክታሉ?

---

የዐሥርቱ ትእዛዛት አካል የሆኑት የመጀመሪያዎቹ አራት ትእዛዞች ያላቸው ዝምድና ከአምልኮ ጋር ነው፡፡ እነዚህ ትእዛዞች በመጨረሻው ቀውስ ወቅት ለእግዚአብሔር የሚኖረን ታማኝነት መለኪያ እንደሚሆኑ የራእይ መጽሐፍ ይገልጥልናል፡፡ በክርስቶስና በሰይጣን መካከል የሚደረገው የመጨረሻው ውዝግብ በግልጽ የሚያጠነጥነው በአምልኮና በመጀመሪያዎቹ አራት ትእዛዛት ዙሪያ ይሆናል፡፡

በመጨረሻው ቀውስ ወቅት አጽንኦት የተሰጠው ቁልፍ ጉዳይ የመጀመሪያው መልአክ መልእክት ልባዊ ምክር ነው፡፡ "'ሰማይንና ምድርን፣ ባሕርንና የውሃ ምንጮችን ለፈጠረው ስገዱ'" (ራእ. 14፡7) በሚል የቀረበው ጥሪ የዐሥርቱ ትእዛዛት አካል የሆነውን አራተኛ ትእዛዝ በተዘዋዋሪ ይነካል (ዘፀ. 20፡11)፡፡ ፈጣሪ የሆነው እግዚአብሔር አምላክ እንዲመለክ የቀረበው ጥሪ ሰንበትን በመጠበቅ ዐውድ መሰጠቱን ከዚህ እንመለከታለን፡፡

በዐሥርቱ ትእዛዛት እንዲሁም በተቀረው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እንደ ተወሳው፤ እውነተኛ አምልኮ ከትክክለኛው የአምልኮ ቀን ጋር ዝምድና አለው፡፡ ሰባተኛው ቀን ሰንበት ከእግዚአብሔር ጋር ላለን ግንኙነት የተለየ ምልክት ነው (ዘፀ. 31፡13፤ ሕዝ. 20፡12)፡፡ በመጨረሻው ጊዜ የዓለም ሕዝቦች እውነተኛ ፈጣሪ ወደ ሆነው አምላክ እንዲመለሱና የሕይወታቸውን የባለቤትነት ስፍራ እንዲሰጡት ጥሪ እንደሚቀርብላቸው የመጀመሪያው መልአክ መልእክት ያሳየናል፡፡ ይህ መልእክት ሰይጣን በመጨረሻው ጊዜ ዓለምን ወደ ሐሰተኛ ኃይማኖትና እውነት መሳይ አምልኮ በመሳብ በሚሠራቸው የማታለያ ተግባራት ላይ ተግዳሮት ይኖረዋል፡፡ የዚህ ጉዳይ አስኳል አራተኛው ትእዛዝ የሆነው ሰባተኛው ቀን ሰንበት ይሆናል፡፡

"ሐሰተኛውን ሰንበት ማክበር ከአራተኛው ትእዛዝ በተቃራኒ ከመንግሥታዊው ሕግ ጋር እንድናብርና እግዚአብሔርን በመቃወም ለቆመው ኃይል ታማኝነትን ማጽናት ይሆናል፡፡ የእግዚአብሔርን ሕግ በመታዘዝ እውነተኛውን ሰንበት መጠበቅ፤ ለፈጠረን አምላክ ያለንን ታማኝነት የምናሳይበት ተጨባጭ ማስረጃ

ነው። አንደኛው ኢጋማሽ ራሱን ለምድራዊው ኃይል በማስገዛት የአውሬውን ምልክት ሲቀበል፤ የተቀረው በመለኮታዊው ሥልጣን ስር በታማኝነት መዋልን በመምረጥ የእግዚአብሔርን ማኅተም ይቀበላል፡፡"—Ellen G. White, The Great Controversy, p. 605.

## ረቡዕ የካቲት 27

# የሁለተኛው መልአክ መልእክት

የመጀመሪያው መልአክ ሰዎች እግዚአብሔርን እንዲፈሩና እውነተኛውን አምላክ እንዲያመልኩ ጥሪ ሲያቀርብ፤ ሁለተኛው ደግሞ ሐሰተኛ ኃይማኖታዊ ተቋም የሆነችውን ባቢሎን መጨረሻ ይፋ ያደርጋል፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 14፡8፣ 18፡1፣ ኢሳ. 21፡9፡፡ "ወደቀች" በሚል ሁለት ጊዜ ተደጋግሞ የቀረበው ይህ ቃል የመጨረሻውን ጊዜ የባቢሎን ውድቀት እርግጠኝነት ያመላክታል፡፡ ምንም እንኳ የባቢሎን ውድቀት ገና ወደፊት የሚጠበቅ ቢሆንም ነገር ግን ተቋሟ ካሁኑ እንደ ወደቀች ሆና የቀረበችበት ምክንያት ምንድን ነው?

---

---

እዚህ ላይ ባቢሎን በታላቅ ከተማነት ቀርባለች፡፡ ለዚህ ምክንያቱ በራእይ መጽሐፍ በምሳሌ የተጠቀሰችው ባቢሎን የተወሰደችው በታሪክ እግዚአብሔርን ስትቃወምና ሕዝቡን ስትጨቁን የኖረችውን ከሐዲ ሥረ መሰረት ተከትሎ በመሆኑ ነው፡፡ ኢሳ. 14፡12-15 ባቢሎንን ከሰይጣን ጋር እኩል አድርጎ በማቅረብ ራሷን ከእግዚአብሔር ጋር ለማስተካከል ያደረገችውን ሙከራ ያሳየናል፡፡ በዘመን መጨረሻ በራእይ መጽሐፍ የተከሰተችው ባቢሎን ሐሰተኛውን ሥላሴ ከሌሎች ከህደት የፈጸሙ ኃይማኖቶች ጋር አጣምራ ይዛለች (ራእ. 17፡5)፡፡ እነዚህ በክህደት ውስጥ የሚገኙ ኃይማኖታዊ ተቋሞች ከእግዚአብሔር ሕዝቦች በተቃራኒ እየሠሩ ማንነታቸውን ለሰይጣን አገልግሎት ያውላሉ (ራእ. 13፡11-18)፡፡ ክህደት የፈጸመው ኃይማኖታዊ ኅብረት ራሱን ከእግዚአብሔር በላይ ከፍ ከፍ እያደረገና ጌታ በዚህ ምድር ያለውን ስፍራ ለመውሰድ እየተመኘ የጥንቷን ባቢሎን ዕብሪተኝነት በይፋ ያሳያል፡፡ እንደ ጥንቷ ባቢሎን ሁሉ ይህ የረከሰ አምልኮአዊ ተቋምም በተመሳሳይ እንደሚያከትምለት የሁለተኛው መልአክ መልእክት ለእግዚአብሔር ሕዝቦች ማረጋገጫ ይሰጣል፡፡

ጥቅሶቹን በድጋሚ ያንብቡ፡ ራእ. 14፡8፤ 17፡2፤ 18፡3፡፡ ባቢሎን የምንዝሯን ወይን ጠጅ ለዓለም የምታጠጣው እንዴት ነው? የዚህ ወይን አንደምታስ ምንድን ነው?

---

---

ባቢሎን የቁጣዋን ወይን ጠጅ ለምድር ነዋሪዎች በማጠጣቷ ተወንጅላለች፡፡ ሕዝቦች ከባቢሎን የወይን ጠጅ እንደ ጠጡና እንደ ሰከሩ ኤርምያስ ይናገራል (ኤር. 51፡7)፡፡ የዘመን መጨረሻዋ ባቢሎን የምድር ሕዝቦችን በምንዝሯ ወይን ጠጅ የምታሰክርበትን ትዕይንት ራእ. 17 ይሰጠናል (ራእ. 17፡2)፡፡ ይህ ደግሞ ሰይጣናዊው ሥላሴ የምድር ሕዝቦች ለአውሬውና ለምስሉ እንዲሰግዱ (ራእ. 13፡11-18) ወደሚያባብልበት ራእ. 13 ይወስደናል፡፡

የባቢሎን የወይን ጠጅ በዚህች ክህደት የፈጸመች ኃይማኖታዊ ተቋም የሚሰጠውን ሐሰተኛ አስተምህሮ እና ወንጌል ይወክላል፡፡ በስካር ውስጥ ያሉ ሰዎች ራሳቸውን መቆጣጠር ስለሚሳናቸው በትክክል ማሰብ አይችሉም፡፡ ሰዎች በባቢሎን የወይን ጠጅ መንፈሳዊ ስካር ስር ሲውሉ፤ ኅሊናቸው ለአውሬው ለመስገድም ሆነ ምልክቱን ለመቀበል ይማልላል፡፡ የአስተሳሰብ አድማሳቸውን አነሁልሎ የነበረው ስካር ሲለቃቸው፤ ውሳኔዎቻቸውንና ድርጊቶቻቸውን ለማጤን ቢሞክሩም ጊዜው ረፍዶአል (ራእ. 17፡15-17)፡፡

**አንድ ሰው የባቢሎንን ወይን ጠጅ ለመጠጣት ባቢሎን ውስጥ መኖሩ የግድ ይሆናል? ለመሆኑ ከባቢሎን የወይን ጠጅ የሚጠጣው እንዴት ነው?**

## ሐሙስ — የካቲት 28

# የሦስተኛው መልአክ መልእክት

የእግዚአብሔር ታማኝ ሕዝቦች በራእ. 14፡12 የቀረቡበት መንገድ ምን ይመስላል?

---

---

ከእነዚህ ሕዝቦች በተቃራኒ የእግዚአብሔርን ቁጣ ስለሚቀበሉ ሰዎች አስመልክቶ ራእ. 14፡9-10 ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፡፡ የእግዚአብሔርን ቁጣ የወይን ጠጅ ስለ መጠጣት የሚገልጽ ተምሳሌታዊ አባባል በብሉይ ኪዳን ቀርቦአል (ኤር. 25፡15-16)፡፡ ለአውሬው በሚሰግዱ ላይ የሚኖረው የፍርድ ጽናት--ምንም ያልተቀላቀለበትን የእግዚአብሔር ቁጣ የወይን ጠጅ ጽዋ መጠጣት በሚል ተገልጾአል፡፡ በጥንት

ዘመን የወይን ጠጅ ሲጠነክር በውሃ ተበርዞ የማስከር ኃይሉ እንዲቀንስ ሲደረግ፤ በተቃራኒው የማስከር ኃይሉ እንዲጨምር ደግሞ ልዩ ልዩ እጸዋትና ቅመማ ቅመሞች ጣል ይደረጉበት ነበር፡፡ በእግዚአብሔር ቁጣ የወይን ጠጅ የተሞላው ይህ ጽዋ ምንም አልተቀላቀለበትም ማለት ምኅረቱ አልገባበትም የሚል ፍቺ አለው (መዝ. 75፡8)፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 14፡10-11፤ 20፡10-15፡፡ " 'የሥቃያቸውም ጢስ ከዘላለም እስከ ዘላለም ወደ ላይ ይወጣል' " በተሰኘው አባባል ላይ ኢሳ. 34፡8-10 እና ይሁዳ 7 የሚፈነጥቁት ብርሃን ምን ይመስላል?

________________________________________________________

________________________________________________________

________________________________________________________

እሳት እና ዲን የሚካተቱበት መግለጫ አጠቃላይ ውድመትን ይጠቁማል፡፡ እሳት እና ዲን ፍርድ የሚሰጥበት መንገድ ነው (ዘፍ. 19፡24፤ ኢሳ. 34፡8-10)፡፡ ወደ ላይ እየተትጎለጎለ የሚወጣው የውድመት ጢስ በመጽሐፍ ቅዱስ የሚታወቅ ትዕይንት ነው፡፡ ወደ ፊት በእሳት እና በዲን ስለሚደርሰው ውድመት አስመልክቶ ኢሳይያስ እንዲህ ይላል "እሳቷ ሌሊትና ቀን አይጠፋም፤ ጢሷም ለዘላለም ይትጎለጎላል" (ኢሳ. 34፡10)፡፡ ይሁዳ ሰዶምና ገሞራ ስለደረሰባቸው ጽኑ ቅጣት ሲናገር "በዘላለም እሳት" (ይሁዳ 7) ተቃጡ ይለናል፡፡ ዛሬ በዘላለም እሳት እየነደደ የሚገኝ ስፍራ እንደ ሌለ ሁሉ እነዚህም ጥቅሶች ማብቂያ ስለሌለው ቃጠሎ አይናገሩም፡፡ ዘላለማዊ የሆነው እሳቱ ሳይሆን ውጤቱ ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ "ዘላለማዊ እሳት" ድምጥማጡን ማጥፋት የሚል ፍቺ አለው፡፡ እሳት ለፈጀው ምን ይበጀው እንዲሉ የእሳቱ ቃጠሎ ምንም ዓይነት ነገር ሳያስቀር ሁሉንም በልቶ ይጨርሳል፡፡

**ምንም እንኳ የገሐነም እሳት የጠፉትን ለዘላለም ሲያሰቃይ አይኖርም የሚለውን እውነት በማስተዋላችን አመስጋኝ ብንሆንም--ቅጣቱ እጅግ አሰቃቂ ለመሆኑ አንድና ሁለት የለውም፡፡ ስለሚመጣው ፍርድ ሌሎችን ማስጠንቀቅ እንደሚኖርብን አስመልክቶ በተጣለብን የተቀደሰ ብርቱ ኃላፊነት ዙሪያ ይህ ምን ሊነግረን ይገባል?**

# አርብ

የካቲት 29

ተጨማሪ ሀሳብ፡ Read Ellen G. White, “The Final Warning,” pp. 603–612, in The Great Controversy.

የእግዚአብሔር ሕዝቦች የመጨረሻውን ጊዜ ወንጌል ለዓለም የሚያውጁበት ተልዕኮ እንደተሰጣቸው የራእይ መጽሐፍ ያሳየናል፡፡ ከፊት ለፊታችን የሚጠብቀን ሥራ ተስፋ አስቆራጭና የማይቻል ቢመስልም ነገር ግን አምላካዊው ተስፋ አለን፡፡

“ታላቁ የወንጌል ሥራ የወንጌል ዘር ሲዘራ ከተገለጠው አምላካዊ ብርቱ ኃይል ባነሰ አይደመደምም...

“መልእክቱ ከእግዚአብሔር መንፈስ ጥልቅ መነካት ውጪ በክርክርና በጭቅጭቅ የትም አይደርስም፡፡ ጭቅጭቁና ንትርኩ በጌታ እግር ስር እንዲውል ሆኗል፡፡ ዘሩ እንደተዘራ ሁሉ እነሆ ጎልብቶ የሚያፈራበት ወቅት ላይ ደርሶአል፡፡”—Ellen G. White, The Great Controversy, pp. 611, 612.

የአምላካዊው የመጨረሻ መልእክት እወጃ መደምደሚያ--የምድር ሕዝቦች ከሁለት ጎራ እንዲከፈሉ መንስዔ ይሆናል፡--ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ያላቸው እና አውሬውን ለመከተል የመረጡ፡፡ እንዲህ ያለው መለያየት በሁለቱ የምድር መከሮች ተመልክቶአል፡ የስንዴው ወደ ጎተራ መግባት (ራእ. 14፡14-16) እና የወይኑ በወይን መጭመቂያ መረገጥ (ራእ. 14፡17-20)፡፡ ይህ የራእ. 17-18 አበይት ርዕሰ ጉዳይ ነው፡፡

## የመወያያ ጥያቄዎች፡

**1.ከሰባተኛ ቀን አድቬንቲስቶች ውጪ የሦስቱን መላእክት መልእክት እየሰበከ የሚገኝ ተቋም ማነው? የዚህ ምላሽ ስለ ሥራችን አስፈላጊነት ምን ይነግረናል? የተሰጠንን ተልዕኮ ምን ያህል የምር ይዘነዋል?**

**2.አምላካዊው ፍርድ በብዙ ክርስቲያኖች ዘንድ ገሸሽ የተደረገ ዓይነት የሆነው ለምን ይመስሎታል? የቅድመ ምጽአቱ ፍርድ ጽንሰ ሃሳብ ለዛሬዎቹ ክርስቲያኖች ምን ዓይነት አንደምታ አለው? ወዳጆችዎ እውነተኛውን የቅድመ ምጽአቱ ፍርድ ጽንሰ ሃሳብ በተሻለ ማስተዋል እንዲችሉ እንዴት ሊረዷቸው ይችላሉ?**

3. በሰንበት ዙሪያ የሚነሱን ጥያቄዎች ከመጨረሻው ጊዜ ቀውሶች ዐውድ አሰብ ያደርጉ፡፡ መጀመሪያ ከፍጥረት ጊዜ አንስቶ የተቋቋመው ሰባተኛው ቀን ሰንበት (ዘፍ. 2፡2-3) ይህን ያህል የጉዳዮች ማዕከል የመሆን ሚና እንዲጫወት የላቀ ትርጉም የሰጠው ምን ይመስሎታል? ጉዳዩ ለማን እንስገድ--"ሰማይንና ምድርን ለፈጠረው" (ራእ. 14፡ 7) ወይስ ለአውሬው ሥልጣን--የሚል ከሆነና፤ ሰባተኛው ቀን ሰንበት ጥንታዊ፣ እጅግ መሰረታዊና እግዚአብሔር "ሰማይንና ምድርን" መፍጠሩን የሚያረጋግጥ ምልክት ነው ካልን፤ ታዲያ ለምን ይሆን ሰንበት እንደ አንድ የእግዚአብሔር ሕግ (ራእ. 14፡12) እንዲህ በግልጽ የሚታይ ሚና የማይጫወተው?

# 11ኛ ትምህርት

ከየካቲት 30 - መጋቢት 6

# ሰባቱ የመጨረሻ መቅሰፍቶች

ሰንበት ከሰዓት

ለዚህ ሣምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ራእ. 15:1፣ 7:1–3፣ 14:9-10፣ 16:1–12፣ 17:1፣ ዳን. 5፣ ራእ. 16:16፣ 2ተሰ. 2:9–12፡፡

**መታሰቢያ ጥቅስ፡- " 'ጌታ ሆይ፤ አንተን የማይፈራ ስምህን የማያከብርስ ማነው? አንተ ብቻ ቅዱስ ነህና፡፡ የጽድቅ ሥራህ ስለ ተገለጠ፣ ሕዝቦች ሁሉ ይመጣሉ፤ በፊትህም ይሰግዳሉ' " ራእ. 15፡ 4)**

**"አሕዛብ ተቆጥተው ነበር"** በሚል ዓይነት--በእግዚአብሔር ትሩፋን ላይ የመጨረሻውን ጦርነት ለመክፈት የሚደረገውን ዝግጅት ራእ. 11፡18 በአጭሩ ያጠቃልላል፡፡ እግዚአብሔር ንስሐ ባልገቡ ዐመጸኞች ላይ በሰባቱ መቅሰፍቶች አማካይነት በቁጣው ምላሽ የሚሰጥበት ጊዜ እነሆ አሁን ደረሰ፡፡ ራእ. 15 በዚህ መለኮታዊ ቁጣ የተሞሉ ሰባት መቅሰፍቶችን በያዙ ሰባቱ መላእክት ትዕይንት ይጀምራል፡፡ ሆኖም መቅሰፍቶቹ ከመውረዳቸው አስቀድሞ የእግዚአብሔር ታማኞች የትዕይንቱ አካል ሆነው እንመለከታለን (ራእ. 15፡1-4)፡፡ እነዚህ በአውሬውና በምስሉ ላይ ባለ ድል የሆኑ ወገኖች የብርጭቆ በሚመስል ባሕር አጥገብ ቆመው የሙሴንና የበጉን መዝሙር ይዘምሩ ነበር፡፡ ትዕይንቶቹ እስራኤላውያን እግዚአብሔር በግብፃውያን ላይ ለሰጣቸው ድል በቀይ በሕር ዳርቻ ተሰብስበው የነበራቸውን የደስታና የፍስሐ ጊዜ የሚያስታውስ ዓይነት ነበር (ዘፀ. 15)፡፡

እነዚህ ባለ ድል ቅዱሳን 144,000 በሚል በራእ. 14፡1-5 ከተጠቀሱት ወገኖች ጋር አንድ ዓይነት ናቸው፡፡ የአውሬውን ምልክት ለመቀበል አሻፈረኝ በማለታቸው አውዳሚ ውጤት ካላቸው ሰባት መቅሰፍቶች ተጠብቀው ማለፍ ችለዋል፡፡ የሱስ በኃይልና በክብር ሲገለጥ (1ተሰ. 4፡17) አንቀላፍተው የነበሩ ጻድቃን የማይበሰብሰውን አካል ለብሰው ሲነሱ፣ እነሱም የማይጠፋውን በመልበስ ይለወጣሉ (1ቆሮ. 15፡51-54)፡፡

**እሁድ** *መጋቢት 1*

# የሰባቱ የመጨረሻ መቅሰፍቶች ፍቺ

በዚህ ወቅት ሰዎች በግል ምርጫና ውሳኔአቸው መሰረት በእግዚአብሔር ወይም በባቢሎን በኩል ቆመዋል፡፡ አሁን ክርስቶስ ዳግም ሊገለጥ ዝግጅቱን ጨርሶአል። ሆኖም ከዚያ አስቀድሞ በመላእክት ተይዘው የነበሩት (ራእ. 7፡1-3) አውዳሚ ነፋሳት አሁን ይለቀቃሉ፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 15፡1፣ ራእ. 7፡1-3፣ ራእ፣ 14፡9-10፡፡ በግብፃውያን ላይ የወረዱት መቅሰፍቶች ከዓላማና ትርጉማቸው አኳያ ለእነዚህኞቹ እንደ መነሻ መታየት ይችላሉ?

---

---

ሰባቱ የመጨረሻ መቅሰፍቶች ከሰባቱ የመለከት ድምፅ መቅሰፍቶች በኋላ ስለሚመጡ “የመጨረሻዎቹ” በሚል ይታወቃሉ፡፡ መለከቶቹ መላውን የክርስትና ዘመናት አጠቃልለው የሚሸፍኑ ሲሆን የያዙት ዓላማና ጽንሰ ሃሳብም ውሱን ነው። በሥራ ላይ እንዲውሉ የሆኑት ወንጌል እየተሰበከና (ራእ. 10፡8፣ 11፡14) የማማለድ ሥራም እየተሠራ ባለበት ወቅት ነው (ራእ. 8፡2-5)፡፡ ከምኅረት ጋር የተቀላቀሉ በመሆናቸው ዓላማቸው ለእግዚአብሔር ጠላት የሆኑ ሕዝቦችን ወደ ንስሐ ማምጣት ነው፡፡

በሌላ በኩል የመጨረሻዎቹ ሰባት መቅሰፍቶች የሚወርዱት ከዳግም ምጽአቱ ጥቂት ጊዜያት ብቻ ቀደም ብለው ይሆናል፡፡ አንዳንዶቹ ዓለማቀፋዊ ስርጭት ስለሚኖራቸው ምድርን በሙሉ ይመታሉ፡፡ ልቦቻቸውን እንደ ፈርዖን አደንድነው ወደ ንስሐ ለመምጣት አሻፈረኝ ባሉ ላይ ይወርዳሉ (ራእ. 16፡11)፡፡ የሰዎችን ምርጫ ትከትሎ መለኮታዊው ቁጣ ሲወርድ (ሮሜ 1፡26-28)፤ የጠፉትም የገዛ ምርጫቸው ያስከተለውን ውጤት ለማጨድ ይገደዳሉ፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 15፡5-8፣ ዘፀ. 40፡34-35፣ 1ነሥ. 8፡10-11፡፡ “ማንም ወደ ቤተ መቅደሱ መግባት አልቻለም” የሚለው ሃረግ ስለ መጨረሻዎቹ ሰባት መቅሰፍቶች ምን ይናገራል?

---

---

“ማንም ወደ ቤተ መቅደሱ መግባት አልቻለም” (ራእ. 15፥8) በሚል የቀረበው አገላለጽ የምኅረትን በር መዘጋት ያመለክታል፡፡ የክርስቶስ ሰማያዊ የምልጃ አገልግሎት ወደ ፍጻሜ ሲመጣ፤ ወደ ንስሐ መግቢያው ምቹ ጊዜ ያበቃና የምኅረት ደጃፍ ይዘጋል፡፡ የመጨረሻዎቹ መቅሰፍቶች ማንንም ወደ ንስሐ አያመጡም፡፡ ይልቁንም ከባቢሎን ጎን ለመቆም የመረጡትን ልብ እያደነደኑ ከቀድሞው በበለጠ እግዚአብሔርን እንዲጠሉ ይገፋፋሉ፡፡

**ከጊዜ ወደ ጊዜ እየባሰባት ያለችውን የዛሬዋን ዓለም ይመልከቱ፡፡ ዛሬ ድረስ የዘገዩት መቅሰፍቶች ስለ አምላካዊው ምኅረትና ትዕግሥት ምን ያስተምሩናል?**

## ሰኞ *መጋቢት* 2

# የመጨረሻዎቹ መቅሰፍቶች መውረድ

ክርስቶስ በሰማያዊው መቅደስ የሚሰጠውን የምልጃ አገልግሎት ሲያቋርጥ የእያንዳንዱ ግለሰብ ሁኔታ ባለበት ለዘላለም ተወስኖ ይቀራል፡፡ ወንጌልን በጥላቻ ያሽቀነጠሩ ሁሉ አምላካዊውን ቁጣ በሙላት የሚቀምሱበት እነሆ ጊዜው ደረሰ፡፡

ሰባቱ የመጨረሻ መቅሰፍቶች በግብፃውያን ላይ ወርደው የነበሩትን መቅሰፍቶች የሚያሳዩ መስታወት ናቸው (ዘፀ. 7-11)፡፡ መቅሰፍቶቹ እስራኤላውያንን ሳይነኩ በግብፃውያን ላይ ግዙፍ ጉዳት እንዳደረሱ ሁሉ፤ ከእነዚህ የመጨረሻ መቅሰፍቶች መሃል የመጀመሪያዎቹ አራቱ--እግዚአብሔርን የሚያመልኩ ወገኖችን ዘልለው ለአውሬው የሚሰግዱት ላይ ጉዳት ማድረስ ተቀዳሚ ተግባራቸው ይሆናል፡፡ በግብፅ ላይ የወረዱት መቅሰፍቶች የፈርዖንን ልበ ደንዳናነትና ግብፃውያን ያመልኳቸው የነበሩ አማልክትን ከንቱነት ገልጠው ያሳዩ ነበሩ፡፡ በተመሳሳይ የመጨረሻዎቹም መቅሰፍቶች ለአውሬው የሚሰግዱ ሕዝቦችን ልብ ይበልጥ እንዲደነድን ከማድረጉ በተጨማሪ ባቢሎን ከመለኮታዊው ፍርድ ልትከላከልላቸው የሚያስችል አቅም እንደሌላት የሚገልጥ ይሆናል፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 16፥1-11፡፡ እየሆነ ያለው ነገር ምንድን ነው? ክስተቱ የቀረበበት ትዕይንት ምን ይመስላል?

የመጀመሪያዎቹ አራት አምላካዊ ቁጣዎች ወይም መቅሰፍቶች መላውን የምድር ሕዝብ ይመታሉ፡፡ የመጀመሪያው መቅሰፍት የአውሬውን ምልክት በተቀበሉና ለምስሉም በሰገዱ ሰዎች ላይ ከፉኛ የሚያሠቃይ ቁስል እንዲወጣባቸው መንስኤ ይሆናል፡፡ ሁለተኛው እና ሦስተኛው መቅሰፍቶች ደግሞ ባሕሩን፣ ወንዞችንና ምንጮችን ወደ ደም በመቀየር ከፍተኛ ጉዳት ያደርሳሉ፡፡ የሚጠጣ ውሃ በሌለበት ሁኔታ ዐመጸኛው ሰብዓዊ ዘር መኖር አይችልም፡፡ አራተኛው መቅሰፍት በፀሐይ ላይ ጉዳት ስለሚያደርስ ሰዎች ሊቋቋሙት በማይችሉት ንዳድ ይመታሉ፡፡

በመቅሰፍቶቹ የተነሳ የሚደርሱ ከፉኛ የሚያሠቃዩ ህመሞች፤ ከዐመጻ አስተሳሰባቸው ይመለሱ ዘንድ የሰዎችን ልብ አያለሳልሱም፡፡ ይልቁንም መቅሰፍቶቹን ያወረደውን እግዚአብሔር ይሳደባሉ፣ ይራገማሉም፡፡ አንዳቸውም ቢሆኑ ወደ ንስሐ አልመጡም፡፡

አምስተኛው መቅሰፍት--ራእ. 16፡10-11 (ዘፀ. 10፡21-23) የአውሬውን ዙፋን መምታቱን መመልከት እንችላለን፡፡ እዚህ ላይ ሰይጣን የራሱን ዙፋን ለአውሬው ሰጥቶት እንደ ነበር ልብ ይሏል (ራእ. 13፡2)፡፡ አሁን ሰይጣን በኃይል የሚቀመጥበት ዙፋን ሳይቀር እነዚያን የሚወርዱ መቅሰፍቶች መቋቋም አልተቻለውም፡፡ ሰዎች ብርቱ ህመም የሚያስከትል ሥቃይ ሲደርስባቸው ባቢሎንን እንደ ጥላ ከለላ ተመልክተው ነበር፡፡ ሆኖም በእግዚአብሔር ላይ ከፉኛ በመታበያቸው እነዚያ የሚወርዱ አሰቃቂ መቅሰፍቶችም እንኳ ልቦቻቸውን መለወጥ አልቻሉም፡፡

አሳዛኝ ክስተት ደርሶ በሥቃይ ውስጥ የምንወድቅበት አጋጣሚ ሊፈጠር ቢችል እንኳ--ስለ እግዚአብሔር ፍቅር እርግጠኞች ሆነንና በእርሱ ታምነን ከጌታ ጋር ያለን ቅርበት እንደ ተጠበቀ መራመድ የምንችለው እንዴት ነው?

## ማክሰኞ — መጋቢት 3

## የኤፍራጥስ ወንዝ መድረቅ

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 16፡12፣ 17፡1፣ 15፡፡ ኤፍራጥስ የምን ተምሳሌት ነው? የኤፍራጥስ ወንዝ መድረቅ ከሰባቱ የመጨረሻ መቅሰፍቶች ዐውድ ምን ያመለክታል?

በብሉይ ኪዳን ዘመን የኤፍራጥስ ወንዝ የእስራኤል ጠላቶች ለነበሩት ባቢሎን እና አሦር ወሳኝ ጉልበት ነበር (ኢሳ. 7፡20፣ ኤር. 46፡10)፡፡ ባቢሎንን አቋርጦ የሚፈሰው የባቢሎን ወንዝ የተዘራውን የሚያጠጣና ለሕዝቡም ዋንኛ የውሃ አቅርቦት ምንጭ ሆኖ በማገልገሉ ለከተማዋ በእጅጉ መሰረታዊ ነበር፡፡

በዘመኑ መጨረሻ ላይ የምትገኘውን ባቢሎን ራእ. 17፡1 በብዙ ውሆች ላይ እንደተቀመጠች አድርጎ የሚገልጻት ምናልባት ኤፍራጥስን እንደ ማመሳከሪያ በማቅረብ ሊሆን ይችላል (ኤር. 51፡13)፡፡ የመጨረሻው ዘመኗ ባቢሎን መኖሪያዋ የሆነው ብዙ ውሃ--አቅፎና ደግፎ የያዛትን ሕዝብ፤ ይኸውም የተቋሟ ደጀን የሆነውን በዓለም ዙሪያ የሚገኝ መንግሥታዊና ፖለቲካዊ ኃይል ይወክላል፡፡ የሆነው ሆኖ እነዚህ ኃይላት ኋላ ላይ የቀድሞ ድጋፋቸውን ያቋርጣሉ፡፡ የስድስተኛው መቅሰፍት ትዕይንት የጥንታዊው ባቢሎንን በሜዶንና ፋርስ ምርኮ ስር መውደቅ ያንጸባርቃል (ዳን. 5)፡፡ እንደ የጥንቱ የታሪክ ጸሐፊ ሔሮዱተስ ዘገባ ከሆነ፡ ንጉሥ ቤልሻጽር ለሺህ መኳንንቱ ታላቅ ግብዣ ባደረገበት በዚያ የፈንጠዝያ ምሽት የፋርስ ሰዎች የኤፍራጥስ ወንዝ የሚፈስበትን ሸለቆ ይዘው ወደ ከተማዋ በመግባት ሳይታሰብ ከመዳፋቸው አስገቧት፡፡

በራእ. 16፡12 የቀረበው የተምሳሌታዊው ኤፍራጥስ ወንዝ መድረቅ በመጨረሻ ዕውን የሚሆነውን የባቢሎን ውድቀት ያስከትላል፡፡ በራእይ መጽሐፍ የቀረበው የኤፍራጥስ ወንዝ የዓለም መንግሥታትና ፖለቲካዊ ኃይላት ለባቢሎን የሚሰጡትን ድጋፍ እንደሚወክል ሁሉ፤ የወንዙ መድረቅ የድጋፋቸው መቋረጥና የተቋሟ መገርሰስ ተምሳሌት ነው፡፡ በተፈጥሮአዊው ምስቅልቅል ሥቃይ ውስጥ የወደቁት የዓለም ሕዝቦች (ራእ. 16፡10-11) ከለላ ፍለጋ ፊታቸውን ባቢሎን ላይ ያደርጋሉ፡፡ ሆኖም አምስተኛው መቅሰፍት የባቢሎንን ዙፋን እንደ መታ ሲገነዘቡ እቅዳቸው ከንቱ መሆኑን ይገነዘባሉ፡፡ በባቢሎን መታለላቸው የተሰማቸው እነዚህ ሕዝቦች በእርሷ ላይ ይነሱባታል (ራእ. 17፡16)፡፡ ይህም ቢሆን ቀደም ብለን እንደ ተመለከትነው ልባቸው በእግዚአብሔር ላይ እንደ ደነደነ ይቀራል፡፡ ይህ ሁኔታ ዓለምን ከእግዚአብሔር ጋር ለፍልሚያ ለሚያነሳሳው ለመጨረሻው የሰይጣን ማታለያ ምቹ አድርጎ ያዘጋጃቸዋል፡፡

***መታመናችንን በሰዎችና በሰብዓዊ ተቋማት ላይ ማድረጋችን ምን ያህል አደጋ እንዳለው አስመልክቶ ያገኙት ትምህርት ምን ይመስላል?***

## ረቡዕ **መጋቢት 4**

# ታላቁና የመጨረሻው የሰይጣን ማሳቻ

የኤፍራጥስን ወንዝ የደረቀበት ምክንያት "ከምሥራቅ ለሚመጡ ነገሥታት መንገድ እንዲዘጋጅላቸው" መሆኑን ራእ. 16፡12 ይነግረናል፡፡ በብሉይ ኪዳን "የምሥራቅ ነገሥታት" ከምሥራቅ በኩል በባቢሎን ላይ የሚመጡ የቂሮስና የእርሱ ኃይሎች ናቸው (ኢሳ. 41፡25)፡፡ የእነርሱ ባቢሎንን በቁጥጥር ስር ማዋል የእግዚአብሔር ሕዝቦች ወደ ትውልድ አገራቸው እንዲገቡ አስችሎአቸዋል (ኢሳ. 44፡27-28)፡፡ በተመሳሳይ የተምሳሌታዊው ኤፍራጥስ ወንዝ መድረቅ የእግዚአብሔርን የመጨረሻ ዘመን ሕዝቦች ለመታደግ ከምሥራቅ ለሚመጡ ነገሥታት መንገዱን የሚጠርግ ይሆናል፡፡

በራእ. 16፡12 የቀረቡት ከምሥራቅ የሚመጡ ነገሥታት፤ ክርስቶስ እና የእርሱ ታማኝ ሰራዊት ናቸው፡፡ የሱስ በሰማይ መላእክት ታጅቦ ዳግም በሚገለጥበት ጊዜ የመጨረሻው ውጊያ በክርስቶስ ታማኝ ትሩፋንና በሰይጣን መካከል እንደሚደረግ ራእ. 17፡14 ያሳየናል፡፡ በራእ. 19፡14 እንደ ቀረበው የበጉ ልብስ የሆነውን (ራእ. 19፡8) "ነጭ፣ ንጹህና ከተልባ እግር የተሠራ ቀጭን ልብስ" የለበሱ የሰማይ ሰራዊትን የሱስ ይመራል፡፡ በራእ. 7 በተጓዳኝ በምድር የሚገኘው 144,000 ሰራዊት ለመጨረሻው ውጊያ መዘጋጀቱ ተመልክቶአል፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 16፡13-14፡፡ ለመጨረሻው ውጊያ በሚደረገው ዝግጅት የሦስቱ እንቁራሪት መሳይ እርኩሳን መናፍስት ሚና ምንድን ነው? በራእ. 14 ለቀረበው የሦስቱ መልእክት መለእክት ሐሳዊ የአጻፋ ምላሽ የሚሆኑት እንዴት ነው?

የኤፍራጥስ መድረቅ በሰይጣናዊው ሦስትዮሽ አካል ላይ መናወጥ ይፈጥራል። በዚህ ወቅት እንቁራሪት የሚመስሉ ሦስት እርኩሳን መናፍስት ከአፉ እንደ ወጡ ዮሐንስ ተመልክቶአል፡፡ በግብፃውያን ላይ ወርደው በነበሩት መቅሰፍቶች፤ እንቁራሪት የፈርዖን አስማተኞች አስመስለው ማድረግ የቻሉት የመጨረሻው ሙከራቸው ነበር (ዘፀ. 8፡1-15)፡፡ በተመሳሳይ እነዚህ ሦስት እርኩሳን መናፍስት ሰይጣን የእግዚአብሔርን ሥራ አስመስሎ የሚሠራበት መጨረሻ ሙከራው ይሆናል፡፡

ከሰይጣናዊው ሦስትዮሽ አካላት "አፍ" የሚወጡት ሦስቱ እርኩሳን መናፍስት የሰይጣንን የመጨረሻ ስልት ይወክላል፡፡ ሰይጣን የሙታን መንፈስ እንጠራለን የሚሉን አካትቶ ማንኛውንም ትኩረት በግ ወደሚመስለው አውሬ (ራእ. 13፥13-14) የሚስብ ታምራዊ ምልክቶችን እንዲያደርጉ ያስችላቸዋል፡፡ ዓለም በእውነተኛው አምላክ ምትክ እርሱን እንዲያምንና እንዲከተል ከሚጠቀማቸው የመጨረሻው ዘመን ስልቶች አንዱ ታምራዊ ምልክቶች ይሆናሉ (2ተሰ. 2፥9-12)፡፡

እንቁራሪት የሚመስሉት እርኩሳን መናፍስት የተላኩት ከሐሰተኛው ወንጌል ሲሆን ይኸውም በእግዚአብሔር ላይ ለሚደረገው ውጊያ ዓለምን ለማነሳሳት ነው፡፡ ምንም እንኳ ሁኔታው የዓለም መሪዎችን ተስፋ አስቆራጭ ሁናቴ ውስጥ ቢከትም ነገር ግን ለእግዚአብሔር ሕዝቦች ጀርባቸውን ሰጥተው ከሰይጣን ጋር ግንባር ይፈጥራሉ፡፡ በዚህ ወቅት ይህንን ምድር ወደ ፍጻሜ ለሚያመጣው የመጨረሻው የአርማጌዶን ጦርነት መድረኩ ይመቻቻል፡፡

## ሐሙስ　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　መጋቢት 5

## ለመጨረሻው ጦርነት መሰብሰብ

ጥቅሱን ያንብቡ፡ ራእ. 16፥16፡፡ ሰይጣን የዓለምን ሕዝቦች አስቶ ለውጊያ በአርማጌዶን በመሰብሰቡ ምን ያህል ውጤታማ ይሆናል?

---

---

አሳቾቹ የክፉ መናፍስት ታምራቶች ዓለማቀፋዊ ስኬት ያስገኛሉ፡፡ ሰዎች እውነተኛውን ወንጌል እየጠሉ በሐሰተኛ ታምራቶች የተደገፈውን ሸንገላ ያምናሉ። በዕብራውያን ቋንቋ አርማጌዶን ወይም የመጊዶ ተራራ በመባል በሚታወቀው ተምሳሌታዊ ስፍራ በአንድነት ይሰበሰባሉ፡፡ በኢይዝራኤል ሸለቆ በቀርሜሎስ ተራራ ግርጌ ጉብታ ላይ ይገኝ የነበረው የምሽግ ከተማ--መጊዶ አካባቢውን ለመቆጣጠር የሚያስችል ገዢ ስፍራ ነበር፡፡ በእስራኤላውያን ታሪክ ይህ ስፍራ አያሌ ወሳኝ ውጊያዎች ተካሂደውበታል (መሳ. 5፥19፣ 6፥33፣ 2ነገሥ. 9፥27፣ 23፥29-30)

የራእይ መጽሐፍ አርማጌዶን በመባል የሚታወቀውን ይህን በእግዚአብሔርና በክፉ ኃይላት መካከል የሚደረገውን የመጨረሻ ታላቅ ፍልሚያ ለማሳየት ይህን ጭብጥ ጥቅም ላይ ሲያውል ይስተዋላል፡፡ የዓለም ሕዝብ በሰይጣን ሕብረት መሪነት ስር ውህደት የፈጠረ ሰራዊት ሆኖ ቀርቦአል፡፡

ቀርሜሎስ ተራራ የሚል አንደምታ ሊኖረው የሚችለው መጊዶ ተራራ መገኛ ከከተማዋ አጠገብ ነበር፡፡ ስፍራው የነቢዩ ኤልያስንና ስንና በዓልን ተግዳሮት ጨምሮ (1ነገሥ. 18) በእሰራኤል ታሪክ እጅግ ወሳኝ ውጊያዎች ከተካሄዱባቸው ዐውደ ግንባሮች አንዱ ነበር፡፡ እዚህ ላይ ጉዳዩ የሚያጠነጥነው በእውነተኛው አምላክ ማንነት ጥያቄ ዙሪያ መሆኑ እሙን ነው፡፡ ከሰማይ የወረደው እሳት ጌታ ብቸኛው እውነተኛ አምላክ መሆኑንና እርሱ ብቻ በብቸኝነት መመለክ እንዳለበት ያሳየ ነበር፡፡ ከምድር የወጣው አውሬ የእግዚአብሔርን ሥራ አስመስሎ እሳት ከሰማይ በማውረድ መላውን የዓለም ሕዝብ እንደሚያስት ራእ.13፡13-14 ግልጽ አድርጎ ያስቀምጥልናል፡፡

አርማጌዶን በአንድ የሆነ የመካከለኛው ምሥራቅ ግምባር የሚደረግ ወታደራዊ ውጊያ ሳይሆን በክርስቶስና በጨለማ ኃይላት መካከል ተግባራዊ የሚሆን መንፈሳዊ ውጊያ ነው (2ቆሮ. 10፡4)፡፡ በዚህ የመጨረሻ ውጊያ በዩኒቨርስ ሕጋዊ ገዢነት ዙሪያ የሚነሳው ጥያቄ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መፍትሔ ያገኛል፡፡ የመጨረሻውን ውጊያ ተከትሎ የሚመጣው ውጤት በቀርሜሎስ እንደሆነው--ውሎ አድሮ እግዚአብሔር በጨለማ ኃይላት ላይ አሸናፊነቱ የሚረጋገጥበት ይሆናል፡፡

ብዙዎች በመካከለኛው ምስራቅ የሚስተዋለውን የማያባራ ፖለቲካዊና ወታደራዊ ውጥንቅጥ የመጨረሻው ብሎም የአርማጌዶን ፍጻሜ ምልክት አድርገው ሲመለከቱ ይታያል፡፡ ምንም እንኳ በአርማጌዶን ዙሪያ ብዛት ያላቸው ትንቢቶች ቢነገሩም፣ ቀናት ቢቆረጡም ነገር ግን አንዱም አልሰመረም፡፡ እንደነዚህ ዓይነቶቹን አንድን አካባቢ ያማከሉ ክስተቶች እንደ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትንቢት ፍጻሜ አድርጎ ፍቺ ከመስጠት ተመሳሳይ ስህተት እንዴት መጠበቅ እንችላለን?

## አርብ　　　　　　　　　　　　　　　　　　　መጋቢት 6

ተጨማሪ ሀሳብ፡ “አስደናቂ ታምራቶችን በሚያደርጉ ክፉ መናፍስት ፈታዉራሪነት አውራሪነት ልዕለ ተፈጥሮ ባህሪ ያላቸው አስፈሪ ክስተቶች በቅርቡ በሰማያት ይገለጣሉ፡፡ የዲያብሎስ መናፍስት በአሳች ማማለያ ሊተበትቧቸው ወደ ምድር ነገሥታት ብሎም መላው የዓለም ሕዝብ በማምራት፤ ሰይጣን በሰማይ መንግሥት ላይ ለሚያደርገው የመጨረሻ ትንቅንቅ ከእርሱ ጋር እንዲያብሩ ይገፋፏቸዋል። ገዢዎችም ሆኑ ተገዢዎች በእነዚህ ወኪሎች ተመሳሳይ መታለልው ውስጥ ይወድቃሉ. . .

“ታላቁ ሕዝቦችን የማሳት ድራማ የመጨረሻው ከፍታ ሰይጣን ክርስቶስን ተመስሎ መምጣቱ ይሆናል፡፡ ቤተ ክርስቲያን የተስፋዋ ፍጻሜ የሆነውን የአዳኙን ዳግም ምጽአት ለረጅም ዘመናት ስትጠባበቅ ኖራለች፡፡ አሁን ታላቁ አሳች ክርስቶስ ዳግም እንደ ተገለጠ አድርጎ ምድራዊ ድራማውን ያቀናብራል፡፡ ሰይጣን በዮሐንስ ራእይ በቀረበው የእግዚአብሔር ልጅ መግለጫ መሰረት በድምቀት የሚያበራ የፀሐይ ገጽታን ተላብሶ በተለያዩ የምድር ክፍሎች ይገለጣል፡፡ ዙሪያውን የሚከብበው ክብርና ውበት ሟቹ ሰብዓዊ ዐይን ከተመለከተው ሁሉ በእጅጉ የላቀ ይሆናል፡፡ የሰማዩ አድማስ “እነሆ ክርስቶስ መጣ! ክርስቶስ መጣ!” በሚል በድል አድራጊነት የተሞላ እልልታ ዳር እስከ ዳር ያስተጋባል፡፡ ሰዎች ለእርሱ አክብሮት በመስጠት ከፊቱ ይነጠፋሉ. . . በተረጋጋና ርኅራኄ በተሞላው ድምፀት አዳኙ ተናግሮአቸው የነበሩ ደርባባ ሰማያዊ እውነቶችን ይናገራል፡፡ የታመሙትን ይፈውሳል፣ እንዲሁም የክርስቶስን ባህሪ የተላበሰ በሚመስል ሁኔታ ሰባተኛውን ቀን ሰንበት ወደ እሁድ መለወጡን ይናገራል፡፡ እርሱ የባረከውን ይህን ቀን ሰው ሁሉ እንዲቀድሰውም ያዛል፡፡ ሰባተኛውን የሰንበት ቀን በቅድስና በመጠበቅ የሚጸኑ በብርሃንና በእውነት ወደ እነርሱ የተላኩ መላእክቱን ለመስማት በመቃወም የእርሱን ስም እንደሚሳደቡ ይፋ ያደርጋል፡፡ ይህ እጅግ የበረታና በብርቱ ኃይል አእምሮን መቆጣጠር የሚችል ማታለያ ነው፡፡”—Ellen G. White, The Great Controversy, p. 624.

# የመወያያ ጥያቄዎች፥

**1.የሱስ ለአርማጌዶን ውጊያ ስለሚደረግ ዝግጅት በራእ. 16፡15 የተናገረውን ማስጠንቀቂያ ያንብቡ፡፡ ክርስቶስ ቀደም ሲል ለሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን የሰጠውን ተማጽኖ በጥንቃቄ ይመልከቱ (ራእ. 3፡18)፡፡ ለመጨረሻው ውጊያ ዝግጅት በሚደረግበት ወቅት ለሚኖሩ ማለትም ለሎዶቅያ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ይህ መልእክት ያለው አንደምታ እንዴት ይታያል? መልእክቱ ከእርስዎ የግል ሁኔታ ጋር መገናዘብ የሚችለው እንዴት ነው?**

**2.በራእይ መጽሐፍ ነጭ ልብስ የክርስቶስን ጽድቅ ያመለክታል (ራእ. 3፡4-5፣ 19፡7-9)፡፡ በመጨረሻው አሰቃቂ ወቅት ጸንተው መቆም የሚችሉ የክርስቶስን ጽድቅ የሚለብሱ ብቻ ይሆናሉ፡፡ አንድ ሰው በበጉ ደም ልብሱን ማንጻት የሚችለው እንዴት ነው (ራእ. 7፡14)?**

# 12ኛ ትምህርት

ከመጋቢት 7 -13

# በባቢሎን ላይ የተሰጠ ፍርድ

ሰንበት ከሰዓት

ለዚህ ሣምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ራእ. 17:1–18 ኤር. 51:13፣ ራእ. 13:1–10፣ ዘጸ. 28:2:20–23፣ 13:5–8፡፡

**መታሰቢያ ጥቅስ**፡ - *"ከዚያም ከሰማይ ሌላ ድምፅ እንዲህ ሲል ሰማሁ፤ 'ሕዝቤ ሆይ፤ በኃጢአቷ እንዳትተባበሩ፣ ከመቅሠፍቷም እንዳትካፈሉ፣ ከእርሷ ውጡ፤ ኀጢአቷ እስከ ሰማይ ድረስ ተከምሮአልና፤ እግዚአብሔርም ዐመፃዋን አስታውሶአል፡፡"* (ራእ. 18፡4-5)፡፡

የስድስተኛው መቅሰፍት መውረድ ተምሳሌታዊው የኤፍራጥስ ወንዝ እንዲደርቅ መንስዔ መሆኑን ተመልክተናል፡፡ በዚህም እንዳሰቡት ያልተሳካላቸው የዓለም ሕዝቦች ለመጨረሻዋ ዘመን ባቢሎን ይሰጡ የነበረውን ድጋፍ ያቋርጣሉ፡፡ የሆነው ሆኖ ውድቀቷ የእግዚአብሔርን ሥራ አስመስለው በሚሠሩ ርኩሳን መናፍስት መጠን የለሽ እንቅስቃሴ የታጀበ ይሆናል፡፡ ታምራዊ ምልክቶችን ያደርጋሉ--ምናልባትም የሐሰተኛ ኀይማኖት የማንቂያ ደወል የሆነውን እሳት ከሰማይ ሳይቀር ያወርዳሉ (ራእ. 13፡13)፡፡ መላውን ዓለም አንድ አድርጎ በእግዚአብሔር ታማኝ ትሩፋን ላይ ለሚከፈተው የአርማጌዶን ጦርነት በማዘጋጀቱ ረገድ ርኩሳን መናፍስት ስኬታማ ይሆናሉ፡፡

በጥቃቱ መጀመሪያ የሰባተኛው መቅሰፍት አካል የሆነ ታላቅ የመሬት መናወጥ ይከሰታል፡፡ የመሬት መናወጡ በባቢሎንና በርኩሳን መናፍስት መሃል የነበረውን አንድነት ብትንትኑን አውጥቶ ለሦስት ይሰነጥቀዋል (ራእ. 16፡18-19)፡፡ የከተማ ቅርጽ ይዛ የቀረበችው የመጨረሻዋ ዘመን ባቢሎን የእግዚአብሔርን ሕዝቦች በመቃወም ከዓለም ኃይማኖታዊ ኀይላት ጋር ባላት ሕብረት ለአጭር ጊዜ ብቻ የሚዘልቀውን የዘንዶውን፣ ከባሕር የወጣውን አውሬና ከምድር የወጣውን አውሬ ሰይጣናዊ ኅብረት ታመለክታለች፡፡ የመጨረሻ ዘመኗ ባቢሎን መፈረካከሷን ተከትሎ ይህ ሕብረት እንኩትኩቱ ይወጣል፡፡ እዚህ ላይ የመጨረሻ ዘመኗ ባቢሎን መፈረካከሷን የሚያውጀው ራእ. 16፡19 ብቻ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡ ምዕ. 17 እና 18 ደግሞ ይህ

ውድቀት እንዴት ገቢራዊ እንደሚሆን ይነግረናል፡፡ ጥቅሶቹ (ራእ. 17፡12-18፡24) የመጨረሻ ዘመኗ ባቢሎንን ውድቀትና የውድቀቷን መንስዔ ከማብራራታቸው አስቀድሞ--ይህች ክህደት የፈጸመች ተቋም በጉያዋ ካቀፈቻቸው መሰል ተቋማት ጋር ባላት ኅብረት በአውሬው ላይ ተቀምጣ መላው ዓለም በእግዚአብሔር ላይ እንዲነሳ ታደርጋለች (ራእ. 17፡1-11)፡፡

## እሁድ                                                                መጋቢት 8

## አመንዝራዋ ባቢሎን

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 17፡1፡፡ ባቢሎን የተቀመጠችበት "ብዙ ውሃ" የኤፍራጥስ ወንዝ መሆኑን ኤር. 51፡13 ያሳየናል፡፡ ብዙ ውሃ በራእ. 17፡15 መሰረት ምን ያመለክታል?

---

---

በመጽሐፍ ቅዱስ ሴት የእግዚአብሔርን ሕዝቦች ትወክላለች፡፡ በራእይ መጽሐፍ የእግዚአብሔር እውነተኛ ቤተ ክርስቲያን በንጽህት ሴት ተመስላ ቀርባለች (ራእ. 12፡ 1፣ 22፡17)፡፡ በተቃራኒው አመንዝራዋ ሴት ክህደት የፈጸሙትን እና ታማኝ ያልሆኑትን ሕዝቦች ትወክላለች፡፡ ይህች አመንዝራ ሴት በራእ. 17፡5 ታላቂቷ ባቢሎን በሚል ስያሜ ትታወቃለች፡፡ የጥንታዊቷ ባቢሎን ህልውና የቆመው በኤፍራጥስ ወንዝ ላይ እንደነበር ሁሉ የመጨረሻ ዘመኗም ባቢሎን እቅዷን ለመተግበር የምትተማመነው በብዙሃኑ ላይ ይሆናል፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 17፡2፣ 14፡8፣ 18፡2-3፡፡ ከመጨረሻ ዘመኗ ባቢሎን ጋር ሕገ ወጥ ግንኙነት ውስጥ የገቡና በሐሰተኛ ሽንገላዋ ስር የወደቁ በሁለት ቡድን የቀረቡ ሕዝቦች እነማን ናቸው?

---

---

የመጀመሪያው ቡድን ሕዝብን የመግዛትና የማስተዳደር ሥልጣን ያላቸው የፖለቲካ ኀይላት ሲሆኑ እነርሱም የምድር ነገሥታት በሚል ቀርበዋል፡፡ ይህ ቡድን ከአመንዝራዋ ባቢሎን ጋር አብሮ እንዳመነዘረ ሆኖ ቀርቦአል፡፡ በብሉይ ኪዳን--ጣዖቶቿን ተከትላ በእግዚአብሔር ላይ ክህደት የፈጸመችውን እስራኤል ለማመልከት ምንዝር የተሰኘው ቃል በተደጋጋሚ ጥቅም ላይ ውሎአል (ኢሳ. 1፡21፣

ኤር. 3፡1-10)፡፡ በምድር ነገሥታትና በአመንዝራዋ መካከል የቀረበው የምንዝር ግንኙነት በመጨረሻ ዘመኗ ባቢሎን እና በገዢዎቹ የፖለቲካ ኃይላት መካከል የሚከሰተው ያልተገባ ሕብረት ተምሳሌት ነው፡፡

ከአመንዝራዋ ባቢሎን ጋር ሕገ ወጥ ግንኙነት ውስጥ የሚገባው ሁለተኛው ቡድን--ተገዢው ማለትም ብዙሃኑ የምድር ነዋሪ ይሆናል፡፡ እነዚህ--ከመንፈሳዊው የባቢሎን ምንዝር ወይን ጠጅ እንዲጠጡ የሆኑ ናቸው፡፡ በሥልጣን ላይ ካሉት የፖለቲካ ኃይላት በተጓዳኝ፤ ባቢሎን ጥላ ከለላ ትሆነናለች ብሎ በስህተት ያሰበው አብላጫው ሕዝብ በተቋሟ አሳች አስተምህሮና ልማድ ይሰክራል፡፡ ሰው ሲሰክር በአልኮል ተጽእኖ ስር ስለሚወድቅ በአግባቡ ማሰብ ይሳናቸዋል (ኢሳ. 28፡7)፡፡ ከእግዚአብሔር ታማኝ ትሩፋን ውጪ የተቀረው ዓለም በተሳሳተ መንገድ ይመራል፡፡

***በቀደሙት ጊዜያት እንዲሁም ዛሬ እየሆነ እንዳለው በመጨረሻውም ጊዜ አብላጫው ሕዝብ በተሳሳተ አቅጣጫ ያመራል፡፡ ይህ በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት ያላቸውን ዝነኛ አመለካከቶች ተከትሎ መንጎድ ስለሚያስከትለው አደገኛ ውጤት ምን ሊነግረን ይገባል?***

**ሰኞ** *መጋቢት 9*

## በአውሬው ላይ የተቀመጠችው አመንዝራ ሴት

ጥቅሱን ያንብቡ፡ ራእ. 17፡3፡፡ አመንዝራዋ ሴት በብዙ ውሃ ላይ መቀመጧን የሚነግረን ዮሐንስ በአውሬው ላይ መቀመጧንም ይገልጽልናል፡፡ የውሃ እና አውሬ ተምሳሌት የባቢሎንን ደጋፊዎች ጥሩ አድርጎ የሚገልጸው እንዴት ነው?

---

---

ዮሐንስ በራእይ ወደ በረሃ ከተወሰደ በኋላ በውሃዎች ሳይሆን በቀይ አውሬ ላይ የተቀመጠች ሴት እንዲመለከት ይደረጋል፡፡ አመንዝራነቷ ኃይማኖታዊውን አካል ሲወክል አውሬው ደግሞ የፖለቲካዊው ሥልጣን ተምሳሌት ነው፡፡ ኃይማኖታዊው ኅይል እምነት ዐልባውንና የፖለቲካዊውን ኃይል መጋለቡን የሚያሳየው ትዕይንት፤ በቀደሙት ዘመናት ኃይማኖትና ፖለቲካ ጋብቻ ሲፈጥሩ ያልታየ ክስተት ነው። ትንቢቱ እንደሚያሳየን ከሆነ በመጨረሻ ላይ እነዚህ ሁለቱ ሕብረት ይፈጥራሉ። አውሬን የመጋለብ ጽንሰ ሃሳብ--የበላይነትን ያሳያል፡፡ ይህ ደግሞ በመጨረሻው

ጊዜ እምነት ዐልባውና የፖለቲካው ዓለም በኃይማኖታዊ ሥርዓት ተጽእኖ ስር እንደሚውሉ ያሳያል፡፡

በራእ. 12 እና 13 ከቀረቡት ከባሕር ከወጣው አውሬ እና ከምድር ከወጣው አውሬ የትኛው ባህሪ ወደ ዘንዶው ያመላክታል?

ሐምራዊ ቀይ ልብስ በመጎጸናፍ፣ በወርቅ፣ በከበሩ ድንጋዮችና በዕንቁዎች በማጌጥ ተሽሞንሙና የቀረበችው የዚህች አመንዝራ ሴት ሁኔታ፤ በጥንት ዘመን ሴተኛ አዳሪዎች የሰዉን ልብ ለማማለል ይጠቀሙበት የነበረ ዓይነተኛ ዘዴ ነው (ኤር. 4፡ 30)፡፡ የተጎናጸፈችው ልብስ የደም ዓይነት ቅላት፤ ያዚህን ኃይማኖታዊ ሥርዓት ጨቋኝ ባህሪ ያመለክታል፡፡

በተጨማሪ አመንዝራዋ የለበሰችው ልብስ በብሉይ ኪዳን--ከሐምራዊ፣ ቀይ ማግ እና ወርቃማ የሊቀ ካህናቱ ልብሰ ተክኅኖ አንዱን ያመለክታል (ዘፀ. 28፡5-6)፡፡ እንዲሁም በማኅተም ተቀርጾ በካኅኑ ግምባር በጥምጣም ከሚታሰረው “ቅድስና ለእግዚአብሔር” ከሚለው በተመሳሳይ በእርሷም ግምባር ላይ የምስጢር ሥም ተጽፎ ነበር፡፡ በእጇ የያዘችው ጽዋ በመቅደሱ በግልባጭ የቀረበ የመጠጥ መሥዋዕት ነው (ዘፀ. 30፡9)፡፡ ይህ የመጨረሻው ዘመን ኃይማኖታዊ ሥርዓት በዚያው ታሪካዊ አቋሙ ጸንቶ ዓለምን እያማለለ ከአምላካዊው መንገድ በማሳት የሰይጣን ብርቱ መሣሪያ ይሆናል፡፡ ኃይማኖታዊ ተቋሟ የቱንም ዓይነት ውጪያዊ ገጽታ ልትላበስ ብትችልም፤ ነገር ግን አመንዝራና የአመንዝራዎች እናት ናት፡፡

ከዚህ ባለፈ አመንዝራዋ ሴት በቅዱሳን እና ለክርስቶስ ምስክር በመሆናቸው በተሰዉ የየሱስ ሰማዕታት ደም የሰከረች ሆና ተገልጣለች፡፡ ይህ ደግሞ የመጨረሻዋን ዘመን ባቢሎን በመካከለኛው ዘመን በጳጳሳዊው ሥርዓት ይመራ የነበረውንና ለወንጌል ታማኝ ሆነው በመጽናታቸው ሰማዕት በሆኑ በሚሊዮን በሚቆጠሩ የምዕራብ አውሮፓ ክርስቲያኖች ላይ ከተፈጸመው የክህደት ሁኔታ ጋር ያስተሳስራታል፡፡

**ክህደት የፈጸመችው አመንዝራዋ ባቢሎን የተገለጠችበት መንገድ በትያጥሮን ቤተ ክርስቲያን የቀረበችውን ኤልዛቤል ያንጸባርቃል (ራእ. 2፡ 20-23)፡፡ በእነዚህ ሁለት ሴቶች መካከል የቀረበው መመሳሰል የዘመን መጨረሻዋን ባቢሎን ባህሪ እንዴት ያብራራል?**

ማክሰኞ                                                                 መጋቢት 10

# የአውሬው መለያ ባህሪ

የዮሐንስ በራእ. 17፡6-7 በተመለከታት አመንዝራ ሴት በእጅጉ ተደንቆአል፡፡ ምናልባት የተደነቀበት ምክንያት አንዳንድ ባህሪዎቿ ቅዱሳንን እንዲዋጋና ድል እንዲነሳ (ራእ. 13፡5-7) ኃይል ከተሰጠው ከራእ. 13ቱ ከባሕር የወጣው አውሬ ጋር ካለው መመሳሰል አኳያ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ኃይል ሴቲቱ ለ1200 ዓመታት (መካከለኛው ዘመን) ወደ በረሓ እንድትሰደድ መንስዔ ሆኗታል፡፡ ፕሮቴስታንቶች ያለፈውን አስከፊ የስደት ዘመን በማስታወስ በክርስትና ድርጅቶች መሃል የተሻለ መግባባትና የቀረበ ትብብር ሊኖር ይገባል ለሚለው ለዚህ ዘመኑ ኃይማኖታዊ ፍልስፍና የተሻለ ለመሥራት የሚያስችላቸውን ዕድል ሊጠቀሙ ይገባል፡፡ ምክንያቱም ትንቢቱ እንደሚናገረው ከሆነ፤ ካለፈው ጋር የሚመሳሰል ግን የከፋ ሁኔታ ዳግም መከሰቱ አይቀሬ ነው፡፡

ጥቅሱን ያንብቡ፡ ራእ. 17፡8፡፡ የዚህን ጥቅስ የቃላት አገባብ ከራእ. 13፡8 ጋር ያስተያዩ፡፡ ራእ. 13፡3 የአውሬውን የሕልውና እና እንቅስቃሴ ሦስት ምዕራፎች እንዴት ያብራራቸዋል?

---

---

ቀዩ አውሬ--ቀደም ሲል የነበረ፣ አሁን ግን የሌለ፣ በኋላ ከጥልቁ ጉድጓድ የሚወጣና ወደ ጥፋት የሚሄድ በሚል ተገልጾአል፡፡ ሲጀመር ይህ ሦስት የለውጥ ምዕራፍ--የሚንቀሳቀሰው በሐሰተኛ መለኮታዊ ስያሜ ነው--"ካለው፣ ከነበረውና ከሚመጣው" (ራእ. 1፡4፣ 4፡8)፡፡ በተጨማሪ አውሬው ያለፈባቸውን የሚከተሉትን ሦስት ምዕራፎች ያመላክታል፡

(1)አውሬው ቀደም ሲል "ነበረ"፡፡ ይህ ቃል አውሬው በትንቢታዊዎቹ 1,260 ቀናት የነበረውን እንቅስቃሴ ይጠቁማል (ራእ. 13፡5)፡፡

(2)"የሌለ፡፡" አውሬው በገጠመው ለሞት የሚያደርስ ቁስል (ራእ. 13፡3) ወደ የሌለ ሁናቴ ውስጥ ለመግባት ተገደደ (1798)፡፡ ለተወሰኑ ጊዜያቶች ከዓለም ዕይታ ቢሰወርም--ተርፎ ማንሰራራት ችሎአል፡፡

(3)በመጨረሻ ለሞት ያደርሰው ከነበረው ቁስል መፈወሱን ተከትሎ፤ አውሬው በሙሉ ሰይጣናዊ ቁጣ ወደ ህይወት ይመለሳል፡፡

በራእ. 13፥1-8 የቀረበው አውሬው ከቁስሉ በተፈወሰበት ወቅት ያለውን ሁናቴ ራእ. ምዕ. 17 ይገልጸዋል፡፡ እንዲሁም አመንዝራዋ ባቢሎን በዚህ በዳነው አውሬ ላይ ተቀምጣበታለች፡፡

በመካከለኛው ዘመን እንደሆነው ሁሉ አሁንም በኃይማኖትና በፖለቲካ መሃል ለአጭር ጊዜ የሚዘልቅ ሕብረት ይፈጠራል፡፡ ከዚያም ስደት ዳግም ያገረሻል፡፡

"ተቃውሞ ቢነሳ፣ አክራሪነትና አለመቻቻል ቢያገረሽ፣ ስደት ዳግም ቢቀጣጠል፣ በግማሽ ልብ ያሉ ቢዋልሉም--እውነተኛ ክርስቲያን ግን ከብልጽግናዎቹ ዘመናት ይልቅ በዚህ ወቅት እንደ ዐለት ጸንቶ ይቆማል፣ እምነቱ የበረታ፣ ተስፋውም ያበራ ይሆናል፡፡"—Ellen G. White, The Great Controversy, p. 602.

***የመጨረሻዎቹ አስፈሪ ክስተቶች ተግባራዊ ከመሆናቸው አስቀድሞ የዛሬው የክርስትና ተሞክሮአችን ምን ሊመስል እንደሚገባ ከዚህ መልእክት ልንወስድ የሚገባው ማስጠንቀቂያ ምንድን ነው?***

## ረቡዕ                                                              *መጋቢት 11*

## ሰባቱ የአውሬው ራሶች

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 17፥9-11፣ ራእ. 13፥18፡፡ ሰባቱን ራሶች ለማስተዋል ጥበብ ያለው አእምሮ ይጠይቃል፡፡ እዚህ ላይ የቀረበው ጥበብ ምን ዓይነት ነው? ለመሆኑ አንድ ሰው ይህን በመለኮት የሚሰጥ ጥበብ ማግኘት የሚችለው እንዴት ነው (ያዕ. 1፥5)?

---

---

ሰባቱ ራሶች ሰባት ተራሮች መሆናቸውን መልአኩ ሲገልጽ ይታያል፡፡ አንዳንድ ተርጓሚዎች እነዚህ ሰባት ተራሮች የሮም ከተማ የምትገኝባቸው ሰባት ኮረብታዎች እንደሆኑ ያስባሉ፡፡ በዚህ የተነሳ በግርክኛው oroi ወይም ተራሮች የሚለውን ቃል ኮረብቶች ብለው ይተረጉማሉ፡፡ እንዲሁም በሰባቱ ተራሮች የተመሰሉ ሰባት ነገሥታት አሉ፡፡ ምንም እንኳ እነዚህ ተራሮች ተከታታይ ቢሆኑም--በአንጼ ፍጻሜ የሚያገኙ አይደሉም፡፡

የራእይ መጽሐፍ ተዛምዶ ወጥነት ካለው ሥርዓት ጋር በመሆኑ፤ የሥርዓቱ አካል ሳይሆኑ የሚነሱ ነገሥታትን እነዚህ ተራሮች አይወክሉም፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ብዙውን ጊዜ ተራሮች የዓለም ልዕለ ኃያል መንግሥታትን ይወክላሉ (ኤር. 51፥

25፣ ሕዝ. 35፡2-3)፡፡ “*ነገሥታት*” በመጽሐፍ ቅዱሳዊው ትንቢት--*መንግሥታት* የሚል ፍቺ አለው (ዳን. 2፡37-39፣ 7፡17)፡፡ በዚህ የተነሳ ሰባቱ ተራሮች ሰይጣን እግዚአብሔርን ሲቃወምና የእግዚአብሔርን ሕዝቦች ሲጎዳ በኖረባቸው፣ በዘመናት በዓለም ላይ ተጽእኖ ያሳደሩ ልዕለ ኃያል መንግሥታትን እንደሚወክሉ ይታሰባል፡፡

ዮሐንስ በነበረበት ዘመን ከእነዚህ መንግሥታት አምስቱ ሲወድቁ አንዱ ግን ነበር፤ ሌላኛው ደግሞ ገና አልመጣም፡፡ እነዚህ በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበሩ፣ የወደቁ ልዕለ ኃያል መንግሥታት አልፎ አልፎ በእግዚአብሔር ሕዝቦች ላይ ጉዳት ያደረሱ ሲሆን እነርሱም፡ ግብፅ፣ አሦር፣ ባቢሎን፣ ፋርስ እና ግሪክ ናቸው፡፡

“ገና ያልመጣው” ሰባተኛው መንግሥት በራእ. 13 የተጠቀሰው አውሬ ሲሆን ይኸውም በእግዚአብሔር ሕዝቦች ላይ ተጽእኖና ጉዳት ያደረሰ በመካከለኛው ዘመን ቤተ ክርስቲያንን የመራ ጳጳሳዊ ሥርዓት ነው፡፡ ሥርዓቱ ከዮሐንስ በኋላ እና ከአረማዊው ሮም ውድቀት በኋላ የመጣ ነበር፡፡ እነዚህ ክስተቶች ከመገለጣቸው ከአያሌ መቶ ዓመታት አስቀድሞ ለተጻፉት ትንቢቶች እውነተኘት ታሪክ እማኝነቱን ይሰጣል፡፡

ቀዩ አውሬ ወደ ስምንተኛ ራስነት የማምራት ሂደት ላይ መሆኑን ዮሐንስ አክሎ ቢናገርም ሆኖም ይህ ራስ ከሰባቱ አንዱ እንደሆነ ይገልጽልናል፡፡ ከሰባቱ መሃል ስምንተኛ የሆነው የቱ ነው? ራሶቹ የዘመንን ቅደም ተከተል ጠብቀው የሚሄዱ እንደመሆናቸው ስምንተኛው ራስ ለሞት የሚያደርስ ቁስል ደርሶበት የነበረው ሰባተኛ ራስ መሆኑን በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡ ቀዩ አውሬ አመንዝራዋን ባቢሎን በስምንተኛው ራስ የተሸከማት በዚህ ወቅት መሆኑን ልብ ይሏል፡፡ እነሆ ዛሬ ለሞት የሚያደርሰው ቁስል የተፈወሰበት ዘመን ላይ እንገኛለን፡፡ የምድር መጨረሻ ሲደርስ ጥቂት ሲቀር የስምንተኛው ራስ ትዕይንት ተገልጦ ወደ ዘላለማዊ ጥፋት ያመራል፡፡

## ሐሙስ *መጋቢት* 12

## የባቢሎን ውድቀት

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 17፡12-15፣ ራእ. 16፡12-16፡፡ ከጥቅሶቹ ስለ “*ዐሥሩ ነገሥታት*” ምን ይማራሉ?

ዐሥሩን ነገሥታት አስመልክቶ የተለያዩ ፍቺዎች ሲሰጡ ቆይተዋል፡፡ ለነገሩ የራእይ መጽሐፍ የነገሥታቱን ማንነት አይነግረንም፡፡ ከጥቅሶቹ የምናገኘውን መረጃ ለማጠናከር ስንሞክር መጨረሻው ከመምጣቱ ጥቂት ቀደም ብሎ የሚከሰቱና አመንዝራይቱን በመደገፍ ለአጭር ጊዜ ብቻ የሚቆዩ የፖለቲካ ኅብረት ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ ቁጥራቸው ለአውሬው ታማኝነታቸውን የሚገልጹትን የዓለም ኃይላት ድምር ይወክላል፡፡ ቀደም ሲል በራእ. 12፡12-17 የተዋወቀውን የአርማጌዶን ጦርነት ራእ. 17፡13-14 በአጭሩ ደጋግሞ ይናገረዋል፡፡ በሰይጣናዊው ኅብረት የተዋወቀው ዓለማቀፉ የፖለቲካ ኪዳን ጥምረት በበጉ ላይ ጦርነት ይከፍታል፡፡ የመጨረሻው ዐውደ ውጊያ በመካከለኛው ምስራቅ የሚደረግ ወታደራዊ ትንቅንቅ ሳይሆን--ሰይጣንና የፖለቲካ ኪዳን ጥምረቱ እንዲሁም ክርስቶስና ታማኝ ሕዝቦቹ የሚያደርጉት ፍልሚያ ነው፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 17፡16-18፡፡ በራእ. 16፡2-12 መሰረት ዐሥሩ ነገሥታት በባቢሎን ላይ ያላቸውን አመለካከት ከመለወጣቸው ጀርባ ምን አለ? በባቢሎን ላይ ከተከሰተው ነገር ጀርባ ማን አለ?

የኤፍራጥስ ወንዝ መድረቅ ሌላው የታሪኩ አጠቃላይ ገጽታ መግለጫ መንገድ ነው (ራእ. 16፡12)፡፡ በጥላቻ ተሞልተው የነበሩት ዐሥሩ ቀንዶች ሳይታሰብ በአመንዝራዋ ባቢሎን ላይ ይነሱና ባዶዋን ማለትም ራቁቷን ያስቀሯታል፡፡ ሥጋዋንም በልተው በእሳት ያቃጥሏታል፡፡ ዮሐንስ በአመንዝራዋ የሩሳሌም ላይ የተሰጠውን ይህን ፍርድ የሚያመለክተውን ትዕይንት ለመግለጽ ጥቅም ላይ ያዋለውን ቋንቋ የወሰደው ከብሉይ ኪዳን ነው (ኤር. 4፡30)፡፡ በእሳት የማቃጠል ቅጣት ሥራ ላይ ይውል የነበረው የካህን ሴት ልጅ ዝሙት አዳሪ ሆና ስትገኝ እንደ ነበር በዘሌዋ. 21፡19 እንመለከታለን። ባቢሎን ከሚወርደው መቅሰፍት ለሳቱት የፖለቲካ ኃይላት ጥላ ከለላ ልትሆን አለመቻሏ ነገሩ ሁሉ የተገላቢጦሽ እንዳደረገባቸው በራእ. 16፡10-12 ቀርቦአል፡፡ እነዚህ ኃይላት እንደ ተታለሉ ስለገባቸው በብርቱ ጥላቻ ጥቃት ይሰነዝሩባታል፡፡ ይህ በመጨረሻው ዘመን ከህደት የሚፈጽም ኃይማኖታዊ ተቋምና ራሳቸውን ከዚህ ሥርዓት ጋር ለመፈረጅ የሚመርጡ ሁሉ አምላካዊውን ፍርድ በሙላት ይቀበላሉ፡፡

**ከመጨረሻው ጊዜ አኳያ አሁንም ገና ያልተመለሱና ግራ ሊያጋቡ የሚችሉ አያሌ ጥያቄዎች መኖራቸው እሙን ነው፡፡ በራእ. 17፥14 ምን ዓይነት ፍቱን ተስፋ ተሰጥቶአል? ይህ ተስፋ ለእኛ ምን ማለት ሊሆን ይችላል?**

## አርብ **መጋቢት 13**

*ተጨማሪ ሀሳብ፡* በባቢሎን ላይ ውድቀት ከመድረሱ አስቀድሞ "' ሕዝቤ ሆይ፣ ከእርሷ ውጡ' " (ራእ. 18፡4) የሚል ከሰማይ የመጣ ድምፅ በባቢሎን ለሚገኙ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ጥሪ ያቀርባል፡፡ አያሌ እግዚአብሔርን የሚያመልኩ ወገኖች በተለያዩ ምክንያቶች ዛሬም በባቢሎን አሉ፡፡ እነዚህ ወገኖች ክህደት ከፈጸመችው ኃይማኖታዊ ተቋም ኃጢአት ጋር እንዳይተባበሩ እግዚአብሔር የመጨረሻዋን ዘመን ቤተ ክርስቲያኑን ተጠቅሞ ጥሪ ያደርግላቸዋል፡፡ ከሚደርስባት አስከፊ መጨረሻ ለማምለጥ ከእርሷ መውጣታቸው የግድ ይሆናል፡፡ በባቢሎን ያለ ማንም ሰው ይጠፋ ዘንድ የእግዚአብሔር ፍላጎት አይደለም፡፡ አያሌ በባቢሎን የሚገኙ ፈሪሐ እግዚሓር ያላቸው ወገኖች ለዚህ ጥሪ ምላሽ እንደሚሰጡ ራእ. 19፡1-10 ይናገራል። እንደ እግዚአብሔር ትሩፋን ሕዝብነታችን የተጣለብንን ብርቱ ኃላፊነት ያስቡ። የእግዚአብሔር ኃይል በእጅጉ በሕይወታችን ማስፈለጉን አስመልክቶ ይህ ምን ሊነግረን ይገባል?

## *የመወያያ ጥያቄዎች፡*

**1.እግዚአብሔር "ሕዝቤ" ብሎ የሚጠራቸው፤ እርሱን የሚፈሩ እጅግ ብዙ ሕዝቦች እንዳሉት ራእ. 18፥4 ያሳየናል፡፡ "ይህ መልእክት መሰጠቱ የግድ ቢሆንም ነገር ግን ይህ ሲሆን፤ እኛ ብርሃን ያለን--ብርሃን የሌላቸውን እንዳናስገድድ፣ እንዳናስጨንቅና እንዳንኮንን ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርብናል፡፡ ካቶሊኮችን በጣም በመጫን ከመንገዳችን ማፈንገጥ የለብንም፡፡ በካቶሊክ እምነት ተከታዮች መሃል የሚበራላቸውን ብርሃን ተከትለው የሚራመዱና እግዚአብሔር ስለ እነርሱ የሚሠራላቸው አያሌ ጥንቁቅ ክርስቲያኖች አሉ፡፡ ታላላቅ ጥቅሞችና አጋጣሚዎች እጃቻቸው ገብተው እያሉ አካላዊውን፣ አእምሮአዊውንና ሥነ ምግባራዊውን ማንነት ከማጎልበት የተሰናከሉ. . . በተሳሳተ ኃይማኖታዊ አስተምህሮ ውስጥ እየተመላለሱ ለሌሎች መልካም ለማድረግ ከሚጥሩት ይልቅ በከፋ አደጋና**

ኩነኔ ውስጥ ናቸው፡፡”—Ellen G. White, Evangelism, p. 575. ሌሎችን እንዴት ልንቀርብና ተገቢውን ጥንቃቄ ልናደርግ እንደሚገባ አስመልክቶ ይህ ምን ሊነግረን ይገባል?

2.ራእ. 17 በቀይ አውሬ ላይ ስለ ተቀመጠችው አመንዝራ ሴት ገለጻ ያደርጋል፡፡ በራእ. 12 የምናገኛት ሴት የእግዚአብሔርን ታማኝ ቤተ ክርስቲያን ስትወክል፤ በምዕ. 17 የምናገኛት ደግሞ ዓለምን እያባበለች ከእግዚአብሔር የምታርቀዋ ተምሳሌት ነች፡፡ በእርስዎ አመለካከት በእነዚህ በሁለቱ መካከል ያለው መመሳልና መለያየት ምንድን ነው? በዋነኝነት--ከዚህ ንጽጽር ምን እንማራለን?

3.በዚህ ሣምንት የተመለከትናቸው ጥቅሶች ክርስቶስ በድል አድራጊነት ዳግም ከመመለሱ አስቀድሞ ባሉት የመጨረሻ ምዕራፎች ኃይማኖታዊውና ፖለቲካዊው ዓለም የሚገኝበትን አስጠሊታ ሁናቴ ያስቃኛሉ፡፡ እግዚአብሔር ለሰጠን መልእክቶች አሁኑኑ ታማኝ፣ እውነተኛ እና ንጹህ መሆናችን በእጅጉ አስፈላጊ ስለ መሆኑ ይህ ምን ሊነግረን ይገባል? ዓለም በክህደት ስትተለቀለቅ እኛ ግን በታማኝነት እንድንራመድ ስለ ቀረበልን ጥሪ ራእ. 16፡15 ያንብቡ፡፡ ይህን ማስጠንቀቂያ አሁኑኑ በየግላችን መተግበር የምንችለው እንዴት ነው?

# 13ኛ ትምህርት

ከመጋቢት 14-20

# “እኔ ሁሉን ነገር አዲስ አደርጋለሁ”

ሰንበት ከሰዓት

ለዚህ ሣምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ራእ. 19:6–19፣ ዮሐ. 14:1–3፣ 2ተሰ. 1:8–10፣ ራእ. 21:1–21፣ ኤር. 4:23–26፣ 1ቆሮ. 6:2-3፡፡

**መታሰቢያ ጥቅስ፡ - “በዙፋኑ ላይ የተቀመጠውም ‘እነሆ፤ እኔ ሁሉን ነገር አዲስ አደርጋለሁ’ አለ፡፡ ደግሞም ‘ይህ ቃል እውነት ስለ ሆነና ስለ ታመነ ጻፍ’ አለኝ” (ራእ. 21፡5)፡፡**

ስለ መጨረሻው ጊዜ የተሰጠው መግለጫ ከዚህች ክህደት የፈጸመች ኃይማኖታዊ ተቋም ጋር ላበሩ መጥፎ ዜና--በተቃራኒው ለእግዚአብሔር ሕዝቦች ደግሞ መልካም የምሥራች ነው (ራእ. 19፡7)፡፡ የፖለቲካ ኃይላት በእግዚአብሔር ሕዝቦች ላይ ስደት እንዲያደርሱና ጉዳት እንዲያስከትሉ ቀንደኛዋ አነሳሽና ተዋናይ ባቢሎን ናት (ራእ. 18፡24)፡፡ የዚህ ታላቅ ጠላት ውድመት የቅዱሳን ደኅንነት መሆኑ የማይታበል ሐቅ ነው፡፡

የባቢሎንን ውድመት ይፋ የሚያደርገውን አምስተኛውን ማኅተም ተከትሎ በመጨረሻ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ጸሎት ምላሽ ያገኛል፡፡ “ጌታ ሆይ፤ እስከ መቼ አትፈርድም?” የተሰኘው የሥቃይ ድምፅ ከአቤል ዘመን አንስቶ እግዚአብሔር በመጨረሻ ስለ ሕዝቡ እስኪበቀል ያለውን የሕዝቦቹን ሰቆቃ ይወክላል (መዝ. 79፡5፣ ዕምባ.1፡2፣ ዳን.12፡6-7)፡፡ በመጨረሻ ክፋት፣ ጭቆና እና ሥቃይ እንደሚያከትም የራእይ መጽሐፍ ለእግዚአብሔር ሕዝቦች ማረጋገጫ ይሰጣል፡፡

ክርስቶስ በዳግም ምጽአቱ የሚገለጥበት ጊዜ እነሆ አሁን ነው፡፡ ቀሪዎቹ የራእይ መጽሐፍ ምዕራፎች ገለጻ የሚያደርጉት ስለ መጨረሻዋ ጊዜ ባቢሎን ውድመት ብቻ አይደለም--የክፋት ሁሉ ምንጭ ስለሆነው ቀንደኛው ሰይጣን መወገድ ጭምር እንጂ! ከዚህ በተጨማሪ ስለ እግዚአብሔር ዘላለማዊ መንግሥት መመስረትም በጨረፍታ ይነግሩናል፡፡

**እሑድ** *መጋቢት 15*

# የበጉ ሠርግ እራት

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 19፡6-9፣ ዮሐ. 14፡1-3፡፡ ሠርግ የተሰኘው ቃል ለረጅም ዘመን በተስፋ ሲጠበቅ የቆየውን በክርስቶስና በሕዝቡ መካከል ገቢራዊ የሚሆን ሕብረት እንዴት ባግባቡ ይገልጸዋል?

---

---

ጌታ አምላካዊውን እውነት ለእኛ ለማስተማር የጥንት አይሁድን የጋብቻ ሁኔታ ሲጠቀም ይታያል፡፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ባል ይሆናል ተብሎ የሚጠበቀው እጮኛ እጮኛውን ለማጨት ወደ ቤቷ ያመራል፡፡ ከዚያም እንደ ሕጉ ተገቢውን ጥሎሽ ሲያቀርብ ጥንዶቹ በጋብቻ እንደ ተሳሰሩ ሆነው ይታያሉ፡፡ ሆኖም አብረው መኖር ግን አይችሉም፡፡ አሁን ሙሽራው በጋራ የሚኖሩበትን ስፍራ ለማዘጋጀት ወደ አባቱ ቤት ይመለሳል፡፡ ሙሽራዋም ራሷን እያዘጋጀች በአባቷ ቤት ትቆያለች፡፡ ሙሽራው አስፈላጊውን ዝግጅት እንዳጠናቀቀ ሙሽራዋን ለማምጣት ወደ አባቷ ቤት ያመራል። በዚህ ወቅት የሠርግ ሥነ ስርዓት ይካሄዳል፡፡

ክርስቶስ ከሁለት ሺ ዓመታት በፊት ሰማያዊ ቤቱን ትቶ በምድር ያለችውን ሙሽራ ሊያጭ መጣ፡፡ ለሙሽራዋ መክፈል የነበረበትን ጥሎሽ አስመልክቶ፤ በቀራኒዮ ሕይወቱን ከሰጠ በኋላ ከሙሽራዋ ጋር የሚኖሩበትን “ስፍራ ለማዘጋጀት” ወደ ሰማያዊ አባቱ ቤት ተመለሰ (ዮሐ. 14፡2-3)፡፡ ሙሽራዋም ራሷን እያዘጋጀች በምድር ትቆያለች፡፡ በዘመኑ መጨረሻ ሙሽራው ተመልሶ ይመጣና ወደ አባቱ ቤት ይወስዳታል፡፡ ክርስቶስ የሚያንጸባርቅና ንጹሕ፣ ከተልባ እግር የተሠራ ልብስ ለሙሽራዋ እንደሰጣት ራእ. 19፡8 ይጠቅሳል፡፡ ይህ ሁኔታ የእግዚአብሔር ሕዝቦች የሠሩትን የጽድቅ ሥራ ከራሳቸው እንደሆነ አድርገው አለመቀበላቸውን ያሳያል፡፡ የእግዚአብሔር ሕዝቦች የለበሱት ልብስ በእነርሱ ውስጥ ከሚኖረው ከክርስቶስ ጋር የፈጠሩት ሕብረት ውጤት የሆነውን “የቅዱሳንን የጽድቅ ሥራ” ይወክላል፡፡ እነዚህ ልብሶች በበጉ ደም ታጥበው ነጽተዋል (ራእ. 7፡14)፡፡ የሱስ በምድር በነበረበት ወቅት ሠርግን ምሳሌ አድርጎ ብርቱ መልእክት አስተላልፎአል፡፡ አንድ ታላቅ ሠርግ ተደገሰና በሠርጉ እንዲገኙ የታደሙ እንግዶች በሥነ ስርዓቱ ላይ ለብሰው የሚመጡት የሠርግ ልብስ በንጉሡ ታደሉ፡፡ ታዲያ በሠርጉ ግብዣ ከተገኙት አንዱ በንጉሡ የተሰጠውን የሠርግ ልብስ ትቶ የራሱን ልብስ ለብሶ በመገኘቱ ከሰርጉ ግብዣ እንዲባረር ተደረገ (ማቴ. 22፡8-11)፡፡

በክርስቶስ የተሰጠው ልብስ በመጨረሻው ዘመን ለሚኖሩ የእግዚአብሔር ሕዝቦች በእጅጉ እንደሚያሻ ራእ. 3፡18 ይነግረናል፡፡ የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን ይህን ነጭ ልብስ ከእርሱ እንትድገዛ ጥሪ ሲያቀርብላት፤ ለሚሰጣት ነገር በምላሹ ከእርሷ የሚጠባበቀው መኖሩን ያሳያል፡፡ ይኸውም ራሳችንን ብቁ አድርገን ማየትና በሥራችን መመጻደቅ አቁመን የእርሱን የጽድቅ ሥራ ብቸኛው የደኅንነታችን ተስፋ አድርገን መታመን ነው፡፡

***እርስዎ የዳኑት በሥራዎ ሳይሆን በክርስቶስ "የጽድቅ ሥራ" መሆኑን የዛሬ ህይወትዎ ምን ያህል ይገልጻል?***

## ሰኞ መጋቢት 16

# የአርማጌዶን ፍጻሜ

ጥቅሱን ያንብቡ፡ ራእ. 19፡11-16፡፡ የክርስቶስ ስም "የእግዚአብሔር ቃል" (ራእ. 19፡13) በሚል መጠራቱና ስለታም ሰይፍ ከአፉ መውጣቱ ስለ መጨረሻው ጦርነት ባህሪ ምን ይጠቁማል?

---

---

እዚህ ላይ በተለያዩ ዘመናት የኖሩ አማኞች አጥብቀው ሲናፍቁት የኖረው የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ፍጻሜ ሥዕል ቀርቦአል፡፡ መልእክቱ የቀረበበትን ቃና ልብ ብለው ሲያጤኑ በድል አድራጊነት መሞላቱን ያስተውላሉ፡፡ የሱስ ሰይጣንን በሰማይ፣ በምድረ በዳ እና በመስቀል ላይ ድል እንዳደረገው ሁሉ በዳግም ምጽአቱም ድል ይነሳዋል!

"ከዚያም ከሰው እጅ በግማሽ የሚያንስ የሚመስል ጥቁር ደመና በምሥራቅ በኩል ታየ፡፡ አዳኙን የከበበው ደመና ከሩቅ ሲታይ ጥቁርና ጥቅልል ገጽታ ይስተዋልበታል፡፡ ሁኔታው የእግዚአብሔር ልጅ መገለጥ ምልክት መሆኑን የእግዚአብሔር ሕዝቦች አውቀዋል፡፡ ከግርጌው በኩል እንደሚባላ እሳት ከአናቱ ደግሞ የኪዳኑ ቀስተ ደመና ግርማ ያለው--ነጩ ደመና እጅግ ግዙፍ እስኪሆን እያደገ፣ በብርሃን እየተሞላና የከበረ እየሆነ ወደ ምድር እየተቃረበ ሲመጣ በተረጋጋ ጸጥታ ይመለከቱታል፡፡ የሱስ እንደ ኃያል ባለ ድል ወደ ፊት ይገሰግሳል፡፡ አሁን የተገለጠበት መንገድ አሳፋሪውን የውርደትና ወዮታ ጽዋ የሚጠጣን 'የሐዘን ሰው' ገጽታ የተላበሰ ሳይሆን፤ በሕወት ያሉትንና የሞቱትን የሚፈርድ የሰማይና የምድር ድል አድራጊ ሆኖ ነው፡፡ 'ታማኝና እውነተኛ' የሆነው እርሱ 'በጽድቅ ይፈርዳል ይዋጋልም'፡፡ 'የሰማይ ሰራዊትም

ይከተሉት ነበር’ (ራእ. 19፡11-14)፡፡ መላእክት በታላቅ ሰማያዊ ዜማ አጅበውት በብዙ ሆታና እልልታ ይገለጣል፡፡ ሰማዩ “ቁጥራቸው ሺህ ጊዜ ሺህና እልፍ ጊዜ እልፍ” በሆኑ አንጸባራቂ ቅርጾች ይሞላል፡፡ ይህን ትዕይንት ሰብዓዊው ብዕር ሊገልጸው ከቶ አይችልም፡፡ ውበቱንና ድምቀቱን ሟቹ አእምሮ መረዳት አይሆንለትም፡፡”—Ellen G. White, The Great Controversy, p. 641.

ጳውሎስ ስለ ዳግም ምጽአቱ የመጨረሻው የክርስቶስ ድል አስመልክቶ በ 2ቆሮ 1፡ 8-10 በሚሰጠን ሌላ መግለጫ፤ በእርሱ ላይ ያሴሩ ዓለማዊና ኃይማኖታዊ ኀይላት በሙሉ ሲወገዱ ሕዝቦቹ ግን ለዘላለም እንደሚድኑ ይነግረናል፡፡

ራእ. 19 በቁ. 9 እንዲሁም 17-18 ስለ ሁለት ዓይነት እራት ይናገራል፡፡ በአንደኛው እራት ተጋባዡ ሲበላ፤ በሌላኛው ግን ራሱ ይበላል፡፡ በታላቁ ቅራኔ ውስጥ የሚኖረው እያንዳንዱ ሰብዓዊ ፍጡር ላይ ሊደርስ የሚችለውን በአደጋ የተሞላ ሁናቴ እያነጻጸሩ በዐይነ ህሊና ለማየት መሞከር በራሱ አስቸጋሪ ነው፡፡ ይህ ተምሳሌታዊ አቀራረብ እምነታችንን እና እምነታችን የሚያቀርብልንን ተልዕኮ ምን ያህል አጥብቀን መያዝ እንዳለብን እንዴት ሊያስተምረን ይገባል?

## ማክሰኞ መጋቢት 17

## የሺህ ዓመቱ መንግሥት

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 20፡1-3፣ ኤር. 4፡23-26፡፡ በሺህ ዓመቱ ዘመን ምድር በምን ዓይነት ሁናቴ ውስጥ ትቆያለች? ሰይጣን በሰንሰለት የሚታሰረው እንዴት ነው?

---

---

1ሺ ዓመቱ በክርስቶስ ዳግም ምጽአት ይጀምራል፡፡ በዚህ ወቅት ሰይጣንና የወደቁ መላእክቱ በሰንሰለት ይታሰራሉ፡፡ መናፍስት በእስራት አንድ ቦታ ላይ መገደብ የማይችሉ እንደመሆናቸው የሰይጣን መታሰር ተምሳሌታዊ ነው፡፡ የሰይጣን እስራት በሁናቴዎች ላይ የተገደበ ነው፡፡ የወረዱት መቅሰፍቶች ምድርን ያለ ሰው አስቀርተው ምስቅልቅሏን በማውጣት ከፍጠረት አስቀድሞ ወደ ነበረችበት ሁናቴ መልሰዋታል (ዘፍ. 12)፡፡ ይህ ሁናቴ ምድርን በዚህ አንድ ሺ ዓመት የሰይጣን እስር ቤት ያደርጋታል፡፡ ሰይጣን ሊፈትነው ወይም ሊጎዳው የሚችል አንድም ሰብዓዊ ፍጡር ምድር ላይ አለመኖሩን ተከትሎ እርሱና ዲያብሎሳዊ ማኅበሩ ማድረግ የሚችሉት ነገር ቢኖር፤ በእግዚአብሔር ላይ የፈጸሙት ዐመጻ ያስከተለውን ውጤት ማሰላሰል ይሆናል፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 20፡4-15፡፡ በተጠቀሰው 1ሺህ ዓመት ቅዱሳን ምን ያደርጋሉ?

---

---

የእግዚአብሔር ሕዝቦች በዚህ ሺህ ዓመት ክርስቶስ ባዘጋጀላቸው ሰማያዊ ስፍራ እንደሚሆኑ የራእይ መጽሐፍ ይናገራል፡፡ እንደ ነገሥታትና ካህናት በዙፋኖች ላይ ተቀምጠው ዓለምን ሲዳኙ ዮሐንስ ተመልክቶአል፡፡ "በዐሥራ ሁለት ዙፋን ላይ ተቀምጣችሁ በዐሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገድ ላይ ትፈርዳላችሁ" (ማቴ. 19፡28) ሲል የሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ቃል ገብቶላቸዋል (ማቴ. 19፡28)፡፡ ቅዱሳን በዓለም ላይ ፍርድ እንደሚሰጡ ጳውሎስ ይናገራል (1ቆሮ. 6፡2-3)፡፡ ይህ ፍርድ የእግዚአብሔርን አሠራር ፍትሐዊነት ፍንትው አድርጎ ያሳያል፡፡ ሰይጣን በእግዚአብሔር ባህሪና ከፍጥረታቱ ጋር ባለው መስተጋብር ዙሪያ ለረጅም ዘመናት ብርቱ ጥርጣሬ ሲያስነሳ ኖሮአል፡፡ በዚህ ሺህ ዓመት--የጠፉትን አስመልክቶ በአጠቃላይ በእርሱ ፍትሐዊነት ዙሪያ ለሚነሱ ጥያቄዎች እግዚአብሔር የሰጣቸው ውሳኔዎችና በገዛ ህይወታቸው ላይ ከነበረው ምሪት አኳያ ምን ያህል ቅን እንደ ነበር--እያንዳንዷን የታሪክ መዛግብት የሚፈትሹበት ፈቃድ ከእግዚአብሔር ይቀበላሉ፡፡ በእግዚአብሔር ፍትሐዊነት ዙሪያ የሚነሱ ሁሉም ጥያቄዎች በሺህ ዓመቱ መዝጊያ ለዘላለም መፍትሔ ያገኛሉ፡፡ የእግዚአብሔር ሕዝቦች መሰረተ ቢስ ከሆኑት የሰይጣን ክሶች የጥርጣሬ ጥላ ባሻገር ማየት የሚችሉ ይሆናሉ፡፡ አሁን እግዚአብሔር በመጨረሻ ላይ ለሚሰጠው ፍትሐዊ አሠራርን ለተከተለ ፍርድ ምስክር ለመሆን እነሆ ዝግጁ ናቸው፡፡

**ዛሬ በዚህ ምድር መመለስ የማይችሉ ጥያቄዎች የሌሉን ስንቶቻችን ነን? ይህ--አንድ ቀን ለሁሉም ጥያቄዎች መልስ ስለሚሰጠን ስለ እግዚአብሔር ጸባይ ምን ይነግረናል?**

## ረቡዕ — መጋቢት 18

# "አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር"

ኃጢአት ከተወገደ በኋላ ምድር የዳኑት መኖሪያ ሆና ትለወጣለች፡፡ ለመሆኑ ምን ትመስል ይሆን?

የሐንስ በራእ. 21፡1 "አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር" ማየቱን ይናገራል፡፡ አይሁዳውያን ስለ ሦስቱ ሰማዮች ማለትም፡ ሰማይ፣ ከዋክብት የሚገኙበት ዩኒቨርስ እና የእግዚአብሔር ማደሪያ ስለሆነው ስፍራ ዕውቀት ነበራቸው (2ቆሮ. 12፡2)። በራእ. 21፡1 ምድራዊው ሕዋ ተወስቶአል፡፡ በኃጢአት ብክለት የደረሰበት ይህ

ምድር እና ሰማይ የእግዚአብሔርን መገኘት መቋቋም አይችልም (ራእ. 20፡11)፡፡ አዲስ የተሰኘው ቃል ፍቺ የተወሰደው ከግሪክኛው kainos ሲሆን፤ ቃሉ አዲስነትን የሚገልጸው ከዓይነት እንጂ ከሥረ መሰረት እና ከጊዜ አኳያ አይደለም፡፡ ይህች ፕላኔት ከእርኩሰቷ በእሳት ትነጻና ወደ ቀደመ ማንነቷ ትመለሳለች (2ጴጥ. 3፡10-13)፡፡

ሌላው ልዩ ትኩረት የሚያጭረው ነገር በአዲሲቱ ምድር ባሕር አለመኖሩ የተወሳበት ክፍል ነው፡፡ ዮሐንስ ባሕርን የገለጸበት መንገድ የተወሰነ ገላጭ ወይም አንድን ነገር ለይቶ አመላካች ዓይነት ዘይቤን የተከተለ እንደመሆኑ፤ ቃሉን ጥቅም ላይ ያዋለው ምናልባት የመለያየትና የሥቃይ ተምሳሌት የሆነውን፣ የፍጥሞ ደሴት ዙሪያ ገባን የከበበውን ባሕር በአእምሮው ይዞ ሊሆን ይችላል የሚል እሳቤ አለ፡፡ በአዲሲቱ ምድር የባሕር አለመኖር፤ ለእርሱ ያለ ህመም እና ያለ ሥቃይ እንደ መሆን ማለት ነው፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 21፡2-8፤ 7፡15-17፡፡ በአዲሲቱ ምድር እና በዘፍጥረት የኤደን የአትክልት ስፍራ መሃል  በቀረበው መግለጫ ምን ዓይነት መመሳሰል እናገኛለን?

---

---

የእግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር መገኘት ከሥቃይና ሞት ነፃ ሆና ወደ ቀድሞ ንጽህናዋ የተመለሰችው ምድር ዋስትና የተጠበቀ እንዲሆን ያደርጋል። አዲሲቱ የሩሳሌም እግዚአብሔር በሕዝቡ መሃል የሚያድርባት መቅደስ ሆና ቀርባለች (ራእ. 21፡3)የእግዚአብሔር በሕዝቡ መሃል ማደር ወደ ቀድሞ ንጽህናዋ የተመለሰችውን አዲሲቱን ምድር የቤተ መቅደስ ገጽታ ያጎናጽፋታል፡፡

እግዚአብሔር በዚያች አገር ማደሪያውን በማድረጉ የኃጢአት ውጤት የሆኑት፡ እንባ፣ ሞት፣ ሐዘን፣ ልቅሶ ወይም ህመም አይኖርም፡፡ የኃጢአትን መወገድ ተከትሎ “ ‘የቀድሞው ሥርዐት ዐልፎአልና’ ” (ራእ. 21፡4)፡፡

ይህ ጽንሰ ሀሳብ ግልጽ ሆኖ ከቀረበባቸው መንገዶች አንዱ ማርያምና ማርታ ወንድማቸውን አልዓዛር በሞት ያጡበት ሁናቴ ነበር፡ “‘ጌታ ሆይ፤ አንተ በዚህ ብትሆን ኖሮ፣ ወንድሜ ባልሞተ ነበር’ ” (ዮሐ. 11፡21)፡፡ ሞት ክርስቶስ ባለበት ስፍራ መኖር እንደማይችል እህትማማቾቹ ጠንቅቀው ያውቁ ነበር፡፡ በተመሳሳይ የእግዚአብሔር በአዲሲቱ ምድር መኖር ዛሬ በዚህ ህይወት እየተለማመድን ካለነው ህመምና ሥቃይ እንድንጠበቅ ያደርገናል፡፡ ይህ እንግዲህ በክርስቶስ ደም ታትሞ የተበረከተልን ታላቁ ተስፋችን ነው፡፡

**ለመሆኑ ይህ የአዲሲቱ ምድር አዲስ ህይወት ባለቤትነት የአጠቃላይ እምነታችን ማዕከላዊ ክፍል የሆነው ለምንድን ነው? እምነታችን ያለዚህ እውነታ ምን ያህል መልካም ሊሆን ይችል ነበር?**

**ሐሙስ** *መጋቢት* **19**

## አዲሲቱ የሩሳሌም

አሁን ዮሐንስ የአዲሲቱን ምድር ርዕሰ መዲና--አዲሲቱ የሩሳሌም በማለት ሲገልጻት ይስተዋላል፡፡ ምንም እንኳ ተጨባጭ ሰዎችና ተጨባጭ ስፍራዎች ቢኖሩም፤ አዲሲቱ የሩሳሌምና በዚያ የሚገኘው ሕይወት ግን ከማንኛውም ምድራዊ መግለጫ ባሻገር ነው ፣ቆሮ. 2፡9)፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 21፡9-21፡፡ ለመሆኑ የአዲሲቱ የሩሳሌም ውጪያዊ ገጽታዎች ምን ይመስላሉ?

---

---

አዲሲቱ የሩሳሌም እንደ ሙሽራ ማለትም የበጉ ሚስት ሆና ተመስላ ቀርባለች፡፡ ይህ ዘይቤአዊ አቀራረብ በተጨባጭ የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ሕዝቦች ነው። አዲሲቱ የሩሳሌም ክርስቶስ በስተመጨረሻ ከሕዝቡ ጋር ኅብረት የሚፈጥርባት ስፍራ ትሆናለች፡፡

ከተማዋ የተከበበችው ዐሥራ ሁለት በሮች ባሉት ከፍ ያለ ቅጥር ሲሆን በአራቱም ማዕዘናት ከየትኛውም አቅጣጫ ለመግባት የሚያስችሉ ሦስት፣ ሦስት በሮች አሉ። ይህ ሁኔታ የከተማዋን ዩኒቨርስ አቀፍነት ያመለክታል፡፡ በአዲሲቱ የሩሳሌም ማንኛውም አካል በእግዚአብሔር ሕልዎት ፊት የመቅረብ ያልተገደበ መብት አለው።

ከዚህ ባለፈ አራት መአዘን ቅርጽ ያላት ይህች ከተማ 12,000 ምዕራፍ የሚደርስ ርዝመት፣ ስፋትና ከፍታ እንዳላት ቀርቦአል፡፡ 12 መሰረቶች የነበሯት የዚህች ከተማ ቅጥር ስፋት 144,000 ሲሆን ይህ ተምሳሌታዊ ቁጥር በዘመናት የዳኑትን የእግዚአብሔር ሕዝቦች አኻዝ ይገልጻል (ራእ. 7፡4)፡፡ በብሉይ ኪዳን የነበረው የቤተ መቅደሱ ቅድስተ ቅዱሳን ክፍል እኩል በእኩል የሆነ ቅርጽ ነበረው (1ነገሥ. 6፡20)፡፡ በዚህም አዲሲቱ የሩሳሌም እንደ መቅደስ ብቻ ሳይሆን እንደ ቅድስተ ቅዱሳን--አገልግሎት ትሰጣለች፡፡ በቀደመችው ምድራዊ ቤተ መቅደስ ወደ ቅድስተ

ቅዱሳኑ ክፍል መግባት የሚችለው ሊቀ ካኅኑ ብቻ ሲሆን፤ በአዲሲቱ የሩሳሌም ግን ይህ ልዩ መብት ለሁሉም የተዋጁ ወገኖች ተሰጥቶአል፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 21፡21-22፡5፡፡ የኤደን አትክልት ስፍራን የሚያስታውሶ የትኛው የከተማዋ ውስጣዊ ክፍል ነው? በከተማዋ ከዚህ በኋላ ርግማን እንደማይኖር የመጠቀሱ አንደምታ ምንድን ነው (ራእ. 22፡3)?

---

---

ስለ አዲሲቱ የሩሳሌም በተለይ የተገለጸው በእጅጉ ዝነኛ ትዕይንት ከእግዚአብሔር ዙፋን የሚፈልቀው ውሃ ነው (ዘፍ. 2፡10)፡፡ የእግዚአብሔር ሕዝቦች የሩሳሌምን እየናፈቁ በግዞተኝነት ከተቀመጡበት የባቢሎን ወንዝ በተቃራኒ (መዝ. 137) እነሆ በዘመናት ሲንከራተቱ የኖሩ ሕዝቦቹ በአዲሲቱ የሩሳሌም የሕይወት ወንዝ ዳርቻዎች መኖሪያቸውን አገኙ፡፡

በወንዙ ግራና ቀኝ የሕይወት ዛፍ የነበረ ሲሆን "የዛፉ ቅጠሎች ሕዝብ የሚፈወስባቸው ነበሩ" (ራእ. 22፡2)፡፡ በአዲሲቱ ምድር ምንም ዓይነት በሽታ እንደ ሌለ ሁሉ ይህ ፈውስ ከበሽታ ጋር ቁርኝት የለውም፡፡ በዘመናት ሰዎችን ሲነጣጥል የኖረ ማንኛውም ግድግዳ ያስከተለው ቁስል ፈውስ ማግኘቱን ይጠቁማል፡፡ ከተለያዩ ዘመናት የመጡ የዳኑ ወገኖች አሁን አንድ የእግዚአብሔር ቤተሰብ ናቸው፡፡

## አርብ *መጋቢት* **20**

ተጨማሪ ሀሳብ፡ Read Ellen G. White, "Desolation of the Earth," pp. 653–661; "The Controversy Ended," pp. 662–678, in The Great Controversy.

የራእይ መጽሐፍ የሚደመደመው በመግቢያው ላይ በቀረበው መልእክት ሲሆን ይኸውም የክርስቶስን በኃይልና በክብር ዳግም መገለጥና የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ መንግሥት መመስረት በማብሰር ነው፡፡ ክርስቶስ በመጨረሻ ከሙሽራው ጋር የሚገናኝበት ዳግም ምጽአት የመጽሐፉ ወሳኝ ክፍል ነው፡፡

ሆኖም መጽሐፉ እነዚህን ክስተቶች ተጨባጭነት ከሌለው ዐውድ አኳያ ማቅረብ አይፈልግም፡፡ ስለዚህ የየሱስ በቅርብ መገለጥ ተቀዳሚ ተጨባጭ እውነታ ነው። ሁለተኛው ተጨባጭ እውነታ ደግሞ የእርሱን መመለስ እየተጠባበቅን አሁን

ድረስ በዚህ ምድር መኖራችን ነው፡፡ እርሱን እየተጠባበቅን እያለ የራእይ መጽሐፍ መልእክት ግልጽ ማስተዋል ሊኖረን የግድ ይሆናል፡፡ ይህን ማግኘት የምንችለው ደግሞ የሁሉም ነገር ፍጻሜ እስኪመጣ መጽሐፉን በተደጋጋሚ በማንበብ ነው። ዐይኖቻችን ብቸኛ ተስፋችን የሆነውን እርሱን ከመጠባበቅ ውጪ ወደ ዓለማዊ ነገሮች እንዳያማትሩ የራእይ መጽሐፍ መልእክት ያለማቋረጥ ያሳስበናል፡፡ ምንም እንኳ ሕይወት በምስጢርና እንቆቅልሽ የተሞላች ብትሆንም፤ ነገር ግን የራእይ መጽሐፉ ክርስቶስ የሁሉም ሰብዓዊ ተስፋና መናፈቅ መልስ ነው፡፡ እርሱ የዚህን ዓለም እንዲሁም የእኛን የወደፊት ሁኔታ በእጆቹ ይዞአል፡፡

እንዲሁም መጨረሻው ከመምጣቱ አስቀድሞ በቅርብ የመገለጡን መልእክት ለመላው የምድር ሕዝቦች የማወጅ ኃላፊነት እንደ ተሰጠን መጽሐፉ ያሳስበናል። የእርሱን ዳግም መገለጥ የምንጠባበቀው ተነሳሽነት በጎደለው መንፈስ ሳይሆን በንቁ እንቅስቃሴ ሊሆን የተገባ ነው፡፡ መንፈስና ቤተ ክርስቲያን “ ‘ና’ ” ይላሉ (ራእ. 22፥17)፡፡ የዚህ ጥሪ አካል መሆናችን የግድ ይሆናል፡፡ ይህ መልካም የምሥራች እንደመሆኑ ለዓለም ሕዝቦች መሰበኩ የግድ ነው፡፡

## የመወያያ ጥያቄዎች፡

**1.ስለ ሺህ ዓመቱ እና ከዚያ በኋላ ብቻ ስለሚሆነው ፍርድ ያስቡ። የዳኑት አንድ ሺ ዓመት ከነገሡና ጥያቄዎቻቸው በሙሉ መልስ ካገኙ በኋላ እግዚአብሔር በጠፉት ላይ የመጨረሻውን የቅጣት ብይን መስጠቱ ስለ እርሱ ምን ያስተምረናል?**

**2.የራእይ መጽሐፍ ትንቢቶችን የሚሰሙ፣ የሚያነቡና የሚጠብቁ በረከት ያገኛሉ ሲል ራእ. 1፥3 ተስፋ ይሰጣል፡፡ የዚህን መጽሐፍ ጥናት ስናጠቃልል--ትኩረት ሊሰጡና ሊጠብቁአቸው እንደሚገቡ ያስተዋሏቸው ነገሮች ምንድን ናቸው?**